# አምሳለ



# ገነት

ከተክለ ፡ ማርያም ፡ ፋንታዬ ።

R
ቀ.ዘ08
12/68/፪ 18/6 ፺፫ሺ

# አምሳለ ገነት

ከተክለ ማርያም ፋንታዬ

አምሳለ ገነት፡

መጽሐፍ፡

የትምህርትና ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡
በሥርዓተ ፡ ትምህርትና ፡ መጻሕፍት ፡ ዝግጅት ፡
ዋና ፡ ዲሬክሲዮን ፡ አዲስ ፡ አበባ ።

መብቱ ፡ በትምህርትና ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

መጀመሪያ ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታተመ ።
እንደገና ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታተመ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።
አዲስ ፡ አበባ ፡ ኢትዮጵያ ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ንጉሠ፡ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ከተማሪ፡ ገብረ፡ ሄለዝር፡ በዛብህ
የተሰጠው ነው

ሀ ፡ የሀገራችንን ፡ ትምህርት ፡ ሳይማሩ ፡ የውጭ ፡ አገርን ፡ ዕውቀት ፡ እማራለሁ ፡ ማለት ፡ በድቡሽት ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ እንደሠራው ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ ነው ።

ግ ፡ ቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡

ለ ፡ ቋንቋ ፡ የሥልጣኔ ፡ ክፍል ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የሥልጣኔ ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የገዛ ፡ ቋንቋን ፡ ማጥናትና ፡ አመዳደቡን ፡ ማወቅ ፡ የአገርን ፡ ታሪክና ፡ ቅርስ ፡ ማጥናትና ፡ ማቆየት ነው ። እያንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ በየቋንቋው ፡ የተመሠረተ ፡ ነውና ፡ ቋንቋችንን ፡ በደንብ ፡ ያጠናን ፡ እንደሆነ ፡ ራሳችንንም ፡ በደንብ ፡ ልናውቀው ፡ እንችላለን ። ራስንም ፡ ማወቅ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከአሉት ፡ ትልልቆች ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ነው ።

ሚሊዮን ፡ ነቅንቅ ፡

ሐ ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ መጀመሪያ ፡ መደማመጥ ፡ በማስፈለጉ ፡ የቋንቋ ፡ ሚዛን ፡ በየጊዜው ፡ እየደፋ ፡ ይሄዳል ። መደማመጥ ፡ መግባባትን ፡ ያስከትላል ፡ መግባባትም ፡ ወደስምምነት ፡ እየመራ ፡ ያደርሳል ። በስምምነት ፡ ሥራ ፡ ይጀመርና ፡ ከፍጻሜ ፡ ይደርሳል ። እንግዲህ ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ቋንቋ ፡ የአእምሮ ፡ መንቀሳቀሻ ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ መግለጫ ፡ ነው ። ለአእምሮ ፡ መንቀሳቀሻ ፡ ቋንቋ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ለቋንቋም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሳቦች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልኮች ፡ ተገልጸው ፡ የንባብ ፡ ጥማትን ፡ የሚያረኩ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ ያስፈልጉታል ።

ተክለ ፡ ማርያም ፡ ፋንታዬ ፡

# መግቢያ ።

በምን ፡ ምክንያት ፡ ይህን ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ የተባለ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፍ ፡ ደረስኸው ? ተብዬ ፡ ብጠየቅ ።
ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተመላላሽ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ወደምርመራና ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ እድገት ፡ መምሪያ ፡ ተዛውሬ ፡ በጽሑፍ ፡ አዘጋጅነት ፡ ስሠራ ፡ በአማርኛ ፡ ካን ደኛ ፡ እስከ ፡ አምስተኛ ፡ የተዘጋጁትን ፡ የንባብ ፡ መጻሕ ፍት ፡ እንድመለከታቸው ፡ እየተሰጡኝ ፡ አነበብኳቸው ። እነዚህ ፡ ያነበብኳቸው ፡ መጻሕፍት ፡ እስትጉቡአውያን ፡ ድርሰቶችንና ፡ ተረቶችን ፡ የያዙ ፡ ናቸው ። አንዳቸውም ፡ ዋና ፡ መስተዋንይን ፡ በጠቅላላ ፡ ጽሑፋቸው ፡ አይዙም ። እንደዚሁም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎችን ፡ ሲገልጹ ፡ የማጣመር ተግባር ፡ እምብዛም ፡ አይገለጽባቸውም ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ለሥራ ፡ በተባበሩ ፡ መስተዋንያን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተግባሮችን ፡ ለማሳየት ፡ እንዲችል ፡ ተደርጎ ፡ ቢጻፍ ፡ አስ ቀድሞ ፡ ከተዘጋጁት ፡ መጻሕፍት ፡ ቀጥሎ ፡ ያገለግላል ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ ተቀሰቀሰብኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አሳብ ፡ እንደተቀሰቀሰብኝ ፡ ይህን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፍ ፡ ለማ ዘጋጀት ፡ የሥራ ፡ ጊዜዬ ፡ አልፈቀደልኝም ። ከዚህም ፡ የተ ነሣ ፡ በአሳቤ ፡ ብቻ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ተጠንስሶ ፡ ቆየ ።
እነሆ ፡ የመጽሐፉ ፡ መዘጋጀት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፡ በሌ ላው ፡ ሥራዬ ፡ ላይ ፡ ደርቤ ፡ በተለይ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እቤቴ ፡ እያውጠነጠንሁና ፡ እየጻፍሁ ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ልደርሰው ፡ ቻልሁ ። የመጽሐፉ ፡ አጀማመር ፡ በረ ጅም ፡ መንገድ ፡ የሚመራ ፡ ስለሆነ ፡ ገና ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ ሳለ፡ ቆሟል ።

ተክለ ፡ ማርያም ፡ ፋንታዬ ፡

# ምዕራፍ ፡ ፮ ።

ጎጃም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ አንዱ ፡ ነው ። በውስጡም ፡ ብዙ ፡ አውራጆችን ፡ የያዘ ፡ ሀገር ፡ ነው ። በሀብት ፡ በኩል ፡ ሲመለከቱት ፡ የእህል ፡ የማር ፡ የቅቤና ፡ የሰንጋ ፡ ሀገር ፡ ሆና ፡ በመገኘት ፡ እጅግ ፡ በልጽጎ ፡ ይታያል ። በስተምዕራብ ፡ በኩል ፡ አቀማመጡን ፡ አሳምሮ ፡ ለንግድ ፡ መደብርነት ፡ ምቹነትን ፡ ቀድሞ ፡ ይዟል ። በስተሰሜኑ ፡ ወሎና ፡ በጌምድር ፡ በስተምዕራቡ ፡ በጌምድርና ፡ ሱዳን ፡ በስተደቡብ ፡ ሱዳን ፡ ብቻ ፡ በስተምሥራቁ ፡ ወለጋና ፡ ሸዋ ፡ ይዋሰኑታል ። የባሕር ፡ ጠረፍን ፡ ከማጣቱ ፡ በስተቀር ፡ ከአካባቢ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶችና ፡ ሀገሮች ፡ ጋር ፡ እንደልቡ ፡ ለመነገድ ፡ የሚችል ፡ ጠቅላይ ግዛት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ታላቁን ፡ የዐባይን ፡ ወንዝና ፡ የጣናን ፡ ባሕር ፡ በብዙ ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ ተፈጥሮታዊ ፡ መብት ፡ ፈቅዶለታል ።

መተከል ፡ የዚህ ፡ ሀብታም ፡ ሀገር ፡ ዘርፍ ፡ ሆና ፡ በመገኘቷ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ደስ ፡ እንደሚላት ፡ ለመገመት ፡ አያስቸግርም ። መተከል ፡ በአቀማመጧ ፡ የጎጃምን ፡ ምዕራብ ፡ ትይዛለች ። ከወለጋና ፡ ከሱዳንም ፡ እየተዋሰነች ፡ ወደቡሬ ፡ ዳሞት ፡ ትመጣለች ። ይህች ፡ አውራጃ ፡ ቆላም ፡ ወይና ፡ ደጋም ፡ ክፍሎች ፡ ስላሉዋት ፡ ባለልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀብት ፡ ነች ። ማር ፡ ቅቤ ፡ ወርቅ ፡ የመጀመሪያ ፡ ሀብቶቿ ፡ ናቸው ። በዘመናዊ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ አልምታ ፡ በየዓመቱ ፡ የምትልከው ፡ ጥጥና ፡ የእህል ፡ ዘሮች ፡ በዓለምና ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ ገበያዎች ፡ ተገቢ ፡ ሥፍራን ፡ ይዘዋል ። እነጤፍ ፡ እነማሽላ ፡ እነሰሊጥ ፡ እነፍራፍሬዎች ፡ ወደውጭ ፡ በመላክ ፡ የሚኮራባቸው ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ።

በመተከል ፡ ውስጥ ፡ ቆላውንና ፡ ወይና ፡ ደጋውን ፡ አማክሎ ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ ጦጥልሽ ፡ የተባለ ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ አዲስ ፡ ተስፋፍቶ ፡ የቆየ ፡ ቀበሌ ፡ አለ ። ይህ ፡ ቀበሌ ፡ በበለያ ፡ ወረዳ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። ጦጥልሽ ፡ ዛሬ ፡ ቢጠሩት ፡ የማይሰማ ፡ የሀብታሞች ፡ ሀገር ፡ ሆኗል ። በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ አምሳለገነት ፡ የተባለች ፡ መንደር ፡ አለች ።

አምሳለ ፡ ገነት ፡ ከቆላው ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ደመቅ ፡ ብላ ፡ የምትታይ ፡ መንደር ፡ ነች ። እጅግም ፡ ነፋስ ፡ በማያጠቃው ፡ አነስተኛ ፡ ተረተር ፡ ጥግ ፡ በዘመናዊ ፡ የቤቶች ፡ ቅያስ ፡ ተሠርታ ፡ ዓይንን ፡ ትማርካለች ። የመስኖ ፡ ውኃ ፡ ከተረተሩ ፡ ጥግ ፡ በብዙ ፡ በኩል ፡ ይፈስላታል ። የቤት ፡ ጓሮና ፡ ደጃፎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አበቦችና ፡ አትክልት ፡ አጊጠዋል ። የመንደሩ ፡ ቤቶች ፡ በሙሉ ፡ ባላጥሮች ፡ ናቸው ፡ አጥሮቹም ፡ ባላራት ፡ ማዕዘን ፡ በመሆናቸው ፡ በማዕዘን ፡ ለቆመ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ አጥር ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ። የቤቶቹም ፡ አሠራር ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። የሁለቱም ፡ ምክንያት ፡ የአራት ፡ ማዕዘን ፡ ቅያስ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ይህች ፡ መንደር ፡ ሁለት ፡ የሽማግሌዎች ፡ መዶለቾች ፡ (ተቀምጦ ፡ መወያዮች) ፡ አሉአት ።

በዚች ፡ መንደር ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ የመኪና ፡ መንገድ ሰንጥቆ ፡ ያልፋል ። ከብዙ ፡ መንደሮች ፡ ቀበሌዎችና ፡ ወረዳች ፡ አውራጃችም ፡ በዚሁ ፡ የመኪና ፡ መንገድ ፡ ተሳስራለች ። ልዩ ፡ ልዩ፡ ሀብቶችን ፡ ትልካለች ። በለውጣቸውም ፡ ሸቀጦችንና ፡ የእርሻ ፡ መሣሪያዎችን ፡ ታስመጣለች ። በዚች ፡ መንደር ፡ ሁለት ፡ ሱቆች ፡ ወይም ፡ መደብሮች ፡ ይገኙባታል ። ሕዝቡ ፡ የሚፈልጉትን ፡ የሚገዙት ፡ ከነዚህ ፡ ሁለት ፡ መደብሮች ፡ ነው ።

አምሳለ ፡ ገነት ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃንና ፡ የአጥቢያ ፡ ትምህርትን ፡ አጣምሮ ፡ የሚሰጥ ፡ አንድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አላት ። የብዙ ፡ መንደሮች ፡ ልጆች ፡ ከሩቅ ፡ እየመጡ ፡ ይማሩበታል ። በዚህ ፡ ትምህርት፡ ቤት ፡ ተግባራውያንና ፡ አዕምሮታውያን ፡ ትምህርቶች ፡ እየተመዛዘኑ ፡ ይሰጡበታል ። የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ መርጠው ፡ የሚያሾሙት ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ናቸው ። ከመምህራኑ ፡ መካከል ፡ የሚመረጠው ፡ መምህር ፡ በትምህርቱ ፡ በዐመሉና ፡ በትጋቱ ፡ በአስተዳደሩም ፡ ተሽሎ ፡ መታየት ፡ አለበት ።



## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

አምሳለ ፡ ገነት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አማካሪዎች ፡ አሏት ። አንደኛው ፡ የትምህርትና ፡ የርዳታ ፡ አማካሪ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ሁለተኛው ፡ የመንደሪቱ ፡ ቅያስና ፡ ዕድገት ፡ ክፍል ፡ ነው ። ሦስተኛው ፡ የመንደሪቱን ፡ የሀብት ፡ ምንጭ ፡ አጥኚና ፡ እቅድ ፡ አዘጋጅ ፡ ክፍል ፡ ነው ። ሦስቱም የመንደሪቱ ፡ ሥራ ፡ መምሪያዎች ፡ ከመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች፡ ጋር ፡ በመግባባት ፡ አምሳለ ፡ ገነትን ፡ እየኰተኰቱ ፡ ያሳድጓታል ።

በአልጋ ፡ ላይ ፡ ከዋሉ ፡ በሽተኞችና ፡ የዘወትር ፡ ደዌ ፡ ካጠቃቸው ፡ ሰዎች ፡ በስተቀር ፡ በአምሳለ ፡ ገነት ፡ ገልዋዮች ፡ ፈጽመው ፡ አይገኙም ። የመንደሪቱ ፡ የሀብት ፡ ምንጭ ፡ አጥኚና ፡ እቅድ ፡ አዘጋጅ ፡ ክፍል ፡ የጉልበት ፡ ሀብት ፡ እንዳይባክን ፡ አጥብቆ ፡ ይቆጣጠራል ። አላንዳች ፡ ተግባር ፡ ሥራ ፡ ፈቶ ፡ በመንደር ፡ የሚያውደለድል ፡ ወይም ፡ መንደር ፡ ለመንደር ፡ እየዞረች ፡ ጥርስዋን ፡ የምትፈለቅቅ ፡ ሴትን ፡ በሥራ ፡ ፈትነት ፡ ይወቅሳሉ ፡ አለበለዚያም ፡ የበለጠ ቢያስቸግሩ ፡ ይቀጣሉ ።

ዕድሜአቸው ፡ ያለትምህርት ፡ የገሠገሠባቸው ፡ ወጣቶችና ፡ ጎበዛዝት ፡ በየፈናቸው ፡ መምህራንን ፡ እየጠየቁ ፡ ይማራሉ ። ትናንሾቹ ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ እየተማሩ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ በተወሰኑ ፡ ሰዓቶች ፡ በተራ ፡ ቤተሰቦቻቸውን ፡ በትምህርት ፡ ይረዳሉ ። የመንደሪቱ ፡ ዓላማ ፡ በአካባቢዋ ፡ ሀብቶች ፡ ሠርታ ፡ በልጽጋ ፡ በዓለም ፡ ገበያዎች ፡ ውስጥ ፡ ተገቢ ፡ ሥፍራን ፡ መያዝ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከደቂቅ ፡ እስከልሒቅ ፡ የግድ ፡ ለዕውቀት ፡ መታገል ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ። ሀብት ፡ ያለዕውቀት ፡ ዕውቀት ፡ ያለብዙ ፡ ትግል ፡ አይገኙም ። አምሳለ ፡ ገነት ፡ ብልኅት ፡ ጉልበት ፡ ዕውቀትም ፡ ለእድገትዋ ፡ አስፈላጊዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ተረድታ ፡ ትፍረመረማለች ።

የመንደሪቱ ፡ ቅያስና ፡ እድገት ፡ ክፍል ፡ አማካሪዎች ፡ የቤቶች፡ አሠራር ፡ እንዳይዛነፍ ፡ መንገዶች ፡ እንዳይጣመሙና ፡ ቦዮች ፡ በድንጋይ ፡ እየተሠሩ ፡ ከላይ ፡ በተላላፊ ፡ ጥርብ ፡ ድንጋዮች ፡ እንዲገ

ጠሙ ፡ አዳዲስ ፡ ቤቶች ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ በሚገጥማቸው ፡ የቅያስ ፡ ችግር ፡ እንዳይጉላሉና ፡ ሥራቸው ፡ የሚቃናበትን ፡ ምክር ፡ እንዲሰጡ ፡ የመንደሪቱ ፡ አበቦችና ፡ የጓሮ ፡ ተክሎች ፡ ሁሉ ፡ መሥመሮችን ፡ እየተከተሉ ፡ እንዲተከሉ ፡ በየመንገዶች ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ የሚተከሉ ፡ ዛፎችም ፡ ሕገኛ ፡ አቅድንና ፡ ማራኪ ፡ ውበትን ፡ እንዲያሳዩ ፡ ይሠራሉ ። አደባባዮቹ ፡ ጥላና ፡ መቀመጫ ፡ እንዲኖራቸው ፡ የከተማው ፡ መጫወቻ ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡ ቅያሱን ፡ እንደያዘ ፡ ዳርዳሩን ፡ በዛፎች ፡ እንዲያጌጥና ፡ ተመልካቾችን ፡ በጥላ ፡ እንዲያረካ ፡ ዙሪያውን ፡ በጠንካራ ፡ እንጨቶች ፡ ታጥሮ ፡ ባለጥንክር ፡ መዝጊያዎች ፡ ያሉአቸው ፡ በሮች ፡ እንዲሠራለት ፡ እያቀዱ ፡ ያስፈጽማሉ ።

የሀብት ፡ ምንጭ ፡ አጥኚና ፡ እቅድ ፡ አዘጋጅ ፡ ስለእርሻና ፡ ስለከብት ፡ ርቢ ፡ ስለደን ፡ ልማትም ፡ ጠቃሚ ፡ ምክሮችንና ፡ አስፈላጊ ፡ ረዳቶችን ፡ በየጊዜው ፡ ከእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ የቅርብ ፡ ባለሥልጣኖች፡ ያገኛል ። ይህንም ፡ ለሕዝቡ ፡ እያስታወቀ ፡ ዘመናዊ ፡ የእርሻ ፡ ተግባርን ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ። በዚህም ፡ የትጋት ፡ ሥራ ፡ መሠረት ፡ የሕዝቡ ፡ ኑሮና ፡ የየዓመቱ ፡ የእህል ፡ ገቢ ፡ እያደገ ፡ ይሄዳል ። ፍራፍሬዎች ፡ ሐምሎችና ፡ ወተት ፡ ከነጓዙ ፡ በየሰዓታቸው ፡ ወደአቅራቢያ ፡ ከተሞች ፡ ይላከሉ ። መጓጓዣቸውንና ፡ ገበያዎቻቸውን ፡ እየተመለከተ ፡ ሥራውን ፡ የሚመራው ፡ የሀብት ፡ ምንጭ ፡ አጥኚና ፡ እቅድ ፡ አዘጋጅ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ነው ።

በመንደሪቱ ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ የሳምንት ፡ ገባዮች ፡ ተቋቁመዋል ። ከሩቅ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ ገበያተኞች ፡ ይመጣሉ ። በነዚህ ፡ ገበያዎች ፡ ብዙ  ነገሮች ፡ ይገዛሉ ፡ ይሸጣሉ ።  ግንዲሎች ፡ ጠርቦችና ፡ መጠነኞች ፡ ማዕዘኖች ፡ ይመጣሉ ። እነሽመል ፡ እነቀርቅሃና ፡ እነጭረት ፡ ይጎርፋሉ ። እንዲሁም ፡ ብዙ ፡ ገመዶች ፡ ይመጣሉ ። ጥሩ ፡ ጥሩ ጌጠኛ ፡ ቀፎችም ፡ ከያሉበት ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ይላሉ ። እነማርና ፡ እነቅቤ ፡ ገበያዎቹን ፡ ርስት ፡ አድርገዋቸዋል ። የወፍጮና ፡ የቅባት ፡ እህሎች ፡ በብዛት ፡ ይገኛሉ ። ቡና ፡ በብዛት ፡ ይጎርፋል ። የሀብት ፡ አጥኚና ፡ እቅድ ፡ አዘጋጅ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የአምሳለ ፡ ገነትን ፡ ሀብታዊ ፡ የደም ፡ ሥሮች ፡ በየጊዜው ፡ እያጠና ፡ በተሻለ ፡ መንገድ ፡ ይመራል ። በተጨማሪ ፡ በሀብት ፡ ምንጭ ፡ አጥኚና ፡ እቅድ ፡ አዘጋጅ ፡ አማካሪዎች ፡ ሥር ፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ውሎች ፡ አጥኚ፡



ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ተቋቁሟል ። ይህ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የመሬቶችን ፡ ኪራይ ፡ ያሻሽላል ። የለም ፡ መሬቶችን ፡ ኪራይ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፡ እንደዚሁም ፡ የለም ፡ ከጠፎችን ፡ ያሳንሳል ። ይህ ፡ ንኡስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በመቋቋሙ ፡ አራሾች ፡ በዝተዋል ፡ እንዲያውም ፡ ብዙ ፡ ባይተዋሮች ፡ መጉረፍ ፡ ይዘዋል ። ኢንዱስትሪዎችንም ፡ ለማቋቋም ፡ ብዙ፡ ሀብታም ፡ ነጋዴዎች ፡ ማንዣበብ ፡ ጀምረዋል ።

የትምህርትና ፡ የርዳታ ፡ አማካሪ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ችግር ፡ መርጃ ፡ የሚሆን ፡ ከሕዝቡ ፡ ላይ ፡ የእድር ፡ ገንዘብ ፡ ይቀበላል ። በሚያገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ረዳት ፡ የሌሏቸውን ፡ ልጆች ፡ ያስተምራል ፡ ጧሪ ፡ የሌላቸውን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይረዳል ፡ በየመንደሩ ፡ እየዞሩ ፡ የአፍአና ፡ የቤት ፡ ውስጥ ፡ ሙዮችን ፡ የሚያስተምሩ ፡ መምህራንን ፡ ይረዳል ።

አምሳለ ፡ ገነት ፡ የአካባቢ ፡ መንደሮችን ፡ በትምህርትና ፡ ሠርቶ ፡ በማሳየት ፡ ትመራለች ። የእርስዋን ፡ አርአያ ፡ ለመከተል ፡ ብዙ ፡ መንደሮች ፡ ይሞክራሉ ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ እየተመረጡ ፡ የአምሳለ ፡ ገነትን ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋቋምና ፡ አመራር ፡ ያጠናሉ ። አምሳለ ፡ ገነት ፡ ከአካባቢ ፡ መንደሮች ፡ በሥፍራዋ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አትሻልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥራ ፡ ከደማቸው ፡ የተዋሐደባቸው ፡ ሰዎች ፡ ስለሠፈሩባት ፡ ብቻ ፡ ትልቃለች ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ከጥዋት ፡ እስከ ፡ እኩለ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አእምሮታውያን ፡ ትምህርቶችን ፡ በትጋት ፡ ያስተምራል ። ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ ግን ፡ ተግባራውያን ፡ ትምህርቶችንና ፡ ድራማን ፡ ( ተውኔትን ፡ ) በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስልት ፡ ያስተምራል ። በዚህ ፡ የትምህርት ፡ አመራር ፡ ወላጆች ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደስተውበት ፡ ለመማሪያ ፡ መሣሪያዎች ፡ መግዣ ፡ በየጊዜው ፡ እጃቸውን ፡ ይዘረጋሉ ።

አእምሮታውያን ፡ ትምህርቶች ፡ የሚባሉት ፡ የቋንቋ ፡ የጥበብ ፡ የመልክዓ ፡ ምድር ፡ የታሪክ ፡ የሒሣብ ፡ የግብረ ፡ ገብነትና ፡ የሙ

ዚቃ ፡ ትምህርቶች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ አርእስት ፡ እንደገና ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ቢዘረዘሩ ፡ አገር ፡ ምድሩን ፡ ይሞላሉ ። የነዚህ ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ ቋንቋ ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ጥቂት ፡ ገልጸን ፡ ለተመልካች ፡ ምዘናና ፡ ምርመራ ፡ እናልፋቸዋለን ።

መምህር ፡ ለተማሪዎቹ ፡ ትምህርቱን ፡ የሚያስተላልፈው ፡ በምን ፡ ይሆን ? የቤተሰብና ፡ የጎረቤቶች ፡ አሳብ ፡ መለዋወጫ ፡ ምን ፡ ይሆን?እያሉ ፡ ራስን ፡ በራስ ፡ ቢጠይቁት ፡ አእምሮ ፡ ሁሉንም ፡ አቀነባብሮ ፡ ይመልሳል ። ራስን ፡ በራስ ፡ ካልጠየቁና ፡ አእምሮን ፡ ካላንቀሳቀሱት ፡ የምርመራ ፡ ተግባር ፡ ይተኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሲያንቀሳቅሱት ፡ መምህርና ፡ ተማሪዎች ፡ ቤተሰብና ፡ ጎረቤቶች ፡ የዕለት ፡ ተግባራቸውን ፡ ለማካሄድ ፡ በቋንቋ ፡ ይግባባሉ ። መጀመሪያ ፡ መደማመጥ ፡ በማስፈለጉ ፡ የቋንቋ ፡ ሚዛን ፡ በየጊዜው ፡ እየደፋ ፡ ይሄዳል ። መደማመጥ ፡ መግባባትን ፡ ያስከትላል ። መግባባትም ፡ ወደስምምነት ፡ እየመራ ፡ ያደርሳል ። በስምምነት ፡ ሥራ ፡ ይጀመርና ፡ ከፍጻሜ ይደርሳል ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ያለ ፡ ቋንቋ ፡ አእምሮ ፡ አይንቀሳቀስም ። በዚህ ፡ አነጋገራችን ፡ ድዶችንና ፡ ምላስ ፡ ቁርጦችን ፡ አንጨምራቸውም ። ሰው ፡ ሲያስብ ፡ አሳቡን ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ የሚመራው ፡ በቋንቋ ፡ ስለሆነ ፡ አሳብ ፡ ከቋንቋ ፡ በኋላ ፡ እንጂ ፡ አስቀድሞ ፡ አይመጣም ። ሳይታሰብም ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ አይነደፍም ። ስለዚህ ፡ የአእምሮታውያን ፡ ትምህርቶች ፡ መሠረት ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡ እንላለን ።

የእጅ ፡ ሥራ ፡ ትምህርት ፡ በተለይ ፡ በአናጢነት ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ስንመለከት ፡ የመለካት ፡ የመሰንጠቅ ፡ የመቁረጥ ፡ የመላግ ፡ የማገጣጠምና ፡ ቅርጽ ፡ የማውጣትን ፡ ተግባር ፡ ያጠቃልላል ። እንዚህም ፡ ተጠናቀው ፡ ሲታወቁ ፡ ዝርግ ፡ መቀመጫን ፡ መደርደሪያን ፡ ወንበርንና ፡ ጠረጴዛን ፡ ወደመሥራት ፡ ይመራሉ ። እያደርም ፡ የበለጡ ፡ ጌጣጌጦችን ፡ ጭምር ፡ እስከ ፡ መሥራት ፡ ያደርሳሉ ። የቤት ፡ ውቅርና ፡ መዝጊያዎች ፡ ሁሉ ፡ ከነዚህ ፡ ካለፉት ፡ የተለዩ ፡ አይደሉም ። ሁሉም ፡ ነገር ፡ ይያያዛል ። በእንጨት ፡ ሥራ ፡ መሠረት ፡ የቀሩትንም ፡ የተግባር ፡ ቅርንጫፎች ፡ ቢመለከቱአቸው ፡ በቀላሉ ፡ ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ ሊታዩ ፡ ይችላሉ ።

ድራማ ፡ (ተውኔት) የሕዝብን ፡ አመራር ፡ ወይም ፡ ዝንባሌ ፡ ምላ ፡ ከጎደል ፡ በወርቃወርቅ ፡ ወይም ፡ በሰምና ፡ በወርቅ ፡ ወይም ፡



በኅብር ፡ ወይም ፡ በሰም ፡ ለበስ ፡ ወይም ፡ በአንጻር ፡ አነጋገር ፡ የሚገልጽ ፡ ተግባር ፡ ነው ። ድራማ ፡ የወጠነውን ፡ አሳብ ፡ በቃላት ፡ በሰውነትና ፡ በተግባር ፡ እያስማማ ፡ ወይም ፡ እያቀነባበረ ፡ ለአድማጮች ፡ ያስረዳል ። መጽሐፍ ፡ ይናገራል ፡ ስንል ፡ ሰው ፡ በመጽሐፍ ፡ ይጠቀማል ፡ ማለታችን ፡ እንደሆነ ፡ እንዲሁም ፡ ድራማ ፡ ያስረዳል ፡ ስንል ፡ የድራማ ፡ ተጨዋቾች ፡ በድራማ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ አሳብ ፡ ይገልጻሉ ፡ ማለት ፡ ነው ።

የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ልጆች ፡ አእምሮታውያንንና ፡ ተግባራውያንን ፡ ትምህርቶች ፡ አጣምረው ፡ በመማራቸው ፡ ቢተ ፡ ሰቦቻቸውን ፡ ለመርዳት ፡ ይችላሉ ። በተወሰነላቸው ፡ ፕሮግራም ፡ መሠረት ፡ ትምህርታቸውን ፡ እያጠናቀቁ ፡ በቤት ፡ ደግሞ ፡ ወላጆቻቸውን ፡ ያግዛሉ ። በአናጢነት ፡ ተግባር ፡ የገፉት ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ የተጓደለን ፡ አነስተኛ ፡ የእንጨት ፡ ሥራ ፡ ያቃናሉ ። በእርሻም ፡ በኩል ፡ ዝንባሌ ፡ ያላቸው ፡ ልጆች ፡ በቤት ፡ ጓሮ ፡ ተክሎችን ፡ በመኮትኮትና ፡ በማጠጣት ፡ በማረምም ፡ ይረዳሉ ። ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ በዶሮ ፡ አረባብ ፡ ተግባር ፡ በመሠልጠን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አገልግሎትን ፡ ይሰጣሉ ። የነጋዴዎቹም ፡ ልጆች ፡ በሒሳብ ፡ በኩል ፡ ቤቶቻቸውን ፡ ያግዛሉ ። በጠቅላላው ፡ ልጆች ፡ በየተማሩት ፡ መሥመር ፡ በተለይ ፡ ዝንባሌአቸው ፡ ባመዘነበት ፡ በኩል ፡ ቤቶቻቸውን ፡ በመርዳታቸው ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ የኑሮ ፡ ችግር ፡ እየተቃለለ ፡ ይሄዳል ።

የድሮው ፡ የቃል ፡ ትምህርትና ፡ የዛሬው ፡ ሲወዳደር ፡ ልዩነቱ ፡ እንደ ፡ ሰማይና ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ ነው ። የድሮው ፡ ከእጅ ፡ ጽሕፈት ፡ ጋር ፡ ባለመያያዝ ፡ ይጠና ፡ ስለነበር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የቃል ፡ ጥናት ፡ ኃይል ፡ እንደገነነ ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ድረስ ፡ ኖረ ። እገሌ ፡ መጽሐፍ ፡ በጉንጩ ፡ ነው ፡ እያሰኘ ፡ ብዙ ፡ የቃል ፡ ሊቃውንትን ፡ ሲያስመሰግን ፡ ኖሯል ። የዛሬው ፡ ግን ፡ ከእጅ ፡ ጽሕፈት ፡ ጋር ፡ ተባብሮ ፡ መሄድ ፡ ስላለበት ፡ የቃል ፡ ጥናት ፡ ኃይል ፡ እየተቀነሰ ፡ መሄድ ፡ ይዟል ። የድሮ ፡ ትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ እጅግ ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ የዛሬው ፡ የትምህርት ፡ ዓይነቶች ፡ እጅግ ፡ የበዙ ፡ ናቸው ። እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ በቀላሉ ፡ በቃል ፡ ለማጥናት ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የእጅ ፡ ጽሕፈትን ፡ ተምሮ ፡ በየጊዜው ፡ ማስታወሻን ፡ እየጻፉ ፡ መመልከት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ። ከዚ

ሀም ፡ በላይ ፡ የመጻሕፍት ፡ ዝግጅት ፡ የደብዳቤዎች ፡ ጎርፍንትና ፡ የመዝገቦች ፡ አጻጻፍ ፡ እየበረከተ ፡ በመሄዱ ፡ በየትምህርቱ ፡ ጽሕፈት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነ ።

የቦታ ፡ ርቀት ፡ በማመላለሻ ፡ ድርጅቶች ፡ ስለተሸነፈ ፡ ሰዎች ፡ በጣም ፡ ተቀራርበዋል ። ራሳቸውም ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ለመገናኘት ፡ ችለዋል ። በደብዳቤዎችማ ፡ ዘወትር ፡ እንደተገናኙ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የጽሑፎች ፡ ኃይል ፡ እየበረከተና ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ። እንዲያውም ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ እንዲያነብና ፡ እንዲጽፍ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ታውቆ ፡ የአጥቢያ ፡ ትምህርት ፡ በመፋጠን ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

ትምህርት ፡ ቤትንና ፡ ኑሮን ፡ አዋሕዶ ፡ በመጠቀም ፡ በአንደኛነት ፡ ማዕርግ ፡ የተገኘች ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ እንደምትገኝ ፡ ለመገመት ፡ ቀላል ፡ ነው ። ይህ ፡ ተፋጣኝ ፡ ርምጃዋ ፡ እየገፋ ፡ ባለማቋረጥ ፡ የቀጠለ ፡ እንደሆነ ፡ በተገመተችበት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ለመገኘት ፡ የሚያዳግታት ፡ ምንም ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ አይኖርም ። የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሕዝብ ፡ በኑሮው ፡ መንዛዛትን ፡ በማስወገዱ ፡ ገንዘቡ ፡ በከንቱ ፡ አልሆነ ፡ ሥፍራ ፡ አይወድቅም ። ትምህርት ፡ ኑሮውን ፡ መጥኖለታል ፡ ብንል ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አዳጋች ፡ አነጋገር ፡ አይሆንብንም ።

የሰው ፡ ጉልበት ፡ አላገባብ ፡ ሊባክን ፡ አልቻለም ፡ ሕዝቡ ፡ ኑሮውን ፡ በፕሮግራም ፡ አግብቶታል ። የሥራና ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜያትም ፡ በየቤተሰቦች ፡ ኑሮ ፡ መጠን ፡ ተመዛዝነውና ፡ ተስተካክለው ፡ ይፈራረቃሉ ። ሥራ ፡ ፈቶች ፡ ባለመኖራቸው ፡ ጭቅጭቅና ፡ ክርክር ፡ ፈጽሞ ፡ አይገኙም ። በአምሳለ ፡ ገነት ፡ እንጀራ ፡ በከንቱ ፡ አይበላም ። የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሕዝብ ፡ ሠራተኛ ፡ በመሆኑ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ነው ። ተርፎት ፡ ሀብቱን ፡ ያራባል ፡ እንጂ ፡ አይቸገርም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የመንግሥቱ ፡ ግብር ፡ በየጊዜያቱ ፡ ይገባል ። የግብሩም ፡ ገቢ ፡ ከሌሎች ፡ መንደሮች ፡ ጋር ፡ ሲወዳደር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የላቀ ፡ ነው ።

ሥራ ፡ ሕይወታችሁ ፡ ሲጋብዛችሁ ፡
ቶሎ ፡ አቤት ፡ በሉ ፡ እንጂ ፡ አትሳቁ ፡ እንዲሁ ።



እኔ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ እጄን ፡ ስዘረጋ ፡
በዙሪያዬ ፡ አጅቡኝ ፡ እንደመልካም ፡ መንጋ ።
ትምህርት ፡ ከሥራ ፡ ጋር ፡ ካልተገናዘበ ፡
ትምህርት ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ ብሎ ፡ ካልታሰበ ፡
ወደፊት ፡ መራመድ ፡ መግሥገሥ ፡ የለም ፡
በንግግር ፡ ብቻ ፡ ቢቀድሙ ፡ ካለም ።
ስለዚህ ፡ ልጆቼ ፡ አደራ ፡ አደራ ፡
እጃችሁ ፡ ይቀልጥፍ ፡ አእምሯችሁ ፡ ይሥራ ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ከአምሳለ ፡ ገነት ፡ አራሾች ፡ በግብርናው ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የገነነ ፡ አቶ ፡ እውነቱ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ነበር ። አቶ ፡ እውነቱ ፡ አራሽ ፡ ገበሬ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በግብረ ፡ ገብነት ፡ የተጠመደ ፡ ጸሎተኛ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ባለቤቱም ፡ እመት ፡ ትብለጥ ፡ ትዕግሥት ፡ የብራና ፡ ዳዊትዋን ፡ በቀን ፡ እየመጠነች ፡ ሳታንበለብል ፡ አትውልም ፡ ነበር ። አቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታ ፡ ከባለቤቱ ፡ ከእመት ፡ ትብለጥ ፡ ትዕግሥት ፡ ሳይማከር ፡ በሀብታቸው ፡ ብቻውን ፡ አያዝበትም ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ትክክለኛውን ፡ መሥመር ፡ ይዘው ፡ በመጓዛቸው ፡ በምሳሌነት ፡ ተግባራዊ ፡ ትምህርትን ፡ ዘወትር ፡ ያስተምራሉ ።

አቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታና ፡ እመት ፡ ትብለጥ ፡ ትዕግሥት ፡ አራት ፡ ልጆች ፡ ወልደዋል ። ልጆቹም ፡ ዘለቀ ፡ እምቧ ፡ አሳለፈልኝና ፡ ደማሜ ፡ ናቸው ። በቤትም ፡ ደመቀ ፡ በጊዜውና ፡ ካብትሽ ፡ ይመር ፡ ዘር ፡ ይሁን ፡ የተባሉ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አሽከሮች ፡ አሉ ። አሽከሮቹ ፡ ቅኖችና ፡ ታዛገሮች ፡ በመሆናቸው ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ እጅግ ፡ የተወደዱ ፡ ናቸው ። ደመቀ ፡ በጊዜው ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ወንጭፍ ፡ ስለሆነ ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ አርአያውን ፡ ለመከተል ፡ ይሞክራሉ ። የሥራ ፡ እምረትና ፡ ቅልጥፍና ፡ ለማንም ፡ አልተሰጠም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ እንኳን ፡ ቤተሰቡን ፡ የውጭ ፡ ሰዎችንም ፡ ያስቀናል ።

አቶ ፡ እውነቱ ፡ መኪታ ፡ ደሙቀ ፡ በጊዜውን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ማለዳ ፡ ጠርቶ ፡ በቆላ ፡ እርሻቸው ፡ የሚገኙትን ፡ ገበሬዎች ፡ ጠይቆ ፡ እንዲመለስ ፡ ላከው ። እርሱም ፡ መልእክቱን ፡ ለመፈጸም ፡ ወደ ፡ ቆላ ፡ ሲወርድ ፡ የኢየሱስን ፡ የፍልውኃ ፡ ጠበለተኞች ፡ አግኝቶ ፡ እየተጫወተ ፡ ከቆላው ፡ አፋፍ ፡ ደረሰ ። ከጠበለተኞቹ ፡ ጋር ፡ ዳገቱን ፡ ጨርሰው ፡ ከዘብጡ ፡ ሲደርሱ ፡ ተለያዩና ፡ ወደየሚሄዱበት ፡ አመሩ ። ደመቀ ፡ ሽንቱን ፡ ለመሽናት ፡ ከመንገዱ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ከአንድ ፡ ቋጥኝ ፡ ሥር ፡ እንደቆመ ፡ አንድ ፡ ጊንጥ ፡ ከእግሩ ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ ላይ ፡ ነደፈችው ። ለጊዜው ፡ ሕመሙ ፡ ምንም ፡ አልተሰማውም ፡ ነበርና ፡ መርዙን ፡ የመከላከያ ፡ ዘዴ ፡ አላሰበም ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደመንገዱ ፡ ተመልሶ ፡ ገብቶ ፡ ጉዞውን ፡ እንደቀጠለ ፡ የእግሩ ፡ አውራጣትንድፍ ፡ ይነዝረው ፡ ጀመር ። አሁንም ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ እንዳለ ፡ ሰውነቱን ፡ ወረረውና ፡ መሄድ ፡ አቃተው ። ጠበለተኞቹ ፡ እንዳይረዱት ፡ አንድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተረተር ፡ አልፈው ፡ ርቀው ፡ ሄደዋል ። እርሱ ፡ ወደፊት ፡ ገፍቶ ፡ እንዳይሄድ ፡ የጊንጥ ፡ መርዝ ፡ አብረክርኮታል ። በአውራ ፡ ጎዳና ፡ ላይ ፡ አይደል ፡ ተላላፊ ፡ መንገደኛ ፡ አይረዳው ። እርሱ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ እርሻቸው ፡ ከሚወስደው ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ወድቋል ። እንዲያውም ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እንዳይጮህ ፡ ሰውነቱ ፡ ዝሎ ፡ ተዝለፍልፎአል ።

እንግዲህ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ከመጋደም ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ ሊያደርግ ፡ አልቻለም ። አደጋ ፡ ሲመጣ ፡ የችግሩ ፡ ጋጋታ ፡ መቼም ፡ አያድርስ ፡ ነው ። ውኃ ፡ ጥም ፡ አነደደው ፡ የቆላው ፡ ሙቀት ፡ ገረፈው ። ሰው ፡ ጠፋ ፡ ልቡ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ባባ ፡ ሰውነቱ ፡ ይንዘፈዘፍ ፡ ጀመር ። አይዋል ፡ የለም ፡ ዋለ ፡ ቀኑም ፡ ያመት ፡ ያህል ፡ ከመርዘሙ ፡ በስተቀር ፡ መሸ ። ጀንበሪቱ ፡ ተቆለቆለች ። እንዳጋጣሚ ፡ በአቅራቢያው ፡ አንድ ፡ የወደቀ ፡ ጥንብ ፡ ኖሯል ። ድንግዝግዝ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ የጅብ ፡ ልጆች ፡ ወደጥንቡ ፡ ተሰበሰቡ ። እየዘነቸሩ ፡ ያስካካሉ ፡ ያጎራሉ ፡ ይፈነድቃሉ ። ድምፃቸው ፡ የደም ፡ አይጠማሽን ፡ ገመገም ፡ እስኪዞር ፡ ድረስ ፡ ሸለቆ ፡ ለሸለቆ ፡ እየተቀባበለ ፡ ይጫጪሃል ። ደመቀ ፡ በጊዜው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጨነቀው ፡ ጠበበው ፡ እዬጉድ ! ደከሚል ፡ ዝሏል ፡ አሞቱ ፡ ሁሉ ፡ ፈስዋል ። እንዲሁ ፡ እንደተጨነቀ ፡ እንደተጠበበ ፡ ጅቦቹም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጥተው ፡ ሳይናጠ



ቁት ፡ ነጋ ። እንዳይነጋ ፡ የለም ፡ እኮ ! ባሳር ፡ በመከራ ፡ ነጋ ። የጊንጢቱ ፡ መርዝ ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ አልሰጠውም ፡ እንጂ ፡ ሰውነቱን ፡ ጨርሶ ፡ በማድከም ፡ አፍዞታል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ደመቀ ፡ በጊዜው ፡ ማታ ፡ ይመለሳል ፡ ተብሎ ፡ ቢጠበቅ ፡ ከወዴት ፡ ይምጣ ። እርሱ ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ወድቋል ። ቤተ ፡ ሰቡ ፡ አሥር ፡ አሥራ ፡ ምስቱን ፡ መላ ፡ ይመታ ፡ ጀመር ። እመት ፡ ትብለጥ ፡ ትዕግሥት ፡ « ደመቀ ፡ በጊዜው ፡ ጤና ፡ አይደለም ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ሊቆይ ፡ አይችልም ፡ ሥጉ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ » እያለች ፡ ታስብ ፡ ጀመር ።

አቶ ፡ እውነቱ ፡ መኪታ ፡ ደግሞ ፡ « ይህ ፡ መንገድ ፡ ዘወትር ፡ ጠሙን ፡ አይውልም ፡ አያድርምም ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ከብት ፡ የደከመበት ፡ ሰው ፡ በመንገድ ፡ አግኝቶ ፡ ሲረዳ ፡ ቆይቶ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ አንዳችም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ አይገጥመውም ። ስለዚህ ፡ ሲሆን ፡ እስከ ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ወይም ፡ ጧት ፡ ይመጣ ፡ ይሆናል ፡ » ሲል ፡ ተናግሮ ፡ መላ ፡ ቤተሰቡን ፡ አጽናናው ።

አሳለፈልን ፡ እውነቱ ፡ « ደመቀ ፡ በጊዜው ፡ የሄደው ፡ ወደ ፡ ገበሬዎቻችን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እነርሱ ፡ ከእኛ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሲወርድላቸው ፡ ይደሰታሉ ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ውለህ ፡ አድረህ ፡ ትወጣለህ ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ባሁኑ ፡ አትመለስም ፡ ብለውት ፡ ይሆናል ። እርሱም ፡ በበኩሉ ፡ የሥፍራና ፡ የሥራ ፡ ለውጥ ፡ ስለሚሆንለት ፡ ጥቂት ፡ ልቆይ ፡ ብሎ ፡ አስቦ ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ አትጨነቁ ፡ እርሱ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ሲጠግባቸው ፡ ይመለሳል ። አለበለዚያ ፡ ዘለቀና ፡ እኔ ፡ ነገ ፡ እንውረድና ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ አይተን ፡ እንመለስ ፡ » ሲል ፡ አሳቡን ፡ ገለጸ ።

ዘለቀ ፡ እውነቱ ፡ « ነገ ፡ ፈተና ፡ አለብን ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመቅረት ፡ አንችልም ። ምናልባት ፡ ነገ ፡ ያልመጣ ፡ እንደሆነ ፡ ከነገወዲያ ፡ እንወርድና ፡ ጠይቀን ፡ እንመለሳለን ፡ እንጂ ፡ ነገስ ፡ ፈጽሞ ፡

አይሆንልንም ። ደግሞስ ፡ ቅድም ፡ አሳለፈልን ፡ እንደተናገረው ፡ ገበሬዎቹ ፡ አቆይተውት ፡ እንደሆን ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ ይመጣ ፡ የለምን ? ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ ስለምን ፡ እንቸገራለን ፡ » ሲል ፡ ተናገረ ።

ካብትሽ ፡ ይመር ፡ ዘሪይሁን ፡ « እባካችሁ ፡ ጌቶቼ ፡ ዝም ፡ አትበሉ ፡ ልጁ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ የሚማግጥ ፡ አይደለም ። የተነገረውን ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አትቍጠሩት ። ደመቀ ፡ በጊዜውን፡ አደጋ ፡ አግኝቶት ፡ ይሆናል ። አለበለዚያ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የሥራ፡ ጊዜውን ፡ በከንቱ ፡ ሊያሳልፍ ፡ የሚችል ፡ አይደለም ። እንደ ፡ እኔ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ጨምራችሁ ፡ አሁኑኑ ፡ በዳቦት ፡ ብትወርዱና ፡ ብትፈልጉት ፡ ይሻላል ፡ » አለች ።

እመት ፡ ትብለጥ ፡ ትዕግሥተ ፡ « አሁን ፡ ካብትሽ ፡ ይመር ፡ የምትናገረው ፡ ባለማሰብ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ ለመፈለግ ፡ አንድ ፡ ጎራ ፡ ሕዝብ ፡ በጨለማ ፡ እየተደናበረ ፡ ይለቅ ፡ ማለት ፡ እኮ ፡ ይሆናል ። እኔ ፡ ከልጆቼ ፡ ውስጥ ፡ አሁን ፡ በጨለማ ፡ አንዱንም ፡ አልለቅ ። ስለዚህ ፡ ሁላችሁም ፡ አሁን ፡ ራታችሁን ፡ ብሉና ፡ እርፉችሁ ፡ ተኙ ። ነገ ፡ ያልመጣ ፡ እንደሆን ፡ በጉዳዩ ፡ እናስብበታለን ፡ » ብላ ፡ ንግግራቸውን ፡ ገታችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ ወደ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ተያይዘው ፡ ሄዱ ።

በማግሥቱ ፡ አሳለፈልን ፡ ዘለቀና ፡ አምኃ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ የታቀደላቸውን ፡ ፈተና ፡ አራገፉት ። አቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታም ፡ ከደጋው ፡ እርሻው ፡ ከሠራተኞች ፡ ጋር ፡ ውደቅ ፡ ተነሣ ፡ ሲል ፡ ዋለ ። ሴቶቹም ፡ እንደተለመደው ፡ የቤት ፡ ሥራቸውን ፡ ሲያካሂዱ ፡ ዋሉ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ካብትሽ ፡ ይመር ፡ እጅግ ፡ ተጨንቃ ፡ ውላለች ። ማታ ፡ ቤተሰቡ ፡ ሲሰበሰብ ፡ እንደገና ፡ የደመቀን ፡ ነገር ፡ አንሥቶ ፡ ሲነጋገርበት ፡ አመሸ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አጥጋቢ ፡ ፕሮግራም ፡ አልተደረገም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ወርደው ፡ እንዲጠይቁ ፡ በጉዳዩ ፡ ተነጋግረው ፡ ሰዓቱን ፡ ሳይወስኑ ፡ አደሩ ።

በማግስቱ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ከአሳለፈልን ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቆላ ፡ እንዲወርዱ ፡ ተደረገና ፡ አሳለፈልን ፡ ለድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ መርጃ ፡ የሚሆን ፡ መድኃኒትና ፡ የቁስል ፡ ማሰሪያ ፡ እንደዚሁም ፡ ለትኩሳትና ለብርታት ፡ የሚያገለግል ፡ መድኃኒት ፡ ይዞ ፡ አብረው ፡ ወረዱ ።



## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

አሳለፈልን ፡ የመጀመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ የሕክምና ፡ ርዳታን ፡ ከየት ፡ ለመማር ፡ እንደቻለ ፡ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ አብራርቶ ፡ እንዲነግራቸው ፡ ጠየቁት ።

አሳለፈልን ፡ —

« የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንኳን ፡ ይህን ፡ የመጀመሪያ ፡ የሕክምና ፡ ርዳታ ፡ ሌሎችንም ፡ ከፍተኞች ፡ ነገሮች ፡ ያስተምራል ። ከትምህርቶቻችን ፡ አንዱ ፡ ራሳችንንና ፡ ሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ አጋጣሚ ፡ አደጋ ፡ ሲያገኘንና ፡ ሲያገኛቸው ፡ እንዴት ፡ ለመርዳት ፡ እንደምንችል ፡ መማር ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ ትምህርትአችን ፡ መጀመሪያ ፡ ከአደጋ ፡ መጠበቅን ፡ እንማራለን ።

እናንት ፡ እንደምታውቁት ፡ በአምሳለ ፡ ገነት ፡ መንደር ፡ መካከል ፡ የሚተላለፉት ፡ መኪኖች ፡ ብዛት ፡ በየጊዜው ፡ እየቀጠለ ፡ መሄድ ፡ ይዟል ። ስለዚህ ፡ ልጆች ፡ ከድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ እንዳይወድቁና ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸውን ፡ እንዳያሳቅቁ ፡ ትምህርታዊ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ በየጊዜው ፡ ይሰጣቸዋል ። የመኪና ፡ መንገዶችን ፡ ለማቋረጥና ፡ በመኪና ፡ መንገዶች ፡ ዳር ፡ መሄድ ፡ ለትንንሽ ፡ ልጆች ፡ ምንም ፡ አደጋ ፡ የሚያመጣ ፡ አይመስላቸውም ። እንዲያውም ፡ አንዳንዶቹ ፡ በመኪና ፡ ኋላ ፡ ለመንጠላጠል ፡ ይፈልጋሉ ። ስለዚህ ፡ መጀመሪያ ፡ ለማቋረጥ ፡ ሲመጡ ፡ የመኪና ፡ መንገዱን ፡ ግራና ፡ ቀኝ እየተመለከቱ ፡ ሲያቋርጡ ፡ ከግራና ፡ ከቀኛቸው ፡ የሚመጡት ፡ መኪኖች ፡ እንደማይደርሱባቸው ፡ ሆነው ፡ እንዲያቋርጡ ፡ ያስተምሯቸዋል ። ቀጥሎም ፡ ካቋረጡም ፡ ወዲያ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ሳያቋርጡ ፡ በመኪና ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ ሲሄዱ ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ እንዲሄዱና ፡ የመኪናውን ፡ መንገድ ፡ ፈጽመው ፡ ለመኪና ፡ እንዲለቁ ፡ ይነገራቸዋል ። እንደዚሁም ፡ ከመኪኖች ፡ ኋላ ፡ እንዳይንጠላጠሉና ፡ በመኪና መንገድ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይጫወቱ ፡ ይመከራሉ ። ይህ ፡ አሁን ፡ የምነግራችሁ ፡ ሁሉ ፡ ትምህርት ፡ መሆኑን ፡ አትርሱ ።

ልጆች ፡ አንድ ፡ ዛፍ ፡ በሚቆረጥበት ፡ አቅራቢያ ፡ ሲያልፉ ፡ ርቀው ፡ እንዲሄዱ ፡ አለበለዚያ ፡ ግን ፡ ቆራጮችን ፡ ጠይቀው ፡ ማለፍ ፡ እንዳለባቸው ፡ ወይም ፡ በገመድ ፡ ተወጥሮ ፡ እንደሆን ፡ የሚወድቅበትን ፡ አቅጣጫ ፡ ገምተው ፡ መሄድ ፡ እንዳለባቸው ፡ ብርቱ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ይሰጣቸዋል ። እንደዚሁም ፡ ስለኩሬዎች ፡ ስለባሕሮች ፡ ስለወንዞችና ፡ ስለጫወታ ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ሕጎችን ፡ በየጊዜው ፡ ይማራሉ ።

አሁን ፡ እንግዲህ ፡ ስለመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ የሕክምና ፡ ርዳታ ላትትላችሁ ፡ እፈትዳለሁ ። ማንም ፡ ሰው ፡ መጀመሪያ ፡ ሲቆስል ፡ አልኮል ፡ በሚባል ፡ ለብላቢ ፡ ውኃ ፡ ዓይነት ፡ መድኃኒት ፡ ተጠርጎ ፡ አይዲን ፡ በሚባል ፡ ሁለተኛ ፡ መድኃኒት ፡ ተቀብቶ ፡ በንጹሕ ፡ እራፊ ፡ ከተሸፈነ ፡ በኋላ ፡ ጥጥ ፡ ተደርጎበት ፡ ይታሰርለታል ። ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ትምህርት ፡ የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ መምህር ፡ ያስተምራል ። እባብ ፡ ወይም ፡ ጊንጥ ፡ የነከሱት ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት፡ ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ የሚደረገውን ፡ ሕክምና ፡ ያስተምራል ፡» ሲል ፡ አስረዳቸው ።

እነዚያ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ሲጠይቁና ፡ አሳለፈልን ፡ ሲያስረዳ ፡ የመንገዱ ፡ ድካምና ፡ ርቀት ፡ ሳይታወቃቸው ፡ ወደ ፡ እናሳለፈልን ፡ እርሻ ፡ መገንጠያ ፡ መንገድ ፡ ደረሱ ። እነሆ ፡ እስካሁን ፡ ምንም ፡ ፍንጭ ፡ አላገኙም ። ብቻ ፡ እየተጨዋወቱ ፡ ሲሄዱ ፡ የአንድ ፡ አቃሳች ፡ ድምፅ ፡ ሰምተው ፡ ደነገጡና ፡ ቆመው ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ይመለከቱ ፡ ጀመር ። እንዳጋጣሚ ፡ ካንድ ፡ ትልቅ ፡ ዛፍ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ አንድ ፡ የተኛ ፡ ሰው ፡ በጣቱ ፡ ሲጠቅሳቸው ፡ አዩ ። ተሩጥነው ፡ ቢሄዱ ፡ ደመቀ ፡ በጊዜው ፡ ካንድ ፡ ትልቅ ፡ ዛፍ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ። አሳለፈልን ፡ እያዘነ ፡ ተጠግቶ ፡ ቀና ፡ አድርጎ ፡ ቁጭ ፡ እንዲል ፡ አገዘውና ፡ እየተናጠ ፡ ቁጭ ፡ አለ ።

ደመቀ ፡ በጊዜው ፡ በደከመና ፡ በሞተ ፡ ድምፅ ፡ «እባካችሁን ፡ ውኃ ፡ ይዛችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ከንፈሬን ፡ አርጥቡልኝና ፡ ልሙት ፡» ሲል ፡ ተናገረ ። አሳለፈልን ፡ ይህን ፡ ንግግር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከያዙት ፡ ውኃ ፡ በመስጠት ፡ ፊንታ ፡ እንባውን ፡ ያዥጎደጉደው ፡ ጀመር ። ከነዚያ ፡ ከሁለት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ተሩጥኖ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ውኃ ፡ አጠጣው ። ቀጥሎም ፡ ለአሳለፈልን ፡ «ማልቀስ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ፡» ሲል ፡ ግሣጼ ፡ ጭምር ፡ አስረዳው ።

ደመቀ ፡ በጊዜው ፡ እባክህን ፡ ትንሽ ፡ እህል ፡ ቅመስ ፡ ብለው ፡ ቢለምኑት ፡ አሁንም ፡ በደከመና ፡ በሞተ ፡ ድምፅ ፡ «ጉረሮዬ ፡ ቆስሏል ፡ ስለዚህ ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ልበላ ፡ እችላለሁ? አልችልም ፡» ሲል ፡ መለሰላቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አሳለፈልን ፡ ልብ ፡ ገዛና ፡ የደመቀን ፡ ትኩሳት ፡ ቢለካው ፡ ፻፬ ፡ ሴንት ፡ ግሬድ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። ቀጥሎም ፡ ሰውነቱን ፡ ቢመረምረው ፡ አንድ ፡ እግሩን ፡ አብጦ ፡ አገኘው ። አሁንም ፡ ከተመከረ ፡ በላይ ፡ እንባውን ፡ አዝረከረከው ። «ወይኔ ፡ ወንድሜ ፡ ወይኔ ፡ ወንድሜ ፡» እያለም ፡ አለቃቀሰ ። ይሁንና ፡ የጀመረውን ፡ ምርመራ ፡ ከልቅሶ ፡ ጋር ፡ ጨርሶ ፡ የትኩሳትና ፡ የብርታት ፡ መድኃኒት ፡ መጀመሪያ ፡ ሰጠውና ፡ ስለእግሩ ፡ እብጠት ፡ ጥቂት ፡ ሲያስብ ፡ ቆየ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደመቀ ፡ ጊንጢ ፡ የነከሰችበትን ቦታ ፡ ለአሳለፈልን ፡ አሳየው ። አሳለፈልንም ፡ ወዲያው ፡ በአልኮል ፡ የአበጠውን ፡ ቦታ ፡ ጠራርጎ ፡ በትንሽ ፡ ስል ፡ ቀረባ ፡ (ምላጭ) በጣለትና ፡ ጥቂት ፡ ጥቀርሻ ፡ የመሰለ ፡ ደም ፡ ፈሰሰለት ። ቀጥሎም ፡ ጠራርጎ ፡ አይዲን ፡ ቀብቶ ፡ አሰረለት ።

ቀኑን ፡ በዚያ ፡ በጥላ ፡ ሥር ፡ ውለው ፡ ወደማታ ፡ ለአሳለፈልን ፡ በተሜኑችው ፡ በቅሎ ፡ እየደጋገፉ ፡ ወደቤት ፡ አመጡት ። ወዲያውም ፡ ዶክቶር ፡ ጥግነህ ፡ ተጣድፈው ፡ መጥተው ፡ በሚገባ ፡ ከመረመሩት ፡ በኋላ ፡ አሳለፈልን ፡ ያደረገውን ፡ የመጀመሪያ ፡ የሕክምና ፡ ርዳታ ፡ ሁሉ ፡ ጠያይቀው ፡ ለብቻ ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ ተኝቶ ፡ እየተመላለሱ ፡ ቢያክሙት ፡ በቶሎ ፡ እንደሚድን ፡ ለእቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታ፡ ተስፋ ፡ ሰጥተው ፡ ተለያዩ ።

## ተመስገን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ተመስገን ፡ አምላኬ ፡ ተመስገን ፡ ጌታዬ ፡
ለዚህ ፡ ያበቃኸኝ ፡ ያላንዳች ፡ ዋጋዬ ።
እኔስ ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ አለቀች ፡ ሕይወት ፡
እኔስ ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ ከዳችኝ ፡ ሕይወት ፡
እኔስ ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ ገባሁ ፡ ከመሬት ፡
ለካስ ፡ ገና ፡ ኖሯል ፡ የቅጥቡ ፡ ዕለት ።

ካራዊት ፡ አዳንኸኝ ፡ ከነጣቂ ፡ ጅቦች ፡
ከነምር ፡ አዳንኸኝ ፡ ካጥቂው ፡ እንደ ፡ ተምች ፡
ካንበሳ ፡ አዳንኸኝ ፡ ከጉልበት ፡ እንካች ፡
ከዝሆን ፡ አዳንኸኝ ፡ በኩምቢ ፡ ተማች ፡
ከጥማት ፡ አዳንኸኝ ፡ ከአድራቂ ፡ አከች ፡
እንግዲህ ፡ ምን ፡ ላቅርብ ፡ ላንተ ፡ የሚመች ?
ብቻዬን ፡ ነኝ ፡ ብዬ ፡ ልቤ ፡ ሲሸበር ፡
ለካ ፡ አንተም ፡ ኖረሃል ፡ ከመላእክትህ ፡ ጋር ።
የምመልስልህ ፡ ታላቅ ፡ ወረታህ ፡
ተመስገን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንደትእዛዝህ ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለገና ፡ በዓል ፡ እንደተዘጉ ፡ ስንቃቸውን ፡ እያመላለሱ ፡ የሚማሩት ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ። የአምሳለ፡ ገነትና ፡ የአካባቢው ፡ መንደሮች ፡ ልጆችም ፡ በቀጥታ ፡ ቤቶቻቸውን ፡ መርዳት ፡ ጀመሩ ። የአዝመራ ፡ ስብሰባውም ፡ ተግባር ፡ እጅግ አጣድፎ ፡ ነበርና ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ተመልሰው ፡ ለየቤተሰቡ ፡ ጉልበት ፡ በጨመሩለት ፡ ጊዜ ፡ ወላጆች ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደሰቱ ። እባብ ፡ ያየ ፡ በልጥ ፡ በረየ ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ በአለፈው ፡ ዓመት ፡ ዝንጋታ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰው ፡ ጉዳት ፡ ዘንድሮም ፡ እንዳይደርስ ፡ በማለት ፡ ተግተው ፡ በጥንቃቄ ፡ ይሠሩ ፡ ጀመር ።

አሳለፈልን ፡ ዘለቀና ፡ አምኃም ፡ በአባታቸው ፡ እርሻ ፡ ጤፍ ፡ የማጨድንና ፡ ድከን ፡ የማጋዝን ፡ ሥራ ፡ በቶሎ ፡ ተጣውረው ፡ ይሠሩ ፡ ጀመር ። በዚሁም ፡ ሰሞን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለጤፍ ፡ ውቂያ ፡ የደቦ ፡ ጠላ ፡ በብዙ ፡ ተጠምቆ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተለምነው ፡ መጡ ። አንዳች ፡ ከሚያህል ፡ ውድማ ፡ አጠገብ ፡ ቤት ፡ የሚያካክሉ ፡ ሦስት ፡ ጉቾች ፡ ተከምረው ፡ ተመቻችተው ፡ ተደንስረዋል ። በዚያ ፡ አንዳች፡ በሚያህል ፡ ውድማ ፡ ላይ ፡ ሦስቱም ፡ የጤፍ ፡ ጉቾች ፡ ተዘርጥጠው ፡ ዛላቸውን ፡ የሎንደንን ፡ ጎራዴ ፡ እያስመሰሉ ፡ ተንዠራገዱበት ። እነ



መበርበሪያ ፡ እነመንሽ ፡ እነሙጭ ፡ እነማርገቢያና ፡ እነማጦያ ፡ አስቡቾች ፡ በሰልፍ ፡ መጥተው ፡ ከውድማው ፡ አጠገብ ፡ ተደረደሩ ። አሳለፈልንና ፡ ዘለቀ ፡ ከሁለት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ሃያ ፡ በሬዎች ፡ ያህል ፡ ነድተው ፡ አምጥተው ፡ የተጣለውን ፡ ጤፍ ፡ ማሄድ ፡ ወይም ፡ ማበራየት ፡ ጀመሩ ። ወቂዎቹም ፡ በመንሽና ፡ በመበርበሪያ ፡ በአንዶም ፡ ጢፉን ፡ ማገላበጥ ፡ ያዙ ። አሂያጆቹም ፡ «ተው ፡ መልስ ፡ ኧረ ፡ ተው ቀልስ ፡» እያሉ ፡ የጤፉን ፡ ዛላና ፡ አገዳ ፡ ያስነኩቱ ፡ ጀመር ። ካሂያጆቹም ፡ አንዱ ፡ እንደ ፡ ሚከተለው ፡ ያንጎራጉር ፡ ነበር ።

አሂዱ ፡ መልሱ ፡ አሂዱ ፡ ቀልሱ ፡ እናንተ ፡ በሬዎች ፡
ምርቱን ፡ እንጣለልነው ፡ እንድንል ፡ ጌቶች ፡
ነቃ ፡ ነቃ ፡ በሉ ፡ እናንት ፡ በሬዎች ፡
ጤፎ ፡ ጤፎ ፡ እንድንል ፡ ለሙጭ ፡ እንዲመች ።
በአንዶ ፡ ይበርበር ፡ በመንሽም ፡ ይበርበር ፡
መበርበሪያ ፡ ይሥራ ፡ ከላይ ፡ ታች ፡ ይዳከር ፡
ተይ ፡ ጤፎ ፡ ተነሥቶ ፡ በቶሎ ፡ እንዲዘመር ።
ዳለችና ፡ ሻሾ ፡ ከኩልኩል ፡ አትውጡ ፡
ዳለችና ፡ ሻሾ ፡ መሥመር ፡ አትልቀቁ ፡
ዳለችና ፡ ሻሾ ፡ ተው ፡ አታንበራጡ ፡
ምርቱ ፡ በርከት ፡ እንዲል ፡ ጤፎን ፡ ተረገጡ ።
ጉራች ፡ አፏጭልን ፡ ምራቸው ፡ በሮቹን ፡
ተከተል ፡ ደግዬ ፡ ግንባረ ፡ ጉራችን ፡
አሻል ፡ ፈንዛ ፡ ቦሩ ፡ ቀጥሉ ፡ አሂዶውን ፡
እንደሻሾ ፡ ዳለች ፡ ትታችሁ ፡ መርገጡን ፡
እንደዳለች ፡ ሻሾ ፡ ትታችሁ ፡ ማበጡን ፡
እንደ ፡ ሻሾ ፡ ጉራች ፡ ትታችሁ ፡ ማንጎጡን ።
ፈንዛ ፡ አምሮብሃል ፡ ምራቸው ፡ በቅጥ ፡
እንደ ፡ አሻሉ ፡ በሬ ፡ አትበል ፡ ቅብጥብጥ ፡
እንዳሻሉ ፡ በሬ ፡ አትሂድ ፡ ግርንቢጥ ፡
እንዳሻሉ ፡ በሬ ፡ አትበል ፡ ልምጥምጥ ።
ኧረ ፡ እሰይ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ አማረ ፡ አሂዶ ፡
ገለባው ፡ ነኮተ ፡ ጤፉን ፡ ጥሎ ፡ አብዶ ።

እንዲህ ፡ ይመር ፡ እንጂ ፡ አሂዶና ፡ መንሽ ፡
ለሙጭ ፡ እንዳያውክ ፡ እንዳይል ፡ ገሸሽ ።

ልክ ፡ ፀሐዪቱ ፡ በአናት ፡ ላይ ፡ ስትሆን ፡ የጤፍ ፡ ገለባ ፡ ሁሉ ፡ መሸከችና ፡ ውቂያው ፡ ተጀመረ ፡ አውራጁም ፡ እንደ ፡ ሚከተለው ፡ ደጋግሞ ፡ አንጎራጎረ ።

ያገሬ ፡ ጤፍ ፡ ውቂያ ፡ መቼ ፡ እንደዱሮሽ ፡
አጎልባች ፡ ገብቶሻል ፡ ባንድዬ ፡ እሚያሻሽ ፡
መኪና ፡ ገብቶሻል ፡ ባንድዬ ፡ እሚያሻሽ ።
ኧረ ፡ ጤፎ ፡ ኧረ ፡ ጤፎ ፡ ኧረ ፡ ጤፎ ፡
መቼ ፡ ነው ፡ እምትለቂን ፡ ጤፍሽ ፡ ባንድዬ ፡ ረግፎ ።
ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡
ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡
ከበሮቹ ፡ አጎዳ ፡ ሙጬ ፡ አጉረመረመ ፡
አንዶውና ፡ መንሹ ፡ ተጋጭቶ ፡ ገመመ ፡
አጓራ ፡ አከላላ ፡ ድምፁ ፡ በላይሽ ፡ ላይ ፡
ተይ ፡ ቶሎ ፡ ውረጂ ፡ እምሮብሽ ፡ ተንቧለይ ።
ኧረ ፡ ጤፎ ፡ ኧረ ፡ ጤፎ ፡ ኧረ ፡ ጤፎ ፡
አሁንስ ፡ አልሆንሽም ፡ እንደአራቧ ፡ ገንፎ ።
ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡
ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ፡ ሐይ ።

አሂደው ፡ አልቆ ፡ በሬዎቹ ፡ ከውድማ ፡ ወጡ ። የአፋቸውም ፡ እሥራት ፡ ተፈታላቸው ። ወደ ፡ ውኃ ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ ለአንዳፍታ ፡ ያህል ፡ ጭድ ፡ እንዲበሉ ፡ ተፈቀደላቸውና ፡ በተስገበገበ ፡ መልክ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ አሻመዱት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ተስናዳላቸው ፡ መጠጫ ፡ ተቀጣጥለው ፡ ሄዱ ። ከዚያም ፡ ሲደርሱ ፡ ውኃው ፡ በቦይ ፡ ወደ ፡ መጠጫቸው ፡ ተለቆ ፡ አገኙትና ፡ አፋቸውን ፡ ተከሉበት ።

ደቦኞቹም ፡ ውቂያቸውን ፡ እንደጨረሱ ፡ እጃቸውን ፡ ራሳቸውንና ፡ እግራቸውን ፡ ታጥበው ፡ ለጎተሮች ፡ በተሠራው ፡ ሰቀላ ፡ አጠ



ገብ ፡ በተንጣለለው ፡ ድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ሥፍራቸውን ፡ ያዙ ። በገበታው ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ሙዳ ፡ ሥጋ ፡ የሚያካክሉ ፡ የጎብስት ፡ ፍትፍቶች ፡ በየሰዎቹ ፡ ፊት ፡ በእንጀራ ፡ ላይ ፡ ተደርድረዋል ። የዶሮ ፡ ዓይንና ፡ እንኮይ ፡ የመሰለው ፡ ጠላ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በማብረጃች ፡ ተሰልፏል ። ባነስተኛ ፡ እግረ ፡ መሶቦች ፡ እንትርንጎ ፡ እንቷፋሕ ፡ እንጊሽጣ ፡ እንማንጎ ፡ እንብርቱካንና ፡ እንዘይቱን ፡ አልፈው ፡ አልፈው ፡ ጉች ፡ ጉች ፡ ብለዋል ። ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ፈንጠር ፡ ብለው ፡ በባለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ ጨርቆችን ፡ ተገልብበው ፡ የተቀመጡ ፡ ድስቶችና ፡ ረጃጅም ፡ እግረ ፡ መሶቦች ፡ ይታያሉ ። ድንኳኑ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አበቦችና ፡ ጌጦች ፡ አሸብርቆ ፡ በአድናቆት ፡ ጥላው ፡ ሰዎችን ፡ አፍዟል ። አሳላፊዎች ፡ ብቻ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ወይም ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ድምፅ ፡ ባለማሰማት ፡ ይፋጠናሉ ፡ ሲተላለፉ ፡ ፈጽሞ ፡ ኮሽታ ፡ አይሰማባቸውም ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ከምሳ ፡ መልስ ፡ ደቦኞች ፡ በሙሉ ፡ ወደ ፡ ጤፉ ፡ ውድማ ፡ ተመልሰው ፡ ጭዱን ፡ በሙሉ ፡ አራግፈው ፡ ካወጡ ፡ በኋላ ፡ ጠመቃ ፡ ተጀመረ ። ጠመቀ ፡ ማለት ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ አነጋገር ፡ በእጅ ፡ ስብርባሪውን ፡ ገለባ ፡ ከላይ ፡ በመግፈፍ ፡ መልክ ፡ አነሣ ፡ ማለት ፡ ነው ። የጠመቃው ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ተጀመረ ፡ በደቦኞች ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ የዳተኝነት ፡ መልክ ፡ ይታይባቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እያደር ፡ እንደ ፡ ጎሲ ፡ አሞሮች ፡ እያኮበኮቡ ፡ ያጓልቡት ፡ ጀመር ። ከደቦኞቹ ፡ አንዳንዶቹ ፡ በውድማው ፡ ላይ ፡ ተደንስረው ፡ ይሠራሉ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ ቁጢጥ ፡ ብለው ፡ ይጠምቃሉ ። ራቅ ፡ ብሎ ፡ በተረተር ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ለሚመለከታቸው ፡ በተነሣ ፡ ውድማ ፡ ላይ ፡ የፈሰሱ ፡ ዝንጀሮችን ፡ ይመስላሉ ።

የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሰዎች ፡ ሥራቸውን ፡ ሲያከናውኑ ፡ ንጽሕና ፡ ያለውን ፡ አፈር ፡ መሳይ ፡ ልብሳቸውን ፡ ለብሰው ፡ ይሠራሉ ። በሥራ ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ ሀብታሙና ፡ ድኃው ፡ ፈጽሞ ፡ አይለዩም ። ሁሉም ፡ በእ

ኩልነት ፡ ደረጃ ፡ ለሥራ ፡ ስለሚሰለፉ ፡ አሠሪዎችና ፡ ሠራተኞች ፡
አይለዩም ። ነገር ፡ ግን ፡ በበዓላት ፡ ቀናት ፡ ያላቸውና ፡ መጠነኞች ፡
በአለባበስ ፡ በየከፍተኛ ፡ ሥፍራዎች ፡ ላይም ፡ በአቀማመጥ ፡ እንደ
ዚሁም ፡ በቤት ፡ ኑሮ ፡ ብቻ ፡ ይለያያሉ ። ማለት ፡ ሀብታሞች ፡ በማ
ኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ይከበራሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በስተቀር ፡
በቀረው ፡ እጅግም ፡ ልዩነት ፡ የለም ።

የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ሰውን ፡ እግዚአብሔር ፡
ከቀን ፡ መኝታ ፡ ከሰወረውና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እየዋለ ፡ ከገባ ፡ ማናቸ
ውንም ፡ ሰው ፡ ሀብታም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ስለሚያምኑ ፡ በሀብት ፡
ማነስና ፡ ማደግ ፡ ምክንያት ፡ መናናቅ ፡ የለም ። በሰዎቹ ፡ አስተያየት
የሀብታሞች ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ጠቅላላው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ንብ
ረቶች ፡ የተገኘው ፡ ጥሪት ፡ ከጉልበት ፡ ጋር ፡ ይወዳደራል ። ሠራተ
ኞች ፡ ከሌሉ ፡ የሀብታሞች ፡ ገንዘብ ፡ አይሠራም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሠራ
ተኞች ፡ ኅበዞች ፡ ከሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ ፈጥረው ፡ በጉልበታ
ቸው ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብን ፡ ወይም ፡ እህልን ፡ ስለሚያገኙ ፡ ባለሕይወት ፡
ጉልበት ፡ ጥቅምን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ ያስገኛል ። ስለዚህ ፡
ሰው ፡ ራሱ ፡ ጉልበቱን ፡ እንደሀብት ፡ ሊቆጥር ፡ ይችላል ፡ በማለት ፡
ሀብታምና ፡ ድኃ ፡ ተመዛዝነው ፡ በመከባበር ፡ ይኖራሉ ። በሌላም ፡
መንገድ ፡ እንደዚሁ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ አላቸው ። ዕውቀት ፡ ከሀ
ብት ፡ በላይ ፡ ግምትን ፡ ከማግኘቱ ፡ በላይ ፡ ነዋሪ ፡ ቅርስ ፡ እንደሆ
ነም ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሰዎች ፡ ያምናሉ ። ስለዚህ ፡ ትምህርት ፡ ዕው
ቀትን ፡ ሥራ ፡ መፍጠርን ፡ ጉልበት ፡ ሥራ ፡ ማከናወንን ፡ የሥራ ፡
ክንውን ፡ ሀብትን ፡ ወይም ፡ ገንዘብን ፡ እንደሚፈጥሩ ፡ በአለመጠራ
ጠር ፡ ያምናሉ ። እነዚህ ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ ባንድነት ፡ ተጨፈላ
ልቀውም ፡ ሆነ ፡ ለየብቻቸው ፡ ሰውን ፡ በኑሮ ፡ ላይ ፡ አስችለው ፡
የሚያስጉዙ ፡ ናቸው ። እንግዲህ ፡ በጠቅላላው ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ የአ
ምሳለ ፡ ገነት ፡ ሰዎች ፡ በመልካም ፡ ምክንያት ፡ ላይ ፡ ተደላድለው ፡
ቆመዋልን ? የለም ፡ በሙሉ ፡ አልተደላደሉም ። መከባበር ፡ የሚገ
ባው ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በተፈጥሮ ፡ በተሰጠው ፡ መብት ፡ መሠረት ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ በሀብት ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ መሥራትም ፡ የተፈ
ጥሮ ፡ መብት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በልዩ ፡ አስተያየት ፡ ሰው ፡ በአለው ፡
ነገር ፡ ቢከባበር ፡ በተፈጥሮ ፡ የተሰጠው ፡ መብቱ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡
እንችላለን ።



እስኪ ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ጤፍ ፡ ውቂያችን ፡ እንመለስና ፡ በሩቁ
ሲታዩ ፡ በውድማ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጥቁሬዎችና ፡ እንደ ፡ ነጩዎች ፡ የፈ
ሰሱትን ፡ ደቦኞች ፡ እንከተላቸው ። እስከ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ተኩል ፡
ድረስ ፡ ሲያወዛውዙ ፡ ቆይተው ፡ ጠመቃቸውን ፡ ጨረሱ ። ቀጥለ
ውም ፡ ከአንዳንድ ፡ ደቃቅ ፡ ገለባና ፡ እብቅ ፡ ያልተለየውን ፡ ጤፍ ፡
በውድማው ፡ ውስጥ ፡ ወደዳር ፡ አስጠግተው ፡ ከሁለት ፡ ትይዩ ፡
ሥፍራዎች ፡ ላይ ፡ ከመሩትና ፡ በረጅሙ ፡ እየረጩ ፡ ያራግቡት ፡
ጀመር ። አራጋቢዎቹ ፡ በሁለቱም ፡ ወገን ፡ አራት ፡ አራት ፡ ናቸው ።
በስምንት ፡ አራጋቢዎች ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሳይቆነጥሩለት ፡ የማራ
ገቡ ፡ ሥራ ፡ እንዲሁ ፡ በውዝፍ ፡ አደረ ።

አቶ ፡ እውነቱ ፡ መኪታ ፡ ደቦኞቹን ፡ ሁሉ ፡ በሙዳ ፡ ሥጋ ፡ ሲያ
ማቱትና ፡ ሲያሳክሩት ፡ አምሽተው ፡ ከምሽቱ ፡ ባራት ፡ ሰዓት ፡
ገደማ ፡ ላይ ፡ ወደየቤቱ ፡ እየሄደ ፡ እንዲያርፍ ፡ ፈቀዱለት ። በማግ
ሥቱ ፡ ጧት ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ሰዎች ፡ ያህል ፡ ተመራርጠው ፡ መጥ
ተው ፡ የማራገቡን ፡ ሥራ ፡ አከናውነውት ፡ ዋሉ ። ምርቱም ፡ ግር
ዱም ፡ ሦስተኛውም ፡ እንደማሽላ ፡ እንችፍ ፡ ያለውም ፡ በየመልኩ ፡
ተጣራ ። ምርቱ ፡ ብቻ ፡ ቢሰፈር ፡ ፳ ፡ ዳውላ ፡ ሆነ ።

አሳለፈልን ፡ ዘለቀና ፡ አምኃም ፡ የውቂያው ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡
በብዙ ፡ አገልግለዋል ። ለሠራተኞች ፡ ዕቃ ፡ አቅራቢዎችና ፡ ውኃ ፡
አቀባዮችም ፡ ነበሩ ። እያፈነገጡ ፡ ከውድማ ፡ ይወጡ ፡ የነበሩትን ፡
በሬዎችም ፡ መልሰው ፡ ከውድማ ፡ የሚያስገቡ ፡ እነርሱ ፡ ነበሩ ።
ሲያስፈልግም ፡ በደቦው ፡ መሰናዶ ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ይላላኩ
የነበሩት ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ። አባታቸው ፡ ሠራተኞች ፡ ሞልተዋል ፡
ልጆቼን ፡ ፀሐይና ፡ ውርጭ ፡ በግብርና ፡ በኩል ፡ አይንካቸው ፡ አይ
ልም ፡ ነበርና ፡ ልጆቹ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ተፍረምራሚ ፡
ሆነዋል ።

እህሉ ፡ በሙሉ ፡ ተጭኖ ፡ ከተወሰኑለት ፡ ጎተሮች ፡ ውስጥ ፡
ገብቶ ፡ ተገማሸረ ። ጭዱም ፡ በሚገባው ፡ ሥፍራ ፡ ተከምሮ ፡ የተጣ
ዳና ፡ ቅልብጭ ፡ ያለ ፡ ደረባ ፡ ተሠራለት ። ቀጥሎም ፡ በማይጣስ ፡
ጥንካሬ ፡ ታቅዶ ፡ ታጠረ ። እነሆ ፡ ጤፎ ፡ ከነገለቦቿ ፡ በሥርዓት ፡
ተሰበሰበች ።ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ደግሞ ፡ በሁለት ፡ ውድሞች ፡ ላይ፡
የሚወቁ ፡ የተራራቁ ፡ የጤፍ ፡ አዝመሮች ፡ አሉ ። እንደዚሁም ፡ በሦ

ስት ፡ ላይ ፡ የሚወቁ ፡ የእገዳና ፡ የአበባ ፡ እህሎች ፡ አሉ ። ሦስተኛም፡ በሁለት ፡ ውድሞች ፡ የሚወቁ ፡ የብርዕ ፡ እህሎች ፡ አሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ውቂያው ፡ ገና ፡ ወደፊት ፡ እየቀጠለ ፡ የሚሄድ ፡ ነው ። መቼም ፡ አጀማመሩ ፡ ያማረ ፡ ነገር ፡ ፍጻሜውም ፡ ያምራል ፡ እንደሚባለው ፡ የመጀመሪያው ፡ ውቂያ ፡ እንዳማረ ፡ የሚቀጥሉትም ፡ ውቂያዎች ፡ እያማሩ ፡ ይሄዳሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

መቼም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀን ፡ አይሞላምና ፡ አንዳንድ ፡ አስገ. ፡ ነገሮች ፡ ሳይታሰቡ ፡ መፈጠራቸው ፡ አይቀርም ። ተፈጥረውም ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ሳያስከትሉ ፡ አይቀሩም ። በአገራችን ፡ ሥጋ ፡ ከመሬት ፡ ወድቆ ፡ አፈር ፡ ሳያነሣ ፡ አይቀርም ፡ እየተባለ ፡ ዘወትር ፡ ሲተረት ፡ ይኖራል ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታ ፡ በእውነቱ ፡ በግብርና ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ በመጠኑ ፡ ገልጠን ፡ በልዩ ልዩ ፡ ማስረጃች ፡ አትተን ፡ አቅርበናል ። አሁንም ፡ ለማስረጃቹ ፡ ደጋፊ ፡ የሆነውን ፡ የስንዴ ፡ ውቂያቸውን ፡ በመጠኑ ፡ ለማተት ፡ እሞክራለሁ ። የስንዴው ፡ እርሻቸው ፡ ከወይና ፡ ደጋው ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ነበር ። ደራሲው ፡ ርሻውን ፡ ተመልክቶ ፡ ባጠናበት ፡ ዘመን ፡ ስንዴና ፡ ጤፍ ፡ እንዳለወገን ፡ ሆነው ፡ ነበር ። የስንዴው ፡ ውቂያ ፡ ዝግጅት ፡ ከጤፉ ፡ ይልቅ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ፈጀ ። ውድማው ፡ የተሰናዳው ፡ በእርሻቸው ፡ ዳር ፡ በሚገኘው ፡ ትልቅ ፡ ወይራ ፡ ሥር ፡ ነው ። ወይራው ፡ ባራቱም ፡ ማዕዘን ፡ ቅርንጫፎቹን ፡ እንደዳስ ፡ አስቧል ። የውድማው ፡ መጠን ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ አሁን ፡ በጣም ፡ ልቋል ። የውድማው ፡ ኩልኩሎች ፡ በሁለት ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ በግድ ፡ ከሚነሡ ፡ ትልልቅ ፡ ድንጋዮች ፡ ተሠርተዋል ። የውድማው ፡ ልቅልቅ ፡ ተመላልሶ ፡ በመሠራቱ ፡ በስሚንቶ ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ ወለል ፡ አምሮ ፡ ተከርችሞ ፡ አወልውሏል ።

በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ውቂያ ፡ ዕለት ፡ አሳለፈልን ፡ ዘለቀና ፡ አም፡ነም፡



ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ ተቀብለው ፡ መጥተው ፡ የተለመደውን፡ አገልግሎት ፡ ለመስጠት ፡ ተዘጋጅተዋል ። እነሆ ፡ የቀኑ ፡ ዕለት ፡ ሠላሳ ፡ የሚያሄዱ ፡ በሬዎች ፡ ተመርጠው ፡ መጥተው ፡ ከውድማው፡ ዳር ፡ ጭድ ፡ ይበላሉ ። የስንዴ ፡ ጉቾች ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ውድማ ፡ ውስጥ ፡ ተዘርጥጠው ፡ የተፈረካከሱ ፡ ብሆችን ፡ መስለዋል ። በመጨረሻ ፡ ላይ ፡ ደቦኞች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ተኸሯጎድጉደው ፡ ከያለበት ፡ መጡ ። በሬዎቹ ፡ በሙሉ ፡ አፋቸውን ፡ ታስረው ፡ ከውድማ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ማበራየትን ፡ ቀጠሉ ።

የብርበራው ፡ የውቂያውና ፡ ላይዳ ፡ የመጣሉ ፡ ተግባር ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በጤፍ ፡ ውቂያ ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ ሲሠራ ፡ ውሎ አሁንም ፡ ሥራው ፡ በውጥን ፡ አደረ ። ደቦኞቹም ፡ እንደተለመደው ፡ ማታ ፡ ወደ ፡ አቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታ ፡ ቤት ፡ ተሰብስበው ፡ ሲበሉና ፡ ሲጠጡ ፡ አምሽተው ፡ ከምሽቱ ፡ ባምስት ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ።

የአቶ ፡ እውነቱ ፡ ቤት ፡ ከእምሳለ ፡ ገነት ፡ ቤቶች ፡ በጣም ፡ ፈንጠር ፡ ያለ ፡ ነው ፡ የግቢው ፡ አጥር ፡ ሁለት ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ እጅግ፡ በጣም ፡ ለነበር ፡ ሆኖ ፡ ተሠርቷል ። የሁለቱም ፡ አጥር ፡ በሮች ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ በትይዩ ፡ ተሠርተዋል ። ጎተሮች ፡ ከአንደኛው ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ተደርድረው ፡ ሰቀላዊ ፡ ባርኔጣን ፡ ባንድነት ፡ ደፍተዋል ። እንደዚሁም ፡ የጋማ ፡ ከብቶች ፡ ከትልቅ ፡ አዳራሽ ፡ በስተኋላ፡ ከሁለተኛው ፡ አጥር ፡ ውስጥ ፡ ከእህል ፡ ጎተሮች ፡ ሰቀላ ፡ እንደማይቀርቡ ፡ ሆነው ፡ በጥንክር ፡ ቅይድ ፡ ተከልክለው ፡ ከሰቀላቸው ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ አርፈዋል ። ከብቶቹ ፡ ግን ፡ በሁለተኛው ፡ አጥር ፡ ውስጥ ፡ ደንበኛ ፡ በረት ፡ ተሠርቶላቸው ፡ ታጉረዋል ።

ደቦኞቹ ፡ በሙሉ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ውሾቹ ፡ ተለቀው ፡ ራታቸውን ፡ በሚገባ ፡ በሉ ። ሁለቱም ፡ ደጆች ፡ በጥብቅ ፡ ተዘጉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቤተሰቡ ፡ ተሰብስቦ ፡ በትልቅ ፡ አዳራሽ ፡ ራት ፡ ሲበላ ፡ ካብትሽ ፡ ይመር ፡ ጠላ ፡ ለማምጣት ፡ ወዳንዱ ፡ ክፍል ፡ ስታልፍ ፡ ሻማዋን ፡ እንደያዘች ፡ ካንድ ፡ ታኒካ ፡ ላይ ፡ ወደቀች ። ያም ፡ ታኒካ ፡ በጎኑ ፡ ሲወድቅ ፡ ምስማር ፡ በሳውና ፡ የያዘውን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ረጨው ። ለካስ ፡ ይህ ፡ የተረጨው ፡ ነገር ፡ በንዚን ፡ ኖሯል ። አዬ ፡ ጉድ ! በሻማው ፡ እሳት ፡ ቡግ ፡ ብሎ ፡ ቤቱ ፡ ተያያዘ ! ! ካብትሽ ፡

ይመርም ፡ ለማስጠንቀቅ ፡ እንኳ ፡ ሳትበቃ ፡ እዚሁ ፡ ቀረች ።

አቶ ፡ እውነቱ ፡ መኪታ ፡ በእሳቱ ፡ ወላፈን ፡ ያሉበት ፡ ክፍል ፡ መዝጊያ ፡ ሲያያዝ ፡ አይቶ ፡ ከመ ፡ ቅጽበት ፡ ተነሥና ፡ ዕቃ ፡ ማሸሽ ፡ ጀመረ ። እዬ ፡ ሥቃይ ! እሳቱ ፡ ላንድዬው ፡ ወይቅይዱ ፡ አጥርና ፡ ወደየሰቀሎቹ ፡ በቶሎ ፡ ተዛመተ ። ተጮኸና ፡ ሰዎች ፡ ከያለበት ፡ እየተሰበሰቡ ፡ መጡ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መዝጊያውን ፡ ሰብረው ፡ ሲገቡ ፡ ውሾቹ ፡ ጥቂት ፡ አስቸገሯቸው ። ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ እስኪደርሱ ፡ ድረስ ፡ የግቢው ፡ እሳት ፡ እጅግ ፡ ተፋፋመና ፡ አስቸገረ ። አቶ ፡ እውነቱ ፡ አሳለፈልንና ፡ ዘለቀ ፡ ዕቃዎችን ፡ ሲያሸሹ ፡ ከእሳቱ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ቦምቦች ፡ ፈነዱና ፡ አበላሿቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እሳቱ ፡ ዘመተና ፡ የጋማ ፡ ከብቶቹን ፡ ቤት ፡ እልፎ ፡ የበርበሬና ፡ የጥጡን ፡ ሰቀላ ፡ አያያዘው ። ነገር ፡ ግን ፡ እምኃና ፡ ደማሜ ፡ ጥቂት ፡ በወላፈን ፡ ከመደንገጣቸው ፡ በስተቀር ፡ እንስሶቹን ፡ አዳኗቸው ። ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ገና ፡ የአባትና ፡ የልጆቹ ፡ ሞት ፡ አልታወቀም ። ከጥቂት ፡ የቤት ፡ ዕቆች ፡ ከጋማ ፡ ከብቶችና ፡ ከሁለተኛው ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የተረፈ ፡ ነገር ፡ የለም ። እህል ፡ ሁሉ እንዳለች ፡ በጎተራዋ ፡ ውስጥ ፡ ሾቀች ። አወይ ፡ አለመታደል ! እንደዚህ ፡ ሆንና ፡ የዚህ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ትዳር ፡ ፈረሰ ! እንደዚሁም ፡ ሳይታወቅ ፡ እመት ፡ ትብለጥ ፡ ትዕግሥተ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ገብታ ፡ ሳለች ፡ እሳቱ ፡ አስቀርቷት ፡ ኖሯል ። ደመቀ ፡ በጊዜውም ፡ እንደዚሁ እንደጌታው ፡ በቦምብ ፡ ፍንጣሪ ፡ ተቆራርጦ ፡ ወድቋል ። አወይ ፡ የአሟሟት ፡ ክፋት ! አወይ ፡ የአልታሰበ ፡ ውርጅብኝ ! አወይ ፡ መመጠጥ ! ምንም ፡ እንኳ ፡ የአካባቢው ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ ቢሰበሰብ ፡ የእሳቱን ፡ ድንፋታ ፡ ሊያበርደው ፡ አልቻለም ። ነገር ፡ ግን ፡ እሳቱ ፡ እያደር ፡ የሚበላው ፡ ነገር ፡ እያነሰ ፡ በመሄዱ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ መብረድ ፡ ጀመረ ። እነሆ ፡ ዘመዶችና ፡ የእምሳለ ፡ ገነት ፡ መንደር ፡ ሰዎች ፡ ልጆቹን ፡ የቀንድና ፡ የጋማ ፡ ከብቶቹን ፡ ብቻ ፡ ከቃጠሎው ፡ መልስ ፡ ወደመንደራቸው ፡ ከፊት ፡ ላኩና ፡ ያገኙትን ፡ የሬሶቹን ፡ ልቅምቃሞ ይዘው ፡ ተከተሉ ።

ሲነጋ ፡ በያገሩ ፡ ጠሪ ፡ ተልኮ ፡ ዘመዱ ፡ ሁሉ ፡ ተሰበሰበ ፡ አንዳንዶች ፡ ፊታቸውን ፡ ነጭተዋል ፡ ደረታቸውንም ፡ ጥለዋል ። እንባቸውም ፡ እንደገደል ፡ ውኃ ፡ ይኈርጎደጎዳል ። እምኃና ፡ ደማሜ ፡ ግን ፡



ምንም ፡ እንኳ ፡ እሳቱ ፡ ባይጎዳቸውም ፡ በድንጋጤ ፡ ደድበው ፡ ስለነበር ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ተልከዋል ። ስለዚህ ፡ ስለልቅሶው ፡ ምንም ፡ ያወቁት ፡ ነገር ፡ የለም ። በሬሳ ፡ ላይ ፡ የሚያለቅስ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ፈጽሞ ፡ አልተገኘም ። ነገር ፡ ግን ፡ የእምሳለ ፡ ገነት ፡ ሕዝብ ፡ ግማሹ ፡ ሲያለቅስ ፡ ግማሹ ፡ እየተመለከተ ፡ ከንፈሩን ፡ ያጮህና ፡ ደረቱን ፡ ይደቃ ፡ ነበር ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

አንድ ፡ ደንበኛ ፡ ሬሳ ፡ ባለመገኘቱ ፡ የስድስት ፡ ሰዎች ፡ ቁርስራሽ ፡ አካላት ፡ ተለቃቅመውና ፡ ባንድ ፡ ትልቅ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ታሽገው፡ ሱቲንና ፡ ግምጃን ፡ ለበሱ ። ስምንት ፡ ሰዎች ፡ ባንድ ፡ ባማረ ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ የሬሳውን ፡ ሣጥን ፡ አውጥተው ፡ አስቀመጡ ። በአራት ፡ ጥቋቁር ፡ ፈረሶች ፡ የሚሳበውም ፡ ሠረገላ ፡ መንቀሳቀስ ፡ ከመጀመሩ በፊት ፡ ካህናት ፡ ሁለተኛውን ፡ የጉዞ ፡ ፍታት ፡ አደረሱ ። ከሬሳው ፡ ሠረገላ ፡ በፊት ፡ ሴቶች ፡ ተሰልፈዋል ፡ ከሠረገላው ፡ በኋላም ፡ ካህናት ፡ በልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ሰልፋቸውን ፡ አሳምረዋል ። ከካህናቱም ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ እንባቸውን ፡ እንደ ፡ ኃይለኛ ፡ ዝናም ፡ ያፈሱት ፡ ነበር ። ከካህናት ፡ ቀጥለው ፡ ወንዶች ፡ ተከትለዋል ። እነሆ ፡ በተዘረዘረው ፡ መልክ ፡ ጉዞው ፡ ሲያመራ ፡ በመንገዱ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ያሉት፡ ዕፀዋት ፡ የሚረግፉ ፡ ድንጋዮችም ፡ ቢቶችም ፡ የሚግተለተሉ ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ። ለተስተኛው ፡ በሬሳ ፡ ጉዞ ፡ ላይ ፡ መንገዱንና ፡ የመንገዱን ፡ አካባቢ ፡ አጥለቀለቀው ፡ እንዲያውም ፡ መሬቱን ፡ አበሰው ፡ ቢባል ፡ ይሻላል ።

ለጉዞው ፡ ፍታት ፡ እልፎ ፡ እልፎ ፡ ሠረገላው ፡ ቆም ፡ ይላል ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከበሮው ፡ ይንራል ፡ ጸናጽሎችና ፡ ጥናች ፡ ይንሻሻሉ ። በተለይ ፡ ጥናች ፡ እየተንሿሹ ፡ ዕጣናቸውን ፡ በሠረገላው ፡ ዙሪያ ፡ ቡልቅ ፡ ቡልቅ ፡ ያደርጉታል ። ሠረገላው ፡ ቆም ፡ ባለ ፡ ቍጥር ፡ ዋየታዎችና ፡ ረገዶች ፡ በየዓይነታቸው ፡ ይቀልጣሉ ። መንስቅስቅና ፡ መስረቅረቅ ፡ ሠረገላውን ፡ ያጅባሉ ።

## ያልቃሾች ፡ እንጉርጉሮ ።

ምኑ ፡ ጥላ ፡ ወጊ ፡ ትናንቱን ፡ ለከፈው ፡
ሳያሳድር ፡ እንኳ ፡ አካሉን ፡ ያስበላው ።
እውነቱ ፡ መኪታ ፡ ያገር ፡ ሽማግሌ ፡
እንዴት ፡ ትለያለህ ፡ ጥለህ ፡ እንቢ ፡ ለሌ !
በሥራ ፡ ቀን ፡ ጉዞ ፡ እንዴት ፡ ፈቀድህና ?
በውቲያ ፡ ቀን ፡ ጉዞ ፡ እንዴት ፡ መረጥህና ?
አማላጅ ፡ መጣሱን ፡ መቼ ፡ ደፈርህና ?
ቅር ፡ እንኳ ፡ ሳይልህ ፡ ገባህ ፡ ከጎዳና ።
ብቻህን ፡ እንኳ ፡ አይደል ፡ ከትብለጢ ፡ ጋራ ፡
ብቻህን ፡ እንኳ ፡ አይደል ፡ ከልጆችህ ፡ ጋራ ፡
አለሰው ፡ እንኳ ፡ አይደል ፡ ከደመቀ ፡ ጋራ ፡
ለማን ፡ አስረከብኸው ፡ የቤቱን ፡ አደራ ?
ካብትሽ ፡ እንኳ ፡ የለች ፡ ርቃ ፡ ሄዳለች ፡
ሕፃናቱም ፡ ቢሆን ፡ ያሉት ፡ በሐኪሞች ፡
እንዴት ፡ አመንህና ፡ ለቀቅህ ፡ እኒያን ፡ ቤቶች ?
አፈራለሁ ፡ ብለህ ፡ የበለጠ ፡ ሀብት ፡
ሕዝቡን ፡ ሰበሰብኸው ፡ አረግኸው ፡ ድርገት ።

መቼም ፡ ምንም ፡ ጻ ፡ ሲባል ፡ ቢዘገም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡
ቅርብ ፡ ነበርና ፡ ከተወሰነው ፡ ሥፍራ ፡ መደረስ ፡ አልቀረም ። ሬሶች
ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጽር ፡ እንደገቡ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደወ
ሎች ፡ ድምፃቸውን ፡ ያከላሉት ፡ ያስተጋቡትና ፡ ያከሉት ፡ ያንሩትም
ጀመር ። ዋየታ ፡ ጸሎት ፡ እንደመግናናቸው ፡ መጠን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
አንዱ ፡ ቀጥሎም ፡ ሌላው ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡
ጆሮን ፡ የሚመርግ ፡ ጩኸት ፡ እየተሰማ ፡ ያን ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ያን ፡ የዝ
ምተኞች ፡ ሠፈር ፡ ያን ፡ የከቡራትና ፡ የከቡራን ፡ እናቶችና ፡ አባቶች
ሠፈር ፡ እያንቀጠቀጠ ፡ በጣም ፡ አናወጠው ።

አዬ ፡ ክፉ ፡ ወግ ! አዬ ፡ ክፉ ፡ ሥርዓት ! በግድ ፡ መለያየት !
ግባ ፡ መሬት ፡ ደረስ ፡ ሬሶች ፡ ባንድ ፡ ማጥን ፡ ተጠራቅመው ፡ በት



ከሻ ፡ ሠረገላ ፡ ወደ ፡ እቅጩ ፡ መቃብር ፡ ተተራማሹን ፡ ሕዝብ ፡ እየ
ጣጣሱ ፡ አመሩ ። ካህናትና ፡ ሕዝብ ፡ በአሁኒቱ ፡ ጉዞ ፡ ላይ ፡ እየተጋ
ፉና ፡ እየተጨናነቁ ፡ ደረሱ ። ሬሶች ፡ ከመቃብራቸው ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡
አረፉ ። ጥቂት ፡ ደቂቆች ፡ ለሕዝብ ፡ ምራምር ፡ ቀዘማ ፡ ሲባል ፡
ቆየት ፡ ታሉ ፡ በኋላ ፡ በረዳቶቻቸው ፡ አማካይነት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡
ከፍ ፡ ዝቅ ፡ እያሉ ፡ የአምሳለ ፡ ገንትንና ፡ የአካባቢውን ፡ ሕዝብ ፡ በደ
ከመ ፡ ጉልበታቸው ፡ ተንጠራውዘው ፡ ተሰናበቱ ፡ ቁልቁልም ፡ ወደ
ዘለዓለም ፡ ቤታቸው ፡ አመሩ ። አዬ ፡ ጉድ ፡ የአሁኒቱ ፡ ሁኔታ ! ኧረ ፡
የገላጋይ ፡ ያለህ ፡ ሆነቻ !

የአቶ ፡ እውነቱ ፡ መኪታና ፡ የወይዘሮ ፡ ትብለጥ ፡ ደግነት ፡
ርዳታ ፡ ጠያቂነትና ፡ አለንላችሁ ፡ ማለት ፡ መቀበራቸው ፡ ነው ፡
እንዴ ? እያሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያዙን ፡ ልቀቁን ፡ ይሉ ፡ ጀመር ። አዬ ፡
ጉድ ፡ እንቦች ፡ እንደገደል ፡ ውኖች ፡ ተቀንዘፉ ፡ መሐረቦችም ፡ ከየ
ተደበቁበት ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ወጥተው ፡ እንዲያው ፡ ውኃ ፡ ሆኑ ።
አዬ ፡ ተስፋ ፡ የማይጥሉበት ፡ ክፉ ፡ ስንብት ፡ አፈር ፡ ድንጋይ ፡ መዝ
ጊያ ፡ እንግዶቹ ፡ የገቡበትን ፡ የመቃብር ፡ ደጃፍ ፡ ለዘለዓለም ፡ ገጠ
መው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሙታኑ ፡ ንስሐ ፡ አባት ፡ ወደሚያሳርጉበት ፡
ሥፍራ ፡ ለቃስተኞች ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ተሰበሰቡ ።

## መሬት ፡ ነህና ፡ ወደመሬት ፡ ትመለሳለህ ።

«የጢትን ፡ ጥላ ፡ ከመካከላችን ፡ ከነሁኔታው ፡ የተመለከተው ፡ ሰው
አለን ? አዎን ፡ የተመለከተም ፡ ያልተመለከተም ፡ ከመካከላችን ፡
አይጠፋም ። የጢት ፡ ጥላ ፡ ጢት ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡
በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ይጋደማል ፡ ይንጣለላል ፡
ይጋረጻል ። ነገር ፡ ግን ፡ እያደር ፡ ፀሐይ ፡ እየታየች ፡ ስትሄድ ፡ የጥላ ፡
ርዝሙትና ፡ ስፋት ፡ እያደር ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ይሰበሰባል ። ልክ ፡ ስድ
ስት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ፀሐይ ፡ በሰው ፡ አናት ፡ ላይ ፡ ስትሆን ፡
የጢት ፡ ጥላ ፡ በአንድ ፡ አንድ ፡ ወራት ፡ ፈጽሞ ፡ ይጠፋል ። በዚሁ ፡
አንጻር ፡ የሰዓት ፡ በላይ ፡ ጥላ ፡ እስከ ፡ ጀንበር ፡ ጥልቀት ፡ ድረስ ፡ እያ
ደገ ፡ ይሄድና ፡ ጀንበር ፡ ስትጠልቅ ፡ ይጠፋል ።

እስኪ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የገለጸናቸውን ፡ ሁለት ፡ የጥላ ፡

ዓይነቶች ፡ አዘዋውረን ፡ እንገጣጥማቸው ። ከስድስት ፡ እስከ ፡ ጀንበር ፡ ጥልቀት ፡ ያለውን ፡ መጀመሪያ ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ያለውን ፡ ሁለተኛ ፡ ብናደርጋቸው ፡ የሰውን ፡ አፍላና ፡ በራድ ፡ ዘመናት ልንመስልባቸው ፡ እንችላለን ። ጥላ ፡ ያድጋል ፡ ይቀነሳል ፡ ይጠፋል ፡ እንደገናም ፡ ተመልሶ ፡ ይመጣል ።

እንግዲህ ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ከጥላ ፡ ጋር ፡ ብናወዳድረው ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የተራራቀ ፡ ሆኖ ፡ አናገኘውም ። ስለዚህ ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ ጥላ ፡ ነው ፡ ብንል ፡ እጅግም ፡ አያጎዳም ። ሰው ፡ ይወለዳል ፡ ይወልዳል ፡ ያድጋል ፡ ከአፍላ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ። እንደገና ፡ እየበረደ ፡ ይሄድና ፡ በመጨረሻ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይለያል ። በኋለኛውም ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ጊዜ ፡ ይነሣል ። ስለዚህ የሰው ፡ ሕይወት ፡ እንደጥላ ፡ እየተለዋወጠ ፡ የሚወድቅና ፡ የሚነሣ ፡ ወይም ፡ የሚጠፋ ፡ ከሆነና ፡ በተለይም ፡ በነዚህ ፡ በምታዩአቸው ፡ ልስንና ፡ ጌጠኞች ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ሰውነቱ ፡ በተፈጥሮታዊ ፡ የቅመማ ፡ ተግባር ፡ ሲተነተንና ፡ ሥረተ ፡ ሰውነት ፡ ወደየመጣበት ፡ ጎሣ ፡ ሲመለስ ፡ የሚኖር ፡ ከሆነ ፡ ሰው ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ራሱን ፡ የሚረሳበት ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ ይኖረዋል ?

እንግዲህ ፡ እንደቅጠል ፡ ረጋፊ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ጠፊ ፡ እንደልብስ ፡ አላቂ ፡ እንደማናቸውም ፡ እንስሳ ፡ ፈራሽና ፡ በስባሽ ፡ መሆናችንን ፡ ተገንዝበንና ፡ እንደገናም ፡ በተወሰነልን ፡ ጊዜ ፡ ተነሥተን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ መቀበል ፡ እንዳለብን ፡ ዐውቀን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ቀናውን ፡ መንገድ ፡ ብንከተል ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ብንጠራ ፡ የሚያሳስበን ፡ ነገር ፡ የለም ።

ዛሬ ፡ የሸኘናቸው ፡ የአቶ ፡ እውነቱ ፡ ቤተሰቦችና ፡ ራሳቸው ፡ አቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታ ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ ባልታሰበ ፡ ምክንያት ፡ ከመካከላችን ፡ ለዘለዓለም ፡ ተሰናበቱ ። «መሬት ፡ ነህና ፡ ወደመሬት ፡ ትመለሳለህ ፡» በተባለው ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ እናንተና ፡ እኔ ፡ በአፍአዊ ፡ ሁኔታቸው ፡ እንደተገነዘብነውና ፡ እንዳወቅነው ፡ ከዓለማዊው ፡ ኑሮአቸው ፡ ጋር ፡ የተከተሉት ፡ መንፈሳዊ ፡ ኑሮ ፡ ተመዛዛኝ ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ የሚያሰጋቸው ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ድንገተኛ ፡ ጉዞአቸውን ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ ጋርደን ፡ እንጽናናለን ። እኛም ፡ ለወደፊቱ ፡ ራሳችንን ፡ ከጠፊው ፡ ጥላ ፡ ጋር ፡ እያወዳደርን ፡ ኑሮአችንን ፡



በኅብረት ፡ እንምራ ። የሰይጣንም ፡ ፈረሶች ፡ ሆነን ፡ ዓለምን ፡ በየደቂቃው ፡ በምኞት ፡ አንዙራት ።

ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ደግሞ ፡ አደራ ፡ የምላችሁ ፡ «ራሳችሁ ፡ ሥራፈት ፡ ሆናችሁ ፡ በወሬ ፡ መደብርነት ፡ ሌሎቹን ፡ እውነተኞችና ፡ ጠቃሚ ፡ ሠራተኞች ፡ በቀጥታም ፡ ሆነ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ እንዳታውኩ ፡ ነው ። ማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ሰው ፡ የሰይጣን ፡ ማኅደር ፡ ነውና ፡ ቦዝናችሁ ፡ እንደባዶ ፡ ቤት ፡ ተከፋፍታችሁ ፡ የእኩይ ፡ ተግባር ፡ ማኅደር ፡ አትሁኑ ።

በልጓም ፡ እንደተያዘ ፡ ከብት ፡ ብቻ ፡ ካልተመራን ፡ እኛ ፡ ምንቸገረን ፡ እያላችሁ ፡ ዓይናችሁን ፡ እያጉረጠረጣችሁ ፡ ደረታችሁን ፡ እየለጠጣችሁ ፡ ሆዳችሁን ፡ እንደጎተራ ፡ እየዘረጠጣችሁ ፡ እግራችሁን ፡ በማጣመር ፡ ወይም ፡ እንደቀብራሮች ፡ ባለጌዎች ፡ በጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ እያጋደማችሁ ፡ እጃችሁንም ፡ እንደመልካም ፡ ዋናተኛ ፡ እየነዛችሁ ፡ እንደሲካካ ፡ ዶሮ ፡ አታስካኩ ፡ ግልገሏንም ፡ እንዳየች ፡ ፈረስ ፡ ሂ ፡ ሂ ፡ ሂ ፡ ሂ ፡ አትበሉ ፡» ያለውን ፡ ሰው ፡ ንግግር ፡ አጥብቃችሁ ፡ እንድታስቡ ፡ ነው ።

«እኔ ፡ ዛሬ ፡ ሥራ ፡ የለኝም ፡ ፈጽማችሁ ፡ አትበሉ ። ሰው ፡ ሥራን ፡ ይፈጥራል ፡ እንጂ ፡ ሥራ ፡ ሰውን ፡ አይፈጥረውም ። ባይሆን ፡ ሰው ፡ በመልካም ፡ ዕቅድ ፡ አስደናቂ ፡ ሥራዎችን ፡ ሠርቶ ፡ ሊጠቀም ፡ እንደሚችል ፡ እያሰባችሁ ፡ በመጠናችሁ ፡ የሥራ ፡ ፈጣሪዎችና ፡ አከናዋኞች ፡ ለመሆን ፡ ዘወትር ፡ ጣሩ ። እንዲህ ፡ ያደረጋችሁ ፡ እንደሆነ ፡ የሥራ ፡ ጭብጥና ፡ መሥመር ፡ ወይም ፡ ሕገኛ ፡ ፈርጁ ፡ ስለሚገባችሁ ፡ በተንኮልና ፡ በምቀኝነት ፡ ብቻ ፡ ተገፋፍታችሁ ፡ ቅን ፡ ሠራተኞችን ፡ ከመወንጀል ፡ ትድናላችሁ ።

እንግዲህ ፡ እንደጥላ ፡ ማለፍ ፡ ለማንኛችንም ፡ እንደማይቀር ፡ ተገንዝበንና ፡ አስተንትነን ፡ ዘወትር ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ በመታጠቅ ፡ ክርስቲያንነታችንን ፡ በጮሌ ፡ አፋችን ፡ ሳይሆን ፡ በእውነተኛ ፡ ተግባር ፡ እንግለጠው ። ምንም ፡ ሺ ፡ ጊዜ ፡ ቢያነጠንጡ ፡ ቢያንበራጥጡ ፡ እንደልብም ፡ ቢያጓምጡ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ቢሽቆጠቆጡ ፡ እንደለበቅ ፡ ወይም ፡ እንደጅራፍ ፡ ቢንጣጡ ፡ ወይም ፡ በይስበረኝ ፡ ይሰንጥረኝ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ሺ ፡ ጊዜ ፡ ቢለማመጡ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ተለይቶ ፡ መፍረስና ፡ መበስበስ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አይቀ

ሩም ። መሬት ፡ ነህና ፡ ወደመሬት ፡ ትመለሳለህ ፡ ተብሎ ፡ ለእያንዳንዳችን ፡ ሲነገረን ፡ እንዳናፍር ፡ የልብ ፡ እምነት ፡ ቀሪና ፡ ተከታይ ፡ ምግባር ፡ ይኑረን ።

ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሙታኑን ፡ ነፍስ ፡ ይማር ፡ ከአብርሃምና ከያዕቆብ ፡ ማኅበር ፡ ይቀላቅላቸው ። አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ እንበል ፡ » ብለው ፡ ካሳረጉ ፡ በኋላ ፡ የቀብር ፡ መልስ ፡ ሆነ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

አምኃና ፡ ደማሜ ፡ በሆስፒታል ፡ ተኝተው ፡ ሰውነታቸውን ፡ ሲያውቁት ፡ እናትና ፡ አባታቸውን ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ ደመቀ ፡ በጊዜውንና ፡ ካብትሽ ፡ ይመርን ፡ አሥር ፡ ጊዜ ፡ ጥሩልን ፡ እያሉ ፡ አስቸገሩ ። ተጠያቂዎቹም ፡ ጧት ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ወደማታ ፡ ማታ ፡ ይመጣሉ፡ እያሉ ፡ የውሸት ፡ ቃላት ፡ እየሰጡ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይደልሉአቸው ፡ ነበር ።

አዬ ፡ ጉድ ፡ አለማወቅ ! እነርሱ ፡ አገር ፡ ጥለው ፡ ቁርበት ፡ ጠቅልለው ፡ ሄደዋል ። ሁለተኛ ፡ ወደዚህ ፡ አይመለሱም ። ሁለቱንም ፡ ልጆች ፡ ለዓለም ፡ አደራ ፡ ሰጥተዋል ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ይሆናል ? ልጆቹ ፡ አደራውን ፡ ገና ፡ አላወቁም ። እንዲያው ፡ ባለማወቅ ፡ እማማ ፡ መቼ ፡ ትመጣለች ? አባባስ ፡ እንዴት ፡ እስካሁን ፡ ልቡ ፡ ጨከነለት ? ልጆቹስ ፡ አንናፍቅቸውም ፡ እንዴ ፡ ማለት ፡ የየሰዓቱና ፡ የየቀኑ ፡ ጉዳይ ፡ ሆነ ።

ልጆቹ ፡ በጣም ፡ ሲሻላቸው ፡ አጎታቸው ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ ከቤቱ ፡ ወሰዳቸው ፡ የቤተሰባቸውንም ፡ እልቂት ፡ ነገራቸው ። ለጊዜው ፡ ሁለቱም ፡ ልጆች ፡ ክች ፡ አሉና ፡ የሚይዙትን ፡ እጡት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እያደር ፡ እንባቸው ፡ በጉንጫቸው ፡ ላይ ፡ ተንፎለፎለ ። ዋየታውንና ፡ እዬዬውን ፡ አቀለጡት ። ቀጥለውም ፡ - « ለማን ፡ ጥላችሁን ፡ ሄዳችሁ ? ፍቅራችን ፡ እንደዚህ ፡ ባንድዬ ፡ ሊቆረጥ ፡ ቻለ ? ፍቅሩ ፡ በእኛ ፡ በኩል ፡ እንደነደደ ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ በቶሎ ፡ ይበርዳል ፡ ብለን ፡ አላሰብንም ፡ ነበር ። አዬ ፡ የቀን ፡ ጨለማ ! እንግዲህ ፡ ዋጠና



አቤት ! አቤት ! ኧረ ፡ እኔ ፡ የገላጋይ ፡ ያለህ ! » እያሉ ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ እየተንሰፈሰፉ ፡ ተንሰቀሰቁ ።

አጎታቸው ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ ከጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በብዙ ፡ ልመናና ፡ ማጽናናት ፡ ለማረጋጋት ፡ ሞከረ ። እነርሱም ፡ እያደር ፡ ሲበርዱ እንደገናም ፡ ኀዘናቸውን ፡ ያገንኑት ፡ ነበር ። በዚህ ፡ በመራራ ፡ ሁኔታ ፡ እነዚህ ፡ ወይዘሮ ፡ ዓለሚቱ ፡ የፈረደችባቸው ፡ ልጆች ፡ አንድ ፡ ወር ፡ አሳለፉ ።

የአቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታና ፡ የወይዘሮ ፡ ትብለጥ ፡ ትዕግሥት ፡ ዘመዶች ፡ ስለአምኃና ፡ ስለደማሜ ፡ ከተነጋገሩ ፡ በኋላ ፡ በሞግዚትነት ፡ የሚያሳድጋቸው ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ እንዲሆን ፡ ወሰኑ ። በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ በውድማ ፡ ላይ ፡ ያለውና ፡ ወደፊት ፡ የሚቃወም ፡ በሙሉ ፡ በአቶ ፡ ደገፉ ፡ ኃላፊነት ፡ ተሰብስቦና ፡ ተጠቃልሎ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ሥራ ፡ ተጀመረ ። ከብቶቹና ፡ የውጭ ፡ ገንዘቦችም ፡ ከያለበት ፡ እየተሰበሰቡ ፡ ለአቶ ፡ ደገፉ ፡ ተሰጡ ። ለልጆቹም ፡ ከዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ለወደፊቱ ፡ በሞግዚትነት ፡ የሚያሳድጋቸው ፡ እንደሆነ ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ ተረድተው ፡ በአባትነት ፡ መልክ ፡ እየተመለከቱ ፡ ራሳቸውን ፡ እስኪችሉ ፡ እንደሚረዱ ፡ በዝርዝር ፡ ተገለጸላቸው ።

አቶ ፡ ደገፉ ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ እጅግም ፡ የማይተጋና ፡ በተለይም ፡ የሃይማኖትን ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ እየተመለካከተ ፡ የሚያጠብቅ ፡ በመሆኑ ፡ አምኃን ፡ ለዜማ ፡ ለቅኔና ፡ ለመጻሕፍት ፡ ትምህርት ለማዘጋጀት ፡ አሰበ ።

መቼም ፡ ለአሳብ ፡ ደጋፊ ፡ ነገሮች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በአጋጣሚ ፡ መገኘታቸው ፡ አይቀርምና ፡ የአምሳለ ፡ ገነትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተጠግተን ፡ ዜማንና ፡ ቅኔን ፡ መጻሕፍትንም ፡ እናስተምራለን ፡ የሚሉ ፡ ሦስት ፡ መምህራን ፡ ከነተማሪዎቻቸው ፡ በድንገት ፡ መጡ ። የነዚህ ፡ መምህራንም ፡ መምጣት ፡ ከመ ፡ ቅጽበተ ፡ ዓይን ፡ ባንዴ ፡ በአምሳለ ፡ ገነት ፡ መንደርና ፡ አካባቢ ፡ ተነዛ ። ሕዝበ ፡ ክርስቲያኑም ፡ እጅግ ፡ ተደሰተ ። እነዚህ ፡ መምህራን ፡ መጀመሪያ ፡ ከካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ጋር ፡ ስለምን ፡ ወደዚህ ፡ ሥፍራ ፡ እንደመጡ ፡ በሰፊው ፡ ተነጋግረው ፡ አንዳች ፡ ውሳኔ ፡ እስኪደረግላቸው ፡ ድረስ ፡ የአምሳለ ፡ ገነትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እያገለገሉ ፡ ተቀመጡ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

የዜማው ፡ መምህር ፡ አለቃ ፡ ይገባሃል ፡ ቁም ፡ ጽሕፈትን ፡ ሥዕልንና የልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጠኛ ፡ ሐረጎችን ፡ አጣጣል ፡ አጠናቀው ፡ ያውቃሉ ። እኒህ ፡ መምህር ፡ ቀዋሚ ፡ መጽሐፎችን ፡ ሥዕሎችንና ፡ ሐረጎችን ፡ የሚያዘጋጁት ፡ በብራና ፡ ላይ ፡ ነው ። ብራኖችንም ፡ ከማንም ፡ ሰው ፡ ሳይገዙ ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ከበግና ፡ ከፍየል ፡ ቆዳ ፡ ላይ ፡ ያዘጋጁአቸዋል ። ብራኖቻቸውን ፡ የሚቀጹቸውና ፡ ጽሑፎቻቸውን ፡ የሚደጉሷቸው ፡ ማኅደሮችም ፡ የሚሰፉላቸው ፡ ራሳቸው ፡ ናቸው ። ተግባራቸውን ፡ በፍጥነት ፡ ለማከናወንና ፡ የተሻሻሉ ፡ እድርጎ ፡ ለመሥራት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደጣሩ ፡ ናቸው ። ተግባሮችን ፡ ማዛመድና ፡ ማነጻጸር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ስለሚፈቅዱ ፡ ብዙ ፡ መንገዶችን ፡ በፍጥነት ፡ እያለዋወጡ ፡ ይሠራሉ ። የሰውም ፡ አስተያየት ፡ ለተግባራቸው መሻሻያ ፡ እንዲሆን ፡ ይቀበላሉ ።

ዛሬም ፡ ቢሆን ፡ በአገራችን ፡ በተለይ ፡ ቁም ፡ ጽሕፈትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገው ፡ የሚከታተሉ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ የጽሕፈት ፡ ተግባር ፡ ሊቃውንት ፡ የቀለም ፡ ቅመማን ፡ ይከታተላሉ ። እንደዚሁም ፡ አለቃ ፡ ይገባሃል ። በተፈጥሮአቸው ፡ ፍጥረትን ፡ ተመልክቶ ፡ የመደሰት ፡ ልምድ ፡ ስላላቸው ፡ ከሕፃንነታቸው ፡ ጀምረው ፡ የአበቦችን ፡ ቀለማት ፡ ተለዋዋጭነት ፡ ይገነዘቡ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በገዛ ራሳቸው ፡ በየዓይነታቸው ፡ ቀለማትን ፡ እያቆነጃጁ ፡ በወሩ ፡ ቅጠሎችና ፡ በእጥንቶች ፡ ላይ ፡ አበቦችን ፡ ያዘጋጁ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ተግባራቸው ፡ እያደር ፡ ወደ ፡ ሥዕልና ፡ ወደ ፡ ቀለም ፡ ቅመማ ፡ መራቸው ። ስለዚህ ፡ የሚጽፉባቸውንና ፡ የሚሥሉባቸውን ፡ ቀለማት ፡ በየዓይነታቸው ፡ የሚያዘጋጁ ፡ ራሳቸው ፡ ነበሩ ። እኒህ ፡ መምህር ፡ በተለይ ፡ በቀለም ፡ ማሰናዳቱ ፡ እጅግ ፡ ጥቅም ፡ አግኝተውበታል ።

የአለቃ ፡ ይገባሃል ፡ የዜማ ፡ ትምህርት ፡ እንዲሁ ፡ ደረቅ ፡ አይደለም ። ወዝ ፡ አለው ፡ የሰውን ፡ ስሜት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጽርሐ ፡ አርያም ፡ ያወጣል ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሸንተረር ፡ ለሸ



ንተረር ፡ ያንከራትታል ። ወንገ ፡ ለወንገ ፡ ሸለቆ ፡ ለሸለቆ ፡ ያሽሎከልካል ። እንደ ፡ ዋናተኛ ፡ ያስነዛል ። ሰውነትን ፡ ያሰብቃል ፡ ያዋኝርቃል ፡ ያመሻሽካል ። ስለዚህ ፡ እርሳቸው ፡ በዜማ ፡ የማይነኩት ፡ ማለት ፡ መንፈሱን ፡ የማይቀሰቅሱት ፡ ምናልባት ፡ በድንን ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ።

ዜማቸው ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ ለመለዋወጥ ፡ ስለሚችል ፡ የዚቅ ፡ አወራረዳቸውና ፡ አቋቋማቸው ፡ በሽብሸባ ፡ የተጌጠ ፡ ወረባቸውም ፡ ለሥጋውያን ፡ ዜሞች ፡ እጅግ ፡ ይስማማል ፡ በመሠረትነትም ፡ መነሻ ለመሆን ፡ ይችላል ። እነሆ ፡ በሰጠነው ፡ መግለጫ ፡ አለቃ ፡ ይገባሃል ፡ ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሙያዎች ፡ ውስጥ ፡ አንዱን ፡ ትልቅ ፡ መሥመር ፡ ጠልቀው ፡ ያወቁና ፡ አጣፍጠው ፡ ለማቅረብ ፡ የቻሉ ፡ ታላቅ ፡ ዘዴኛ መምህር ፡ መሆናቸውን ፡ በመጠኑ ፡ ገለጥን ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ ተግባር ፡ እንመለስ ።

አለቃ ፡ ክንፉ ፡ በባሕረ - ሐሳብ ፡ መንገድ ፡ ጥበበ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የተከታተሉ ፡ በመሆናቸው ፡ መልክዓ - ሰማይን ፡ በብዙ ፡ አጥንተው ፡ ለአስረጅነት ፡ የደረሱ ፡ ሊቅ ፡ ናቸው ። በመጠኑም ፡ ተክሎችን ፡ በመድኃኒትነት ፡ መንገድ ፡ ተከታትለው ፡ በብዙ ፡ ተገንዝበው ያውቃሉ ። የዘወትር ፡ ምርመራቸውና ፡ መጻሕፍትን ፡ ማገላበጣቸው የድሮ ፡ ዘመንንና ፡ የራሳቸውን ፡ ዘመን ፡ አገናኝ ፡ አድርጓቸዋል ። መጻሕፍትን ፡ ሲያገላብጡ ፡ በዘመናት ፡ ጉዞ ፡ ላይ ፡ በመገኘት ፡ የተፈጸሙትን ፡ ሥራዎችና ፡ ተሰንዝረው ፡ የነበሩትን ፡ አስተያየቶች ፡ እንደዚሁም ፡ ፍጥረትንና ፡ የፍጥረትን ፡ አስተሳሰቦች ፡ ለማዐሕየት ፡ የተሰጡትን ፡ መግለጮች ፡ ልብ ፡ እያደረጉ ፡ ይመለከታሉ ። በዘወትር ፡ ምርመራቸውም ፡ የሚጽፉትን ፡ ካጠኑት ፡ ጋር ፡ እየመዛዘኑ ፡ እንደገና ፡ ያጠኑታል ። ይህ ፡ ተግባራቸው ፡ ወዳጅም ፡ ጠላትም ፡ አፍርቶላቸዋል ። በጥርስም ፡ እስከ ፡ መቀርጨጭና ፡ እስከ ፡ መቁሰል ፡ አድርሷቸዋል ። በዚህ ፡ አንጻር ፡ ደግሞ ፡ ተመራማሪዎች ፡ ተግባራቸውን ፡ እየፈቀዱ ፡ የበለጠ ፡ ለመረዳትና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ለመመካከር ፡ ይቀርቧቸዋል ። ሰውዬው ፡ አርቀው ፡ በማሰባቸው ፡ በሚለዋወጡ ፡ አሳቦች ፡ የማይለወጡት ፡ ወይም ፡ የማይፈርሱት ፡ ሲተኩ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደሳች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ነገርን ፡ ባንድ ፡ መልኩ ፡ ብቻ ፡ ነክሰው ፡ አልላቀቅም ፡ የሚሉ ፡ ሰው ፡ አይደሉም ።

ስለዚህ ፡ የቅኔ ፡ ትምህርታቸው ፡ ብዙ ፡ ለውጥ ፡ ያለው ፡ በመሆኑ ፡ የቀመሰው ፡ ተማሪ ፡ ሁሉ ፡ ያብዳል ፡ ይሰክራል ። ከእርሳቸውም ፡ መለየትን ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አጥብቆ ፡ ይጠላል ። ቅኔአቸው ፡ እንደ ፡ ጥንታውያን ፡ የግሪክ ፡ ተረቶች ፡ መብረቅ ፡ ሰማይን ፡ ያርሳል ፡ ሰማያት ፡ ደመናትን ፡ ይነድፋሉ ፡ ዝናማትንም ፡ ይፈትላሉ ፡ በረዶችንም ፡ ይለቃሉ ፡ ማያት ፡ የምድር ፡ አልባሳትንም ፡ ይሠራሉ ፡ ማለትን ፡ ብቻ ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ አያበዛም ። ነገር ፡ ግን ፡ ተገላጩን ነገር ፡ በፈርጅ ፡ በፈርጁ ፡ እያደረገ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሳቦችን ፡ እንደ.ያስፈላጊነታቸው ፡ እያስተሳሰረ ፡ ይገልጻል ።

በእንግሊዝኛ ፡ በሥርዓታዊ ፡ መለዋወጥ ፡ የሚቀርቡ ፡ ነገሮች ፡ የሕይወት ፡ ቅመሞች ፡ ናቸው ። እንደተባለው ፡ የሚሠሩትን ፡ ነገር ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልኩ ፡ ማየትና ፡ ከሌሎች ፡ ነገሮች ፡ ጋር ፡ አዛምዶ ፡ ወይም ፡ በማነጻጸር ፡ አራርቆ ፡ ሠርቶ ፡ ማቅረብ ፡ ይገባል ። እንደዚሁም ፡ እቶ ፡ ከንፉ ፡ ለሥራቸው ፡ ጣዕምን ፡ ለመስጠትና ፡ ተማሪዎቻቸውን ፡ በትምህርታቸው ፡ ወደፊት ፡ ለማራመድ ፡ በአንደበት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በተደላደለና ፡ መሠረት ፡ ባለው ፡ ተግባር ፡ ይገልጻሉ ።

ተቃዋሚዎቻቸው ፡ አስተሳሰቡ ፡ እንደድሮው ፡ አይደለም ፡ የራሱን ፡ ግለኛ ፡ ፍልስፍና ፡ ጨምሮ ፡ ነገራትን ፡ በማብራራት ፡ ለማስረዳት ፡ ይሞክራል ፡ እያሉ ፡ ስማቸውን ፡ ለማጥፋትና ፡ ሥራቸውን ፡ ለማባረድ ፡ ይጥራሉ ። ከሁሉም ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ የሚገርመው ፡ እርስ ከእኛ ፡ መካከል ፡ ተወልዶ ፡ አብረን ፡ አፈር ፡ እየፈጨን ፡ አድገን ፡ የትኛውን ፡ ባሕር ፡ ተሻግሮ ፡ አመጣ ? ስለምንስ ፡ ያልተለመዱ ፡ ነገራትን ፡ እየደረደረ ፡ ጆሮችንን ፡ ይበጥሰዋል ፡ በማለት ፡ መወንጀላቸው ፡ ነው ።

ወይ ፡ ጉድ ፡ የማይነቃነቅ ፡ ድንጋይ ፡ ነው ፡ እንደተባለው ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ ካልተንቀሳቀስሁ ፡ ወይም ፡ ካልተጣጣርሁ ፡ ወይም ፡ ካልተመራመርሁ ፡ ሌላው ፡ አይመራመር ፡ አይንቀሳቀስ ፡ ለጥ ፡ ይበል ፡ እንደሚለደፍ ፡ ዝፍት ፡ ይዘፍዝፍ ፡ ባለበት ፡ ይበስብስ ፡ ባለበት ፡ አእምሮውን ፡ ያዝግ ፡ ወይም ፡ ያሻግት ፡ ማለት ፡ ሕያው ፡ ለባዊና ፡ ነባቢ ፡ አድርጎ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረውን ፡ ሰው ፡ በድን ፡ አድርጎ ፡ እንደመቁጠር ፡ ያስ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡



ሐተተኛ ፡ እንቅፋት ፡ የመምህር ፡ ከንፉን ፡ ሥራና ፡ የወደፊት ፡ ርምጃ ፡ አላገደውም ። እስኪ ፡ እንግዲህ ፡ እኒህን ፡ መምህር ፡ ለተቅ ፡ እናድርግና ፡ ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ እንተላለፍ ።

ትምህርቶች ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ሰውን ፡ በተሻለ ፡ የኑሮ ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው ፡ በተጣዳ ፡ አውራ ፡ ጎዳና ፡ ላይ ፡ የሚመሩ ፡ ናቸው ። እነሆ ፡ በቆየው ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ እንኳ ፡ ሁለቱ ፡ አነስተኞች ፡ ቅርንጫፎች ፡ ተገኝተውና ፡ ከዓለም ፡ ትምህርታት ፡ ጋር ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ተቆራኝተው ፡ ሲሠሩ ፡ እናያለን ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሦስተኛውን ፡ ለማየት ፡ እንሞክር ።

አለቃ ፡ ደገ ፡ ነገር ፡ ዜማን ፡ ለራሳቸው ፡ በውቀው ፡ በቅኔም ፡ በኩል ፡ አጠናቀው ፡ ተምረው ፡ ተመርቀው ፡ በመጽሐፍ ፡ መምህርነታቸው ፡ ብቻ ፡ የሚሠሩ ፡ የመምህራን ፡ ቁና ፡ ናቸው ። አለቃ ፡ ደገ፡ ነገር ፡ ብሉያትንና ፡ ሐዲሳትን ፡ መጻሕፍተ ፡ ሊቃውንትም ፡ በወፍጮ ፡ ራሳቸው ፡ አገርሰው ፡ ስልቀው ፡ በማነጻጸር ፡ ወንፈት ፡ ነፍተው ፡ በምርመራ ፡ ውኃ ፡ አቡክተው ፡ በማጣራት ፡ ምጣድ ፡ ጋግረዋቸዋል ። እነሆ ፡ መጥታችሁ ፡ የተዘጋጀውን ፡ ማዕዴን ፡ በደስታ ፡ ብሉልኝ ፡ ጠጡልኝ ፡ እያሉ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ምዕመናንን ፡ በመጋበዝ ፡ ላይ ፡ የተቀመጡ ፡ ሰው ፡ ናቸው ። እኒህ ፡ መምህር ፡ እንደ ፡ አለቃ ፡ ከንፉ ፡ የመጻሕፍት ፡ ቀበኛ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ኑሯቸውን ፡ ከሕዝብ ፡ ለይተው ፡ በምርመራ ፡ ተግባር ፡ እጅግም ፡ አይጠምዱም ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ መጠየቅን ፡ ይወዳሉ ። እርሳቸውም ፡ የጥያቄው ፡ መልስ ፡ ያላጠገባቸው ፡ እንደሆን ፡ እልቆ ፡ መሥፈርት ፡ በሌለው ፡ መልኩ ፡ እያገለባበጡና ፡ ብልቱን ፡ ሁሉ ፡ በሥርዓት ፡ እያወጡ ፡ ምንጥርጥር ፡ አድርገው ፡ ያስረዳሉ ።

መምህር ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በስብከት ፡ ላይ ፡ ካንድ ፡ እጭር ፡ አስተዋጽዖ ፡ ማስታወሻ ፡ በስተቀር ፡ አንዳች ፡ መጽሐፍ ፡ ወይም ፡ አነስተኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ በሰፊው ፡ የተጻፈ ፡ ስብከት ፡ በእጃቸው ፡ አይዙም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሰበኩም ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ አስቀድመው ፡ ሳይሰብኩ ፡ የሚሰብኩበትን ፡ ወይም የሰበኩበትን ፡ አርእስት ፡ ዋጡኝ ፡ ወይም ፡ ስልቅጡኝ ፡ የሚሉ ፡ ማስረጃችን ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ በማደራጀት ፡ በሰፊው ፡ በጽሑፍ ፡ ያዘጋጁታል ። በዚህ ፡ ተግባራቸው ፡ ስብከትና ፡ ድርሰትን ፡ አጣምረው፡

ይዘዋል ። ለሰዎች ፡ የሚያቀርቧቸውንና ፡ የሚያገኟቸውን ፡ መልሶች ሁል ፡ ጊዜ ፡ አጠናቀው ፡ ከጸፉ ፡ በኋላ ፡ ራሳቸው ፡ እንደገና ፡ የጥያቄአቸውን ፡ መልስ ፡ ከብዙ ፡ ሐተታ ፡ ጋር ፡ ያስቀምጣል ። ጽሑፎቻቸውም ፡ ለስብከት ፡ ምርመራ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ በየጊዜው ፡ እየተፈለጉ ፡ ይሠራባቸዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

አለቃ ፡ ይገባሃል ፡ አለቃ ፡ ከንፋና ፡ አለቃ ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡ ከካህናቱ ፡ አለቃ ፡ በተነጋገሩት ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከፈቱ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከተከተሏቸው ፡ በስተቀር ፡ ከሩቅ ፡ ብዙ ፡ ተማሪዎች መጡ ። ከዚህም ፡ የአምሳለ ፡ ገነትና ፡ የአካባቢው ፡ መንደሮች ፡ ዲያቆናት ፡ ከያለበት ፡ ተሰበሰቡ ። ከተሰበሰቡት ፡ ተማሪዎች ፡ ዳዊት ፡ ያልደገመና ፡ ውዳሴ ፡ ማርያምን ፡ ያልጨኸ ፡ እንደዚሁም ፡ አርያምን ፡ ያልቀጸለ ፡ የለባቸውም ። ሁሉም ፡ ማንበብንና ፡ በመጠኑ ፡ መጻፍን ፡ ተምረዋል ። ቅኔ ፡ የሚማሩት ፡ ተማሪዎች ፡ ዜማንና ፡ መጽሐፍን ፡ ካልተማራችሁ ፡ ተብለው ፡ አይገደዱም ። እንደዚሁም ፡ ዜማን ፡ የሚማሩት ፡ ቅኔንና ፡ መጽሐፍን ፡ ካልቀጸላችሁ ፡ ተብለው ፡ አይቸገሩም ። ነገር ፡ ግን ፡ መጽሐፍን ፡ የሚቀጽሉ ፡ ተማሪዎች ፡ መጠነኛ ፡ የዜማ ፡ ትምህርትና ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ የቅኔ ፡ ትምህርት ከሌላቸው ፡ መምህር ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ አይቀበሉም ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ በአፍ ፡ እንደሚተረከው ፡ የቅኔ ፡ ትምህርት ፡ በሰምና ፡ በወርቅ ፡ እያሽሞነሞኑ ፡ ግጥምን ፡ የማስተማሪያ ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። የቅኔ ፡ ትምህርት ፡ በደንብ ፡ ለሚከታተለው የግዕዝን ፡ ቋንቋ ፡ አንጠርጥሮና ፡ አበጥሮ ፡ ያስተምራል ። ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ በቀላሉ ፡ ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ ቅኔን ፡ ያስተምራል ።

በኢትዮጵያ ፡ ምንም ፡ የመጽሐፍ ፡ ትምህርት ፡ በትርጓሜ ፡ መልክ ፡ ቢሰጥ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የተጠናቀቀ ፡ የግዕዝን ፡ ትምህርት፡ አጥብቆ ፡ ይጠይቃል ። ምክንያቱም ፡ የመጽሐፍ ፡ ትርጓሜ ፡ መማሪያና ፡ መረጃ ፡ መጻሕፍት ፡ ተጽፈው ፡ የሚገኙት ፡ በግዕዝ ፡ ስለሆነ ፡



ነው ። እንደዚሁም ፡ ምናልባት ፡ ትርጓሜን ፡ ለማራቀቂያ ፡ ብዙ ፡ አስተያየቶች ፡ የተገለጹባቸውንም ፡ መጻሕፍት ፡ ለማንበብና ፡ ለመረዳት ፡ የሚቻለው ፡ ግዕዝን ፡ አጣርቶ ፡ በማወቅ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የቅኔ ፡ ትምህርት ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ በመስጠቱ ፡ ቅኔን ፡ ያልተማረ ፡ መጽሐፍን ፡ ሊቀጽል ፡ አይችልም ። የሦስቱም ፡ መምህራን ፡ ትምህርቶች ፡ መንፈሳውያንና ፡ ሥጋውያን ፡ ተግባሮች ፡ አጣምረው ፡ በመምራታቸው ፡ ዘመናዊውን ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ በሥርዓት ፡ በመከተል ፡ ጎዳና ፡ ላይ ፡ ይወዛወዛሉ ።

ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የሚያስገርመው ፡ አንድ ፡ ሰውን ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ፍላጎት ፡ መሠረት ፡ በመምራት ፡ ፈንታ ፡ በኔ ፡ መንገድ ፡ ካልሄድህ ፡ ብሎ ፡ በግድ ፡ አሳምኖ ፡ መምራት ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ምናልባት ፡ ከትምህርት ፡ ጉድለት ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ።

አቶ ፡ ደገፋ ፡ የወንድማቸውን ፡ ልጅ ፡ ከአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ዘመናዊ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አውጥተው ፡ ከዜማ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጨመሩት ። አምኃ ፡ ዳዊትን ፡ የደገመው ፡ ገና ፡ በጨቅላነት ፡ ሳለ ፡ ነበር ፤ ከዚያም ፡ በቀጥታ ፡ ከአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ አራት ፡ ዓመታት ፡ ተምሯል ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ አባቱ ፡ ስለሞቱና ፡ በሌሎች ፡ ፍላጎት ፡ ኑሮው ፡ ስለሚመራ ፡ ትምህርቱም ፡ ትምህርት ፡ ቤቱም ፡ ተለወጠበት ። እንቢ ፡ ወይም ፡ አባካችሁን ፡ እያለ ፡ የራሱን ፡ ፍላጎት ፡ እንዳይከተል ፡ ገና ፡ ጨቅላ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ጥግዚቱ ፡ እንዳደረጉት ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ ነው ፡ ያለበት ። መቼውንም ፡ ቢሆን ፡ አላዋቂ ፡ አሳዳጊና ፡ አላዋቂ ፡ አሠልጣኝ ፡ ከችሎታቸው ፡ በላይ ፡ ሰውን ፡ ይመራሉ ፡ ተብሎ ፡ አይታመንም ።

አምኃ ፡ የዜማን ፡ ትምህርት ፡ ሲማር ፡ በዜማው ፡ ጣዕም ፡ የመመሰጥ ፡ ግለታዊ ፡ መንፈስ ፡ አደረበት ። መምህሩም ፡ አለቃ ፡ ይገባሃል ፡ ልጁ ፡ ትንሽ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ እንደዚህ ፡ በመፍጨርጨሩ ፡ ምክንያት ፡ እጅግ ፡ ወደው ፡ አቅርበው ፡ ይረዱት ፡ ነበር ፤ ከልጆቻቸውም ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ መርጠው ፡ እንዲያስቀጽለው ፡ አደራ ፡ ሰጥተውት ፡ ነበር ። አምኃ ፡ በዜማ ፡ ላይ ብቻ ፡ ሙዝኝ ፡ ሳይል ፡ የቀለምን ፡ አገጫጨት ፡ የብራናን ፡ አፋፋቅና ፡ አደማመጥ ፡ አቀጻጽም ፡ ከቁም ፡ ጽሕፈትና ፡ ከሥዕል ፡ ጋር ፡ አጠና ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በአጥንት ፡ ላይ ፡ የነደፈውን ፡ ሥዕል ፡ ለሁለተኛ ፡ ቤተሰቦቹ ፡ እየወሰደ ፡ ያሳያቸው ፡

ነበርና ፡ እንርሱም ፡ በልጁ ፡ ትምህርት ፡ እየተደሰቱ ፡ ይሄዱ ፡ ጀመር በተለይማ ፡ ዋና ፡ ዲያቆን ፡ ሆኖ ፡ በለዘበ ፡ ዜማ ፡ እውራ ፡ ድምፁን ፡ በለቀቀው ፡ ቀን ፡ ይገረሙበት ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ልጅ ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡ ሙሉ ፡ ዜማንና ፡ ከዜማ ፡ ጋር ፡ ያጣመራቸውን ፡ ትምህርቶች ፡ ለራስህ ፡ ይበቃሃል ፡ በሚያሰኝ ፡ ሁኔታ ፡ አጠና ። ቀጥሎም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ ሁኔታ ፡ ቅኔን ፡ ተምሮ ፡ ተቀኘ ። አምኃ ፡ ፊት ፡ ዜማንና ፡ ከዜማ ፡ ትምህርት ፡ ጋር ፡ ያጣመራቸውን ፡ ነገሮች ፡ ሲማርና ፡ ሲያጠና ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ግዕዝንም ፡ ከልጆቹ ፡ ላይ ፡ እየገለባበጠ ፡ ያጠናና ፡ ናሯል ። ስለዚህ ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ እፍ ፡ ቢሏት ፡ ከምትበን ፡ ቅኔ ፡ አልፎ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምሳሌዎች ፡ ያበዱ ፡ ቅኔዎችን ፡ ማዥጎድጎድ ፡ ሲጀምር ፡ ጊዜ ፡ አዳማጭ ፡ ሁሉ ፡ በይበል ፡ አድናቆታዊ ፡ ድምፅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ያናጋው ፡ ጀመር ። ነገር ፡ ግን ፡ አምኃ ፡ አሁን ፡ ነፍስ ፡ እያወቀ ፡ ዘመናዊ ፡ ኑሮን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልኩ ፡ ሲመለከተው ፡ ጊዜ ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ተመርቶ ፡ የደከመበት ፡ ትምህርት ፡ የማይበቃ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። ስለዚህ ፡ በወላጆቹ ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ትምህርታዊ ፡ አስተዳደጉ ፡ አለመሟላቱ ፡ በየጊዜው ፡ እያናደደ ፡ እንደ እሳት ፡ ይለበልበው ፡ ጀመር ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

ደማሜ ፡ እንደ ፡ አምኃ ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ ልትሠራ ፡ የማትችል ፡ በመሆኗ ፡ በአንቷ ፡ ምርጫ ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃን ፡ ትምህርት ፡ እንድትጨርስና ፡ አንድ ፡ ተግባር ፡ እንድትማር ፡ ተወስኖ ፡ ስለነበር ፡ አባቷ ፡ በሞቱ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ተኩል ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃን ፡ ትምህርት ፡ ጨርሳ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ላይ ፡ ከተቋቋመው ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገባች ። ይህች ፡ ልጅ ፡ በወላጆቿ ፡ እልቂት ፡ ምክንያት ፡ ዘወትር ፡ ከሥራዋ ፡ መልስ ፡ ከእንቷ ፡ ከወይዘሮ ፡ እህህ ፡ ትካዜ ፡ ጋር ፡ ሳትጨዋወት ፡ ቀርታ ፡ አታውቅም ።

የደብረ ፡ ማርቆስ ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡



ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርትና ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ ለአራት ፡ ዓመት ፡ ተመድበው ፡ ይሰጣሉ ። ተማሪዎቹ ፡ የአራት ፡ ዓመታት ፡ ትምህርታቸውን ፡ አከናውነው ፡ ተመርቀው ፡ ይወጡና ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ያስተምራሉ ። በዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ያስተማሩባቸውን ፡ ማስታወሾች ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ አዘጋጅተውና ፡ በሚያስተምሩአቸው ፡ አርእስትና ፡ በትምህርታዊ ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ የገጠሟቸውን ፡ ችግሮች ፡ በየፈርጃቸው ፡ አዘጋጅተው ፡ እንደገና ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ ወደ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይመለሳሉ ።

በአሁኑ ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ ኑሮና ፡ ትምህርት ፡ ተያይዘው ፡ ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ ይጠናሉ ። ከነዚህም ፡ ጋር ፡ ማስታወሾቻቸው ፡ እየተመዘኑ ፡ ደረጃቻቸውን ፡ ይይዛሉ ። በየትምህርቱ ፡ አርእስት ፡ የገጠሙት ፡ ችግሮችና ፡ ትምህርታውያን ፡ የአስተዳደር ፡ ጉድለቶች ፡ በክፍል ፡ ክርክር ፡ ወንጠፍቶች ፡ ውስጥ ፡ እየፈሰሱ ፡ ይጣራሉ ።

ይህ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ በኋላ ፡ የሚሰጥ ፡ ትምህርት ፡ መምህራንን ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ሊረዳቸው ፡ ይችላል ። አንደኛ ፡ የሥራ ፡ ጭብጣቸውን ፡ ያቃናል ፤ ሁለተኛ ፡ ያነሳቸውን ፡ ነገር ፡ ሞልቶ ፡ ያስተካክላል ። ሦስተኛ ፡ አስተዳደራዊ ፡ ምራታቸውን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልኩ ፡ እያሳየ ፡ አብራርቶ ፡ ይገልጻል ። አራተኛ ፡ ኑሮና ፡ ትምህርት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደሆኑ ፡ ራሳቸው ፡ መምህራን ፡ ተማሪዎች ፡ ባቀረቧቸው ፡ ችግሮች ፡ መነሻነት ፡ እያገናዘበ ፡ አስተምሮ ፡ ያስጨብጣል ። በዚህ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ተማሪዎች ፡ እንደገና ፡ ተመልሰው ፡ ሲማሩ ፡ ኑሮንና ፡ ትምህርትን ፡ የማዋሐድ ፡ ችሎታቸው ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በመገኘቱ ፡ በትምህርት ፡ ረገድ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሰጡት ፡ አገልግሎት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ይህን ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርታዊ ፡ ዕድገት ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ የተመጣጠነ ፡ ፕሮግራም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሲመራ ፡ እስካሁን ፡ ገና ፡ ከጭቃ ፡ ልስን ፡ ቤት ፡ አልወጣም ። የዚህ ፡ ት/ቤት ፡ ቤቶች ፡ መሠረቶች ፡ መጀመሪያ ፡ በድንጋይ ፡ ተሠርተው ፡ ጥቂት ፡ ከመሬት ፡ ከፍ ፡ እንዳሉ ፡ ማዕዘኖች ፡ እየተጋደ

ሙባቸው ፡ አቋሞች ፡ ተነሥተውባቸዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጣሪያዎች እየተዋቀሩ ፡ ቆርቆሮች ፡ ለብሰዋል ። በቆሙት ፡ ማዕዘኖች ፡ መሠረት ፡ የግድግዳ ፡ እንጨቶች ፡ ሲቆሙ ፡ በሰያፍነት ፡ በተያያዙት ፡ ማገሮች ፡ ውስጥ ፡ እየተሰኩ ፡ ስለሆነ ፡ እምብዛም ፡ ሳያስቸግሩት ፡ በሥራት ፡ ተቋቁመው ፡ ተማግረዋል ።

የመስኮቶቹ ፡ አወጣጥና ፡ ስፋት ፡ እንደንዝርት ፡ በውኃ ፡ ልክ ፡ ከቆመው ፡ ግድግዳ ፡ ጋር ፡ ሲተያይ ፡ ተመጣጣኝ ፡ ውበትን ፡ አግኝቷል ። እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ ሥራዎች ፡ በቀላሉ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ሠራተኞች ፡ የሚካሄዱ ፡ ናቸው ። አጎበሮችና ፡ ወለሎችም ፡ በአገጣጠም ፡ ተስተካክለው ፡ በአገር ፡ ልጆች ፡ ተሠርተዋል ። በተለይ ፡ እነ ልሰናማ ፡ ምንም ፡ የሚያዳግት ፡ ብልኅትን ፡ ይዘው ፡ ባለማስቸገራቸው ፡ እንዳሸዋ ፡ ልስን ፡ አምረው ፡ ተንሳተዋል ።

የመተላለፊያ ፡ ታዛ ፡ ማዕዘኖች ፡ በሥርዓት ፡ አምረው ፡ ቆመው በጌጠኞች ፡ አጫጭር ፡ መከታ ፡ ቅይዶች ፡ ተለይተው ፡ በጌጠኞች ፡ ረጃጅም ፡ ከፈፎች ፡ ላይ ፡ ተደምድመዋል ። በሮችና ፡ ደረጃች ፡ በፍጥነት ፡ የመተላለፍ ፡ ተግባር ፡ እንደሚፈጸምባቸው ፡ ሆነው ፡ በመሠራታቸው ፡ ዓይኖችን ፡ ይጋብዛሉ ።

የትምህርት ፡ መስጫና ፡ የጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ደጃፎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የመደብ ፡ አበቦች ፡ አጊጠው ፡ የዓይንና ፡ የኅሊና ፡ ማረፊያ ፡ ሆነዋል ። የግቢው ፡ መተላለፊያ ፡ የውጭ ፡ መንገዶች ፡ በጣም ፡ አምረው ፡ ከመሠራታቸው ፡ በላይ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መስኮትና ፡ አበቦች ፡ እየታጀቡ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ተጌጠዋል ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተክሎች ፡ መዓዛቸውን ፡ በአራቱም ፡ ማዕዘኖች ፡ እያስራጩ ፡ ግቢውን ፡ እንደመልካም ፡ ሽቱ ፡ በሙሉ ፡ ያውዱታል ። ባንዳንድ ፡ መጠነኞች ፡ ዛፎች ፡ ሥር ፡ ማለት ፡ ባንዳንድ ፡ መስኮች ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ በሚገኙት ፡ ተክሎች ፡ ሥር ፡ ወይም ፡ አጠገብ ፡ አልፈው ፡ አልፈው፡ አንዳንድ ፡ አግዳሚ ፡ ወንበሮች ፡ ጉች ፡ ጉች ፡ ብለው ፡ ይታያሉ ። ተማሪዎች ፡ ወይም ፡ መምህራን ፡ በዕረፍት ፡ ሰዓታቸው ፡ ጥቂት ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ከተናፈሱ ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ በተጠቀሱት ፡ መቀመጮች ፡ ላይ ፡ ያርፋሉ ።

የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ዕድሞ ፡ በደረቁ ፡ ተገንብቶ ፡ ከላይ ፡ በሰቀልኛ ፡ ቆርቆሮ ፡ ቤት ፡ መልክ ፡ ዓይነት ፡ በድንጋይ ፡ ተከድኗል ።



ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ መግቢያና ፡ መውጫ ፡ በሮች ፡ አሉት ። በስተግቢው ፡ በኩል ፡ በሁለት ፡ ሜትር ፡ ርቀት ፡ ላይ ፡ ጥዶችና ፡ ባሕር ፡ ዛፎች ፡ ባንድ ፡ ሜትር ፡ ተኩል ፡ ርቀት ፡ ላይ ፡ ተተክለዋል ። ዛፎቹ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱንና ፡ ት/ቤቱን ፡ እንደ ፡ አማረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገረገራ ፡ ከበው ፡ በአጀብ ፡ ቆመዋል ።

ተከለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ሙዚቃን ፡ እንደሌሎቹ ፡ ትምህርቶች ፡ ስለገመተው ፡ ደንበኛ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ አዘጋጅቶለታል ። በዚህም ፡ ክፍል ፡ ለትምህርት ፡ የሚያገለግሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያዎች ፡ አሉ ። አንዳንድም ፡ የሙዚቃ ፡ ወዳጆች ፡ ተማሪዎች ፡ ለዕረፍት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሲወጡ ፡ እየመጡ ፡ በመሣሪያዎቹ ፡ እንዲሠሩባቸው ፡ ተፈቅዷል ። እንዳጋጣሚ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ የሙዚቃ ፡ ክፍል ፡ ሙዚቃዊ ፡ ድምፅ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደየዕድሞው ፡ ዛፎች ፡ ሥር ፡ እንደጦር ፡ እየተሰበቀ ፡ ተወርውሮ ፡ ሲመጣ ፡ እንደታላላቅ ፡ መርጎች ፡ ሰውነቶችን ፡ እየሰባበረ ፡ ያደቃል ።

ይህ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የምናነበው ፡ ግጥም ፡ ተማሪዎችና ፡ መምህራን ፡ ለዕረፍት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥተው ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ተማሪ ፡ በሙዚቃ ፡ ስሜት ፡ ዘወትር ፡ ይቸገር ፡ የነበር ፡ አንዲት ፡ ልጃገረድ ፡ ከሙዚቃ ፡ ክፍል ፡ በፒያኖ ፡ አንድ ፡ እንደጣፈጠ ፡ ማር ፡ ያለ ፡ መዝሙር ፡ ስትለቅ ፡ ሰምቶ ፡ የገለጸው ፡ የድቁስቁስ ፡ መንፈስ ፡ ውጤት ፡ ነው ። እስኪ ፡ የልጁን ፡ ስሜት ፡ እናንብለት ።

## መንፈሴን ፡ መልሺ ።

ከወዴት ፡ መጥታለች ፡ ይች ፡ ውቢት ፡ ሙዚቃ ?
ከራስ ፡ ይሆን ፡ ከልብ ፡ ወይስ ፡ ከውስጥ ፡ ዕቃ ?

ምናልባት ፡ ይሆናል ፡ ከያንዳንዱ ፡ ሕዋስ ፡
መላ ፡ ሰውነትን ፡ በኅብረት ፡ ለማደስ ።

አይደለም ፡ አይደለም ፡ ከሚታወቅ ፡ ቦታ ፡
እንዲያው ፡ ትመጣለች ፡ ከሰውነት ፡ ነቅታ ።

ሥጋና ፡ ነፍሳችን ፡ እንዴት ፡ ተዋሐዱ ?

እንዴትስ ፡ ገጠሙ ፡ እንዴት ፡ ተዋደዱ ?

ማንስ ፡ አጠናቸው ፡ ማንስ ፡ ከወናቸው ?
በዕውብ ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ ዘወትር ፡ ኑሯቸው ።

ሙዚቃ ፡ እንደዚሁም ፡ ከሰው ፡ ሕይወት ፡ ጋር ፡
ያላንዳች ፡ ምንታዌ ፡ ያላንዳች ፡ እንኳር ።

እንዲያው ፡ ትመጣለች ፡ እንዲያው ፡ ትሄዳለች ፡
መላ ፡ ሰውነትን ፡ እየሰነጠቀች ።

ከየት ፡ ትነሣለች ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለች ?
ከየት ፡ ትገባለች ፡ ምንስ ፡ ታደርጋለች ?
ተብሎ ፡ አይጠየቅ ፡ እርስዋ ፡ እዚህ ፡ አለች ።

መንፈስ ፡ ትቀማለች ፡ አገር ፡ ላገር ፡ ስትዞር ፡
መሬቶች ፡ አይቀሯት ፡ ያዳሙ ፡ ሽንተረር ።

ከተራራ ፡ ወጥታ ፡ ስታይ ፡ ቁልቁለት ፡
እልም ፡ ትላለች ፡ መትሕተ ፡ ታሕቲት ።

ከዚያ ፡ ትወጣና ፡ ከደን ፡ ውስጥ ፡ ስትገባ ፡
ሰውን ፡ ታዝላለች ፡ መስጣ ፡ አደድባ ።

ወዳየር ፡ ስትወጣ ፡ በጣሙን ፡ ስትመጥቅ ፡
ሕይወት ፡ ትስባለች ፡ መንፈስን ፡ በማሞቅ ።

ሙዚቃ ፡ እባክሽን ፡ የትም ፡ እንዳትጥይኝ ፡
መንፈሴን ፡ መልሺ ፡ ለስልሰሽ ፡ አጽናኚኝ ።

ሙዚቃን ፡ በነፋስ ፡ ሰዎችን ፡ በዛፎች ፡
መስለን ፡ ለማጥናት ፡ ብናቀርብ ፡ ድርድሮች ፡

እንዲያው ፡ መወዛወዝ ፡ እንዲያው ፡ እሺሽ ፡ ማለት ፡
እንዲያው ፡ ተርገፍግፎ ፡ ለጥ ፡ ለጥ ፡ ማለት ፡
እንዲያው ፡ አፎጫጭቶ ፡ ተመልሶ ፡ መቅናት ።

መዝመምስ ፡ እንደጤፍ ፡ እንደማሽሎች ፡



ራስን ፡ አክብዶ ፡ ባያሌ ፡ ፍሮች ፡
ራስን ፡ አክብዶ ፡ ባያሌ ፡ ፍሮች ፡

ሙዚቃ ፡ ተመለሽ ፡ ወደ ፡ ነበርሽበት ፡
ወይም ፡ ባይሆን ፡ እንኳ ፡ በዚያው ፡ ባለሽበት ።

ከከተሽ ፡ ከከተሽ ፡ ገረዳደፍሽኝ ፡
አጉርሰሽ ፡ አጉርሰሽ ፡ ሰልቀሽ ፡ ጣልሽኝ ።

በማንኛው ፡ አቅሜ ፡ ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ቅስሜ ፡
በትርሽን ፡ ልቻለው ፡ ከዚህ ፡ ተጋድሜ ።
በትርሽን ፡ ልቻለው ፡ ከዕድሜው ፡ ሥር ፡ ደክሜ ፡
በትርሽን ፡ ልቻለው ፡ ከዕድሜው ፡ ሥር ፡ ደክሜ ።

ተማሪዎች ፡ ደንበኛውን ፡ የሙዚቃ ፡ ትምህርት ፡ ከመቀበላቸው ፡ በላይ ፡ ለየብቻ ፡ በመዘመር ፡ አብሮ ፡ ሦስት ፡ አራት ፡ እየሆኑ ፡ በመዘመርና ፡ ብዙ ፡ እየሆኑ ፡ በመዘመር ፡ ይወዳደራሉ ። እንደንብ ፡ አውራ ፡ የሚጉረመረም ፡ እንደመለከት ፡ የሚከላላ ፡ እንደ ፡ እንቢልታ ፡ ወይ ፡ ዋይ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ያላቸው ፡ ተማሪዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ተዘጋጅተው ፡ ሲዘምሩ ፡ በሰሚዎች ፡ ዘንድ ፡ ያሉ ፡ ስሜቶች ፡ ሁሉ ፡ በመውደቅ ፡ በመነሣት ፡ በመዋዠቅ ፡ እንደቆሬ ፡ ውኃ ፡ በመዋለል ፡ እንደ ፡ ቅጠሎች ፡ በመርገፍና ፡ በመንቆራጠጥ ፡ ይጨነቃሉ ፡ ይጠበባሉ ።

የሰውነት ፡ ማጠንከሪያው ፡ ድርጅት ፡ እንደሌሎቹ ፡ አርእስት ፡ በተስተካከለ ፡ ሥርዓታዊ ፡ ፕሮግራም ፡ እየተመራ ፡ ዘወትር ፡ የግቢውን ፡ ሕዝብና ፡ የውጪውን ፡ መንፈስ ፡ ይማርካል ። የተጨዋቾቹ ፡ ቅልጥፍና ፡ ተራዳኢነትና ፡ በጠቅላላ ፡ የዐመል ፡ አመራር ፡ በኅብረት ፡ ሠርቶ ፡ አንድ ፡ የሥራ ፡ ፍሬን ፡ ለማሳየት ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። በማናቸውም ፡ ጫወታ ፡ ላይ ፡ መራገጥ ፡ መጥለፍ ፡ መደረብ ፡ ወይም ፡ ገፍትሮ ፡ መድፋት ፡ በጭንቅላት ፡ የተቃዋሚን ፡ ክፍል ፡ ባልደረባ ፡ አገጭ ፡ ማውለቅ ፡ መናደድና ፡ ንዴትን ፡ በጫወታ ፡ ሜዳ ውስጥ ፡ መግለጥ ፡ ፈጽሞ ፡ በዚህ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ ላይ ፡ አይታይም ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ሕዝቡን ፡ በአጨዋወት ፡ ሥርዓታ

ቸውና ፡ ታክቲካቸው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እያግተለተሉ ፡ የሚሰቡት ፡ የሚያስተምሩት ፡ መንፈሱንም ፡ የሚያረኩት ። የዚህን ፡ ትምህርት ፡ ቤት የተጫዋችነት ፡ ሥርዓት ፡ እንዲህ ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ክብሮ ፡ ሰው ፡ እንዲያከብረው ፡ ያስደረገው ፡ አመሠራረቱና ፡ ዕድገቱ ፡ ነው ።

መልካም ፡ ጨዋታ ፡ የመልካም ፡ ወይም ፡ የጥሩ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ መሠረት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ማጎልመሻና ፡ የቀጥተኛ ፡ አቋም ፡ ቅርጽ ፡ መስጫ ፡ ነው ። ማናቸውም ፡ ትምህርት ፡ በልፍስፍስ ፡ ሰውነት ፡ ወይም ፡ ዘወትር ፡ በሕመም ፡ በሚጨባበጥ ፡ ሰውነት ፡ ሥር ፡ ሰዶ ፡ በሚገባ ፡ ተስፋፍቶ ፡ አጥጋቢ ፡ ፍሬን ፡ እጅግም ፡ አይሰጥም ። ስለዚህ ፡ ትምህርቶች ፡ ሁሉ ፡ እንደተክሎች ፡ ችግኞች ፡ ተቈጥረው ፡ አግብቶ ፡ ወይም ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ሰብቶ ፡ በታረሰና ፡ በለሰለሰ ፡ መሬት ፡ ሰውነት ፡ ውስጥ ፡ እየተተከሉ ፡ ቢጸድቁና ፡ ቢያድጉ ፡ ዓለም ፡ በአዝመራ ፡ ዕውቀት ፡ ሊጥለቀለቅና ፡ ሊጠግብ ፡ ኑሮውንም ፡ ሊያሻሽል ፡ ይችላል ።

እነሆ ፡ ለሚያስተውል ፡ ጨዋታ ፡ ወይም ፡ የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ትምህርት ፡ ለዕውቀት ፡ ማኅደርነትና ፡ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተግባቢነት ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከሌሎቹ ፡ ትምህርቶች ፡ ጋርጎን ፡ ለጎን ፡ እየሄደ ፡ አጥጋቢ ፡ ውጤትን ፡ አሳይቷል ።

ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ት/ቤት ፡ እንደሌሎቹ ፡ ትምህርቶች ፡ ክርክርን ፡ ጣልቃ ፡ እያስገባ ፡ ከድርሰት ፡ ጋር ፡ ያገናዝባል ። ተማሪዎችም ፡ ሐሳባቸውን ፡ እንደልባቸው ፡ ለመግለጽ እንዲችሉ ፡ ልምምድ ፡ ማድረግ ፡ ስላለባቸው ፡ የክርክር ፡ ልምድ ፡ ባላቸው ፡ መምህራን ፡ ሥራው ፡ እንዲመራ ፡ ያደርጋል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የክርክር ፡ መሪዎች ፡ የሚሆኑት ፡ የቋንቋ ፡ መምህራንናቸው ። የቋንቋ ፡ መምህራን ፡ ድርሰትን ፡ ስለሚያስተምሩ ፡ ክርክርንም ፡ እንደ ፡ ድርሰት ፡ እያሠሩ ፡ በክፍል ፡ ተማሪዎች ፡ እንዲነጋገሩበት ፡ ያደርጋሉ ። ተማሪዎች ፡ በክፍል ፡ ከመከራከራቸው ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ የሚከራከሩበት ፡ አርእስት ፡ ተሰጥቷቸው ፡ በሥርዓት ፡ ይዘጋጁበታል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በክፍል ፡ ወገን ፡ ለይተው ፡ እንዲከራከሩ ፡ መምህሩ ፡ ፈቅዶ ፡ የዳኝነት ፡ ተግባሩን ፡ ያከናውናል ።

እያንዳንዱ ፡ ተከራካሪ ፡ በአርእስቱ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የቋንቋ ፡ መምህሩን ፡ ተጨማሪ ፡ ርዳታን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይፈቀድለታል ። እንደዚሁም ፡ ለክርክሩ ፡ የሚረዱ ፡ መስለው ፡ የሚታዩ ፡ ነገሮችን ፡ ለመቅሰም ፡ እንዲመቸው ፡ የሚናገርበትን ፡ አርእስት ፡ የሚጠቅሱ ፡ መጻሕፍትን ፡ እየመረጠ ፡ ያነባል ። አለበለዚያም ፡ አርእስቱን ፡ በብዙ ፡ መልኩ ፡ ወደሚመለከቱ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ ይጠይቃል ።

ተማሪዎች ፡ በክርክር ፡ ተግባራቸው ፡ ምክንያት ፡ መጻሕፍትን ፡ በማንበብና ፡ ሰዎችን ፡ በመጠየቅ ፡ የምርመራ ፡ ሥራን ፡ ያከናውናሉ ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ክርክር ፡ ራሱ ፡ ትምህርት ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ የምርመራ ፡ ተግባርን ፡ በማስከተሉ ፡ ተማሪዎችን ፡ ለሥራ ፡ ያተጋቸዋል ።

መምህራን ፡ ከተማሪዎች ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ ደንበኛ ፡ የማስተማር ፡ ሥራቸውን ፡ ከመጀመራቸው ፡ በፊት ፡ በሰፊው ፡ ቆሞ ፡ አሳብን ፡ የመግለጽ ፡ ልምምድ ፡ ማድረግ ፡ ዋና ፡ ተግባራቸው ፡ መሆኑን ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አምኖ ፡ ስለሚሠራበት ፡ ተማሪዎች ፡ በደስታ ፡ ተቀብለው ፡ እየተሸቀዳደሙ ፡ ይለማመዱበታል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በከፍተኛ ፡ ተማሪዎች ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በታላቁ ፡ አዳራሽ ፡ የተደረገውን ፡ ተከታይ ፡ ክርክር ፡ እንመልከት ።

## በተለይ ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ አቋም ፡ የተደረገ ፡ ክርክር ።

፩ ፡ ለጊዜው ፡ ከግንብ ፡ ቤት ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ ይሻላል ።
፪ ፡ የለም ፡ ለጊዜውም ፡ ቢሆን ፡ ከእንጨት ፡ ቤት ፡ የድንጋይ ፡ ቤት ፡ ይሻላል ።

### ለጊዜው ፡ ከግንብ ፡ ቤት ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ ይሻላል ።

ለጊዜው ፡ ከግንብ ፡ ቤት ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ ይሻላል ፡ ብለን ፡ የምንከራከር ፡ ተማሪዎች ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድመን ፡ የምናስበው ፡ በክርክራችን ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ ጠንካራ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ አይደለም ፡

በሚል ፡ መንፈስ ፡ ተነሣሥተን ፡ የምናትት ፡ አለመሆናችንን ፡ እንድትገነዘቡልን ፡ ነው ። አሁን ፡ እኛ ፡ አሳባችንን ፡ የምንመሠርተው ፡ ሥልጣኔን ፡ ለማገሥገሥ ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ በቀላሉ ፡ እየሠሩ ፡ መራመድ ፡ ያስፈልጋል ፡ በሚል ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ ነው ። ካሉትም ፡ ነገሮች ፡ ቀለል ቀለል ፡ ያሉትን ፡ እየመራረጡ ፡ በማስቀደም ፡ መነሻ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ መጀመሪያ ፡ የእንጨት ፡ ቤትን ፡ መነሻ ፡ ያደረግነው ።

የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በእንጨት ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ አቅድ ፡ እንደተሠራ ፡ ከሞላ ፡ ጎደል ፡ ባይናችን ፡ ያየነው ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ነን ። ትምህርት ፡ ቤቱም ፡ ይህን ፡ ቀላል ፡ የቤት ፡ አሠራር ፡ የመረጠው ፡ በገንዘብ ፡ ችግር ፡ ሳይሆን ፡ በቀላል ፡ ተግባር ፡ ትምህርትን ፡ ለማራዘም ፡ የሚመርቃቸው ፡ መምህራን ፡ ሕዝቡን ፡ ለማስተማር ፡ የሚችሉበትን ፡ ዘዴ ፡ ለመምራት ፡ ነው ። መቼም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተደጋግሞ ፡ እንደተገለጸልን ፡ ትምህርት ፡ የኑሮ ፡ ምቾትን ፡ እየተፈላለጉ ፡ ማግኛ ፡ ስለሆነ ፡ ሕዝብ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ እንዲጠቀምበት ፡ ከኑሮው ፡ ጋር ፡ አያይዞ ፡ ማስተማር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

የእንጨት ፡ ቤት ፡ አሠራር ፡ ከፍተኞች ፡ መሐንዲሶችን ፡ አይጠይቅም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፕላኑ ፡ ከተነደፈና ፡ አቅድን ፡ ይዞ ፡ ከወጣ ፡ የአገር ፡ ልጆች ፡ ሊሠሩበት ፡ ይችላሉ ። መሠረቱም ፡ አቋሙም ፡ ጣሪያውም ፡ በቀላሉ ፡ ይሠራሉ ። ጭቃውም ፡ ቢሆን ፡ በምንም ፡ በኩል ፡ አያከሥርም ። የእንጨት ፡ ዋጋ ፡ ከእሸዋ ፡ ከኖራ ፡ ከሲሚንቶና ፡ ከሸክላ ፡ ጋር ፡ ሲያወዳድሩት ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ይመስላል ። እጅግ ፡ በጣም ፡ ያነሰው ፡ የእንጨት ፡ ዋጋ ፡ ኪስን ፡ ወይም ፡ የገንዘብን ፡ ሣጥን ፡ በብዙ ፡ አይጠይቅም ። በተለይማ ፡ አፈርና ፡ ጭድ ፡ ከምንም ወደር ፡ አይገቡም ። አፈር ፡ ከራስ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ለመገኘት ፡ ይችላል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያልተገኘ ፡ እንደሆን ፡ ሊጠቀስ ፡ በማያሳስብ ፡ ዋጋ ተገዝቶ ፡ ሊመጣ ፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ በጥንቃቄ ፡ ታስቦበት ፡ በፕላን ፡ ቢሠራ ፡ ወጪው ፡ እጅግም ፡ አይደለም ።

በተለይ ፡ ወደ ፡ ባላገር ፡ ሄደን ፡ ስለቤቶች ፡ ሥራ ፡ ብንነጋገር ፡ የቆርቆሮንና ፡ የሣር ፡ ክዳንን ፡ ለማወዳደር ፡ እንችላለን ። መቼም ፡ የሣር ፡ ዋጋ ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ ከቆርቆሮ ፡ ያነሰ ፡ ለመሆኑ ፡ የሚያጠራ



ጥር ፡ ነገር ፡ የለም ። የእንጨት ፡ ቤት ፡ ዕድሜ ፡ እንደድንጋይ ፡ ቤት ፡ አይቆይም ፡ የሚባለውን ፡ ሐሳብ ፡ ባለመዘንጋት ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ በማናቸውም ፡ አነስተኛ ፡ ሠራተኛ ፡ በቀላሉ ፡ ለመታደስ ፡ መቻሉን ፡ እንገልጻለን ። እስካሁን ፡ በጠቅላላ ፡ የተነጋገርነው ፡ ስለቤት ፡ አቋም ሥራት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ በማናቸውም ፡ በኩል ፡ ባነሰ ፡ ዋጋ ፡ ስለሚሠራና ፡ ባነሰ ፡ ዋጋ ፡ ተጠብቆ ፡ ለመኖር ፡ ስለሚችል ፡ በዘመናችን ፡ ሥልጣኔ ፡ አስተያየት ፡ ሳይሆን ፡ ሥልጣኔን ፡ ለማገሥገሥ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ በሚለው ፡ መንፈስ ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ ከድንጋይ ፡ ቤት ፡ ይሻላል ።

አንድ ፡ የድንጋይ ፡ ቤትን ፡ ለማሠራት ፡ የሚደረገው ፡ ወጭ ፡ ሲታሰብ ፡ ስንትና ፡ ስንት ፡ ብር ፡ ይጠይቃል ፡ በዚሁም ፡ ላይ ፡ ግንቡ የሚይዘው ፡ ሥፍራ ፡ ብዙ ፡ በመሆኑ ፡ በትልቅ ፡ ወይም ፡ በሰፊ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ የተጀመረው ፡ ቤት ፡ ክፍሎች ፡ በጣም ፡ ያናንሳሉ ። እንግዲህ ፡ የግንብ ፡ ቤት ፡ ይጠቅማል ፡ የሚባልበት ፡ አከታትሎ ፡ ፎቆችን ፡ ለመሥራት ፡ ነው ። ይህም ፡ የሚደረገው ፡ ሥልጣኔ ፡ እያደገ ፡ በመሄዱና ፡ ሰው ፡ በመብዛቱ ፡ ለቦታ ፡ ቁጠባ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥልጣኔ ፡ ገና ፡ ለመስፋፋት ፡ እግሩን ፡ በዘረጋጋበትና ፡ የቦታ ፡ ቁጠባ ፡ ባላሰጋበት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ፎቅ ፡ ቤቶች ፡ ፈጽመው ፡ አያስፈልጉም ። ስለዚህ ፡ የእንጨት ፡ ቤቶች ፡ በተለይም ፡ በግድግዳቸው ፡ የከፍላትን ፡ ሥፍራ ፡ እየቀነሱ ፡ የማያጣብቡት ፡ በያለበት ፡ እየተሠሩ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ቢበዙ ፡ ዕውቀት ፡ በየቦታው ፡ ይራዘማል ። ማናቸውም ፡ ሥራ ፡ በብልኀትና ፡ በቅልጥፍና ፡ ይሠራል ። ውጤቱም ፡ ብልጽግናን ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ማከታተል ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ካለው ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ከተደረሰ ፡ በኋላ ፡ የቤቶች ፡ መሥሪያዎችና ፡ አሠራሮች ፡ ይለወጡ ፡ ቢባል ፡ ምንም ፡ የሚያስቸግርና ፡ ርምጃን ፡ የሚቀንስ ፡ ነገር ፡ አይኖርም ።

አለበለዚያ ፡ ግን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በጥቂቶች ፡ የድንጋይ ፡ ቤቶች ላይ ፡ የፈሰሰ ፡ እንደሆነ ፡ አንደኛ የቤቶች ፡ ቍጥር ፡ ያንሳል ። ሁለተኛ ብዙ ፡ ተማሪዎችን ፡ አይዙም ፡ ወይም ፡ ተቀብለው ፡ ለማስተማር ፡ አይችሉም ። ሦስተኛ በቀላሉ ፡ እየተቀጠሉባቸው ፡ ሊሰፉ ፡ ያዳግታሉ ። አራተኛ ገንዘቡን ፡ ድንጋዮች ፡ ስለፈጁት ፡ የመምህራን ፡ መቀጠሪያና ፡ የመማሪያ ፡ መሣሪያዎች ፡ መግዣ ፡ ገንዘብ ፡

እጅግ ፡ ያንሳል ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ለማትረፍና ፡ በየሥፍራው ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችንም ፡ ለመክፈት ፡ አስፈላጊ ፡ መምህራንንም ፡ በየትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለመደልደል ፡ መጻሕፍትንና ፡ ዕቃችንም ፡ በየሥፍራው ፡ ለመመደብ ፡ የእንጨት ፡ ቤቶች ፡ ለጊዜው ፡ ዕውቀት ፡ ማራዘሚያ ፡ ተግባር ፡ ያገለግሉናል ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ « ዘመኑ ፡ የዲናሚዝም ፡ ነው ፡ » ተብሎ ፡ ባቶ፡ ግርማቸው ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ የተነገረውን ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ በማስተዋል ፡ ቢያስተነትኑት ፡ ተቀዋሚዎቻችን ፡ ከድንጋይ ፡ ቤት ፡ ይልቅ ፡ የእንጨት ፡ ቤትን ፡ ለዚህ ፡ አጣዳፊ ፡ ፕሮግራም ፡ ባንድ ፡ ድምፅ ፡ በተቀዳሚነት ፡ እንደሚመርጡት ፡ የሀብት ፡ መጠንና ፡ የትምህርት ፡ ዕድገት ፡ ይመራቸው ፡ ነበር ።

የድንጋይና ፡ የእንጨት ፡ ቤቶች ፡ ምንም ፡ በዋጋና ፡ በአሠራር ፡ ቢለያዩ ፡ የሚያስገኙት ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ስለሆነ ፡ የድንጋይን ፡ ቤት ፡ በመሥራት ፡ መቸገር ፡ አያስፈልግም ። በድንጋይ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ በእንጨት ፡ ቤት ፡ ቢሰጥ ፡ እኔ ፡ በእንጨት ፡ ቤት ፡ የምሰጥ ፡ ትምህርት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ዝቅ ፡ እላለሁ ፡ ብሎ ፡ አያስቸግርም ። ስለዚህ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ተግባሮች ፡ ኖሯቸው ፡ በዋጋ ፡ ከተበላለጡ ፡ ባለዝቅተኛውን ፡ ዋጋ ፡ መምረጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ከትንሽነቱ ፡ ተነሥቶ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ማደግ ይገባዋል ፡ እንጂ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ የለበትም ፡ የግድ ፡ መሆን ፡ አለበትም ፡ ቢባል ፡ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ይከለክላል ። ምናልባት ፡ ከተቀዋሚዎቻችን ፡ የድንጋይ ፡ ቤቶች ፡ ለኋላ ፡ ትውልድ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናሉ ፡ ምክንያቱም ፡ ከአንዱ ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ዘመን ፡ ለመተላለፍ ፡ ስለሚችሉ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለማስረዳት ፡ ይሞክሩ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ አስተያየት ፡ በሌላ ፡ መልኩ ፡ ቢመለከቱት ፡ አጥጋቢ ፡ አይሆንም ። እንደ ፡ እውነተኛው ፡ አስተያየት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ለኋላ ፡ ትውልድ ፡ ማስተላለፍ ፡ የሚገባው ፡ አእምሮታውያንና ፡ ተግባራውያን ፡ ትምህርቶችን ፡ ነው ። እነዚህንም ፡ የማሸጋገሩ ፡ ተግባር ፡ የሚፈጸመው ፡ በትምህርት ፡ በታነጹ ፡ ትውልዶች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በድንጋይ ፡ ቤት ፡ አይደለም ። እስኪ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ትንሽ ፡ ቆም ፡ እንበልና ፡ ጥቂት ፡ እናስብ ፡ የላሊበላ ፡



የድንጋይ ፡ ጥርብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናትና ፡ የአክሱም ፡ ሐውልቶች ፡ ታሪክን ፡ ከማቆየታቸው ፡ በስተቀር ፡ ብቻቸውን ፡ ያተረፉልን ፡ ትምህርት ፡ ምንድር ፡ ነው ? ብለን ፡ ብንጠይቅና ፡ ብንመራመር ፡ ሥልጣኔ ፡ በድንጋይ ፡ ቤት ፡ ዕድሜ ፡ ሊተላለፍ ፡ አለመቻሉን ፡ ልንረዳ ፡ እንችላለን ።

በተነሣንበት ፡ መንገድ ፡ እያደር ፡ ብንገፋ ፡ ወይም ፡ ብንቀጥል ፡ ማለት ፡ በእንጨት ፡ ቤቶች ፡ ዕውቀቶች ፡ በቶሎ ፡ እንዲሸጋገሩ ፡ ብናደርግ ፡ ዕውቀቶች ፡ በብዛት ፡ ይናኛሉ ። መቼም ፡ ነገሩን ፡ ካልቆረጡት ፡ መጫኛ ፡ ማኸሉ ፡ አይቀርምና ፡ ይቅርብን ፡ እናሳጥረው ። እናንተ ፡ የተከበራችሁ ፡ ዳኞችም ፡ እኛ ፡ የድንጋይ ፡ ቤት ፡ አያምርም ፡ አይጠቅምም ፡ በማለት ፡ አለመከራከራችንን ፡ ተገንዝባችሁና ፡ ባለን ፡ ሀብት ፡ ዕውቀቶችን ፡ ለማራዘም ፡ ቀላሉ ፡ መንገድና፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ የማይጠይቀው ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ያልነውን ፡ መዝናችሁ ፡ በዚሁም ፡ ላይ ፡ ትምህርት ፡ ለሁሉ ፡ ሰው ፡ ሊዳረስ ፡ የሚችልበትን ፡ መንገድ ፡ አስተውላችሁ ፡ ፍርዳችሁን ፡ ስጡን ። ትክክለኛውንም ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋውን ፡ ይግለጽላችሁና ፡ ይርዳችሁ ።

የለም ፡ ለጊዜውም ፡ ቢሆን ፡ ከእንጨት ፡ ቤት ፡
የድንጋይ ፡ ቤት ፡ ይሻላል ።

፪ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የተቃዋሚዎቻችንን ፡ ክርክሮች ፡ በጥንቃቄ ፡ አዳመጥን ። ተቃዋሚዎቻችን ፡ ብዙ ፡ ያላጠኗቸውን ፡ ነገሮች ፡ ይዘው ፡ በሽፍንፍን ፡ ይጓዛሉ ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በአገራችን ፡ ሥልጣኔ ፡ ተስፋፍቷል ፡ ብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሠራተኞች ፡ ድንጋይን ፡ መጥረብና ፡ መገንባት ፡ ችለዋል ። ድንጋዮችም ፡ በያለበት ፡ እንዳፈር ፡ ሞልተዋል ። ከየወንዞች ፡ ዳር ፡ በቀላሉ ፡ ሊመጣ ፡ በማይችለውም ፡ አሸዋ ፡ ምትክ ፡ ድንጋዮች ፡ እየተፈጩ ፡ በየአሸዋው ፡ ደረጃ ፡ ያገለግላሉ ፡ ማለት ፡ ጠጠራም ፡ አሸዋ ፡ መለስተኛ ፡ ደቃቅ ፡ አሸዋና ፡ ደንበኛ ፡ አሸዋ ፡ በሚባሉት ፡ ምትክ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሲሚንት ፡ በቀላሉ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ድንጋዮች ፡ ጋር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅመማት ፡ ተደባልቀውና ፡ በሙቀት ፡ ደረ

ጆች ፡ ተላልፈው ፡ ተፈጭተው ፡ የሚገኝ ፡ የአሸዋና ፡ የድንጋዮች ፡ ወይም ፡ የአሸዋ ፡ የድንጋዮችና ፡ የብረቶች ፡ ማያያገሪያ ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ እዚሁ ፡ ይሠራል ። በሲሚንት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ ማዕርጎች ፡ ተሰልፈው ፡ ሌሊት ፡ ከቀን ፡ ይሠራሉ ።

በድንጋይ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ በየጊዜው ፡ ብዙዎች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በመሠልጠን ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ። ድንጋዮችን ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ በማስናዳት ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ቅርጾች ፡ ይወጣሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ተግባራዊ ፡ ትምህርት ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ያላንዳች ዋጋ ፡ በነፃ ፡ ይሰጣል ። ትምህርት ፡ ማለት ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ብቻ የሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ አይደለም ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ትምህርት ፡ ጥንት ፡ በአውሮጳውያን ፡ ዘንድ ፡ በረድነት ፡ የሚገኝ ፡ ትምህርት ፡ እየተባለ ፡ ይታወቅ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ የድንጋይ ፡ ቤቶች ፡ ገንዘብ ፡ መፍጀታቸውን ፡ ብቻ ፡ ተመልክቶ ፡ መንቀፍ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መስሎ ፡ አይታይም ። አንድን ፡ ነገር ፡ ከመንቀፍና ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ከመተካት ፡ በፊት ፡ መጀመሪያ ፡ በብዙ ፡ መልኩ ፡ መመልከትና ፡ ማመዛዘን ፡ ያስፈልጋል ።

የሲሚንት ፡ ፋብሪኮችና ፡ የድንጋይ ፡ መፍጫ ፡ መኪኖች ፡ በብዙ ፡ ሺ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ እንደሚያስተዳድሩ ፡ ሁላችንም ፡ እናውቃለን ። በነዚህም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቴክኒክ ፡ ትምህርቶች ፡ ማለት ፡ የሥራ ፡ ምራት ፡ ተግባሮች ፡ ትምህርቶች ፡ ከሥራ ፡ ጋር ፡ ተጣምረው ፡ ይጠናሉ ። ስለዚህ ፡ የድንጋይ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ በመጣደፉ ፡ ተግባራውያን ፡ ትምህርቶች ፡ ይጣደፋሉ ፡ እንጂ ፡ ጉዳት ፡ አይመጣም ። እስኪ ፡ ደግሞ ፡ ጥቅሙን ፡ በሌላ ፡ መልኩ ፡ እንግለጸው ።

የድንጋይ ፡ ቤት ፡ ከዘመናት ፡ ወደዘመናት ፡ እየተላለፈ ፡ ለዘለዓለም ፡ ለመኖር ፡ ይችላል ። እንደ ፡ እንጨት ፡ ቤት ፡ ልስን ፡ በቀላሉ በውሽንፍር ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ባለመላጡ ፡ በየዓመቱ ፡ አድሱኝ ፡ እያለ ፡ ባለቤቶችን ፡ ወይም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ አያስቸግርም ። ደመቅ ፡ ብሎ ፡ ተደንስሮም ፡ በመታየቱ ፡ የተመልካቾችን ፡ ዓይን ፡ ስለሚማርክ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ያስደስታል ። ስለዚህ ፡ በየጊዜው ፡ እየተቅረፈረፈ ፡ ከሚያስቸግር ፡ የጭቃ ፡ ልስን ፡ ቤት ፡ የግንብ ፡ ቤት ፡ መቶ ፡



በመቶ ፡ ይሻላል ። የጭቃ ፡ ልስን ፡ ምንም ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋና ፡ ዕውቀት ፡ ባይጠይቅና ፡ በቀላሉም ፡ ለመሠራትና ፡ ለመታደስ ፡ ቢቻል ፡ በየጊዜው ፡ ወሽመጥ ፡ መበጠሱን ፡ ባለመርሳት ፡ ሊጠቀሙበት ፡ የማይገባ ፡ አስልች ፡ የቤት ፡ አሠራር ፡ ነው ።

የግንብ ፡ ቤቶች ፡ ጠበብ ፡ ጠበብ ፡ እየተደረጉ ፡ በቀልባሚነት ፡ ይሠራሉ ፡ በመንዛዛትም ፡ የሚኖሩባቸውን ፡ ሰዎች ፡ አያደክሙም ፡ ሁለተኛም ፡ ፎቆች ፡ በቀላሉ ፡ ሊቀጠሉባቸው ፡ ስለሚችሉ ፡ ገንዘብ ፡ ካለ ፡ ለቦታ ፡ ቊጠባ ፡ በጣም ፡ ምቹነትን ፡ ይሰጣሉ ። ስለዚህ ፡ ምንም እንኳ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ቢያስወጡ ፡ የሚሰጡት ፡ አገልግሎት ፡ ከእንጨት ፡ ቤት ፡ በላይ ፡ ስለሆነ ፡ ሀብት ፡ አሚጣጭ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ሊነቀፉ ፡ ወይም ፡ ሊወቀሱ ፡ አይገባም ።

ገንዘብ ፡ አነሰ ፡ ተብሎ ፡ የጭቃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ይሠሩ ፡ ማለት ፡ የሚያሳፍር ፡ ንግግር ፡ ነው ። ሕንፃች ፡ በሥልጣኔ ፡ የመራመድ ፡ ምልክቶች ፡ ስለሆኑ ፡ የሕንፃችን ፡ ሥራ ፡ ማቃለል ፡ አይገባም ። ባይሆን ፡ ገንዘብ ፡ አነሰ ፡ ከተባለ ፡ ግብርን ፡ መቀጠል ፡ ነው ። ሕንፃቹ ፡ የአገር ፡ ቅርስ ፡ ስለሆኑና ፡ ወደፊትም ፡ ስለሚሆኑ ፡ የሕዝብ ፡ አማካሪዎች ፡ ብዙ ፡ የትምህርት ፡ ታክስ ፡ እንዲጨምሩ ፡ መጠየቅ ፡ ነው ። ይህን ፡ ለማድረግ ፡ ምንም ፡ የሚያዳግት ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ ሁላችንም ፡ እናውቃለን ። ስለዚህ ፡ የሥልጣኔያችን ፡ ርምጃ ፡ የሚፋጠነው ፡ በግንብ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእንጨት ፡ ቤት ፡ አይደለም ። ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ የሚያስገርመው ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ግልጽ ፡ ሳይሆን ፡ ቀርቶ ፡ በክርክር ፡ መልክ ፡ መቅረቡ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ከቡራን ፡ ተከራካሪዎቻችን ፡ የክርክራቸው ፡ ፋርሽነት ፡ እንደገባቸውና ፡ ወደእኛ ፡ አስተያየት ፡ እንደተመለሱ ፡ ገጾቸው ፡ ይመሰክራል ። አሁንም ፡ በሕንፃ ፡ የሚተላለፈው ፡ ትምህርት ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ መሬትን ፡ እየቆፈሩ ፡ በሚደረገው ፡ ምርመራ ፡ ደግመን ፡ እናስረዳለን ። ሥልጣኔም ፡ ለዓለምም ፡ ሆነ ፡ ለገዛ ፡ ራስ ፡ ሕዝብ ፡ ጎልቶ ፡ የሚታየው ፡ እንደሰማይ ፡ ፈርጦች ፡ ከዋክብት ፡ ቤቶች ፡ በያለበት ፡ ተራራ ፡ ጠቀስ ፡ መስለው ፡ ሲታዩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደዕንቁላል ፡ በያለበት ፡ ጉች ፡ ጉች ፡ ብለው ፡ በሚታዩት ፡ በእንጨት ፡ ቤቶች ፡ አይደለም ።

ዘመኑ ፡ «የዲናሚዝም ፡» ነው ፡ የሚል ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ለመ

ጥቀስ ፡ ትሞክሩ ፡ ይሆናል ፡ ሞክራችኋልም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የእንጨት ፡ ት/ቤቶች ፡ ይህን ፡ የጥድፊያ ፡ ዘመን ፡ አይደግፉም ። መጀመሪያ ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ ተሠርቶ ፡ ያገለግላል ፡ ከዚያም ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ሕዝቡ ፡ በትምህርቱ ፡ ርምጃ ፡ ሀብቱን ፡ ሲያሻሽልና ፡ ሲገፋ ፡ የድንጋይ ፡ ቤቶች ፡ ጉዳይ ፡ ይታሰብበታል ፡ እያሉ ፡ ራስን ፡ ወደኋላ ፡ መጎተት ፡ ዘመኑ ፡ የዲናሚዝም ፡ ነው ፡ ከሚለው ፡ ጋር ፡ አይስማማም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሁለታችንም ፡ ተከራካሪዎች ፡ ርታታን ፡ ባንድነት ፡ ለማግኘት ፡ ስለማንችል ፡ የተከበራችሁ ፡ ዳኞች ፡ አእምሮአችሁ ፡ ባመለከታችሁ ፡ መሠረት ፡ ፍርዳችሁን ፡ እንድትሰጡን ፡ ከፊታችሁ ፡ ቆመናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

ካልዘነጋን ፡ በስተቀር ፡ የተከለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የአራት ፡ ዓመታት ፡ ትምህርትን ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ተማሪዎቹ ፡ ወደልዩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ተሠማርተው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የማስተማር ፡ ተግባርን ፡ ተለማምደው ፡ እንዲመለሱለት ፡ ወስኖ ፡ ሥራውን ፡ መቀጠሉን ፡ ዐውቀን ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ ከየጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ለመኀብኘት ፡ የሚመጡትን ፡ ዐዋቂዎች ፡ እንደዚሁም ፡ በትምህርትና ፡ በማስተማር ፡ ተግባር ፡ ላይ የበሰሉ ፡ ሰዎችን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለንግግር ፡ እየጋበዘ ፡ ተማሪዎቹን ፡ በዕውቀት ፡ ያደረጅ ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ፕሮግራም ፡ ተማሪዎች ፡ ከአገራቸው ፡ ዐዋቂዎች ፡ ጋር፡ ከመተዋወቃቸው ፡ በላይ ፡ ከክፍል ፡ ትምህርት ፡ ውጭ ፡ ብዙ ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮችን ፡ ለመማር ፡ ችለው ፡ ነበር ። በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ፕሮግራም ፡ ተማሪዎች ፡ መንፈሳቸውን ፡ በትምህርቱ ፡ ለውጥነት ፡ ያድሳሉ ። አዲስ ፡ ንቃትም ፡ ከሚናገሩት ፡ ሰዎች ፡ ለማግኘት ፡ ይችላሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በትምህርት ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ ሕይወትን ፡ አስተባብሮ ፡ የያዘ ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በመምህርነትና ፡



በኢንስፔክተርነት ፡ የቆዩትን ፡ ሰዎች ፡ ት/ቤቱ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየጠራ ፡ እንዲናገሩ ፡ ሲፈቅድ ፡ ተማሪዎቹ ፡ በአንድና ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ የሚያገኙት ፡ ትምህርት ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ የተቀመመ ፡ የሥራ ፡ ልምምድ ፡ በመሆኑ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ይጠቅማል ። በተለይ ፡ አንዳንድ ፡ ዓመት ፡ አስተምረው ፡ የሚመለሱት ፡ መምህራን ፡ የበለጠ ፡ ትምህርት ፡ ይገበያሉ ። ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ለሥራቸው ፡ ይጠቅማቸው ፡ የነበረው ፡ ሲያስተምሩ ፡ ከተመለከቷቸው ፡ ኢንስፔክተሮችና ፡ መምህራን ፡ መካከል ፡ እየተጠሩ ፡ መጥተው ፡ ይሰጡት ፡ የነበረው ፡ ንግግር ፡ ነው ።

ከላይ ፡ የተነገረውን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የተከለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ዶክተር ፡ ከበደ ፡ ባዩ ፡ አብዛኞቹ ፡ ምሩቃን ፡ ተማሪዎቻቸው ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ከሚያስተምሩባቸው ፡ አውራጆች ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ኢንስፔክተሮች ፡ በትጋት ፡ ከመሥራት ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ያገለገለውን ፡ አንደኛ ፡ ኢንስፔክተር ፡ ለንግግር ፡ በደብዳቤ ፡ ጠሩት ፡ የሚናገርበትም ፡ አርእስት ፡ ኀብረተ ፡ መምህራን ፡ ወደቀ ፡ መዛሙርት ፡ የሚል ፡ ነበር ። የተጠራውም ፡ ኢንስፔክተር ፡ ስም ፡ ይጨነቁ ፡ ይባል ፡ ነበር ። ጥሪውም ፡ ከአሥር ፡ ቀናት ፡ በፊት ፡ ቀደም ፡ ተደርጎ ፡ ተሰጥቶት ፡ ተዘጋጀ ።

ክቡር ፡ ፕሬዚዳንት ፡
ክቡራት ፡ ወይዛዝርት ፡
ክቡራን ፡ መኳንንት ፡
ክቡራት ፡ እኅቶቼና ፡ ክቡራን ፡ ወንድሞቼ ፡

## ኀብረተ ፡ መምህራን ፡ ወደቀ ፡ መዛሙርት ፡

ክቡር ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ባደረጉልኝ ፡ ጥሪ ፡ መሠረት ፡ ዛሬ ፡ በፊታችሁ ፡ ቆሜ ፡ በጥቂት ፡ ቃላት ፡ ስለ ፡ ኀብረተ ፡ መምህራን ፡ ወደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ስናገር ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

አባትና ፡ እናት ፡ ልጆችን ፡ በሥጋ ፡ ሲወልዱ ፡ መምህራን ፡ ደግሞ ፡ ልጆችን ፡ በትምህርት ፡ ረገድ ፡ በመንፈስ ፡ ይወልዳሉ ። ልጆች ፡ ለትምህርት ፡ ከደረሱበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ተመርጠው ፡

ሥራ ፡ እስኪይዙ ፡ ድረስ ፡ በመምህራን ፡ ላይ ፡ የተጣለው ፡ ከባድ ፡ ኀላፊነት ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ ተዘርዝሮ ፡ አያልቅም ።

ተማሪዎች ፡ መጀመሪያ ፡ ይዘውት ፡ የሚመጡት ፡ ጠባይ ፡ ከትምህርታዊ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ በመሆኑ ፡ እስኪለምዱትና ፡ ተጣውረው ፡ ትምህርታቸውን ፡ በመጠነኛ ፡ ፈቃድ ፡ እስኪቀበሉ ፡ ድረስ ፡ ራሳቸው ፡ ተቸግረው ፡ መምህራንን ፡ በብዙ ፡ እንደሚያስቸግሩ ፡ በጥናት ፡ ተረጋግጧል ። እነዚህ ፡ ልጆች ፡ ወላጆቻቸው ፡ በግል ፡ የሚያደርጉላቸውን ፡ አፍቅሮታዊ ፡ የቤት ፡ ርዳታ ፡ ብቻ ፡ እያስታወሱ ፡ መምህሮቻቸውን ፡ ሲጠይቁ ፡ የሚያስለቅሱና ፡ የሚስለቁ ፡ መስሎ ፡ አይታያቸውም ። ስለዚህ ፡ ፍላጎታቸው ፡ ብቻ ፡ እንዲፈጸምላቸው ፡ ይጠይቃሉ ፡ እንጂ ፡ በተራ ፡ እየጠበቁ ፡ የመምህራንን ፡ ርዳታ ፡ ለማግኘት ፡ አያስቡም ። ይህንም ፡ የሚያደርጉት ፡ ባለማወቅ ፡ ነው ፡ ልጆቹ ፡ ዐውቀው ፡ በማስቸገር ፡ አይደለምና እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ የሚያደርጉት ። ስለዚህ ፡ ትክክለኛውን ፡ መንገድ ፡ እንዲከተሉ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በመጠናቸው ፡ እያስረዱ ፡ እንዲመሯቸው ፡ ያስፈልጋል ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ማናቸውንም ፡ ትምህርት ፡ ጥቂት ፡ በጥቂትና ፡ ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ እያከታተሉ ፡ ሲያመጡት ፡ መነሻውና ፡ መድረሻው ፡ በቀላሉ ፡ ይለያል ። ጥያቄዎችም ፡ በሥርዓት ፡ ተከታትለው ፡ ቢሄዱ ፡ ጥያቄዎችና ፡ መልሶች ፡ ተገናዝበው ፡ በልጆች ፡ አእምሮ ፡ ውስጥ ፡ ይጸድቃሉ ። ጥያቄዎች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ወይም ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ሲመለሱ ፡ የማድመጥና ፡ የማስተዋል ፡ ተግባሮች ፡ በቀላሉ ፡ ይፈጸማሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ጥያቄዎች ፡ ተደጋግመው ፡ ሊጠየቁ ፡ አይችሉም ። ስለዚህ ፡ ደንበኛ ፡ ሥርዓትና ፡ ትምህርቶች ፡ ጎን ፡ ለጎን ከመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ ቢነሡ ፡ የመምህራን ፡ ሥራ ፡ ሥርዓትን ፡ እያበጀ ፡ ይሄዳል ። ይህም ፡ ትምህርት ፡ እያደር ፡ ራሳቸውን ፡ የመግዛት ፡ ልምድ ፡ ስለሚሰጣቸው ፡ በጥብቅ ፡ ታስቦበት ፡ ሊመሠረት ፡ የሚገባ ፡ ነው ። የልጆች ፡ ቤተ ፡ ሰባዊ ፡ ጠባብ ፡ ኑሮ ፡ ለመስፋፋት ፡ በሚጀምርበት ፡ ጊዜ ፡ ሥርዓትና ፡ አቅድ ፡ ያበጀ ፡ እንደሆን፡ የወደፊት ፡ ርምጃውን ፡ የሚያግደው ፡ እንቅፋት ፡ በብዙ ፡ ሊታገለው አይችልም ።



ላንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የልጆች ፡ ጨዋታ ፡ የማይረባና ፡ የማይጠቅም ፡ ስለሚመስላቸው ፡ ጨዋታው ፡ ሥርዓት ፡ ቢኖረውና ፡ ባይኖረው ፡ ግድ ፡ የላቸውም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ጨዋታቸውን ፡ ሥርዓት ፡ ባለው ፡ አቅድ ፡ አይመሩላቸውም ። ይህ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ አስተያየት ፡ ነው ። ምናልባት ፡ እነዚህ ፡ የልጆችን ፡ ጨዋታ ፡ ቸለል ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ የጨዋታ ፡ ትምህርትነት ፡ ሳይገባቸው ፡ ቀርቶ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ልጆችን ፡ በመጥላት ፡ አይደለም ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ መንፈስ ፡ የሚያሳዩት ። ስለዚህ ፡ እናንት ፡ ከዚህ ፡ ገናና ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የምትመረቁት ፡ መምህራን ፡ የጨዋታን ፡ ትምህርትነት ፡ በሥራ ፡ ለሕዝብ ፡ ለመግለጽ ፡ ትችሉ ፡ ዘንድና ፡ የክፍል ፡ ሥርዓታዊ ፡ አመራራችሁን ፡ ከቤት ፡ ውስጥ ፡ አውጥታችሁ ፡ ከውጭ ፡ ኑሮ ፡ ጋር ፡ ታያይዙት ፡ ዘንድ ፡ በጥብቅ ፡ ልታስቡበት ፡ ይገባል ።

የብዙዎች ፡ መምህራን ፡ ጉድለት ፡ ልጆችን ፡ በፍቅርና ፡ በሥርዓት ፡ ከመምራት ፡ መቦዘን ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። ይኸውም ፡ ቢማሩ ፡ ዐውቀው ፡ ይማሩ ፡ አለበለዚያ ፡ በእነርሱ ፡ ጥቅም ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ መቸገር ፡ የለብንም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ በእውነቱ ፡ የክፋት ፡ አይሆን ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ የምንቸገረኝን ፡ መንፈስ ፡ ተንተርሶ ፡ የሚጓዝ ፡ ይመስላል ። የጥቂቶች ፡ መምህራን ፡ አስተያየት ፡ ደግሞ ፡ ልጆችን ፡ በጠባብ ፡ ቀንበር ፡ ሰንጎ ፡ ይዞ ፡ የመምራት ፡ ሐሳብ ፡ ሆኖ ፡ ይገኝና ፡ የትምህርት ፡ ቤትን ፡ ኑሮ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ያጨልማል ። ተማሪዎችም ፡ ትምህርትን ፡ ወደመጥላት ፡ ያዘነብላሉ ። እንግዲህ ፡ አሁን ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ወይም ፡ የተነገሩትን ፡ የሁለት ፡ ክፍል ፡ መምህራን ፡ አስተያየቶች ፡ በሚቻል ፡ መጠን ፡ ማስታረቅ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ።

ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ ለመምረጥና ፡ ለመያዝ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ባለመብት ፡ መሆኑን ፡ ከመካከላችን ፡ የማያስተውል ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሚመጥነው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ተደቅኖ ፡ ከኑሮ ፡ ጋር ፡ ለመፋተግ ፡ ምርጫ ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተጠንቅቆ ፡ እንዲያስብበት ፡ ያስፈልገዋል ፡ ብለን ፡ አስተያየታችንን ፡ እንገልጻለን ። እንደዚሁም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መምህር ፡ ለመሆን ፡ ሲያስብ ፡ የመምህር ፡ ተግባር ፡ ምን ፡ ምን ፡ እንደሆን

በውቆና ፡ ተረድቶ ፡ መምረጥ ፡ ይገባዋል ፡ ወይም ፡ ይገባው ፡ ነበር ፡ ብለን ፡ እንገምታለን ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ አስተያየት ፡ ማናቸውም ፡ መምህር ፡ የመምህርነትን ፡ ሥራ ፡ የሚመርጠው ፡ በውቆና ፡ ተረድቶ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ወድዶ ፡ የመረጠውን ፡ ሥራ ፡ አጥብቆ ፡ ተከታትሎ ፡ እንዲያጠናውና ፡ በሥርዓት ፡ እንዲመራው ፡ ያስፈልገዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በአስታራቂ ፡ ወይም ፡ በአማካይ ፡ አስተያየት ፡ መምህራን ፡ ሁሉ ፡ የመረጡትን ፡ ትምህርት ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ እየመጠኑና ፡ ረድፍ ፡ እያበጁ ፡ በሥርዓት ፡ እንዲያስተምሩ ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ሥራቸውን ፡ እንዲወዱና ፡ በጣም ፡ ተግተው ፡ እንዲያስቡበት ፡ መጣር ፡ ፈንታቸው ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያደረጉ ፡ እንደሆን ፡ ትምህርታቸው ፡ የማያዳግም ፡ በመሆኑ ፡ የቁጣንና ፡ የምን ፡ ቸገረኝን ፡ መንፈስ ፡ ከላያቸው ፡ ፈጽመው ፡ ያርቃሉ ።

ልጆች ፡ እኛ ፡ እንደምንገምታቸው ፡ የማያስተውሉና ፡ የማያስቡ ፡ አይደሉም ። በትምህርትም ፡ በጨዋታም ፡ በወዳጅነትም ፡ የሚያስቡላቸውን ፡ መምህራንና ፡ ምን ፡ ቸገረን ፡ ብለው ፡ የሚነግሯቸውን ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ያውቋቸዋል ። ስለዚህ ፡ ብልኅ ፡ መምህር ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ተገንዝቦ ፡ የተቀበለውን ፡ ኃላፊነት ፡ በቅንነት ፡ ቢሠራ ፡ በተግባሩ ፡ ላይ ፡ የኅሊና ፡ ደስታን ፡ ያላንዳች ፡ ጥርጥር ፡ ያገኛል ። በመልካም ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮም ፡ የመራቸው ፡ ልጆች ፡ ውጤት ፡ እያስደሰተው ፡ ይሄዳል ።

የመምህራን ፡ ችሎታ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የተለያየ ፡ ነው ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ በትምህርት ፡ የገፉ ፡ መምህራንና ፡ በመጠኑ ፡ የተማሩ ፡ መምህራን ፡ አንድ ፡ አይደሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚያ ፡ ከሁለቱ ፡ የመምህራን ፡ ክፍሎች ፡ ለልጆች ፡ የሚጠቅሙት ፡ የትኞቹ ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡ ቢጠየቅ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ በትምህርት ፡ የገፉት ፡ ተብሎ ፡ ይመለስ ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ መልስ ፡ እውነትም ፡ ውሸትም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። እውነት ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ የተባለው ፡ መምህር ፡ ዕውቀቱን ፡ በሥርዓት ፡ እየመጠነና ፡ ለልጆች ፡ እንደሚገባቸው ፡ አድርጎ ፡ ለማሰናዳት ፡ የቻለ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ሐሰት ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፡ እኔ ፡ በጣም ፡ በትምህርት ፡ የገፋሁ ፡ ነኝና ፡ መሰናዳት ፡ አያስፈልገኝም ፡ ብሎ ፡ እንደፈለገው ፡ ብቻ ፡ ለማስተማር ፡ የሞከረ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ መግለጫ ፡ መሠረት ፡ ለል



ጆች ፡ የሚጠቅሙት ፡ መምህራን ፡ የሚያስተምሩትን ፡ ትምህርት ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ እያዘጋጁ ፡ በመልካም ፡ ሥርዓታዊ ፡ አመራር ፡ የሚያስተምሩና ፡ የሚያስረዱ ፡ በመጨረሻም ፡ ላይ ፡ አጠቃልለው ፡ አጉርሰው ፡ መንፈስን ፡ የሚያሞቁት ፡ ናቸው ። ማናቸውም ፡ በትጋት ፡ የሚሠራ ፡ መምህር ፡ ይህን ፡ አደራረግ ፡ ከሞላ ፡ ጎደል ፡ ማለት ፡ በመጠኑ ፡ ሊፈጽመው ፡ ይችላል ። እንደዚህ ፡ ያለውንም ፡ ሁኔታ ፡ የሚፈጥር ፡ መምህር ፡ ከሚያስተምራቸው ፡ ተማሪዎች ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ልጆች ፡ ጋርም ፡ በጣም ፡ ይፋቀራል ።

ሦስተኛ ፡ አድርገን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ የምንገልጸው ፡ አሳብ ፡ ካለፉት ፡ ሁለቱ ፡ ሥራዎች ፡ ጋር ፡ ይያያዛል ። ከሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ከተሰናዳ ፡ ትምህርት ፡ ጋር ፡ ማናቸውም ፡ የክፍል ፡ ወይም ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ ተስማምቶና ፡ ተዋሕዶ ፡ መቀጠል ፡ አለበት ። ተማሪዎች ፡ በተፈጥሯቸው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ የመሥራት ፡ ዝንባሌ ፡ አላቸው ፡ ማለት ፡ በተፈጥሯቸው ፡ በጣም ፡ መሥራትን ፡ ይወዳሉ ። ጥሩ ፡ ትምህርትን ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ አዘጋጅቶ ፡ በሥርዓታዊ ፡ አመራር ፡ ብቻ ፡ ቢያስተምሯቸው ፡ ፍላጎታቸው ፡ ሊሞላ ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ በመልካም ፡ ቅደም ፡ ተከተላዊ ፡ ሥርዓት ፡ ከተሰናዳው ፡ ትምህርት ፡ ጋር ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ የሚሄዱ ፡ መልመጃች ፡ እየተዘጋጁ ፡ ሊሰጧቸው ፡ ያስፈልጋል ፡ እነዚህም ፡ መልመጃች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በቤት ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በክፍል ፡ እየተሰጡ ፡ ሊለማመዱባቸው ፡ ይገባል ። ተማሪዎች ፡ በዓይናቸው ፡ በማየት ፡ በጆሮአቸው ፡ በመስማትና ፡ በእጃቸው ፡ በመሥራት ፡ ትምህርቶችን የበለጠ ፡ እንደሚያጠኗቸው ፡ መገንዘብና ፡ መሥራትን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ የለም ። እንግዲህ ፡ መምህር ፡ ሁሉ ፡ እነዚህን ፡ ሦስት ፡ ሁኔታዎች ፡ በማስተማር ፡ ተግባሩ ፡ ላይ ፡ ከፈጠረ ፡ ከሚያስተምራቸው ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ እንዳይፋቀር ፡ ምን ፡ የሚከለክለው ፡ ነገር ፡ ሊገኝ ፡ ይችላል ?

አራተኛ ፡ ተግባር ፡ ብናመለከት ፡ መልካም ፡ ይመስለኛል ። ይህም ፡ ተግባር ፡ ከክፍልና ፡ ከቤት ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ የሚሄድ ፡ ነው ። የተማሪዎች ፡ አንባቢነታዊ ፡ ፍላጎት ፡ እየቀጠለ ፡ እንዲሄድና ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ አንብበው ፡ ፍሬ ፡ ፍሬ ፡ ነገሮችን ፡ የመልቀም ፡

ልምምድ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ከሚማሩት ፡ ወይም ፡ ከማይማሩት ፡ አርእስት ፡ ቢሆን ፡ መርጠው ፡ እንዲያነቡና ፡ በክፍል ፡ እንዲያስረዱ ፡ ቢጠየቁ ፡ በመካከላቸው ፡ በትምህርት ፡ የመሽቀዳደም ፡ ፍላጎት ፡ ወይም ፡ ውድድር ፡ ሊፈጠር ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ሁኔታ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የተፈጠረ ፡ እንደሆን ፡ ለትምህርቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ዋና ፡ መርህ ፡ ይሆናቸዋል ። ጥቅሙም ፡ እየገባቸው ፡ ሲሄድ ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ የሚፈጥሩትን ፡ መምህራን ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ እያፈቀሯቸውና ፡ እየወደዱቀቸው ፡ ይሄዳሉ ።

አሁንም ፡ አምስተኛ ፡ ተግባር ፡ ማመልከት ፡ ማስፈለጉ ፡ ነው ፤ ልጆችን ፡ ከቤተ ፡ ሰባዊ ፡ አመራር ፡ ጋር ፡ አጣምሮ ፡ የትምህርት ፡ ቤትን ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮና ፡ በመልካም ፡ አቅድ ፡ የተሰናዳ ፡ ቅደም ፡ ተከተላዊ ፡ አርእስትን ፡ እያስተማሩ ፡ በመልመጆች ፡ ማለስለስ ፡ ብቻ ፡ አለመብቃቱን ፡ ተገንዝበን ፡ ከክፍል ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ ለትምህርቶች ፡ ሁሉ ፡ የሚረዳ ፡ ተግባርን ፡ ጨምረን ፡ እናስረዳለን ። ይኸውም ፡ የክፍልና ፡ የቤት ፡ ሥራዎችን ፡ በጥብቅ ፡ መቈጣጠር ፡ ነው ። መቈጣጠር ፡ ያስፈልጋል ፡ ሲባልም ፡ የሠሩትን ፡ ማመስገንና ፡ ያልሠሩትን ፡ መግረፍ ፡ አይደለም ። የማይሠሩበትን ፡ ሁኔታ ፡ አጥንቶ ፡ እንዲሠሩት ፡ ለማድረግ ፡ መሞከር ፡ ነው ፡ እንጂ ። ልጆች ፡ በሥራ ፡ ካልተበላለጡ ፡ የሥራ ፡ ውድድር ፡ ሊፈጠር ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ የተሰጠው ፡ ሥራ ፡ ምናልባት ፡ ከክፍልም ፡ ውጪ ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ቍጥጥርን ፡ ማግኘት ፡ ያስፈልገዋል ። ይህም ፡ ሁኔታ ፡ ሁል ጊዜ ፡ የመምህርን ፡ ሚዛን ፡ እያከበደ ፡ ያስወድዳል ።

ስድስተኛ ፡ ልጆች ፡ የሚማሯቸው ፡ ትምህርቶች ፡ ከሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ እንዲሰጡ ፡ ያስፈልጋል ። ለምሳሌ ፡ በቋንቋ ፡ ትምህርት ፡ በጽሕፈትና ፡ በንግግር ፡ አሳባቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ እንዲችሉ ፡ እየተረዱ ፡ ቢማሩና ፡ በሥራ ፡ ቢገለጽላቸው ፡ ትምህርቱን ፡ የበለጠ ፡ ይወዱታል ። የድርሰትና ፡ የደብዳቤ ፡ አጻጻፍ ፡ በልጆች ፡ ፊትም ፡ ቆሞ ፡ የመናገር ፡ ልምምድ ፡ ለማስረጃነት ፡ ይጠቅማሉ ። በዚሁ ፡ አንጻር ፡ የመልክዓ ፡ ምድርን ፡ ትምህርት ፡ ቢመለከቱት ፡ ዓለም ፡ በመገበያየት ፡ ረገድና ፡ በመረዳዳት ፡ በኩል ፡ ተደጋጋፊ ፡ እንደሆነ ፡ ያስገነዝባል ። እንግዲህ ፡ የቀሩትንም ፡ አርእስት ፡ አሁን ፡ በተገለጹት ፡ መሠረትነት ፡ ቢመለከቷቸው ፡ የልጆች ፡ መንፈስ ፡ የበለጠ ፡ ይነቃቃል ።



ከዚህ ፡ በላይ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ የተገለጹት ፡ ተግባሮች ፡ በተማሪዎችና ፡ በመምህራን ፡ ተረዳጅነት ፡ በመልካም ፡ ሁኔታ ፡ ቢከናወኑ ፡ አንደኛ ፡ መምህራንና ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ መሪዎች ፡ ተረዳድተው ፡ ጥሩ ፡ ትምህርታዊ ፡ ውጤትን ፡ ያስገኛሉ ። ሁለተኛ ፡ አገርም ፡ በትምህርትና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የታነፁ ፡ ልጆችን ፡ ታገኛለች ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

የአምሳለ ፡ ገነት ፡ አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሥራ ፡ ርምጃ እጅግ ፡ በጣም ፡ እየገነነና ፡ ሥርዓት ፡ እያበጀ ፡ መሄድ ፡ ያዘ ። የአምሳለ ፡ ገነትን ፡ ት/ቤት ፡ የሚመሩት ፡ አማካሪዎች ፡ የእለቃ ፡ ይገባሃልን ፡ የእለቃ ፡ ክንፉንና ፡ የእለቃ ፡ ደጉ ፡ ነገርን ፡ ትምህርትና ፡ የትምህርት ፡ አመራር ፡ በደንብ ፡ ተከታትለው ፡ ተረዱና ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወደዘመናዊው ፡ ትምህርት ፡ ለመሳብ ፡ አሰቡ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የሦስቱንም ፡ መምህራን ፡ ትምህርት ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ በፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ ለማስገባት ፡ እንደሚቻል ፡ ሁለት ፡ ዐዋቂዎች ፡ አጥንተው ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ተጠይቀው ፡ በማጣመር ፡ አሰናድተው ፡ አቀረቡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የተጠናው ፡ ነገር ፡ ለአማካሪዎች ፡ ቀረበላቸው ።

የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ት/ቤት ፡ አማካሪዎች ፡ የቀረበላቸውን ፡ አስተያየት ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ በጥንቃቄ ፡ እየተከራከሩ ፡ አጠኑትና ፡ መምህር ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡ ግብረ-ገብነትን ፡ መምህር ፡ ይገባሃል ፡ ዜማንና ፡ የቁም ፡ ጽሕፈትን ፡ መምህር ፡ ክንፉ ፡ ግዕዝ ፡ ጠቀስ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎችን ፡ እንዲያስተምሩ ፡ ተስማሙ ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ትምህርቶች ፡ ከሰባተኛ ፡ ክፍል ፡ በታች ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ጥቅም ፡ እንደማይሰጡ ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ አማካሪ ፡ አሳስቦ ፡ እንደገና ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ እንደሚጀምሩ ፡ ለማጥናት ፡ በቀጠሮ ፡ ተለያዩ ።

በተወሰነው ፡ ቀጠሮ ፡ አማካሪዎቹ ፡ በሙሉ ፡ ጉዳዩን ፡ አጥንተውት ፡ መጡ ። አሁንም ፡ አሳብ ፡ ለአሳብ ፡ ተለዋውጠው ፡ ለአገባቡ ፡ ወይም ፡ ለአጀማመሩ ፡ ፈርጅ ፡ ካበጁለት ፡ በኋላ ፡ ዜማና ፡ ቁም ፡

ጽሕፈት ፡ ግብረ ፡ ገብነትም ፡ ከአምስተኛ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ግዕዝ ፡
ጠቀስ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ከስምንተኛ ፡ ክፍሎች ፡ እንዲማሩ ፡ ተስማም
ተው ፡ ወስኑ ፡ ቀጥለውም ፡ በአንድ ፡ ሳምንት ፡ ሁለት ፡ የትምህርት ፡
ክፍለ ፡ ጊዜያት ፡ ተሰጥቷቸው ፡ በሥርዓተ ፡ ትምህርቱ ፡ ውስጥ ፡ እን
ዲገቡ ፡ ሁለተኛ ፡ ውሳኔ ፡ አድርገው ፡ የስብሰባው ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ።

እነሆ ፡ በገዛ ፡ ራስ ፡ የደከሙበት ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ዋጋ
ውን ፡ ለማግኘት ፡ መቻሉን ፡ በነዚህ ፡ መምህራን ፡ ልንረዳ ፡ ቻልን ።
ታዲያ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ አንዳንድ ፡ መምህራን ፡ ያገር ፡ ምድሩን ፡
ዕውቀት ፡ ሰብስበው ፡ በራሳቸው ፡ ከተው ፡ እንዲያው ፡ በማዞር ፡ ሳይ
ሠሩበት ፡ ወይም ፡ ሳያሠሩበት ፡ እንቀዋለው ፡ ያስቀሩታል ። እንደነ
ዚህ ፡ ያሉት ፡ መምህራን ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፡ ይበላ
ሻሉ ? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ቢገጥመን ፡ ብዙ ፡ መልስ ፡ ሊኖረን ፡ ይችላል ።

አንደኛ / የሚማሩትን ፡ ትምህርት ፡ በጠቅላላ ፡ እንደልማድ ፡ ስለሚ
ቈጥሩትና ፡ መንፈሳቸውን ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ስለማያነሡት ፡ ነው ።

ሁለተኛ / ትምህርቱ ፡ የሚገኘው ፡ በልመናና ፡ በሙታን ፡ ስንቅ ፡
በመሆኑ ፡ ብዙ ፡ ነገሮችን ፡ እያለዋወጡ ፡ ሠርቶ ፡ ለመጠቀም ፡
በምሳሌነት ፡ የተገኙ ፡ ሰዎች ፡ ባለመብዛታቸው ፡ ነው ።

ሦስተኛ / ልማድ ፡ አያይዞ ፡ ያመጣው ፡ ጠለኛ ፡ ቀልድ ፡ ቁም ፡ ነገ
ራም ፡ ተግባሮችን ፡ ሸፍኖ ፡ መንፈሳቸውን ፡ ስላዛለው ፡ ነው ።

አራተኛ ፡ «ዘኢጾረ ፡ መስቀለ ፡ ሞትየ ፡ ኢይክል ፡ ይጸመደኒ ፡» ያለ
ውን ፡ በልማድ ፡ ዘንግተው ፡ የበሰለ ፡ ጥቅመ ፡ ዓለምን ፡ ብቻ ፡
በማሳደዳቸው ፡ ነው ።

አምስተኛ / ትምህርትንና ፡ ተግባርን ፡ አጣምረው ፡ ባለመያዛቸው ፡
የሥራው ፡ ነገር ፡ እየከበደ ፡ ስለሚያስፈራራቸው ፡ ነው ።

ስድስተኛ / በእነርሱ ፡ ዘመን ፡ የነበሩት ፡ ት/ቤቶች ፡ የሚሰጧቸው
ንም ፡ ትምህርቶች ፡ በፕሮግራም ፡ አሰናድተው ፡ ከዓለማዊው ፡
ኑሮ ፡ ጋር ፡ ባለማዛመዳቸውና ፡ አርቆ ፡ አሳቢነትን ፡ በተማሪዎ
ቻቸው ፡ ላይ ፡ ባለማሳደራቸው ፡ ነው ።

እነሆ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ምክንያቶች ፡
ታግሎ ፡ የሚያጠፋቸው ፡ ወንድ ፡ ባለመኖሩ ፡ ታላላቆቹን ፡ ሰዎች ፡
ሳይቀር ፡ ሲያጉላሉና ፡ ሲያስወቅሱ ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ደረሱ ። ነገር ፡
ግን ፡ ታግለው ፡ ያሸነፏቸው ፡ ትጉሃን ፡ መምህራን ፡ አሮጌውን ፡ የት



ምህርት ፡ ዘዴ ፡ አሻሽለው ፡ ከዘመናዊው ፡ አመራር ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡
እያስታረቁ ፡ እንደሚመሩት ፡ የመምህር ፡ ይገባሃል ፡ የመምህር ፡ ክን
ፋና ፡ የመምህር ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡ ተግባሮች ፡ ይገልጹልናል ።

መምህር ፡ ይገባሃል ፡ መምህር ፡ ክንፋና ፡ መምህር ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡
የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በትምህርት ፡ አመራር ፡ መን
ገድ ፡ አንድ ፡ መምህር ፡ እንዲያስጠናቸው ፡ ሥራ ፡ መሪውን ፡ ጠየ
ቁት ።

መቼም ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ኑሮን ፡ የሚያሻሽል ፡ ነገር ፡ ሲገኝ ፡
ለተገኘው ፡ መሻሻል ፡ መሠረት ፡ የሆነ ፡ ነገርን ፡ ወይም ፡
የሆኑ ፡ ነገሮችን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ማስጣል ፡ እንደማይገባ ፡ በጥቂቶች ፡
ሰዎች ፡ ብቻ ፡ እንደሚታመነው ፡ ሁሉ ፡ አለቃ ፡ ይገባሃል ፡ አለቃ ፡
ክንፋና ፡ አለቃ ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡ ረዳት ፡ አፈ ፡ መምህራንን ፡ በዘመኑ ፡
ሁኔታ ፡ ጎናቸው ፡ በሚፈቅድላቸው ፡ መሠረት ፡ ለመቅጠር ፡ አስ
በው ፡ ሲፈላለጉ ፡ ከሦስቱ ፡ አንዱ ፡ አለቃ ፡ ይገባሃል ፡ ለቁም ፡ ጽሕ
ፈትና ፡ ለሥዕል ፡ ሥራ ፡ ባለማግኘት ፡ በብስጭት ፡ ላይ ፡ የሚብሰለ
ሰለውን ፡ ወጣት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የምናውቀውን ፡ እምኀ ፡ እውነ
ቱን ፡ ለግማሽ ፡ ቀን ፡ ቀጠሩት ። እንዳጋጣሚ ፡ መምህር ፡ ይገባሃል ፡
በአምሳለ ፡ ገነተ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲያስተምሩ ፡ ሲፈቀድላ
ቸው ፡ የትምህርቱ ፡ ክፍለ ፡ ጊዜያት ፡ ተሻሽለው ፡ የሚያስተምሩት ፡
ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ስለነበር ፡ እምኀ ፡ እውነቱን ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ እንዲ
ያስተምርላቸው ፡ የትምህርት ፡ ቤታቸውን ፡ ፕሮግራም ፡ በሥርዓት ፡
አሰናዱ ።

እምኀ ፡ በዚህ ፡ አጋጣሚ ፡ ዕድል ፡ ማለት ፡ በችሎታው ፡ የመ
ሥራት ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ በትምህርት ፡ ችሎታው ፡ በትጋቱና ፡ በአ
መሉ ፡ ስለገጠመው ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደስቶ ፡ ሥራውን ፡ በደስታ ፡
ተቀብሎ ፡ ጀመረ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በቤት ፡ ችግር ፡ ባይኖርባቸው ፡
አቶ ፡ ደገፉም ፡ የደስታው ፡ ተካፋይ ፡ ሆኑ ። ምክንያቱም ፡ በግድ ፡
ሥራ ፡ ካላገኘሁ ፡ እያለ ፡ ልጁ ፡ ዘወትር ፡ ሲበሳጭ ፡ በማየታቸው ፡
ነው ። አቶ ፡ ደገፉ ፡ ልጁ ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ ገፍቶ ፡ የሊ
ቅነት ፡ ማዕርግ ፡ እንዲያገኝ ፡ ያስቡ ፡ ስለነበር ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ሐዘ
ናቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ያበሳጫቸው ፡ ነበር ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በሥራ
ውና ፡ በውሎው ፡ ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ስላልራቀ ፡ ለሐዘናቸው ፡ ማስ

ረሻ ፡ አግኝተው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እያማለጥሀ ፡
የቅኔ ፡ ትምህርትህን ፡ ግፋበት ፡ እያሉ ፡ አሁንም ፡ ማተጋጋታቸው ፡
አልቀረም ።

የትምህርት ፡ እሳት ፡ እንደዶሬ ፡ ፍልጥ ፡ አንድዶ ፡ ያፋመው ፡
ሰው ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እርፎ ፡ ለመተኛት ፡ የማይቻለው ፡
በመሆኑ ፡ ዘወትር ፡ ቁጭቱን ፡ ለመወጣት ፡ ያስባል ። አብዛኛውንም
ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ ተመላልሶ ፡ ከመልካም ፡ አጋ
ጣሚ ፡ ፍጻሜ ፡ ይደርስና ፡ በተመስገናዊ ፡ ደስታ ፡ ይጥለቀለቃል ።
እምኀም ፡ እንደዚሁ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲቸገር ፡ ቆይቶ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡
በማግኘቱ ፡ እንደገና ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርቱን ፡ ለመጨረስና ፡
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ባንድ ፡ ተግባራዊ ፡ ትምህርት ፡ ሠልጥኖ ፡ ለመመ
ረቅ ፡ አሰበ ። በእውነትም ፡ እርሱ ፡ የሚያስተምረው ፡ ከሰዓት ፡
በኋላ ፡ ስለሆነ ፡ ከሰዓት ፡ በፊት ፡ ቢማርና ፡ ጊዜ ፡ ያላገኘላቸውን ፡
ትምህርቶች ፡ ከልጆች ፡ እየተረዳ ፡ ለመቀጠል ፡ ቢሞክር ፡ ምንም ፡
ያህል ፡ ሳይቸገር ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃን ፡ ትምህርት ፡ ፋት ፡ እንደሚላት
ተገነዘበ ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ እንቱ ፡ ለዕረ
ፍት ፡ ስትመጣ ፡ አማክሯት ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ለመጀመር ፡ ቁርጥ
አሳብ ፡ አደረገ ። መቼም ፡ ምንም ፡ ኅበዝ ፡ ሲሆኑ ፡ ቢውሉ ፡ በግማሽ ፡
ጊዜ ፡ በሁለተኛ ፡ ተርም ፡ ላይ ፡ ትምህርቶችን ፡ በሙሉ ፡ ፕሮግራም ፡
መሠረት ፡ ተምሮና ፡ አጥንቶ ፡ ለማለፍ ፡ የሚቻል ፡ ነገር ፡ አይደ
ለም ። እነሆ ፡ የትምህርትን ፡ መጀመሪያ ፡ ዓመትና ፡ ተርም ፡ እምኃ ፡
የጠበቀበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ለዕረፍት ፡ እንደተዘጉ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡
የአንድ ፡ ዓመት ፡ የማስተማር ፡ ሥራዋን ፡ አከናውና ፡ ወደ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተመልሳ
እንደገና ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ በትምህርት ፡
ቤቱ ፡ ፕሮግራም ፡ መሠረት ፡ ተመዝግባ ፡ በአምሳለ ፡ ገነት ፡ ያሉ



ትን ፡ ዘመዶችዋን ፡ ለማየት ፡ ጉዞዋን ፡ ቀጠለች ። ወንድሟ ፡ እምኃ ፡
እውነቱና ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ ከነቤተሰቡ ፡ በናፍቆት ፡ ይጠብቋት ፡ ነበ
ርና ፡ ከአውቶቡስ ፡ ስትወርድ ፡ በናፍቆት ፡ ስስት ፡ እያነቁ ፡ ጨመ
ጨሟት ። ብዙም ፡ የሚያውቋት ፡ ወዳጆች ፡ እንዳጋጣሚ ፡ በዚያ ፡
ነበሩና ፡ የናፍቆት ፡ ሰላምታቸውን ፡ በአክብሮት ፡ አቀረቡላት ። በእ
ንዴት ፡ ነሽና ፡ በእንደምን ፡ አላችሁ ፡ ጥቂት ፡ ደቂቆች ፡ ካሳለፉ ፡
በኋላ ፡ በአቶ ፡ ደገፉ ፡ መሪነት ፡ ወደቤት ፡ ሄዱ ፡ በመንገድም ፡ ብዙ ፡
ሰዎች ፡ በተለይም ፡ የወላጆቿ ፡ ወዳጆች ፡ የነበሩ ፡ ሁሉ ፡ እዚህም ፡
እዚያም ፡ ሲያገኟት ፡ ቆም ፡ እያሉ ፡ የማክበር ፡ ሰላምታቸውን ፡ ያቀር
ቡላት ፡ ነበር ፡ እርስዋም ፡ በፈገግታ ፡ ሰላምታቸውን ፡ እየተቀበለ
ችና ፡ እያነጋገረቻቸው ፡ ስታልፍ ፡ ከቤት ፡ ደረሱ ።

ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ከተዘጋጀላት ፡ ክፍል ፡ ገብታ ፡ ሻንጣዋን ፡
አሳርፋ ፡ ፊቷን ፡ ተጣጥባ ፡ የመንገድ ፡ ልብስዋን ፡ ከለወጠች ፡ በኋላ
ወደማረፊያው ፡ ክፍል ፡ በተመለሰች ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ዘመዶችና ፡ ወዳ
ጆች ፡ መጥተው ፡ ሲጠብቋት ፡ አገኘች ። አሁንም ፡ የተሰበሰቡት ፡
ሁሉ ፡ እንደትርንጎ ፡ ገማመጧትና ፡ በሰላምታ ፡ መካከል ፡ በጥያቄና ፡
መልስ ፡ ጨዋታ ፡ ደራ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የአቶ ፡ ደገፉ ፡ ባለቤት ፡ ወይ
ዘሮ ፡ ላቅሻቸው ፡ ሙዝ ፡ ሙዝ ፡ የሚል ፡ እንኮይ ፡ የመሰለ ፡ ጠላቸ
ውን ፡ ከጠሩ ፡ ብርጭቆች ፡ ጋር ፡ አስመጥተው ፡ በየእንስተኞች ፡
ጠረጴዞች ፡ ላይ ፡ አስደረደሯቸው ። ቀጥሎም ፡ የጠላ ፡ ቁርስ ፡ እን
ዳቦ ፡ ቆሎና ፡ እንጭኮ ፡ በእንስተኞች ፡ ዝርግ ፡ ሣሕኖች ፡ ላይ ፡ እየ
ሆኑ ፡ መጥተው ፡ ተደረደሩና ፡ እንስተኞች ፡ ጠረጴዞችን ፡ አስጌጧ
ቸው ። ከዚህ ፡ ወዲያማ ፡ በመዝናናት ፡ ወሬዎች ፡ በጣም ፡ ደሩ ። ከወ
ሬዎቹ ፡ አርእስት ፡ ውስጥ ፡ አስተማሪዎችና ፡ ተማሪዎች ፡ ትምህር
ትና ፡ ሥራ ፡ ትጋትና ፡ ስንፍና ፡ የሞተ ፡ ብቻ ፡ ተጎዳ ፡ የሚባሉ ፡ ነበ
ሩባቸው ። ሰዎቹም ፡ በየበኩላቸው ፡ ትንንሾች ፡ ጠረጴዞችን ፡ ከበው ፡
ያወጉ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ እምኃ ፡ አንድ ፡ የደስታ ፡ መግ
ለጫ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ኖሮ ፡ ለመዘመር ፡ ያቶ ፡ ደገፉንና ፡ የወይዘሮ ፡ ላቅ
ሻቸውን ፡ ፈቃድ ፡ ጠየቀ ። እነርሱም ፡ በደስታ ፡ ፈቀዱለት ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጸጋ ፡ ነው ።

ምስጋና ፡ ይድረሰው ፡ ለቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡
ያን ፡ ሁሉ ፡ አሳልፎ ፡ ላበቃን ፡ ለዘር ።

ቀኑ ፡ ጨልሞብን ፡ በደመና ፡ ሌሊት ፡
ይኸው ፡ አለፈና ፡ ሊደረግ ፡ ነው ፡ ርስት ።

አባባ ፡ ደገፋ ፡ እማማ ፡ ላቅሻቸው ፡
ባለውለቶቹ ፡ በመልካም ፡ ግብራቸው ፡
በመሰላቸው ፡ አቅድ ፡ ለኑሮ ፡ ምርጫቸው ፡
ይኸው ፡ አሳደጉን ፡ በትምህርት ፡ መርተው ።

ቤቱ ፡ ተጊያጊጧል ፡ አሸብርቋል ፡ ዛሬ ፡
ደማሜ ፡ እኮ ፡ ነች ፡ ተቀበይ ፡ አገሬ ።

ደማሜ ፡ አብባለች ፡ እኔም ፡ ለምልሚያለሁ ፡
መቆያችን ፡ አምሯል ፡ ጨዋታውም ፡ እንዲሁ ፡

ዘመድ ፡ አዝማድ ፡ መጥቷል ፡ ተደርጓል ፡ ፍሥሐ ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጸጋ ፡ ነው ፡ የአምላክ ፡ አምኃ ።

አባባ ፡ አልሞትህም ፡ እማማ ፡ አልሞትሽም ፡
ወንድሞቼ ፡ አላችሁ ፡ ከቶ ፡ አልሞታችሁም ፡
ካብትሼ ፡ አልሞትሽም ፡
ደመቀም ፡ አልሞትህም ፡
ደርሰንላችኋል ፡ በእግራችሁ ፡ ለመቆም ።

የዛሬው ፡ ደስታ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጨዋታ ፡
የምራት ፡ ፍሬ ፡ ነው ፡ የሥራ ፡ ውጤታ ።

እባካችሁ ፡ አሁን ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡ ታዩልን ፡
በማስተንተንማ ፡ መች ፡ ተለያችሁን ።

አምኃ ፡ በአሁኑ ፡ መዝሙሩ ፡ እቶ ፡ ደገፋን ፡ ወይዘሮ ፡ ላቅሻቸውንና፡ የተሰበሰቡትን ፡ እንግዶች ፡ እንደዚሁም ፡ ሕፃናቱን ፡ በመላ ፡ እንደ



ቆሬ ፡ ውኃ ፡ አዋለሳቸውና ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ እንዲያው ፡ በመሐረብ ፡ ይጠርጉ ፡ ጀመር ። ደማሜማ ፡ እዚያው ፡ አለችበት ፡ ውኃ ፡ እየሆነች፡ ልፍረስ ፡ ልፍረስ ፡ በማለት ፡ ተንሰቀሰቀች ። ነገር ፡ ግን ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ባልቴቶች ፡ የዳመነውን ፡ ሐዘን ፡ በቶሎ ፡ ሌሎች ፡ አርእስት ፡ ተክተው ፡ አስወገዱትና ፡ የቤቱ ፡ ድፍርስ ፡ አየር ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ ታደሰ ። እንደቅድሙ ፡ ጨዋታው ፡ አሁንም ፡ ደርቶ ፡ አዳሜ ፡ ሲፍለቀለቅ ፡ ቆይቶ ፡ እየተሰናበተ ፡ ወደየቤቱ ፡ ሄደ ።

ራት ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ እውነቱ ፡ ለእኅቷ ፡ ልጆች ፡ ያመጣችላቸውን ፡ አሻንጉሊቶችና ፡ ጌጠኞች ፡ የጥጥ ፡ ሹራቦች ፡ ከሣጥኗ ፡ ውስጥ ፡ እያወጣች ፡ በጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ከመረቻቸው ። ሕፃናት ፡ በየስማቸው ፡ እየተጠሩ ፡ ቀርበው ፡ በየስማቸው ፡ የተመደቡትን ፡ ተቀብለው ፡ በመደሰት ፡ መፈንጠዝን ፡ ገንዘብ ፡ አደረጉት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራት ፡ ቀርቦ ፡ ሁሉም ፡ በየቦታው ፡ ሲገኝ ፡ ሕፃናቱ ፡ አሻንጉሊቶቻቸውን ፡ በየብብታቸው ፡ እየሻጡ ፡ ቀረቡ ። አዲሱ ፡ የአሻንጉሊት ፡ ፍቅር ፡ የልጆችን ፡ የምግብ ፡ ፍላጎት ፡ በእዚያ ፡ ዕለት ፡ ቀንሶት ፡ ኖሮ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሳይበሉ ፡ ሕፃናት ፡ የበቃንን ፡ ድምፅ ፡ አሰምተው ፡ ተነሡ ። መሳቅ ፡ መሯሯጥና ፡ ማበላለጥ ተግባራቸውን ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ አሳዩ ። የመኝታ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ አንዳንዶቹ ፡ አሻንጉሊቶቻቸውን ፡ እንዳቀፉ ፡ ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ በትራስጊያቸው ፡ እያደረጉ ፡ ከአልጋቸው ፡ ላይ ፡ ወገባቸውን ፡ እንዳሳረፉ ፡ እቶ ፡ እንቅልፍ ፡ እየያዛቸው ፡ ነጎደ ። በማግሥቱ ፡ እሑድ ፡ ስለነበር ፡ እቶ ፡ ደገፋና ፡ ወይዘሮ ፡ ላቅሻቸው ፡ አምኃም ፡ ሆነው ፡ የቤተ ፡ ሰዎቹን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሳሚያ ፡ ልብሶች ፡ እየለዩ ፡ አሰናዱና ፡ እነርሱም ፡ በተራቸው ፡ ተኙ ።

በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ ቤተሰቦቹ ፡ ሁሉ ፡ ከየመኝታቸው ፡ ተነሥተው ፡ ፊታቸውን ፡ ከታጠቡ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተያይዘው ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያደርጉት ፡ እንደነበረው ፡ በስመ ፡ ሥላሴ ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሰግደው ፡ የጸሎት ቦታቸውን ፡ ያዙ ። ሁሉም ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡ የእንብርካዊ ፡ ጸሎትን ፡ በታላቅ ፡ ጸጥታ ፡ አደረሱ ።

አንድ ፡ ካህን ፡ ከመቅደስ ፡ ውስጥ ፡ በዓምደ ፡ ወርቁ ፡ አጠገብ ፡ ብቅ ፡ ብለው ፡ « ሁላችሁም ፡ የሐዲስ ፡ መጽሐፋችሁን ፡ አንሡና ፡-

ሁለተኛዪቱን ፡ የሐዋርያውን ፡ የጳውሎስን ፡ መልእክት ፡ ለተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ የተላከችውን ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ከአንድ ፡ ቁጥር ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ድረስ ፡ አውጡ ፡ ይኸው ፡ እኔ ፡ አሁን ፡ ላነብላችሁ ፡ ነው ፡ » ሲሉ ፡ መምሪያን ፡ ሰጡ ።

## ምንባቡ ።

« በቀረውስ ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ የጌታ ፡ ቃል ፡ እንዲሮጥ ፡ በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ደግሞ ፡ እንደሚሆን ፡ እንዲከበር ፡ እምነትም ፡ ለሁሉ ፡ ስለማይሆን ፡ ከዓመጸኞችና ፡ ከክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ እንድንድን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ጸልዩ ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚያጸናችሁ ፡ ከክፉውም ፡ የሚጠብቃችሁ ፡ ጌታ ፡ የታመነ ፡ ነው ። የምናዛችሁንም ፡ አሁን ፡ እንድታደርጉ ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ ደግሞ ፡ እንድታደርጉ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ በጌታ ፡ ታምነናል ። ጌታም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ወደ ፡ ክርስቶስም ትዕግሥት ፡ ልባችንን ፡ ያቅናው ።

ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ ከእኛ ፡ እንደተቀበለው ፡ ወግ ፡ ሳይሆን ፡ ያለ ፡ ሥርዓት ፡ ከሚሄድ ፡ ወንድም ፡ ሁሉ ፡ ትለዩ ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እናዛችኋለን ። እኛን ፡ ልትመስሉ ፡ እንዴት ፡ እንደሚገባችሁ ፡ ራሳችሁ ፡ ታውቃላችሁና ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ሥርዓት ፡ አልሄድንምና ፡ ከእናንተም ፡ ዘንድ ፡ በአንዱ ፡ ስንኳ ፡ እንዳንከብድበት ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ በድካምና ፡ በጥረት ፡ እየሠራን ፡ እንኖር ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ከማንም ፡ እንጀራን ፡ እንዲያው ፡ አልበላንም ። ይህም ፡ እኛን ፡ ልትመስሉ ፡ ራሳችንን ፡ እንደ ፡ ምሳሌ ፡ እንሰጣችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ያለሥልጣን ፡ ስለሆን ፡ አይደለም ፡ ደግሞ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ሳለን ፡ ሊሠራ ፡ የማይወድ ፡ አይብላ ፡ ብለን ፡ አዘናችሁ ፡ ነበርና ። ሥራ ፡ ከቶ ፡ ሳይሠሩ ፡ በሰው ፡ ነገር ፡ እየገቡ ፡ ያለ ፡ ሥርዓት ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚሄዱ ፡ ስለ ፡ አንዳንዶች ፡ ሰምተናል ። እንደነዚህ ፡ ያሉትንም ፡ በጸጥታ ፡ እየሠሩ ፡ የገዛ ፡ እንጀራቸውን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እናዛቸዋለን ፡ እንመክራቸውማለን ። እናንተ ፡ ግን ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ መልካም ፡ ሥራን ፡ ለመሥራት ፡ አትታክቱ ።

በዚህ ፡ መልእክት ፡ ለተላከ ፡ ቃላችን ፡ የማይታዘዝ ፡ ማንም ፡



ቢኖር ፡ ይህን ፡ ተመልከቱት ፡ ያፍርም ፡ ዘንድ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አትተባበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ወንድም ፡ ገሥጹት ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ አትቍጠሩት ። የሰላምም ፡ ጌታ ፡ ራሱ ፡ በሁሉ ፡ መንገድ ፡ ዘወትር ፡ ሰላምን ፡ ይስጣችሁ ። ጌታ ፡ ከሁላችሁ ፡ ጋር ፡ ይሁን ።

በገዛ ፡ እጄ ፡ የተጻፈ ፡ የእኔ ፡ የጳውሎስ ፡ ሰላምታ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የመልእክቴ ፡ ሁሉ ፡ ማስረጃ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ እጽፋለሁ ። የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከሁላችሁ ፡ ጋር ፡ ይሁን ። »

« አሁን ፡ ያነበብነው ፡ መልእክት ፡ ምሥጢር ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ሥራ ፡ የአምላክ ፡ ትእዛዝ ፡ መሆኑንና ፡ ሠርቶ ፡ መብላትም ፡ የትእዛዙ ፡ ዘርፍ ፡ መሆኑንም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስልት ፡ ይገልጽልናል ። እግዚአብሔር ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶ ፡ ይደር ፡ ሲል ፡ ያዘዘው ፡ ራሱ ፡ እየሠራ ፡ በማሳየት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በከንቱ ፡ አይደለም ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደሚነግረን ፡ እግዚአብሔር ፡ የመፍጠር ፡ ተግባሩን ፡ የፈጸመው ፡ በስድስት ፡ ቀናት ፡ ነው ። ለመሆኑ ፡ አምላካችን ፡ የዓለማት ሁሉ ፡ ገገር ፡ እግዚአብሔር ፡ የመፍጠር ፡ ተግባሩን ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ሥራ ፡ ፈትቶ ፡ ይኖራል ? ወይስ ፡ ዘለዓለም ፡ ይሠራል ? ብለን ፡ ራሳችንን ፡ ብንጠይቅ ፡ ዘወትር ፡ ይሠራል ፡ ወደሚለው ፡ አስተያየት ፡ እናዘነብላለን ። ለማስረጃም ፡ መጀመሪያ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ እንጠቅሳለን ። እንደዚሁም ፡ በተፈጥሮ ፡ ዕውቀታችን ፡ ፍጥረቶቹን ፡ በወሰነላቸው ፡ ሥርዓት ፡ እንዲሄዱ ፡ ሲመለከከት ፡ ሥራው ፡ እንዳይዛነፍ ፡ እንደመጠበቅ ፡ ያህል ፡ ይቆጠራል ። ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጠቅላላ ፡ ዓለማትንና ፡ ሰማያትን ፡ በሥርዓት ፡ ፈጥሮ ፡ በፍጥረት ፡ ሕጋቸው ፡ የሚመራና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥሬያለሁ ፡ ብሎ ፡ ዝም ፡ ሳይል ፡ የሚመለካከት ፡ ገገር ፡ እንኳ ፡ ዘወትር ፡ እንዲህ ፡ ያደርጋል ፡ እንዲህ ፡ ይሠራል ፡ ያዝናል ፡ ይቆጣል ፡ ይቀየማል ፡ በፍርድ ፡ ይቀጣል ፡ እየተባለ ፡ ሲነገርለት ፡ ፍጡርማ ፡ ሠርቶ ፡ ጌታውን ፡ ለማስደሰት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መጣር ፡ ይገባዋል ?

ስለዚህ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥሩ ፡ የሚለው ፡ ሠርቶ ፡ በማሳየት ፡ ስለሆነ ፡ እምነትን ፡ በሥራ ፡ መግለጽ ፡ ግዴታዊ ፡ ተግባር ፡ ነው ። ሰው ፡ ካልሠራ ፡ መጀመሪያ ፡ ራሱን ፡ አይረዳም ። ቀጥሎም ፡ ራሱን ፡ የማይረዳ ፡ ከሆነ ፡ ሌላውን ፡ ሊረዳ ፡ አይችልም ። እንግዲህ ፡ የዛሬውን ፡ ምንባብ ፡ አውጠንጥነን ፡ ራሳችንን ፡ ዘወትር ፡ በጠቃሚ

ተግባር ፡ እንጥመድ ። መጻሕፍት ፡ በሮቻቸውን ፡ ከፍተው ፡ በየቀኑና ፡ በየጊዜው ፡ ሲጋብዙን ፡ ቸልታን ፡ በማብዛት ፡ አንለፋቸው ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ የተጻፉት ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ለእኛ ፡ መመከሪያና ፡ መዘከሪያ ፡ ተጽፈዋል ፡ እንዳለው ፡ እንጠቀምባቸው ፡» ብለው ፡ ስብከታቸውን ፡ ደመደሙ ።

ስብከቱ ፡ እንዳለቀ ፡ ሁለት ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ መዝሙሮች ፡ በማኅበር ፡ ተዘመሩና ፡ ቅዳሴ ፡ ተጀመረ ። ጸሎተ ፡ ቅዳሴውም ፡ በስቲለ ፡ ኅሊና ፡ በሥርዓት ፡ ተከናወነ ። በቅዳሴው ፡ ላይ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ግለኛ ፡ ጸሎቱን ፡ እንሥቶ ፡ በማነብነብ ፡ ባጠገቡ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ አላስቸገረም ። ጸሎቱ ፡ የጋራ ፡ እንጂ ፡ የካህናቱ ፡ ብቻ ፡ አለመሆኑን ፡ በየጊዜው ፡ በሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ መሠረት ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ዐውቆ ፡ ይጨነቅበት ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የእምሳለ ፡ ገነት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕዝብ ፡ በምሳሌነቱ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ይታያል ።

በዚሁ ፡ ቀን ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሚና ፡ እምኀ ፡ ለሽርሽር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥተው ፡ ሳለ ፡ እምኀ ፡ ለእኅቱ ፡ የግማሽ ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ ማግኘቱንና ፡ በመስከረም ፡ እስከ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ እየተማረ ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርቱን ፡ ለመጨረስ ፡ ማሰቡን ፡ አንድ፡ ባንድ ፡ በዝርዝር ፡ ገለጸላት ። ወይዘሪት ፡ ደማሚም ፡ ይህኑ ፡ ነገር ፡ አስቀድማ ፡ አስባበት ፡ ኖሮ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አላትና ፡ « ይህ ፡ አሳብ ፡ ምናልባት ፡ አጎታችንን ፡ አቶ ፡ ደገፉን ፡ ካላሳዘናቸውና ፡ ካልተሰነካከለ ፡ በስተቀር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ እኔ ፡ የምደግፈው ፡ አስተያየት ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዓለም ፡ ሰው ፡ በመጠኑ ፡ ድልል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ቅኔህንም ፡ ከመጽሐፍ ፡ ትምህርት ፡ ጋር ፡ እየቀጸልህ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎት ፡ እንደማትለይ ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ በለስላሳ ፡ አነጋገር ፡ ብትገልጽላቸው ፡ ይህን ፡ አሳብህን ፡ በደስታ ፡ እንደሚቀበሉህ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

አቶ ፡ ደገፉ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አንተንም ፡ እኔንም ፡ አሳድገው ፡ ከልክ ፡ አደረሱን ። አሁን ፡ ግን ፡ እኛም ፡ በበኩላችን ፡ ራሳችንን ፡ መርዳት ፡ አለብን ። ስለዚህ ፡ አንተ ፡ በግማሽ ፡ ቀን ፡ የምታገኘውን ፡ ቀለብ ፡ በሙሉ ፡ ለእርሳቸው ፡ አስረክብ ። እኔ ፡ ለልብስህና ፡



ለመጻሕፍት ፡ ለደብተርም ፡ መግዣ ፡ እሰብልሃለሁ ። ይህንም ፡ አሳብ ፡ መጀመሪያ ፡ ለአቶ ፡ ደገፉና ፡ ለወይዘሮ ፡ ላቅሻቸው ፡ ማካፈል ፡ ይገባል ። እነርሱም ፡ እንደእኛ ፡ በዚህ ፡ አስተያየት ፡ ቢጸኑ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ አማረ ፡ ማለት ፡ ነው ። አለበለዚያ ፡ ግን ፡ እኛ ፡ ልጆች ፡ ስለሆን ፡ በእነርሱ ፡ አሳብ ፡ መሄድ ፡ አለብን ፡» ብላ ፡ ከማስረዳት ፡ ጋር ፡ አሳቡን ፡ ተቀበለችው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

አንድ ፡ የእነ ፡ እምኀ ፡ እውነቱ ፡ ዘመድ ፡ የሚሆን ፡ በአቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታ ፡ አረዳ ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ ከአቶ ፡ ደገፉ ፡ አስፈቅዶ ፡ መሠረት ፡ ለማስጣል ፡ አረዳውን ፡ በቅያስ ፡ ሲያስቆፍር ፡ በሞላላ ፡ አቅድ ፡ የተሠራ ፡ ትልቅ ፡ ባለግጣም ፡ የሸክላ ፡ አገልግል ፡ አገኘ ። ይህ ፡ የሸክላ ፡ አገልግል ፡ በልዩ ፡ ጥበብ ፡ ተገጥሞ ፡ እንደተገኘ ፡ ሊከፈት ፡ የማይቻል ፡ ነገር ፡ ሆነ ። መሠረት ፡ ለመጣል ፡ አስቆፋሪው ፡ ሰውዬና ፡ የአቶ ፡ ደገፉ ፡ ቤተሰብ ፡ በጋብቻ ፡ የተሳሰሩ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ በጣም ፡ ልዩ ፡ ፍቅር ፡ ነበራቸው ። ስለዚህ ፡ ቀኑ ፡ ተቀግዶ ፡ መሽቶ ፡ ሠራተኞቹን ፡ ካሰናበተ ፡ በኋላ ፡ ወስዶ ፡ እስኪሰጣቸው ፡ ድረስ ፡ ጭንቅ ፡ ሆነበት ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ በማስረሳቱ ፡ ምክንያት ፡ ማታ ፡ ረሳውና ፡ በማግሥቱ ፡ ጥዋት ፡ አሸክሞ ፡ ይዞላቸው ፡ ሄደ ። አቶ ፡ ደገፉና ፡ መላ ፡ ቤተሰቡ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የሸክላ ፡ አገልግል ፡ ባለማየታቸው ፡ እጅግ ፡ ተገረሙ ። ነገር ፡ ግን ፡ እምኀ ፡ ከመካከላቸው ፡ አባቱ ፡ ለአሳለፈልንና ፡ ለዘለቀ ፡ ስለእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ ይሰማ ፡ ነበርና ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ሊሆንበት ፡ አልቻለም ። ስለዚህ ፡ እንደቀሩት ፡ እንዳችም ፡ የመገረም ፡ ምልክት ፡ ሳያሳይ ፡ እንዲያው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ በወንበሩ ፡ ላይ ፡ እንደተቀመጠ ፡ ይመለከት ፡ ነበር ።

አቶ ፡ ደገፉ ፡- « የሸክላው ፡ አገልግል ፡ በሙቅ ፡ ውኃና ፡ በሳሙና ፡ ከታጠበና ፡ ቅባት ፡ ተደርጎበት ፡ እምሮ ፡ ከተወለወለ ፡ በኋላ ፡ ይከፈት ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ አይከፈትም ። እናንተም ፡ እንደምትሉት ፡

አሁን ፡ ይከፈት ፡ ቢባልም ፡ እንዳችም ፡ የአገጣጠም ፡ ፍንጭ ፡ ስላላሳየ ፡ ሳይሰበር ፡ በቀላሉ ፡ ሊከፈት ፡ አይችልም ፡ » ብሎ ፡ አሳብ ፡ አቅርቦ ፡ የሸክላው ፡ አገልግል ፡ በሙቅ ፡ ውኃና ፡ በሳሙና ፡ ታጥቦ ፡ በቅባት ፡ ተወለወለ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የጽዳት ፡ ተግባር ፡ ተፈጽሞበት ፡ እንዳችም ፡ የጽዳት ፡ ምልክት ፡ ለመጨበጥ ፡ አላስችል ፡ አለ ። ከዳር ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ይመለከት ፡ የነበረው ፡ እምኃ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እያገላበጠ ፡ እንዲመረምረው ፡ ይፈቅዱለት ፡ ዘንድ ፡ ፈቃድ ፡ ጠየቀና ፡ የሸክላውን ፡ አገልግል ፡ በመስኮት ፡ በገባችው ፡ ጮራ ፡ እያናጸረ ፡ ሲመለከተው ፡ በመከደኛው ፡ ላይ ፡ ከሁለት ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ የፀሐይቱ ፡ ጮሮች ፡ ሲጫወቱ ፡ አየ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በወስፌ ፡ ትኩም ፡ ትኩም ፡ እያደረገ ፡ እንዲመረምራቸው ፡ አኅቱን ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ መከታን ፡ ጠየቀ ። እርሳቸውም ፡ የልጃቸውን ፡ ብልኅነት ፡ ዱሮውኑ ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ፡ ፈቀዱለት ። እምኃም ፡ አንድ ፡ ማለፊያ ፡ ወስፌ ፡ አስመጥቶ ቀስ ፡ እያለ ፡ ካራቱ ፡ አንደኛውን ፡ የላይኛውን ፡ ሥፍራ ፡ ቢተኩመው ፡ ትንሽ ፡ ወደታች ፡ ትምክ ፡ ትምክ ፡ አለለት ። ወዲያውም ፡ ይህ ፡ ትምክ ፡ ትምክ ፡ ያለለት ፡ ነገር ፡ ሰም ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ብሎ ፡ አሰበ ። ስለዚህ ፡ ፍም ፡ አምጥተው ፡ እንዲሰጡት ፡ ጠየቀና ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ፍም ፡ በላዩ ፡ አደረገና ፡ ለአምስት ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ እፍ ፡ እፍ ፡ ይል ፡ ጀመር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀስ ፡ አለና ፡ ቢሠረሥረው ፡ ሰሙ ፡ የደፈነውን ፡ ቀዳዳ ፡ ለቆ ፡ ውልቅ ፡ ብሎ ፡ ወደቀ ። ለካስ ፡ በዚህ ፡ ቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ቀጭን ፡ ብረት ፡ እስከ ሸክላው ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ብቅ ፡ ተደርጋና ፡ ተስተካክላ ፡ አብራ ፡ ተደፍና ፡ ኖራል ። እነሆ ፡ አሁን ፡ ብቻዋን ፡ ትታይ ፡ ጀመር ። ከብረትዋ ፡ ላይ ፡ ተጠልቆም ፡ ውስጡን ፡ ደፍኖ ፡ የዘጋ ፡ አንድ ፡ ቀለበት ፡ ደግሞ ፡ ታየ ። አምኃ ፡ አሁንም ፡ አንድ ፡ ብልኅነት ፡ አሰበና ፡ የፈላ ፡ ውኃ ፡ አስመጥቶ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በዶሮ ፡ ላባ ፡ እየኮራኮረ ፡ አጠበው ። ቀጥሎ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ በጨርቅ ፡ አደረቀውና ፡ በትንሹ ፡ ቅባት ፡ በላዩ ፡ አፈሰሰና ፡ በወስፌው ፡ ይነካካው ፡ ጀመር ። ጥቂትም ፡ እንደኮራኮረው ፡ የብረቱ ፡ ማሠሪያ ፡ ቀለበት ፡ ላላና ፡ ወለቀ ። አምኃ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተደስቶ ፡ ከላይ ፡ የቀረውን ፡ ሁለተኛውንም ፡ ምርግ ፡ በዝግታና ፡ በቀስታ ፡ ከፈተው ።



እነሆ ፡ አሁን ፡ ጣጣው ፡ ያለቀለት ፡ መስላቸውና ፡ ሁሉም ፡ ተደሰቱ ፡ ተከፍቶም ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ለማየት ፡ ጓጉ ። ነገር ፡ ግን ፡ መከደኛው ፡ አልከፈትም ፡ ብሎ ፡ ነክሶ ፡ ይዞ ፡ እንቢ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንደገና ፡ ልዩ ፡ ምርመራ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። አሁንም ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ የምርመራው ፡ ተግባር ፡ ለእምኃ ፡ እውነቱ ፡ ተሰጠና ፡ ይጣጣርበት ፡ ጀመር ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያገለገለው ፡ ወስፌ ፡ አሁን ፡ እንዲረዳው ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ሲጥር ፡ የእናትና ፡ የልጆች ፡ ክንፈሮች ፡ የተያያዙት ፡ በሰም ፡ መሆኑ ፡ ተገለጸለት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በመጀመሪያው ፡ ብልት ፡ ክንፈሮቹ ፡ ተላቀቁና ፡ መከደኛው ፡ ከላይ ፡ ብድግ ፡ ለማለት ፡ ቻለ ።

ከውስጡም ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ የሚፈልቁ ፡ ነገሮች ፡ በመስኮት ፡ ከገባችው ፡ የፀሐይ ፡ ጨረር ፡ ጋር ፡ ተሳደቡና ፡ የተቀማጮችን ፡ ዓይኖች ፡ ከፉኛ ፡ ገላመጧቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አምኃ ፡ መቀመጫቸውን ፡ ሳብ ፡ አድርጎ ፡ ወደጥላው ፡ አስጠጋቸውና ፡ ግልምጫቸውን ፡ ተወ ። የዛጎል ፡ የብር ፡ የወርቅ ፡ የአልማዝ ፡ የዕንቁና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የከበሩ ፡ የድንጋይ ፡ ጌጦች ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥምዝ ፡ ወርቆች ፡ ጋር ፡ በመካከላቸው ፡ ሁለት ፡ ቀጫጭን ፡ የብረት ፡ ዘንጎችን ፡ አስተክለው ፡ በድምቀት ፡ ታዩ ። በዚያ ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ጎምዥተው ፡ ቆበር ፡ ደፈቁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዚያው ፡ ከዳር ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ተገኘና ፡ የአቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ መሆኑን ፡ መሰከረ ። የተቀመጠውም ፡ ለልጆቹ ፡ እንደሆነ ፡ በግልጽ ፡ አብራርቶ ፡ ተናገረ ። ለልጆቹም ፡ ሲል ፡ የሚቾቹንና ፡ አሁን ፡ ያሉትን ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ይዘረዝራል ።

እንደዚሁም ፡ በሌላው ፡ ጥግ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ተገኘ ። ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ ጌጣጌጦቹንና ፡ ዓይነታቸውን ፡ ያልተሠሩትንም ፡ ወርቆች ፡ በሙሉ ፡ ዘርዝሮ ፡ ያመለክታል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ እንዳች ፡ አጠራጣሪ ፡ ነገር ፡ ጠፋ ። ቢሆንም ፡ «የአገሩ ፡ ጭቃ ፡ ሹም ፡ ሰምቶና ፡ በቀበሌው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተረጋግጦ ፡ ለአምኃና ፡ ለደማሜ ፡ መስጠት ፡ አለበት ፡ » ብሎ ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ተናገረ ፡ አቶ ፡ ደገፉም ፡ በዚሁ ፡ ነገር ፡ ተስማምቶ ፡ ጭቃ ፡ ሹሙ ፡ ተጠርቶ ፡ መጣ ። ሰላምታም ፡ ከተለዋወጡ ፡ በኋላ ፡ ጉዳዩን ፡ ቢያስረዱት ፡ ምንም ፡ ሳያመነታ ፡ «ይህ ፡ የጠፍ ፡

ገንዘብ ፡ ነውና ፡ ለመንግሥት ፡ መግባት ፡ አለበት ። ባለገንዘቡ ፡ ቀብሮት ፡ አስታውሶ ፡ ሳያወጣውና ፡ ሳይሠራበት ፡ ወደመጣበት ፡ ተመልሶ ፡ ከሄደ ፡ በመሬት ፡ ማሕፀን ፡ ለተቀመጠ ፡ ነገር ፡ መብት ፡ ኖሮት ፡ ለልጆቹ ፡ ለማስተላለፍ ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ አስቀድመን ፡ እኛ ፡ በቀን ፡ ቀጠሮ ፡ እንነጋገርበትና ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አስፈላጊው ፡ ውሳኔ ፡ ይደረጋል ፡» ብሎ ፡ የደስታውን ፡ መንፈስ ፡ ወደሐዘን ፡ ለወጠውና ፡ ሁሉም ፡ አንዳች ፡ የሚመልሱት ፡ ነገር ፡ አጥተው ፡ እንዲያው ፡ ተፋጠው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተቀመጡ ።

አምኃ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አፈፍ ፡ አለና ፡ «አባታችን ፡ የሞቱት ፡ አሁን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። አሟሟታቸውም ፡ በአደጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጊዜ ፡ አግኝተው ፡ ታመው ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ አስተንትነው ፡ አይደለም ። ይሁንና ፡ አሁን ፡ ለተገኘውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ መልስ ፡ አዘጋጅተዋል ። ጌጦቹና ፡ ገንዘቡ ፡ በጠቅላላ ፡ ለልጆቼ ፡ እንዲሆኑ ፡ ብለው ፡ አባባ ፡ በዝርዝር ፡ ጽፈው ፡ አብሮ ፡ ከተያያዘ ፡ እንደዚሁም ፡ በተቃጠለው ፡ ቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ከተገኘ፡ መሬቱም ፡ አባታቸው ፡ ራሳቸው ፡ በገንዘብ ፡ የገዙት ፡ ከሆነ ፡ በውርስ ፡ መልክ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚገባበት ፡ ምክንያት ፡ የለውም ። ስለዚህ ፡ የሚከሰን ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ በአግባቡ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሲከስን ፡ መልስ ፡ እንሰጣለን ፡ እንጂ ፡ በገዛ ፡ ራሳችን ፡ ሄደን ፡ የምንቸገርበት ፡ ምክንያት ፡ የለንም ። ብቻ ፡ አሁን ፡ መጀመሪያ ፡ የዚያን ፡ አረዳ ፡ ሲቆፍሩ ፡ ያገኙትን ፡ ሰዎች ፡ ስሞች ፡ መጻፍ ፡ ነው ። ቀጥሎም ፡ እዚህ ፡ ሲከፈት ፡ ያላችሁት ፡ ስም ፡ ይጻፋል ፡» ብሎ ፡ በዚያ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ስሞች ፡ ሊጽፍ ፡ ሲል ፡ የሽከላውን ፡ አገልግል ፡ ያመጣው ፡ ሰውዬ ፡ የነዚያን ፡ የቆፋሪዎች ፡ ስሞች ፡ ዝርዝር ፡ ይዞ ፡ ኖሮ ፡ ሰጠው ። ከዚህም ፡ ዝርዝር ፡ ጋር ፡ አያይዞ ፡ በዚያ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ በሙሉ ፡ ጭቃ ፡ ሹሙ ፡ ጻፈ ። ጭቃ ፡ ሹሙ ፡ የልጁን ፡ ድፍረትና ፡ በቆራጥነት ፡ የቀረበ ፡ ብልኀት ፡ ተመልክቶ ፡ አሳቡ ፡ ፋርሽ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳና ፡ በጣም ፡ ተበሳጨ ።

ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ «እኔ ፡ ለእናንተ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ነገሩማ ፡ የሚያወጣችሁ ፡ ከሆነ ፡ መልካም ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከቶ ፡ ምንም ፡ እንደማይረዳችሁ ፡ አረጋግጥላችኋለሁ ። ስለዚህ ፡ አሁንም ፡ ነገሩን ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ድረስ ፡ አስቡበትና ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡



እንነጋገርበታለን ፡» ብሎ ፡ ወጥቶ ፡ እየተጉተመተመ ፡ ሄደ ። ከኪያም ፡ የቀሩት ፡ የጭቃ ፡ ሹሙ ፡ አሳብ ፡ ደጎና ፡ ሆኖ ፡ ስላልገባቸው ፡ መገረማቸውን ፡ በየገጽታቸው ፡ ገልጸው ፡ አርእስታቸውን ፡ ለውጠው ፡ ሲነጋገሩ ፡ አቶ ፡ ያገፉና ፡ አምኃ ፡ እውነቱ ፡ የሽከላውን ፡ አገልግል ፡ እንደነበር ፡ ገጥመው ፡ ካንድ ፡ ትልቅ ፡ የብረት ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ቆለፉበት ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

በወላጆች ፡ ርስት ፡ የማይቆረቆር ፡ የለምና ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሚና ፡ አም፡ኃ ፡ ስለቦታቸው ፡ እንሥተው ፡ ሲነጋገሩ ፡ አምኃ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የአባታችንን ፡ መሬት ፡ ያለእኛ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሠራበት ፡ ስለምንድር ፡ ነው ? ይኸውና ፡ አንቺ ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በከፍተኛ ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ መምህራን ፡ ማዕርግ ፡ ልትመረቂ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አንቺ ፡ ገንዘብ ፡ ስታቀርቢ ፡ እኔ ፡ ጉልበት ፡ ሆኜ ፡ ቤቱን ፡ መልሰን ፡ የምናቆምበትን ፡ ቦታ ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ መልቀቅ ፡ የለብንም ። አሁንም ፡ አጎታችንን ፡ አቶ ፡ ደገፉን ፡ በትሕትና ፡ እንጠይቅና ፡ መጀመሪያ ፡ ምክንያቱን ፡ እንረዳ ፡ ብሎ ፡ የመሬቱን ፡ የወደፊት ፡ ዓላማ ፡ በአጭሩ ፡ አስረዳት ።

ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ እንደዘመኑ ፡ ልጃገረዶች ፡ የተብለጭለጭና ፡ የተምነሽናሽ ፡ የምንቸገረኝና ፡ የግድየለሽነት ፡ ጠባይ ፡ ስላልነበረባት ፡ የወንድሟን ፡ አስተያየት ፡ በዘለቄታ ፡ አመራር ፡ ተመለከተች ፡

አሁን ፡ ያቀረብከው ፡ አሳብ ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ አይጥ ፡ ወልዳ ፡ ወልዳ ፡ እጅራቷ ፡ ስትደርስ ፡ ሲጥ ፡ አለች ፡ እንደሚሉት ፡ ተረት ፡ አጎታችን ፡ ለፍቶ ፡ አሳድጎን ፡ አሁን ፡ የመሬት ፡ ነገርና ፡ የቤት ፡ አሠራር ፡ ጉዳይ ፡ ብናነሣ ፡ መቼ ፡ ራሳችሁን ፡ ቻላችሁና ፡ ነው ፡ አሁን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ የምትቀሰቅሱት ፡ ብሎ ፡ ቢቆጣን ፡ የምንሰጠው ፡ መልስ ፡ አስከፊ ፡ ይሆንብናል ። በሰውፊትም ፡ በአባታቸው ፡ ምትክ ፡ ሆኖ ፡ አሳድጓቸው ፡ ገና ፡ ለትጻር ፡

እንኳ ፡ ሳይደርሱ ፡ እንዴት ፡ የተቀናቃኝነት ፡ መንፈስ ፡ አደረባቸው፡ ተብለን ፡ እንገመታለን ። ስለዚህ ፡ እኅታችን ፡ የጀመረውን ፡ አሳብ ፡ ማሰናከሉን ፡ እንተውና ፡ ዓላማችንን ፡ ብቻ ፡ እንከተል ። እኛ ፡ ከየአሰብነው ፡ ግብ ፡ ከደረስን ፡ በገዛ ፡ እግራችን ፡ ለመቆም ፡ እንችላለን ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በቃልም ፡ በደብዳቤም ፡ እንደገለጽሁልህ ፡ ለእኛ ፡ ቀሪ ፡ ገንዘባችን ፡ ትምህርታችን ፡ ነው ። ይህንም ፡ አሁን ፡ በየፊናችን ፡ የጀመርነውን ፡ ትምህርት ፡ ምናልባት ፡ ቀንቶን ፡ ከግብ ፡ ብናደርሰው ፡ በገዛ ፡ ራሳችን ፡ የምናቋርጥበት ፡ ምክንያት ፡ የለንም ። ትምህርት ፡ እያደር ፡ ጮራውን ፡ በብዙ ፡ እየለቀቀ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ማብራቱን ፡ ሲጀምር ፡ ትምህርት ፡ በየጊዜው ፡ አዲስ ፡ እየሆነ ፡ መሄድ ፡ ይጀምራል ፡ እንጂ ፡ በትምህርት ፡ ፍጹምነት ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ አዳዲስ ፡ ነገሮች ፡ በአሮጌው ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ እየጨመሩ ፡ መሄድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መቆም ፡ የለም ። ሰው ፡ ከመመራመርና ፡ ከመሥራት ፡ ከታገደ ፡ ወይም ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ከተወ ፡ አእምሮውና ፡ ሰውነቱ ፡ አብረው ፡ መቡካት ፡ ጀምረው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የሞት ፡ ጭፍሮች ይጋግሩትና ፡ ትሎች ፡ ያነኩቱታል ። እንግዲህ ፡ ሰው ፡ በተፈጥሮው ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ ድረስ ፡ ራሱን ፡ በሥራ ፡ ጠምዶ ፡ ከአካባቢው ፡ ፍጥረት ፡ ጋር ፡ መታገልና ፡ አብሮ ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ መኖር ፡ የሚገባው ፡ ከሆነ ፡ በትንሽ ፡ ነገር ፡ ሊሰናከል ፡ አያስፈልግም ።

እኛ ፡ በትምህርት ፡ በርትተን ፡ ራሳችንን ፡ ያዋልን ፡ እንደሆነ ፡ ዘመዶቻችን ፡ ይቅሩና ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሕዝብ ፡ ረድቶ ፡ በአባታችን ፡ አረዳ ፡ ላይ ፡ እንድንቆም ፡ ያደርጋል ። ስለዚህ ፡ እኛ ፡ የእኛን ፡ ተግባር ፡ እንፈጽም ፡ እንጂ ፡ የቀረው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በእኛ ፡ ራስ ፡ መቻል ፡ መሠረት ፡ ደኅና ፡ ሆኖ ፡ በሥርዓት ፡ ዐውቆ ፡ ይፈጸማል ።

አባታችን ፡ በሽክላ ፡ አገልግል ፡ ስላስቀመጣቸው ፡ ጌጦችና ፡ ገንዘቦች ፡ ያ ፡ ክፉ ፡ አነጋገር ፡ አጉራፊው ፡ ልብ ፡ አብግን ፡ ሰው ፡ መጥፎ ፡ አስተያየትን ፡ ሲያቀርብ ፡ የሰጠኸው ፡ መልስ ፡ ካንድ ፡ ተራ ሰው ፡ አንደበት ፡ ሊፈልቅ ፡ የማይችል ፡ የትምህርት ፡ ፍሬ ፡ መሆኑን ፡ አትርሳ ። ስለዚህ ፡ ከእንግዲህ ፡ የእኛ ፡ ሀብት ፡ ትምህርታዊ ፡ መልካም ፡ አስተዳደግ ፡ እንጂ ፡ በየቦታው ፡ የሚገኙ ፡ አንዳንድ ፡ ቁራሾች ፡ መሬቶች ፡ አይደሉም ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በቃልም ፡ በደብዳቤም ፡ እንደገለጽሁልህ ፡ የአ



እምሮ ፡ ትምህርትን ፡ ከተግባር ፡ ጋር ፡ አዛምደህ ፡ ብትገፋበት በዚህ ፡ ሰሞን ፡ ካሳየኸው ፡ ይበልጥ ፡ ልትጠቅምበትና ፡ ልትጠቀምበት ፡ ትችላለህ ። አእምሮ ፡ አንድ ፡ የሚከናወን ፡ ሥራን ፡ በእቅድ ፡ ሲያደራጅ ፡ እጅ ፡ ተቀብሎ ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ አስፍሮ ፡ ራሱ ፡ ሠርቶና ፡ አሠርቶ ፡ ከፍጻሜ ፡ ካላደረሰው ፡ የአእምሮ ፡ ባሳብ ፡ መድከም፡ ብቻ ፡ ዋጋን ፡ አይሰጥም ። ይህንም ፡ አሳብ ፡ ከዜማ ፡ ትምህርትህ ፡ ጋር በተያያዘው ፡ የቁም ፡ ጽሕፈትና ፡ የቀለም ፡ ቅመማ ፡ የብራና ፡ አፋፋቅና ፡ አቀጻጽ ፡ የመጻሕፍት ፡ አጠራረዝም ፡ ተጠቅመህበት ፡ እንደነበር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ነግረኸኛል ። ለወደፊቱ ፡ በተለይ ፡ በቀለም ፡ ቅመማ ፡ በኩል ፡ ብትገፋ ፡ ወደፊት ፡ በሚቋቋሙት ፡ የልብስ ፡ ፋብሪኮች ፡ ባንዱ ፡ ውስጥ ፡ ገብተህ ፡ ልትሠራ ፡ ትችላለህ ። አለበለዚያም ፡ በሥዕል ፡ በኩል ፡ ዝንባሌ ፡ እንዳለህ ፡ ዐውቃለሁና ፡ ተግተህ ፡ በማጥናት ፡ ብትገፋና ፡ ስለሥዕልም ፡ የሚናገሩ ፡ መጻሕፍትን ፡ እያማረጥህ ፡ ብታነብና ፡ በአካባቢህ ፡ በሚገኙ ፡ ምን ፡ ፍጥረቶች ፡ እየተደሰትህ ፡ ልትጠቀምባቸው ፡ ብትፈልግ ፡ ወገኖችህንና ፡ ራስህን ፡ ልትጠቅም ፡ ትችላለህ ። ስለዚህ ፡ የእኛ ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ሙሉ ፡ ጤንነትና ዕውቀት ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝበን ፡ ኑሯችንን ፡ ከሥልጣኔ ፡ ርምጃ ፡ ጋር ፡ ለማዛመድና ፡ ለመግፋት ፡ እንድንችል ፡ ጊዜያችንን ፡ ለትምህርት ፡ ቆጥበን ፡ መያዝ ፡ አለብን ። እንግዲህ ፡ እስካሁን ፡ ባተትሁልህ ፡ መሠረት ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ትስማማ ፡ እንደሆን ፡ የመሬቶቻችን ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ በአኅታችን ፡ በአቶ ፡ ደገፋ ፡ እጅ ፡ እንዳሉ ፡ ይቆዩ» ብላ ፡ አሳቧን ፡ አጠቃላ ፡ አቀረበችለት ። እርሱም ፡ የታላቅ ፡ እኅቱን፡ ንግግር ፡ በሥርነት ፡ በማዳመጥ ፡ ተከታትሎት ፡ ነበርና ፡ ራሱን ፡ እንደገና ፡ በራሱ ፡ ወቅሶ ፡ መስማማቱን ፡ «አንቺ ፡ እንዳልሽ ፡ እኅቴ ፡» በማለት ፡ ገለጸና ፡ ጉዳዩ ፡ ተዘጋ ።

ያ ፡ ጭቃ ፡ ሹም ፡ ከሁለት ፡ ሳምንት ፡ ይበልጥ ፡ አዳመጠ ፡ ነገር ግን ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ አልጠየቀውም ። ስለዚህ ፡ ወደ ፡ አቶ ደገፋ ፡ መጥቶ ፡ ነገሩንም ፡ ቢጠይቅ ፡ ማንም ፡ ያላሰበበት ፡ መሆኑን ፡ ለመረዳት ፡ ቻለ ። በዚህም ፡ በጣም ፡ ተቆጥቶ ፡ ነገሩን ፡ በጽሑፍ ፡ ለወረዳው ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አመለከተና ፡ አቶ ፡ ደገፋ ፡ መከታ ፡ እምኃና ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሚ ፡ እውነቱ ፡ በጽሑፍ ፡ ተጠርተው ፡ ቀረቡ ። የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት

ሹም ፡ በጭቃ ፡ ሹሙ ፡ አሳሳቢነት ፡ በተረዳበት ፡ መግለጫ ፡ መሠረት ፡ ነገሩን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ በዝርዝር ፡ ጠየቃቸው ፤ እነርሱም ፡ እውነቱን ፡ ባለመካድና ፡ ባለመብት ፡ መሆናቸውን ፡ በማረጋገጥ ፡ ተገቢ ፡ መልሶችን ፡ ሰጡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሹሙ ፡ እነርሱን ፡ አሰናብቶ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ ፡ ፈጁን ፡ አስጠራ ። እንደገባም ፡ ባንድ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ አረፍ ፡ እንዲል ፡ እጁን ፡ በመዘርጋት ፡ አመልክቶት ፡ ካረፈ ፡ በኋላ ፡ የሸክላውን ፡ አገልግል ፡ ታሪክ ፡ ገለጸለት ። ነገረ ፡ ፈጁም ፡ «ዛሬ ፡ ገንዘብ ፡ ገንዘብን ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ለመውለድ ፡ ወይም ፡ ለማትረፍ ፡ በቻለበት ፡ ዘመን ፡ እንዴት ፡ ያለው ፡ ድንጋይ ፡ ራስ ፡ ሰው ፡ ቀብሮት ፡ ተገኘ ፡ ብሎ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደነቀ ። ነገሩንም ፡ ቀጠል ፡ አደረገና ፡ ዛሬ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ማኅበሮች ፡ የተዋጡ ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ ማኅበርነት ፡ ሳይኖራቸው ፡ ባንድ ፡ ኩባንያ ፡ ኅላፊነት ፡ የተሰበሰቡ ፡ ገንዘቦች ፡ እንዴት ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎችን ፡ አከናውነዋል ? በአከናወኗቸው ፡ ሥራዎችስ ፡ ስንትና ፡ ስንት ፡ ትርፍ ፡ አስገኝተዋል ! ወይ ፡ ጉድ ! እንዴት ፡ እነዚህን ፡ ሁኔታዎች ፡ ያየና ፡ የተገነዘበ ፡ ሰው ፡ ገንዘቡን ፡ ለመቅበር ፡ ቻለ ! ግሩም ፡ ግሩም ፡ » እያለ ፡ ሲያደንቅ ፡ ቆየ ።

ሹሙም ፡ «ተው ፡ እባክህ ፡ አታድንቅ ፤ ዛሬ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሠለጠነበት ፡ ጊዜም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ የሞኝነት ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ወይ ? እያልህ ፡ አታስተንትን ። ሥልጣኔ ፡ አሮጌና ፡ ዘመናዊ ፡ አመራሮች ፡ አሉት ። መቼም ፡ አሮጌ ፡ የምንለው ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ የምንለው ፡ ርቀት ፡ የተሸፈነበትን ፡ ጊዜ ፡ የተቀጠበበትን ፡ ሥራም ፡ ከሰውና ፡ ከእንስሳት ፡ ጉልበት ፡ አልፎ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የአኅላባቾች ፡ ዝምድና ፡ የተከናወነበትንና ፡ በጠቅላላው ፡ ውኃ ፡ የሌለባቸው ፡ ምድረ ፡ በዳዎች ፡ ከአገልግሎት ፡ ለመዋል ፡ የቻሉበትን ፡ ተፋጣኝ ፡ የመሻሻል ፡ ርምጃ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ መሻሻል ፡ በቀን ፡ በሳምንት ፡ በወርና ፡ ባመት ፡ የሚመጣ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። መሻሻል ፡ ከትምህርታዊ ፡ እድገት ፡ ጋር ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ የሚመጣ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። መኪናን ፡ በዓይን ፡ በማየትና ፡ በውስጡ ፡ በመቀመጥ ፡ ብቻ ፡ መሻሻል ፡ አይመጣም ። ሰው ፡ በሠራው ፡ መንገድ ፡ ላይም ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ ቢመላለሱ ፡ መሻሻል ፡ አይመጣም ። ልብስንም ፡ በአባትና ፡ በእናት ፡ ቅርስ ፡ ቢለ



ዋውጡና ፡ ልውጥ ፡ ምግቦችንም ፡ ቢበሉ ፡ መሻሻል ፡ አይመጣም ። መሻሻል ፡ እየተማሩ ፡ ወይም ፡ እየተመለከቱ ፡ በገዛ ፡ ራስ ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ይመጣል ። ስለዚህ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በተፈጥሮ ፡ ሠርቶ ፡ ማግኘትን ፡ ዐውቀው ፡ ቢሠሩበት ፡ ባገኙት ፡ ገንዘብ ፡ ሥራ ፡ መፍጠርን ፡ ወይም ፡ ሥራን ፡ ፈጥሮ ፡ በሚያሠራው ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በባንክ ፡ ውስጥ ፡ ማስቀመጥን ፡ አይገነዘቡም ፤ ምክንያቱም ፡ በትምህርታዊ ፡ እድገት ፡ ተገርተው ፡ ባለመጠቀማቸው ፡ ነው ፡ » ብሎ ፡ አሳቡን ፡ ከወረወረ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ወደዋናው ፡ አሳቡ ፡ ተመልሶ ፡ ነገረ-ፈጁ ፡ ጉዳዩን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲከታተለው ፡ የቀረበለትን ፡ ማስረጃ ፡ ሰጠው ።

ነገረ-ፈጁም ፡ መግለጫውን ፡ በጥንቃቄ ፡ ተመልክቶ ፡ ጭቃ ፡ ሹሙ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲያነጋግረው ፡ በጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ በኩል ፡ ጠይቆ ፡ ጉዳዩን ፡ በዝርዝር ፡ አጠናና ፡ በአቶ ፡ ደገፉ ፡ ላይ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበ ። በማመልከቻውም ፡ ላይ ፡ ዋና ፡ መነሻ ፡ ያደረገው ፡ ተቀብሮ ፡ የተገኘ ፡ ገንዘብ ፡ የመንግሥት ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ ነው ። ይኸውም ፡ አሳብ ፡ በይገባል ፡ እንጂ ፡ በማስረጃ ፡ የተደገፈ ፡ አስተያየት ፡ አይመስልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፳ ።

የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡
ያቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡

አጽቀ ፡ ገነት ፡
ሐምሌ ፡ — ፲፱ ፡ — ዓ ፡ ም

ለክቡር ፡ የመተከል ፡ አውራጃ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡
ሳላይሽ ፡
ክቡር ፡ ሆይ ፡
ከሳሽ ፡- የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡
ተከሳሽ ፡- አቶ ፡ ደገፉ ፡ መኮታ ፡
የክሱ ፡ ዓይነት ፡- ወንጀል ፡

የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡ በማንኛውም ፡ ሥፍራ ፡
የሚገኙትን ፡ የመንግሥት ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ እየዞረና ፡ እያጠና ፡
ተቆጣጥሮ ፡ መጠበቅ ፡ ሥራው ፡ ስለሆነ ፡ ተከታዩን ፡ የክስ ፡ መጣ
ለጫ ፡ ለተከበረው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርባል ።

፩ኛ ፡ አንድ ፡ በሸክላ ፡ ተመርጎ ፡ የተቀበረ ፡ ወርቅ ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ
በቁፈራ ፡ ወጥቷል ።

፪ኛ ፡ ወርቁ ፡ በሸክላ ፡ እንደተመረገ ፡ ያገኙት ፡ የአንድ ፡ ቤተ ፡ ሠሪ ፡
መሠረት ፡ ቆፋሪዎች ፡ ናቸው ።

፫ኛ ፡ በሸክላ ፡ የታሸገውን ፡ ገንዘብ ፡ የወሰደው ፡ አቶ ፡ ደገፋ ፡
መከታ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ገበሬ ፡ ሰው ፡ ነው ።

አሁን ፡ እኔ ፡ ለተከበረው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመንግሥት ፡ ንብ
ረት ፡ ነገረ-ፈጅነት ፡ መብቴ ፡ የማሳስበው ፡ አቶ ፡ ደገፋ ፡ መከታ ፡
የተባለው ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ አስገዳጅነት ፡ ቀርቦ ፡
አንደኛ / ያላገባብ ፡ የወሰደውን ፡ በሸክላ ፡ የተመረገ ፡ ወርቅ ፡ እንዲ
ያስረክብ ፡ ሁለተኛ / በእጀ ፡ መናኛው ፡ የመንግሥትን ፡ ንብረት ፡
በመውሰዱ ፡ እንዲቀጣ ፡ ነው ።

ታዛዥዎ ፡

የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡

ይህ ፡ ማመልከቻ ፡ መጀመሪያ ፡ ለዳኞች ፡ ቀረበና ፡ ተመዝግቦ ፡
ግልባጩ ፡ ከመጥሪያ ፡ ጋር ፡ ለተከሳሹ ፡ እንዲሰጥ ፡ ታዘዘበት ። የመ
ንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅም ፡ ጉዳዩን ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ተከታትሎ
መጥሪያውንና ፡ ግልባጩን ፡ ተቀበለ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ ሁለት ፡ ሰዎችን ፡ ለማስታረቅ ፡ ብዙ ፡
ሽማግሌዎች ፡ በአንድ ፡ ትልቅ ፡ ወይራ ፡ ሥር ፡ ተሰብስበው ፡ ነበር ።
አቶ ፡ ደገፋም ፡ እንዳጋጣሚ ፡ በሽማግሌነት ፡ ተመርጦ ፡ ከሽማግሌ
ዎች ፡ መካከል ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። የእርቁ ፡ ድርድር ፡ ተፋፍሞና ፡
ተሟሙቆ ፡ አስተያየቶች ፡ ከያለበት ፡ እየተወረወሩ ፡ ድርድሮች ፡
በጥያቄና ፡ መልስ ፡ ሲጣሩ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡
ነገረ-ፈጅ ፡ ጽ/ቤት ፡ ሠራተኛ ፡ መጥቶ ፡ በሚገባ ፡ እጅ ፡ ነሳና ፡ ከሽ
ንጎው ፡ ፊት ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ። ወዲያውም ፡ ጌቶቼ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
ይቅርታ ፡ አድርጉልኝና ፡ አቶ ፡ ደገፋ ፡ ለሚባሉት ፡ ሰውዬ ፡ የክስ ፡
ግልባጭና ፡ የመጥሪያ ፡ ወረቀት ፡ ልስጣቸው ፡ ብሎ ፡ ፈቃድ ፡ በጠ



የቀ ፡ ጊዜ ፡ በሸንጎው ፡ ላይ ፡ የመደረጽና ፡ የመገረም ፡ መንፈስ ፡ ወደ
ቀበት ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ አንድ ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ ካሳለፈ ፡
በኋላ ፡ የሸንጎው ፡ መሪ ፡ ሽማግሌ ፡ አቶ ፡ ደገፋን ፡ ጠቅሰው ፡ እንግ
ዳውን ፡ ሰውዬ ፡ እንዲያነጋግሩት ፡ ጠየቁት ። አቶ ፡ ደገፋም ፡ እረፍ ፡
አለና ፡ ከሸንጎው ፡ ማኸል ፡ ወጥቶ ፡ ሰውዬውን ፡ ለማነጋገር ፡ ሲል ፡
እንግዳው ፡ ከኮረጆው ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ወረቀቶች ፡ አውጥቶ ፡ «እነ
ዚህን ፡ ሁለቱን ፡ ወረቀቶች ፡ ለራስዎ ፡ ይውሰዱ ፡ በዚህኛው ፡ ሦስ
ተኛ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ደረሰኝ ፡ ሲሉ ፡ ይፈርሙልኝ ፡» ብሎ ፡
አቀረበለት ። አቶ ፡ ደገፋ ፡ ከመፈረሙ ፡ በፊት ፡ የተቀበላቸውን ፡
ሁለት ፡ ወረቀቶች ፡ በጥንቃቄ ፡ አነበበና ፡ በተሰማው ፡ መሠረት ፡
ራሱን ፡ እያነቃነቀ ፡ ግምባሩን ፡ እየቋጠረና ፡ እየፈታ ፡ ፈረመለት ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንግዳው ፡ በመጣበት ፡ አኳኋን ፡ ተመልሶ ፡ ሄደ ።
አቶ ፡ ደገፋም ፡ ወደቀድሞ ፡ ሥፍራው ፡ ተመልሶ ፡ ተቀመጠና ፡ ሸን
ጎው ፡ ሥራውን ፡ ቀጠለ ።

ሸንጎው ፡ በእርቁ ፡ ድርድር ፡ መሠረት ፡ ሁለቱንም ፡ ወገኖች ፡
ለመምራት ፡ ባደረገው ፡ ጥረት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሳይቀናው ፡ በመቅ
ረቱ ፡ ነገሩን ፡ እንደገና ፡ አጥንቶ ፡ ከፍጻሜው ፡ ለማድረስ ፡ እንዲ
ችል ፡ የአንድ ፡ ሳምንት ፡ ዕድሜ ፡ እንዲሰጠው ፡ ሁለቱንም ፡ ተሸማ
ጋዮች ፡ ጠይቆ ፡ በቀጠሮ ፡ ተነሣ ።

አሁን ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ አቶ ፡ ደገፋ ፡ ጉዳይ ፡ እንመለስና ፡
እስኪ ፡ ስለሙግቱ ፡ ምን ፡ እንደሚያስቡና ፡ እንደሚሠሩ ፡ እንመልከ
ታቸው ። ሸንጎው ፡ እንደተነሣ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በዚያው ፡ በዘር
ፋፋው ፡ ወይራ ፡ ሥር ፡ እየቆሙም ፡ እየተቀመጡም ፡ ስለግል ፡ ጉዳያ
ቸው ፡ ሲነጋገሩ ፡ አቶ ፡ ደገፋ ፡ ተጣድፎ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። እንዳጋ
ጣሚ ፡ ወይዘሮ ፡ ላቅሽቸው ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሚና ፡ አምኃ ፡ ከልጆቹ፡
ጋር ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ በየፊናቸው ፡ ዳማና ፡ ገበጣን ፡ ሰንጠረዥንም ፡
ይጫወቱ ፡ ነበርና ፡ ከቤት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በመካከላቸው ፡ ሲቆም ፡
አላዩትም ። ነገር ፡ ግን ፡ አቶ ፡ ደገፋ ፡ ወደ ፡ አምኃ ፡ አትኩሮ ፡
«አምኃ ፡ አንተ ፡ ነገር ፡ ሰቅለህ ፡ እዚህ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ትጫወታለህ ፤
እኔ ፡ ግን ፡ ስለእናንተ ፡ ሀብት ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚገባኝ ፡ በማ
ውጣትና ፡ በማውረድ ፡ እብሰለሰላለሁ ፡» አለ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መላ ፡ ቤተሰቡ ፡ ደነገጠና ፡ ጫወታውን ፡ አቁሞ ፡

ቀና ፡ አለ ። ወይዘሮ ፡ ላቅሻቸው ፡ ጸጥታውን ፡ አቋረጠችና ፡ « አቶ ፡ ደገፉ ፡ እስኪ ፡ ለሁሉም ፡ ነገር ፡ ጊዜ ፡ አለውና ፡ መጀመሪያ ፡ ቁጭ ፡ በልና ፡ ሻይ ፡ እንጠጣ ፡ » አለችና ፡ በለዘበ ፡ አንደበትዋ ፡ እነጋግሬ ፡ ከአረግራጊ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ አስቀመጠችው ። ቀጠል ፡ አድርጋም ፡ ሻይና ፡ ብስኩት ፡ እንዲያቀርቡ ፡ አዘዘች ። ቀራቢዎችና ፡ ማቅረቢያዎች ፡ በየዓይነታቸው ፡ እየመጡ ፡ በየትናንሾች ፡ ጠረጴዞች ፡ ላይ ፡ ተደረደሩ ። አንዳንድ ፡ ያፈጠነው ፡ ከብስኩቶች ፡ ውስጥ ፡ እያነሣ ፡ ሲቀማምስ ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ሻዩን ፡ ቀድቶ ፡ ፉት ፡ ፉት ፡ ሳብ ፡ ሳብ፡ ሲያደርግ ፡ ገና ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያላፈጠነው ፡ ወይም ፡ ያላደረሰው ፡ ሲርበተበት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የውጭ ፡ በር ፡ አንኳኳ ። አሽከርም ፡ በወይዘሮ ፡ ላቅሻቸው ፡ ትእዛዝ ፡ እየሮጠ ፡ ሄደና ፡ ትልቁን ፡ በር ፡ ከፈተ ። እንግዳው ፡ የአቶ ፡ ደገፉን ፡ መኖር ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ አረጋግጦ ፡ እየተጓደደ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ደጃፍ ፡ ሲያመራ ፡ አሽከር ፡ ሆይ ፡ በአቋራጭ ፡ ሮጦ ፡ ገብቶ ፡ አቶ ፡ ደገፉን ፡ አንድ ፡ ወዳጃቸው ፡ ሊጠይቅ ፡ እንደመጣ ፡ ለእመቤቱ ፡ ተናግሮ ፡ የቤቱን ፡ በር ፡ ለመክፈት ፡ ተፋጠነ ፡ ሰውዬውም ፡ ከደጃፉ ፡ ደርሶ ፡ ከመቆሙ ፡ በፊት ፡ አሽከሩ ፡ በሩን፡ከፈተና፡«ጌታዬ፡ ይግቡ፡»ብሎ፡በእጁ፡እያመለከተ፡ወደ ፡ እንግዳ፡ማረፊያው፡መርቶ፡ሲያስቀምጠው፡ሲል፡አቶ፡ደገፉ፡ብቅ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ዘመዳሞች ፡ አንገት ፡ ላንገት ፡ ተያይዘው ፡ ተሳሳሙ ። አሽከር ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ በቶሎ ፡ ለእመቤቱ ፡ አደረሰና ፡ አንድ ፡ ያማረች ፡ የሻይ ፡ ጠረጴዛ ፡ ተዘጋጀች ። አቶ ፡ ደገፉ ፡ ወዳጁንና ፡ ዘመዱን ፡ እየመራ ፡ ወደሻዩ ፡ ክፍል ፡ ሲገባ ፡ ቤተሰቡ ፡ ሁሉ ፡ እየተነሣ ፡ በእንግዳው ፡ ላይ ፡ ይጠመመጠምበት ፡ ጀመር ። አሽከር ፡ ብቻ ፡ ይህን ፡ ቤተሰቡን ፡ ያስተናነቀውን ፡ እንግዳ ፡ ገና ፡ አላወቀውም ።

ሐዘን ፡ ረቦበት ፡ የነበረው ፡ የማንበቢያና ፡ የሻይ ፡ ክፍል ፡ መፍለቅለቅና ፡ መፍካት ፡ ጀመረ ። አቶ ፡ ደገፉ ፡ በተለይ ፡ ደስ ፡ አለውያ ፡ ግንባሩን ፡ ያስቋጠረውና ፡ ራሱን ፡ ያስነቀነቀው ፡ ጉዳይ ፡ ከፊቱ ፡ ላይ ፡ ዘወር ፡ አለለት ። ተቋርጦ ፡ የነበረው ፡ የሻይና ፡ የብስኩት ፡ ቤተሰባዊ ፡ የበዓል ፡ ግብዣ ፡ እንደገና ፡ ተጀመረና ፡ እነምላስ ፡ እነጥርስና ፡ እነከንፈር ፡ ከአቶ ፡ እጅ ፡ ጋር ፡ እየተረዳዱ ፡ ሥራቸውን ፡ ቀጠሉ ። ጨዋቶችም ፡ ጣልቃ ፡ መግባት ፡ ያዙና ፡ እነሳቅም ፡ እየተከ



ታተሉ ፡ ይሽከመከሙና ፡ ይፍለቀለቁ ፡ ጀመር ።

የሰው ፡ ማጽናናትና ፡ ማረሳሳት ፡ ከውጭ ፡ የሚመጣ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሰውነት ፡ ውስጥ ፡ በቶሎ ፡ ጠልቆ ፡ ሥፍራን ፡ የማይገዛ ሰብአዊ ፡ ጥበብ ፡ ሲሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያቀርበው ፡ ማጽናኛ ግን ፡ ሁኔታን ፡ በሁኔታ ፡ የሚለውጥና ፡ ከሰውነት ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ሥፍራን ፡ የሚያገኝ ፡ እውነተኛ ፡ ከውስጥ ፡ የሚመነጭ ፡ ማጽናኛ ፡ ነው ። እነሆ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ የተናደደበትን ፡ ነገር ፡ ገሸሽ ፡ አድርጎ ፡ በተለወጠው ፡ ሁኔታ ፡ ለመጽናናት ፡ የቻለው ።

እንግዳው ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ የአቶ ፡ ደገፉ ፡ ክርስትና ፡ አባት ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ። አቶ ፡ በላይነህ ፡ የተወለደው ፡ በእምባለገነት ፡ መንደር ፡ ነው ። በዚች ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ እድጎ ፡ ስምንተኛን ፡ ክፍል ፡ ሲጨርስ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ በሚገኘው ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡ ተምሮ ፡ የአራቱን ፡ ዓመታት ፡ ትምህርት ፡ አከናውኖአል ። የትምህርት ፡ እድገቱንም ፡ በመከታተል ፡ የኮሌጅ ፡ ትምህርቱን ፡ ለመጨረስ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥቶ ፡ የአራት ፡ ዓመታት ፡ ትምህርቱን ፡ ካጠናቀቀ ፡ በኋላ፡ መጠነ ፡ ትምህርቱን ፡ (ዲግሪውን) ፡ ተቀብሏል ። ቀጥሎም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ የሕግ ፡ ትምህርቱን ፡ አጠናቅቆ ፡ ተመልስዋል። ከተመለሰም ፡ ወዲህ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በሕግ ፡ ትምህርቱ ፡ ሠርቶበታል ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ አገሩን ፡ ማለት ፡ የተወለደባትን ፡ መንደር ፡ ለትምህርት ፡ ሲል ፡ ለቆ ፡ ከሄደ ፡ ወዲህ ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጉብኝቱ ፡ ነው ። ወደ ፡ እምባለ ፡ ገነትም ፡ ከገባ ፡ ገና ፡ ሦስት ፡ ቀኑ ፡ ነው ። ገና ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አላየውም ። ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ ደብዳቤ ፡ አልጻፈም ፡ ስለዚህ ፡ ቤተሰቦቹ ፡ ተዘጋጅተው ፡ እንኳ ፡ ከአውቶቡስ ፡ ማቆሚያው ፡ አልተቀበሉትም ። መምጣቱም ፡ አልተወራም ፡ የገባው ፡ ዓርብ ፡ ቀን ፡ ስለነበረና ፡ በማግሥቱም ፡ የቅዳሜ ፡ ገበያ ፡ ነፍስ ፡ አሳጥቶ ፡ ያስሠራ ፡ ስለነበር ፡ ከሰው ፡ እንደልብ ፡ ለመገናኘት ጊዜው ፡ አልፈቀደለትም ። እነሆ ፡ እሑድ ፡ የዕረፍቶች ፡ ሁሉ ፡ ራስ ፡ ዛሬ ፡ ፈቅዶለት ፡ ተዝናንቶ ፡ የጥንት ፡ ወዳጆቹን ፡ ለመጠየቅ ፡ ቻለ ።

አቶ ፡ ደገፉ ፡ በተከሰሰበት ፡ ጉዳይ ፡ ለመቅረብ ፡ ሰፊ ፡ ቀጠሮ ፡ ተሰጥቶት ፡ ስለነበር ፡ ጊዜያዊ ፡ ንዴቱ ፡ ከበረደለት ፡ በኋላ ፡ ነገሩን ፡

በዝግታና ፡ በርጋታ ፡ ከቤተሰቡ ፡ ጋር ፡ ማጥናት ፡ ያዘ ። እምነ ፡ እው
ነቱ ፡ ልበ ፡ ሙሉነቱን ፡ ሳይለውጥ ፡ አሁንም ፡ « አይዞህ ፡ አባቴ ፡
በምንም ፡ ነገር ፡ አትቸገር ፡ ነገሩ ፡ በጣም ፡ ቀላል ፡ ነው ። ምንም ፡
ነገሩ ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ ቢጠመጠምና ፡ ቢጎነጎን ፡ ከልኩ ፡ እንደማያልፍ፡
እመን ። እንደዚሁም ፡ አለሕገኛ ፡ ማስረጃና ፡ አለሕገኛ ፡ ምስክር ፡
ነገርን ፡ ለማምታታት ፡ የአሁኑ ፡ ፀሐያዊ ፡ ዘመን ፡ አይፈቅድም ።
ስለዚህ ፡ አሳብን ፡ ረጋ ፡ ባለ ፡ መንፈስ ፡ ገትቶ ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ነክነት ፡
ያላቸውን ፡ ነገሮች ፡ እየሰበሰቡ ፡ ማስረጃና ፡ ምስክር ፡ ማቅረብ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ መደንገጥ ፡ አይጠቅምም ። እንዲያውም ፡ መደንገጥ ፡
ነገርን ፡ እያድሞነሞነ ፡ እንደገና ፡ ከልብ ፡ ውስጥ ፡ ሰባብቆ ፡ ከመ
ከተት ፡ በስተቀር ፡ አገዜታ ፡ የለውምና ፡ አምዘግዝጎ ፡ ሊጥሉት ፡ ይገ
ባል ፡ » ሲል ፡ አስተያየቱን ፡ አቀረበ ። መላ ፡ ቤተ ፡ ሰቡም ፡ ከዚህ ፡
በፊት ፡ እምነ ፡ በደንብ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ከጌጦቹና ፡ ከወርቁ ፡ ገንዘብ ፡
ጋር ፡ ያስቀመጣቸውን ፡ አስረጆችንና ፡ ምስክሮችን ፡ ጠቅሰው ፡
ነገሩ ፡ ምንም ፡ የማያሰጋ ፡ መሆኑን ፡ በአስተያየታቸው ፡ እምነን ፡
ደግፈው ፡ ተናገሩና ፡ ጉዳዩን ፡ እንደገና ፡ ከሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ጋር ፡
እንዲመካከሩበት ፡ ወስነው ፡ አቆዩት ።

አቶ ፡ ደገፉና ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ እጅግ ፡ የጠለቀ ፡ ፍቅር ፡ ነበራ
ቸው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ አቶ ፡ ደገፉና ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ የአ
ባትና ፡ የልጅ ፡ መልክ ፡ በዕድሜያቸው ፡ በኩል ፡ ቢታይባቸው ፡ በነ
ገር ፡ የመግባባትና ፡ የመጣጣም ፡ መንፈስ ፡ ድሮውኑ ፡ ጸድቆባቸው ፡
ነበር ። አቶ ፡ ደገፉ ፡ በአቶ ፡ በላይነህ ፡ መመለስ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡
ተደስቷል ። በዚያው ፡ ተከታይ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡
ቤቶቹ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ጥሪ ፡ ከአቶ ፡ ደገፉ ፡ ደረሳቸውና ፡ ጥሪውን ፡
አክብረው ፡ በራት ፡ ላይ ፡ ለመገኘት ፡ መቻላቸውን ፡ መልሰው ፡ አስ
ታወቁና ፡ በአቶ ፡ ደገፉ ፡ ቤት ፡ መሰናዶው ፡ ተጀመረ ። ዋና ፡ ዋና
ቹም ፡ የአቶ ፡ ደገፉ ፡ ዘመዶች ፡ አለቃ ፡ ክንፉና ፡ አለቃ ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡
አለቃ ፡ ይገባሃልም ፡ በደብዳቤ ፡ ተጠሩ ። የግብዣው ፡ መጠን ፡
አደገ ፡ ወይዘሮ ፡ ላቅሻቸውም ፡ የግብዣውን ፡ መሰናዶ ፡ በፕሮግ
ራም ፡ አግብታ ፡ አጣደፈችው ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜም ፡ የባልትና ፡
ትምህርትዋን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በጣም ፡ ተጣጣረች ።

የግብዣው ፡ ቀን ፡ ደረሰ ፡ የአቶ ፡ ደገፉ ፡ ቤት ፡ እየተደጋገመ ፡



በመታጠብ ፡ መከራውን ፡ አየ ። ቀጥሎም ፡ በስም ፡ ተወለወለና ፡ እን
ደመስተዋት ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ጠራ ። በመጨረሻም ፡ ቀየዎችና ፡ የአ
ትክልት ፡ መደቦች ፡ በሥርዓት ፡ ተስተካከለው ፡ ጸዱ ። እንደዚሁም ፡
በአትክልቱ ፡ መካከል ፡ የተሠራችው ፡ ክብ ፡ ባለሣር ፡ ክዳን ፡ ቤት
ውስጧም ፡ ውጭዋም ፡ በሚገባ ፡ ጸዳ ። ምድጃውም ፡ በሥርዓት ፡
ተጠራርጎ ፡ ዝግጁ ፡ ሆነ ። ይህች ፡ ቤት ፡ የተሠራችው ፡ ለመናፈሻ
ነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ ተግባር ፡ አይደለም ። ግድግዳዋና ፡ መስ
ኮቶችዋ ፡ በሥርዓት ፡ ውበትን ፡ አግኝተው ፡ በመሠራታቸው ፡ የደስ
ደስ ፡ አላት ። የአትክልቱ ፡ አበቦች ፡ መዓዛ ፡ በየሰኮንዱ ፡ በየደቂቃ
ውና ፡ በየሰዓቱ ፡ የማይለያት ፡ በመሆኑ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ገብተው ፡
ተገዝናንተው ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ አስሮ ፡ የሚያስቀምጥ ፡ ማግኔ
ታዊ ፡ ስበት ፡ አለባት ። የእሳት ፡ መሞቂያው ፡ ምድጃ ፡ የተሠራው ፡
በዘመናዊ ፡ አቅድ ፡ ስለሆነ ፡ እንደድሮው ፡ እነ ፡ አቶ ፡ ጭስ ፡ እየተን
ቧለሉ ፡ በማሳቀቅ ፡ ወይም ፡ በማስለቀስ ፡ ሊፎክሩ ፡ አይችሉም ። ስለ
ዚህ ፡ ይህች ፡ መናፈሻ ፡ ቤት ፡ ዘመናዊ ፡ መሐንዲስነት ፡ የወለዳት ፡
የተንቈበበች ፡ ቤት ፡ ነች ። ክፍሊቱ ፡ የግብዣው ፡ ተካፋይ ፡ የምትሆ
ነው ፡ ከግብዣው ፡ የራት ፡ መልስ ፡ በኋላ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ሰዓት ፡
ተሚሙቃ ፡ መጠጦችንም ፡ በአነስተኞች ፡ ጠረጴዞች ፡ ላይ ፡ አስደር
ድራና ፡ ለጊዜው ፡ ሙዚቃ ፡ ተስማሚዎች ፡ ሸክሎችን ፡ በጥሩ ፡ አመ
ራረጥ ፡ አዘጋጅታ ፡ እንግዶችዋን ፡ ትጠብቃለች ።

የግብዣው ፡ ቀን ፡ ደረሰ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ከነቤተሰቡ
ቀደም ፡ ብሎ ፡ መጣ ። እያደርም ፡ እድመኞች ፡ ሁሉ ፡ ተሰበሰቡ ።
ተጋባዦች ፡ በጠሩ ፡ አካሎቻቸው ፡ ላይ ፡ ውትት ፡ የመሳሰሉ ፡ የአገር
ልብሶችን ፡ በመልበስ ፡ ተሽትረዋል ። አቶ ፡ ደገፉና ፡ ወይዘሮ ፡ ላቅ
ሻቸው ፡ እንግዳ ፡ መቀበላቸውን ፡ እንዳቆሙ ፡ ወደሳሎን ፡ ተመለሱና
አቶ ፡ በላይነህን ፡ ከሦስት ፡ ሊቃውንት ፡ ጋር ፡ አስተዋወቁት ። ከዚህ ፡
በኋላ ፡ እንግዶች ፡ ጓድ ፡ እያበጁ ፡ ሲጫወቱ ፡ ጥቂት ፡ እንደቆዩ ፡
አሮጌውና ፡ ዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ ደነቆ ፡ ወደ ፡ አሰናዳው ፡ ራት ፡
በወይዘሮ ፡ ላቅሻቸው ፡ አስተናባሪነትና ፡ መሪነት ፡ ተጠርተው ፡
አመሩ ።

አቆልቋዮቹ ፡ ሰፋፊና ፡ ረጃጅሞች ፡ ናቸው ። ሻሽ ፡ የመሳሰሉ ፡
መሕሙዲዎችን ፡ ለብሰዋል ። በእያንዳንዱ ፡ ወንበር ፡ አንጻር ፡ አን

ዳንድ ፡ ሣሕን ፡ ቢላዎ ፡ ሹካና ፡ ብርጭቆ ፡ ተደርድሯል ፡፡ በአቶል ቋዩ ፡ ማኸል ፡ ለማኸል ፡ ደግሞ ፡ እንጀሮች ፡ በሥርዓት ፡ ተጠቅልለ ውና ፡ በሰላ ፡ ቢላዎ ፡ ተቆራርሰው ፡ በየሣሕኖች ፡ ላይ ፡ እየሆኑ ፡ አል ፊው ፡ አልፊው ፡ ተደርድረዋል ፡፡ የዶሮ ፡ ዓይንን ፡ የመሰለ ፡ ጠላና ፡ ስርዶን ፡ የመሰለ ፡ ጠጅ ፡ በንጫጭ ፡ ጠርሙሶች ፡ እየተንቆረቆሩ ፡ ስልፋቸውን ፡ በቁመት ፡ አሳምረዋል ፡፡ አልፊው ፡ አልፊው ፡ ተጋባ ዦችን ፡ እንደማያውኩ ፡ ሆነው ፡ ተዘጋጅተው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አበቦች ፡ ማኸል ፡ ለማኸል ፡ ቆመዋል ፡፡ መብራቶችና ፡ የጠረጴዛ ፡ መሰናዶች ፡ ከሩቅ ፡ ለሚመለከት ፡ ሰው ፡ የተሳደቡ ፡ ይመስላሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በማናቸውም ፡ በኩል ፡ ተጋባዦችንና ፡ አሳላፊዎችን ፡ አይገላምጡም ፡፡ እነሆ ፡ በነዚህ ፡ አቆልቋዮች ፡ ዙሪያ ፡ እድመኞች ፡ ሥፍራ ፡ ሥፍራቸውን ፡ ያዙ ፡፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወጦች ፡ በተዘጋጀላ ቸው ፡ ፕሮግራም ፡ መሠረት ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ሰልፍ ፡ ገብተው ፡ በገዛግታ ፡ ጉዞ ፡ መጡ ፡፡ ወጦች ፡ በዓይነት ፡ ከመብዛታቸው ፡ የተነሣ ፡ አንድም ፡ በድጋሚ ፡ የተጠየቀ ፡ ወጥ ፡ የለም ፡፡ ተጋባዦች ፡ አንዳ ንድ ፡ ጊዜም ፡ እያወጉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በጸጥታ ፡ ውስጥ ፡ እያ ለፉ ፡ ራታቸውን ፡ እንከት ፡ አድርገው ፡ በሉ ፡፡ ወይዘሮ ፡ ላቅሻቸው ፡ በመሰናዶው ፡ የምስጋናን ፡ ልጅ ፡ ሰበሰቡው ፡፡ ደስታም ፡ በአዳራሹ ውስጥ ፡ ከአየሩ ፡ ጋር ፡ ተዋሕዶ ፡ ረብቦ ፡ ቆሞ ፡ አበላ ፡፡

በመጨረሻ ፡ ላይ ፡ እንፍራፍሬ ፡ በትናንሽ ፡ እግረመሶቦች ፡ እየ ሆኑ ፡ በሰልፍ ፡ መጡ ፡፡ እንብርቱካን ፡ እንመንደሪን ፡ እነ ፡ ዘይቱን ፡ እነ ፡ ወሸመላ ፡ እነ ፡ ሙዝና ፡ እነ ፡ ትርንጎ ፡ በአትክልቱ ፡ መካከል ፡ ጣልቃ ፡ ገብተው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ፡፡ ተጋባዦች ፡ እንደፍላጎታቸው ፡ ከእግረ ፡ መሶቦች ፡ ላይ ፡ እያነሡ ፡ ተመግበው ፡ ሲያበቁ ፡ እጆቻቸ ውን ፡ እየታጠቡ ፡ ወደ ፡ መናፈሻዋ ፡ ቤት ፡ ሄዱ ፡፡ እንግዶች ፡ ወደ ዚች ፡ ክፍል ፡ ሲገቡ ፡ የሸክላ ፡ ሙዚቃው ፡ ያጉረመርም ፡ ያከል ፡ ያስ ረቀርቅ ፡ ያለዝብ ፡ ያወጣና ፡ ያወርድ ፡ ጀመር ፡፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ በዚህ ፡ ማታ ፡ ወደ ፡ አጸቀ ፡ ገነትነት ፡ ተለወጠችና ፡ በመምሰል ፡ ፊንታ ፡ የገነት ፡ ቅርንጫፍ ፡ ሆና ፡ ተገኘች ፡፡ መጀመሪያ ፡ ሲገቡ ፡ የአንዳንድ ፡ እንግዶች ፡ መንፈሶች ፡ ወደ ፡ ጽርሐ ፡ አርያም ፡ ወደ ፡ ተራሮች ፡ ወደ ፡ ሸለቆች ፡ ወደየረባዳ ፡ ደኖችና ፡ ወንዛወንዞች ፡ ሳይ ባክኑ ፡ አልቀሩም ፡፡ በዚህ ፡ ጊዜና ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ በድኖች ፡



ብቻ ፡ እየገቡ ፡ ፈዘው ፡ ተቀመጡ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ መንፈሶችን ፡ ያሸፈ ተው ፡ ሸክላ ፡ ሲለወጥ ፡ እንደገና ፡ መንፈሶችና ፡ በድኖች ፡ እየተዋ ሐዱ ፡ ጨዋታው ፡ ተነሣ ፡፡ በጨዋታው ፡ ውስጥ ፡ የልጅነት ፡ ነገሮች አሮጌውና ፡ ዘመናዊው ፡ ሥልጣኔ ፡ የኑሮ ፡ ዕድገት ፡ የሥራ ፡ ስፋት ፡ ትምህርትና ፡ የትምህርት ፡ ፍሬዎች ፡ ነበሩ ፡፡ በተለይ ፡ ለዚህ ፡ ማታ ፡ ግብዣ ፡ ጨዋታውን ፡ በማጣፈጥ ፡ አለቃ ፡ ይገባሃል ፡ አለቃ ፡ ከንፉና፡ አለቃ ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡ በብዙ ፡ አገልግለዋል ፡፡ ያች ፡ ክብ ፡ መናፈሻ ፡ ባለሣር ፡ ከዳን ፡ ቤት ፡ ደምቃ ፡ አመሸች ፡፡ ተጋባዦችና ፡ ጋባዦች ፡ ተደሰቱባት ፡፡ እንዲጋጣሚ ፡ በዚህ ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ ባለፈውም ፡ ዝናም ፡ አልነበረም ፡፡ ባትክልቱም ፡ ውስጥ ፡ ባለአሸዋ ፡ መተላለፊያ፡ መንገዶች ፡ ነበሩና ፡ ከተጋባዦቹ ፡ አንዳንዶቹ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብርጭቋቸውን፡ እንደያዙ ፡ እየተንሸራሸሩ ፡ አዳዲስ ፡ አየርን ፡ ይቀ በሉ ፡ ነበር ፡፡

እንግዶች ፡ ገና ፡ ነው ፡ በማለ ፡ ሐረግ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቃግደው ፡ ቆዩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አቶ ፡ እንቅልፍ ፡ በግድ ፡ እየተጫጫኑ ፡ ጊዜዩን ፡ አትቀሙኝ ፡ በማለት ፡ ድምፁን ፡ ማሰማት ፡ ጀመረና ፡ የግብዣው ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ፡፡ እንግዶችም ፡ እየተሰናበቱ ፡ እንደወጡ ፡ ከያለበት ፡ የመጠጥ ፡ ዕቆች ፡ በሥርዓት ፡ ተሰበሰቡ ፡፡ ከገበታ ፡ ቤትም ፡ የምግብ ዕቆች ፡ ሁሉ ፡ በመልክ ፡ በመልካቸው ፡ እየሆኑ ፡ ተነሡና ፡ ሁሉም ፡ በሙቅ ፡ ውኃ ፡ እንዳፍታ ፡ ተሏቃለቁ ፡፡ የአቆልቋይ ፡ ልብሶችም ፡ እየተነሡ ፡ ሲራገፉ ፡ እግር ፡ የበዛባቸው ፡ ወለሎችም ፡ ተጠርገው ፡ ጸዱ ፡፡ ዕቆች ፡ ሁሉ ፡ እየተወለወሉ ፡ ወደየሥፍራቸው ፡ ተመልሰው ፡ በሥርዓት ፡ ተቀመጡ ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ወደ ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ ቤት ፡ ለመጫወት ፡ መጥቶ ፡ ሳለ ፡ አምኃና ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ ስለ ፡ ተከሰሱበት ፡ ጉዳይ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ሲመካከሩ ፡ አገኛቸው ። እነርሱም ፡ በተለመደው ፡ አክብሮታቸው ፡ ተቀበሉትና ፡ ቁጭ ፡ ሲሉ ፡ «ሥራችሁን ፡ ቀጥሉ ፡ ስትጨርሱ ፡ እንጫወታለን ፡» ብሎ ፡ ሥራቸውን ፡ ለመቀጠል ፡ አደፋፈራቸውና ፡ ሲመካከሩ ፡ አምኃ ፡ «አቶ ፡ በላይነህ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ቢሰማው ፡ ጥሩ ፡ ምክር ፡ ሊሰጠን ፡ ይችላል ፡» ሲል ፡ አሳቡን ፡ አቀረበ ። አቶ ፡ ደገፉም ፡ የአቶ ፡ በላይነህን ፡ አስተያየት ፡ ከድሮ ፡ ጀምሮ ፡ ይወደው ፡ ነበርና ፡ በልጁ ፡ አሳብ ፡ ተደሰተ ። ቀጥሎም ፡ የሸክላውን ፡ አገልግል ፡ ታሪክ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ አስረዳው ። ከዚያም ፡ አያይዞ ፡ የክሱን ፡ ሥረ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ተረከለት ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ የጉዳዩን ፡ ታሪክና ፡ የክሱን ፡ አነሣሥ ፡ ደኅና ፡ የድርጎ ፡ ካጠና ፡ በኋላ ፡ በእነ ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ በኩል ፡ የተሰበሰቡ ፡ አስረጆች ፡ እንዳሉ ፡ አጥብቆ ፡ ጠየቀና ፡ የጽሑፍ ፡ አስረጆቹ ፡ በሙሉ ፡ ቀረቡለት ። እነዚህንም ፡ የጽሑፍ ፡ አስረጆች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ መረመራቸው ፤ ቀጥሎም ፡ ከይገባል ፡ ክስ ፡ ጋር ፡ አስተያያቸው ። በመጨረሻም ፡ የአቶ ፡ ደገፉንና ፡ የአምኃን ፡ አስተያየት ፡ ተቀበለና ፡ በአሳቡ ፡ አያይዞ ፡ መዘናቸው ።

ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ «ወዳጄ ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ አሁን ፡ ለጥቂት ፡ ደቂቆች ፡ ያህል ፡ አድምጡኝና ፡ በመጨረሻ ፡ በጉዳዩ ፡ እንከራከራለን ። ከጉዳያችሁ ፡ ውስጥ ፡ ነክነት ፡ ያላቸውን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ አጥንቼ ፡ የቀሩኝ ፡ የሰው ፡ ምስክሮች ፡ ናቸው ። የእነርሱንም ፡ ድምፅ ፡ መስማትና ፡ አለመስማት ፡ አሁን ፡ የምንፈጽማቸውን ፡ ተግባሮች ፡ አይከለክለንም ። አሁን ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ፍሬ ፡ ነገራችን ፡ እንመለስና ፡ እስኪ ፡ በጉዳዩ ፡ እንጠያየቅበት ። አባባ ፡ እውነቱ ፡ መኪታ ፡ ጉዳዩን ፡ በሥርዓት ፡ አዘጋጅተው ፡ ሄደዋል ። የጌጦቹን ፡



ዓይነትና ፡ ልክ ፡ የወርቁንም ፡ ዓይነትና ፡ ልክ ፡ ከነአልማዞቹ ፡ በዝርዝር ፡ ጽፈዋል ። ቀጥለውም ፡ በድንገተኛ ፡ ሞት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ቢለዩ ፡ ልጆቹ ፡ በሥርዓት ፡ እንዴት ፡ ሊመካፈል ፡ እንደሚችሉ ፡ ጨምረው ፡ ገልጸዋል ። ይህም ፡ ሀብት ፡ በሰው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሳይሆን ፡ በራሳቸው ፡ አረዳ ፡ ውስጥ ፡ ቤታቸው ፡ በድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ ሲቃጠል ፡ አፈር ፡ ተደርሶብበት ፡ ተገኝቷል ። እነሆ ፡ ያገኙትም ፡ ሰዎች ፡ ስሞች ፡ በዝርዝር ፡ ተጽፈዋል ። ስለዚህ ፡ ጉዳዩን ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ አሳክቶ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አቅርቦ ፡ የሸክላ ፡ አገልግሉን ፡ ሀብትነት ፡ ማረጋገጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አስጊ ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ የለበትም ። የክሱም ፡ መልስ ፡ እንደሚከተለው ፡ ሆኖ ፡ ሊጻፍ ፡ ይችላል ፡ ሲል ፡ አስረዳቸው ።

ለክቡር ፡ የመተከል ፡ አውራጃ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤
ሳላይሽ ፤
ክቡር ፡ ሆይ ፤

ከሳሽ ፡- የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡
ተከሳሽ ፡- አቶ ፡ ደገፉ ፡ እውነቱ ፡
የክሱ ፡ ዓይነት ፡ ወንጀል ፡

መንግሥታችን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ በሕገኛ ፡ ደንብና ፡ ሥርዓታዊ ፡ አመራር ፡ እንዲካሄድ ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ በየአውራጃው ፡ በየወረዳውና ፡ በየቀበሌው ፡ ማቆሙ ፡ የሕዝቡ ፡ መብቶች ፡ እንዲጠበቁለት ፡ ለማድረግ ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ የክሱን ፡ መልስ ፡ እንደሚከተለው ፡ በትሕትና ፡ አቀርባለሁ ።

፩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጦችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የወርቅ ፡ ገንዘቦች ፡ የተመረጉበት ፡ አንድ ፡ የሸክላ ፡ አገልግል ፡ ከባለ ፡ ቤቱ ፡ የቤት ፡ ፍራሽ ፡ ውስጥ ፡ ተቀብሮ ፡ አዲስ ፡ ቤትን ፡ ለመሥራት ፡ መሠረት ፡ ሲቆፈር ፡ መገኘቱ ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

፪ ፡ የሸክላውንም ፡ አገልግል ፡ የአገኙት ፡ የአንድ ፡ ቤተ ፡ ሠሪ ፡ መሠረት ፡ ቆፋሪዎች ፡ መሆናቸው ፡ የማይካድ ፡ ነው ።

፫ ፡ የሚሠራውን ፡ ቤት ፡ መሠረት ፡ የሚያስቆፍረው ፡ ሰውዬ ፡ የሸክላውን ፡ አገልግል ፡ ባለገንዘብነት ፡ መብት ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ለእኔ ፡ ደገፉ ፡ መኪታ ፡ ለምባል ፡ ሰውዬ ፡ አምጥቶ ፡ ማስረከቡ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ።

፬ ፡ በሸክላው ፡ አገልግል ፡ ውስጥ ፡ የተገኘው ፡ ሀብት ፡ የታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ የሟቹ ፡ የአቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታ ፡ ነው ። አቶ ፡ እውነቱ፡ መከታ ፡ በድንገተኛ ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ ሲሞት ፡ ይህ ፡ ሀብት ፡ በቤት ፡ ፍራሽ ፡ ውስጥ ፡ ተቀብሮ ፡ የቆየ ፡ ነው ።

፭ ፡ ሰውዬው ፡ የሸክላውን ፡ አገልግል ፡ አግኝቶ ፡ አምጥቶ ፡ ሲሰጠኝ፡ በውስጡም ፡ ምን ፡ እንደነበረበት ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። እኔም ፡ ስረክብ ፡ በውስጡ ፡ ምን ፡ ምኖችን ፡ ነገሮች ፡ እንደያዘ ፡ አላወቅሁም ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ብልኅ ፡ የወንድሜ ፡ የሟቹ ፡ ልጅ ፡ በአሳር ፡ በመከራ ፡ በብዙ ፡ ማስተንተንም ፡ ቢከፍተው ፡ በዋጋቸው ፡ የከበሩ ፡ ጌጦችና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ወርቆች ፡ ዝርዝር ፡ አብረው ፡ ተገኙ ። ሦስተኛም ፡ የተቀመጡበት ፡ ምክንያትና ፡ ለእነማን ፡ እንደተቀመጡ ፡ የሚነግር ፡ አስረጅ ፡ ተገኘ ።

፮ ፡ ስለዚህ ፡ የወንድሜ ፡ ልጆች ፡ አሳዳጊ ፡ መሆኔ ፡ በአገር ፡ የታወቀ፡ ሲሆንና ፡ ሀብቱም ፡ የወንድሜ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ሲሆን ፡ የወንድሜን ፡ ሀብት ፡ ለወንድሜ ፡ ልጆች ፡ ሰብስቤ ፡ ባኖር ፡ በማናቸውም ፡ መንገድ ፡ በወንጀል ፡ ልከሰስ ፡ የማይገባኝ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፤

፯ ፡ እንደዚሁም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቤቱ ፡ ተቃጥሎበት ፡ ከቃጠሎው ፡ ተርፎ ፡ ዕቃ ፡ ቢወጣለት ፡ ወይም ፡ በፍራሾች ፡ ተቀብሮ ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ቢገኝለት ፡ እንኳን ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ አተረፈለት ፡ ተብሎ ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ ከሚገለጽለት ፡ በስተቀር ፡ እንጡራ ፡ ሀብትህን ፡ ተወረስ ፡ ወይም ፡ ተገፈፍ ፡ ተብሎ ፡ የክስ ፡ ክርክር ፡ ሊሰነዘርበት ፡ ፈጽሞ ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ በመመልከት ፤

፰ ፡ ሟቹ ፡ ወንድሜ ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ፍጹም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሆኖ ፡ በድንገተኛ ፡ ሞት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሲለይ ፡ ልጆቹ ፡ የአገሪቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ በመሆናቸው ፡ ራሳቸው ፡ የሚደገፉ ፡ ወይም ፡ የሚረዱ ፡ እንጂ ፡ የሚወረሱ ፡ አለመሆናቸውን ፡ በማስተዋል ፤

፱ ፡ ከሳሹ ፡ በገዛ ፡ ኪሣራቸው ፡ የሰነዘሩትን ፡ ክስ ፡ እንሥተውና ፡ የቃጡትንም ፡ ወንጀል ፡ ወደራሳቸው ፡ አዙረው ፡ ተቀጥተው ፡ እንዲሄዱ ፡ ክቡር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሚዛናዊ ፡ ፍርዱን ፡ እንዲ



ሰጥ ፡ በማክበር ፡ አመለክታለሁ ።

ይህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የክስ ፡ መልስ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ እየረዳው ፡ አምኃ ፡ እውነቱ ፡ ጻፈው ። መከላከያው ፡ ተጽፎ ፡ ካለቀለት ፡ በኋላ ፡ ሲነበብ ፡ ቤተሰቡን ፡ ሁሉ ፡ አስደሰተው ። አቶ ፡ ደገፉ ፡ አቶ ፡ በላይነህን ፡ በጣም ፡ አመሰገነው ። ከዚህ በኋላ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ከብዶት ፡ የነበረው ፡ ጭንቀት ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ ተገፍፎ ፡ ሲሄድለት ፡ ተሰማውና ፡ አምጦ ፡ አምጦ ፡ እፎይ ፡ አለ ፤ ተዝናንቶም ፡ ተቀመጠ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

በተወሰነው ፡ ቀጠሮ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅና ፡ እነ ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ በፋይላቸው ፡ ተጠርተው ፡ ቀረቡ ። ከሳሽ ፡ በማመልከቻው ፡ መሠረት ፡ ነገሩን ፡ በዝርዝር ፡ አድርጎ ፡ አቀረበ ። እንደዚሁም ተከሳሽ ፡ በከሳሹ ፡ አንጻር ፡ የጻፈውን ፡ መልስ ፡ አብራርቶ ፡ መልስ ፡ ሰጠ ።

ዳኞች ፡ የመንግሥቱን ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡ ተገቢ ፡ ማስረጃችን ፡ እንዲያቀርብ ፡ መላልሰው ፡ ቢጠይቁት ፡ ማስረጃ ፡ እንደሌለውና ፡ በይገባል ፡ በነገሩ ፡ እንደሚገፋ ፡ አመለከተ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዳኞች ፡ « ይህ ፡ አሁን ፡ ያቀረብሽው ፡ ክርክር ፡ በቂ ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፡ በማስረጃ ፡ ሲደገፍ ፡ ስለሆነ ፡ አስፈላጊውን ፡ ማስረጃ ፡ ይዘህ ፡ እንድትቀርብ ፡ የአንድ ፡ ወር ፡ ቀን ፡ ሰጥተንሃል ። ልክ ፡ የዛሬ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ እዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንድትቀርብ ፡ ይሁን ።

እናንተም ፡ ተከሳሾች ፡ እስካንድ ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ በቀጠሮ ፡ ቆይታችሁ ፡ አስረጆቻችሁን ፡ ሁሉ ፡ ይዛችሁ ፡ ቅረቡ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በተጨማሪ ፡ የሰው ፡ ምስክር ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጉዳዩን ፡ መዝነን ፡ አስተያየታችንን ፡ እንገልጻለን ፡ » ብለው ፡ ዳኞች ፡ ተከሳሾችን ፡ ሊያሰናብቱ ፡ ሲሉ ፡ አንድ ፡ ተቺ ፡ ከወንበሩ ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ የዳኞችን ፡ ፈቃድ ፡ ጠየቀ ፤

«ፍርድ ፡ ቤት ፡ እውነተኛ ፡ ሚዛንነቱን ፡ እንዲያ ፡ ለመኖር ፡ የሚችለው ፡ ቀናውን ፡ መንገድ ፡ በትክክል ፡ ለመምራት ፡ ሲችል ፡ መሆኑ ፡ ለሁላችንም ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ክስ ፡ አስረጆችንና ፡ ምስክሮችን ፡ እየያ ፡ ለዳኞች ፡ የጉዳዩ ፡ መከታተያ ፡ ነገሮችን ፡ ካላስገኘ ፡ በይገባል ፡ ብቻ ፡ ለመሟገት ፡ የሚያስችል ፡ አይመስለኝም ። እንዲያውም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አደራረግ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ አይታይም ። ስለዚህ ፡ እርስዎ ፡ ጌታዬ ፡ የመንግሥቱ ፡ ነገረ-ፈጅ ፡ በትምህርትዎና ፡ በሥራ ፡ ልምድዎ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የሠለጠኑ ፡ ሲሆኑ ፡ አሁን፡ በይገባል ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ይዘው ፡ መቅረብዎ ፡ የሚያስወቅስዎ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። ማናቸውም ፡ ይገባል ፡ ከማስረጃ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ከማስረጃ ፡ በኋላ ፡ ይመጣል ፡ እንጂ ፡ በቀጥታ ፡ በዋናነት ፡ መቅረብ ፡ የለበትም ።

ምናልባት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ በመንግሥት ፡ እጅ ፡ ሆኖ ፡ ቢሠራበት ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ በመንገዶች ፡ በፋብሪኮች ፡ በትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በሆስፒታሎችና ፡ በሕዝብ ፡ መናፈሾች ፡ ረገድ ፡ የሚቀርበው ፡ ይገባል ፡ ነው ። አለበለዚያ ፡ ግን ፡ መንግሥቱ ፡ ግብርንና ፡ አሥራትን ፡ እየተቀበለ ፡ ያጸደቀውን ፡ ሀብት ፡ በይገባል ፡ መንግሥት ፡ የሚወስድበት ፡ ከሆነ ፡ የባለቤቱ ፡ ባለመብትነት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ክስ ፡ የማይገባ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊገመትና ፡ ሊወድቅ ፡ የሚችል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ ማስረጃ ፡ ሲሰበስቡ ፡ ነገሩንም ፡ በሚገባ ፡ በልተውት ፡ እንዲመጡ ፡ የሚያስፈልግም ፡ መስሎ ፡ ይታየኛል ፡» ብሎ ፡ አስተያየቱን ፡ ሰጥቶ ፡ ሲጨርስ ፡ ቀጠሮው ፡ ተመዘገበ ።

የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡ ከሳላይሽ ፡ እንደተመለሰ ፡ ለመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የክሱን ፡ ማመልከቻና ፡ መልስ ፡ እንደዚሁም ፡ ዳኞቹና ፡ ተቺዎቹ ፡ የሰጡትን ፡ አስተያየት ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እየዘረዘረ ፡ አስረዳው ። የክሱም ፡ የወደፊት ፡ ርምጃ ፡ ምንም ፡ ያህል፡ ተስፋ ፡ እንደማይሰጥም ፡ በተጨማሪ ፡ እያስተናበረ ፡ ገለጸለት ። ምክንያቱም ፡ በተከሳሾች ፡ በኩል ፡ የቀረቡት ፡ መልስና ፡ አስረጆች ፡ የማያንቃንቁና ፡ በሥርዓት ፡ የሚመሩ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ።

ሹሙ ፡ በቀረበለት ፡ መግለጫ ፡ እጅግ ፡ ተገርሞና ፡ አዝኖ ፡



የጭቃ ፡ ሹሙን ፡ አስጠራው ። ቀጥሎም ፡ ስላቀረበው ፡ ነገር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስረጆች ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ገለጸለት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጭቃ ፡ ሹሙ ፡ የጉዳዩ ፡ አስረጅ ፡ ጌጦቹና ፡ የወርቅ ፡ ገንዘቦቹ ፡ ከመሬት ፡ መገኘት ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ከማስረዳት ፡ በስተቀር ፡ ገንዘቦቹና ፡ ጌጦቹ ፡ የተገኙበት ፡ መሬት ፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የእነ ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ እንደሆነ ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ አልቻለም ። እንዲያውም ፡ በተከሳሾች ፡ በኩል ፡ ለተገኙት ፡ አስረጆች ፡ እንኳ ፡ ዋጋ ፡ ያልሰጣቸው ፡ መሆኑን ፡ ጨምሮ ፡ ገለጸ ። ስለዚህ ፡ በፊት ፡ «ማናቸውም ፡ አስረጅ ፡ ይቀርባል» ብሎ ፡ የነበረው ፡ ጭቃ ፡ ሹም ፡ በጉዳዩ ፡ አፍሮ መሬት ፡ መሬት ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።

የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ይህን ፡ ስቶ ፡ የሚያሳስት ፡ ጭቃ ፡ ሹም ፡ እንዲያው ፡ ሊያሰናብተው ፡ ባለመፍቀዱ ፡

«ማናቸውም ፡ ሠራተኛ ፡ ተሳስቶ ፡ የተሳሳተበትን ፡ ነገር ፡ ሳያርም ፡ ለበላይ ፡ ቢያቀርብ ፡ የበላይ ፡ ሹም ፡ የበታቹን ፡ በማመን ፡ ከስሕተት ፡ ሊወድቅ ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ስሕተት ፡ በቶሎ ፡ ካልተደረሰበት ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ሊያመጣ ፡ ይችላል ። በስሕተት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲሠራ ፡ የሠራተኞች ፡ ጉልበት ፡ በከንቱ ፡ ይባክናል ፤ እንደዚሁም ፡ ለዚሁ ፡ ለስሕተተኛ ፡ ነገር ፡ ማከናወኛ ፡ ገንዘብ ፡ ይጠፋል ። ሦስተኛም ፡ ስንት ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሥራ ፡ የሚከናወንበት ፡ ወርቅ ፡ ጊዜ ፡ ይጠፋል ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ስሕተት ፡ ከፍተኛ ፡ ጉዳት ፡ ስለሚያመጣ ፡ አስቀድሞ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲታሰብ ፡ በጥብቅ ፡ መመርመርና ፡ መጠናት ፡ አለበት ።

አንተ ፡ ግን ፡ አንዳችም ፡ ጥናት ፡ ሳታደርግ ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡ ችኮላ ፡ ሰባራ ፡ ነገር ፡ ይዘህ ፡ መጥተህ ፡ ይኸው ፡ መሥሪያ ፡ ቤታችንን ፡ እስከማስወቀስ ፡ ደረስህ ፤ ሥራ ፡ አስፈትተህ ፡ ገንዘብም አስወጥተህ ፡ ወርቅ ፡ ጊዜም ፡ እንዲባክንብን ፡ ምክንያት ፡ ሆነህ ፡ ከጉዳት ፡ ላይ ፡ ጣልኸን ። እኛ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እምነታችንን ፡ ባንጥልኖሮ ፡ ከስሕተት ፡ ላይ ፡ ወድቀን ፡ ጉዳት ፡ አይደርስብንም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ለወደፊቱ ፡ በምትሠራው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጥንቃቄን ፡ ገንዘብ ማድረግ ፡ አለብህ ፡» ብሎ ፡ መክሮ ፡ ወደ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ እንዲመለስ ፡ አሰናበተው ።

አቶ ፡ ደገፉና ፡ አምኃ ፡ የቀረበባቸው ፡ ክስ ፡ ፋርሽነት ፡ እጅግ ፡ አስገርሟቸው ፡ ሲመለሱ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ከአቶ ፡ በላይነህ ፡ ጋር ፡ በመንገድ ፡ ተገናኙ ። ሰላምታ ፡ ተለዋውጠው ፡ አብረው ፡ ወደ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ሲመጡ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ ጉዳዩ ፡ ከምን ፡ እንደደረሰ ጠየቃቸው ። አቶ ፡ ደገፉ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አምኃ ፡ ነገሩን ፡ እየተረተረ፡ እንዲያጫውተው ፡ ፈቀደ ።

« ከዚህ ፡ በፊት ፡ የቀረበብንን ፡ ክስ ፡ አብረን ፡ ተመልክተን ፡ ካጠናን ፡ በኋላ ፡ መልስ ፡ ስናዘጋጅ ፡ ነገሩን ፡ በሚገባ ፡ የተመለከትኸው ፡ መስሎኛል ። በክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ ከቀረበው ፡ የይገባል፡ አሳብ ፡ በስተቀር ፡ አንዳችም ፡ ክሱን ፡ የሚደግፍ ፡ አስረጅ ፡ አላቀረቡም ። በዚህም ፡ ዳኞቹና ፡ ተቺዎቹ ፡ በጣም ፡ ወቅሰዋቸዋል ፤ ጉዳዩም ፡ ያለ ፡ ማስረጃ ፡ የማይታይ ፡ በመሆኑ ፡ አስረጅ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ በቀጠሮ ፡ አሰናበቱን ፡ » ብሎ ፡ አምኃ ፡ አስረዳው ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ በጉዳዩ ፡ በጣም ፡ ተገርሞ ፡ « ሰው ፡ ሁሉ ፡ በየተግባሩ ፡ በመጽናት ፡ ፈንታ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ተግባር ፡ እየተመለከተና ፡ እየጨለፈ ፡ ሰው ፡ ለማስቸገር ፡ የሚጥረው ፡ በምን ፡ ምክንያት እየተገፋፋ ፡ ይሆን ? ለመሆኑስ ፡ የራሱን ፡ ተግባር ፡ ለማከናወንና ፡ ለማቃናት ፡ ይረዳው ፡ ይሆን ? እንጃ ፡ የሚረዳው ፡ አይመስልም ። ብቻ ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡ ሲጣጣርበትና ፡ ዐመል ፡ ሆኖበት ፡ ሲሠራበት ፡ ይታያል ። ወይ ፡ ጉድ ! ሰው ፡ ሁሉ ፡ መወነጃጀሉንና ፡ ሥራ ፡ መፍታቱን ፡ ቢገነዘብ ፡ ጊዜውን ፡ ሁሉ ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ይጣጣር ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ይሆናል ! ይህን ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ? ሁሉም ፡ ያለዕውቀት ፡ ለውጥ ፡ ዐዋቂ ፡ በሆነበት ፡ ሰዓት ፡ የአእምሮ ፡ መናወጥና ፡ ሥራን ፡ የመፍታት ፡ ጊዜንና ፡ ገንዘብን ፡ ያላንዳች ፡ ጥቅም ፡ ማባከን ፡ እያደር ፡ ብቅ ይላሉ ።

እንግዲህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ ሲፈጠር ፡ እዳር ፡ ለመውጣት ፡ የሚቻለው ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ሁሉ ፡ በደንበኛ ፡ ተግባር ፡ እንዲጠመድ ፡ በማድረግ ፡ ነው ። አሁን ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ የሚያመለክተው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ራሱ ፡ ቦዝኖ ፡ ሰዎችን ፡ ለማቦዘን ፡ የሚጥረው ፡ ነው ። ይህ ፡ የመቦዘንና ፡ የማቦዘን ፡ ተግባር ፡ የአንድ ፡ አገርን ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ ይጠቅሳል ። ገበሬ ፡ ነጋዴ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ባለፋብሪካና ፡ ሥራ ፡ ተቋራጮች ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ተደጋጋፊዎች ፡ ናቸው ። አሁን ፡ ከተጠቀሱት ፡ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የማያገለግል ፡ አንድም ፡ ክፍል ፡ የለም ። ሁሉም ፡ በየተግባራቸውና ፡ በየሥፍራቸው ፡ እየተገኙ ፡ መሥራትና ፡ የሥራ ፡ ፍሬአቸውን ፡ ማሳየት ፡ አለባቸው ። ገንዘብ ፡ ብቻውን ፡ አይሠራም ፤ ጉልበት ፡ በግድ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ በየግንባሩ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። ስለዚህ ፡ ሠራተኛ ፡ ሲጠፋ ፡ ወይም ፡ እያለ ፡ እንደሌለ ፡ ሲሆን ፡ ሥራ ፡ በውዝፍ ፡ ይቀራል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ገንዘብ፡ በውዝፍ ፡ ይቀመጣል ፤ ወይም ፡ በአልምጦች ፡ እየተበላ ፡ በከንቱ ፡ እሳት ፡ እንደፈጀው ፡ ጅማት ፡ ይኮማተራል ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ መቦዘንና ፡ ማቦዘንን ፡ ማጥፋት ፡ ያስፈልጋል ፡ » ሲል ፡ አሳቡን ፡ በማስተንተን ፡ ገለጸላቸው ።

እንደዚህ ፡ እያወጣና ፡ እያወረደ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ሲያጫውታቸው ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ሰፋ ፡ ባለ ፡ መልክ ፡ ለማየት ፡ ቻሉ ። ሰው ፡ አላስተውል ፡ እያለ ፡ የሁሉን ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ ለአምላክ ፡ ይሰጣል ፡ እንጂ ፡ የጥፋትና ፡ የልማት ፡ ምንጩ ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ነው ። ሰው ፡ ዓይኑን ፡ ከፍቶ ፡ በዙሪያው ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ቢመለከት ፡ ነገሮችን ፡ በየፈርጃቸው ፡ እየለየ ፡ በመሥራት ፡ ራሱን ፡ በተግባር ፡ ለመጥመድ ፡ ይችላል ። ከቶ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ የሚሠራው ፡ አጥቶ ፡ ሊንከራተት ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ በተሰጠው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሥራን ፡ እየፈጠረ ፡ በመጨመርና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጠቃሚ ውጤቶችን ፡ በማስገኘት ፡ ሰዎችንና ፡ ራሱን ፡ ያስደስታል ። የሥራ ፡ መቃናትም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የእርሱ ፡ ገንዘብ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ ቤት ፡ ይመጣ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ከወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ እስከመተዋወቅ ፡ ደረሱ ። አምኃ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜና ፡ አቶ ፡ በላይነህ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ እየሆኑ ፡ ለሽርሽር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጡ

ነበር ። በተለይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በላይነህና ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሚ ፡ ለብቻቸው ፡ እየሆኑ ፡ በበዓል ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጡና ፡ ይንሸራሸራሉ ። ወደ ፡ ተራሮች ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ዳሮች ፡ ወደ ፡ ሸለቆችና ፡ ወደ ፡ ጥጋጥጎች ፡ በመኪና ፡ መንገዶች ፡ ዳርዳር ፡ እየሄዱ ፡ ተፈጥሮን ፡ በማጥናት ፡ ይደሰታሉ ። ወይዘሪት ፡ ደማሚ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ትምህርትዋ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የገፋች ፡ ስለሆነች ፡ ይህን ፡ አሁን ፡ የጠቀስነውን ፡ የመናፈስ ፡ ጉዞ ፡ ከሦስት ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ታውለዋለች ።

አንደኛ ሰውነቷን ፡ በዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ለማፍታታት ፡ ስለሚረዳት ፡

የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ጉዞ ፡ አድርጋ ፡ ትቈጥረዋለች ።

ሁለተኛ በዓይንዋ ፡ በምታየው ፡ ነገር ፡ ለውጥነት ፡ ትደሰታለች ።

ሦስተኛ ለትምህርትዋ ፡ የሚጠቅማትን ፡ ነገር ፡ ትቀስማለች ።

አቶ ፡ በላይነህም ፡ በበኩሉ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ትምህርቱ ፡ እጅግም ፡ የማይደሰት ፡ ቢሆን ፡ በወይዘሪት ፡ ደማሚ ፡ ሳቢያ፡ ተፈጥሮን ፡ ወደ ፡ ማጥናት ፡ ማዘንበል ፡ ጀመረ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ የአቶ ፡ ደገፉ ፡ ልጆች ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሚ ፡ አምኃ ፡ አቶ ፡ በላይነህና ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ ለጉዳያቸው ፡ ወደ ፡ ሳላይሽ ፡ ወጥተው ፡ ሲመለሱ ፡ ስምንት ፡ የቦይ ፡ ስካውት ፡ ወጣቶች ፡ በቃሬዛ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተሸክመው ፡ ከወደባላገር ፡ አምጥተው ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ አሳርፈው ፡ መኪና ፡ ሲጠባበቁ ፡ አገኟቸው ። የእነአቶ ፡ ደገፉን፡ መኪና፡ የሚነዳው ፡ አቶ፡ በላይነህ ፡ ነበርና፡ ቁሞ ፡ ከመኪና ፡ ወረደ ። ልጆቹንም ፡ የገጠማቸውን ፡ ችግር ፡ ጠየቀ ።

ከልጆቹም ፡ አንዱ ፡ «እየተዘዋወርን ፡ አገርን ፡ ለማየት ፡ ብለን ከሦስት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ከሳላይሽ ፡ ወጥተን ፡ ወደ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ አቅጣጫ ፡ መጣን ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እንሄድ ፡ የነበረው ፡ ጫካ ፡ ጫካውን ፡ ነበር ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ እየተጓዘን ፡ ከዚያ ፡ ማዶ ፡ ተረተር ፡ ደረስን ። በዚያ ፡ ተረተር ፡ ጥግ ፡ አርፈን ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ አካባቢውን ፡ ጎበኘን። በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ጉብኝት ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ካንድ ፡ ገደል ፡ ጥግ ፡ ደርሰን ፡ ንቦች ፡ ውር ፡ ውር ፡ ሲሉ ፡ አየን ። እንዲሁም ፡ የንቦቹ ፡ ውርውርታ ፡ አስገርሞን ፡ ቆመን ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ስንመለከት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ወድቆ ፡ አየን ። ቀስ ፡ ብለንም ፡ ቀርበን ፡ ብናነጋግረው



ድምፅ ፡ አሰማን ። ለሁለት ፡ ቀና ፡ አድርገንም ፡ ሁኔታውን ፡ ብንመለከተው ፡ ተደብድቦ ፡ የወደቀ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ አገኘነው ። ቀጠል ፡ አድርገንም ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ እንደመጣና ፡ የድብደባ ፡ አደጋ፡ እንዳገኘው ፡ ብንጠይቀው ፡ « በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከተዋወቅኋቸው ፡ የዱር ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ከቀፃ ፡ ውስጥ ፡ ማር ፡ ለመቁረጥና ፡ ወስደን ፡ ለመሸጥ ፡ ተስማምተን ፡ እዚህ ፡ ድረስ ፡ አብረን ፡ መጣን ። ነገር ፡ ግን ፡ ማሩን ፡ ቆርጠን ፡ በስልቾች ፡ ከከተትን ፡ በኋላ ፡ ሽጠን ፡ በምናገኘው ፡ ክፍያ ፡ ላይ ፡ ተጣላንና ፡ አድመው ፡ ደበደቡኝ ። የምትሁ ፡ ስለ ፡ መሰላቸውም ፡ ጥለውኝ ፡ ማሩን ፡ ጭነው ፡ ሄዱ ። እኔ ፡ ግን ፡ አቅም ፡ በማጣቴ ፡ አሁን ፡ እንደምታዩኝ ፡ እዚሁ ፡ ወድቄ ፡ ቀረሁ ። ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ሁለት ፡ ቀኔ ፡ ነው ። ረኀቡና ፡ ጥሙ ፡ ፈጽሞ ፡ አልጎዳኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ የአራዊቱና ፡ የሌሊቱ ፡ ግርማ ፡ እጅግ ፡ አስፈርቶኝ ፡ አደረ ። ካሁን ፡ አሁን ፡ በሉኝ ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ያዙኝ ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ተቦጫጨቁኝ ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ተቀረማመቱኝ ። ወይኔ ፡ ሆይ ! ይህን ፡ የማይረባ ፡ ጥቅም ፡ ስከታተል ፡ ከዚህ ፡ ቀፃ ፡ ሥር ፡ ተደፍቼ ፡ ልቀር ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ መሸከሁኝ ፡ » ብሎ ፡ መለሰልን ።

እኛም ፡ እንሥተነው ፡ ለጊዜው ፡ የሚገባውን ፡ ሕክምናዊ ፡ ርዳታ ፡ አደረግንለት ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሠፈራችን ፡ ወስደን ፡ አሳደርነውና ፡ ወደዚህ ፡ በቃሬዛ ፡ ተሸክመን ፡ አመጣነው ፡ » ብሎ ፡ ታሪካቸውን ፡ በገለጸላቸው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተገረሙ ። በወጣቶቹ ፡ ሥራም፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደንቀው ፡ እዚያው ፡ ፈዘው ፡ ቀሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ኢያደር ፡ እንሠራሩና ፡ አቶ ፡ ደገፉና ፡ አምኃ ፡ ለበሽተኛው ፡ ቦታቸውን ፡ ለቀው ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ መኪናዋን ፡ እየነዳ ፡ ወደ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ጉዞውን ፡ አመራ ። አቶ ፡ ደገፉና ፡ አምኃ ፡ ከቦይስካውቶች ፡ ጋር ፡ ጥቂት ፡ እንደተጓዙ ፡ ከወደኋላቸው ፡ አንድ ፡ አውቶቡስ ፡ መጣና ፡ ተሳፍረው ፡ ወደ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ገሠገሡ ። ምንም ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ሳይፈጅባቸው ፡ ከመንደራቸው ፡ በጊዜ ፡ ደረሱ ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ ከአምሳለ ፡ ገነት ፡ እንደደረሰ ፡ በሽተኛውን ፡ ከሆስፒታል ፡ አስገባው ። በማግሥቱም ፡ ከወደቀበት ፡ አንሥተው ፡ ለሆስፒታል ፡ ያበቁት ፡ ቦይስካውቶች ፡ ወደ ፡ ሆስፒታሉ ፡ ሄደው ፡ ስለሕመምተኛው ፡ ደንበኛ ፡ ሪፖርታቸውን ፡ አቀረቡ ። የሆስፒታሉ

ጎላፊ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ ቦይ ፡ ስካውቶች ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለማየቱ ፡ በመገረም ፡ አመስገናቸው ። ለወደፊቱ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ከፍተኛ ፡ ርዳታ ፡ እንዳያቋርጡ ፡ አደራ ፡ አላቸው ።

የቦይስካውት ፡ ትምህርት ፡ አንድ ፡ ወጣትን ፡ የሕዝብ ፡ አገልጋይ ፡ እንዲሆን ፡ የሚገፋፋና ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚጨመር ፡ ተግባራዊ ፡ ትምህርት ፡ ነው ። ቦይስካውት ፡ የመጀመሪያው ፡ ታማኝ ፡ ወጣት ፡ ነው ፤ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የተቸገረን ፡ ሰው ፡ አይቶ ፡ ሳይረዳው ፡ አያልፍም ። ቦይስካውት ፡ ብልኅተኛ ፡ ነው ፤ አስቀድሞ ፡ ለሚደርስበት ፡ ችግር ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ተጠባባቂ ፡ ነው ። ቦይስካውት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለዕረፍት ፡ ሲዘጋ ፡ ማናቸውንም ፡ ችግር ፡ ለመማር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ መውጣትንና ፡ መለማመድን ፡ በጣም ፡ ይወዳል ። ስለዚህ ፡ በማናቸውም ፡ ደራሽ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ አይደነግጥም ። እየተርበተበተም ፡ ራሱን ፡ አስቸግሮ ፡ ሰውን ፡ እስከማስቸገር ፡ አይደርስም ።

ትምህርት ፡ ቤት ፡ የቀለም ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ጎድለውት ፡ የተሟላ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በቀለምና ፡ በተግባር ፡ ትምህርት ፡ የገፋ ፡ እንደሆነ ፡ የሚገጥሙትን ፡ ችግሮች ፡ እንደየአገባባቸው ፡ ተመልክቶ ፡ ሊመልሳቸው ፡ ይችላል ።

አቶ ፡ አዳፍሬ ፡ በልጅ ፡ ልጅ ፡ ክርስትና ፡ ምክንያት ፡ ግብዣ ፡ ስለነበራቸው ፡ አለቃ ፡ ክንፉን ፡ አለቃ ፡ ይገባሃልን ፡ አለቃ ፡ ደጉ ፡ ነገርን ፡ አቶ ፡ ደገፉን ፡ ከነባለቤቱ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ ጎረቤቶቻቸውንና ፡ የአቶ ፡ እውነቱ ፡ መኪታን ፡ ልጆች ፡ ጠርተው ፡ ነበር ። ይህ ፡ ግብዣ ፡ እጅግ ፡ የቀለጠና ፡ ድልብ ፡ ሰንጎችን ፡ ያጋደመ ፡ ነበር ። አቶ ፡ በላይነህና ፡ እምኃ ፡ የአሳላፊዎች ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ ልባቸው ፡ ውልቅ ፡ እስኪል ፡ ድረስ ፡ በያለበት ፡ እየተሯሯጡ ፡ የጎደሉ ፡ ነገሮችን ፡ ያስተካክሉ ፡ ነበር ። ወይዘሪት ፡ ደማሟ ፡ እርስዋን ፡ ከሚመስሉት ፡ የእምሳለ ፡ ገነት ፡ ልጃገረዶች ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ ተቀምጣ ፡ የግብዣው ፡ ደስታ ፡ ተካፋይ ፡ ሆና ፡ በለሆሳስ ፡ ትጫወት ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በአጠገብዋ ፡ የተቀመጡት ፡ ሁለተኛ ፡ እናትዋ ፡ የአቶ ፡ ደገፉ ፡ ባለቤት ፡ ከሌሎች ፡ ጋር ፡ ስትጫወት ፡ ሳለ ፡ ጣልቃ ፡ እያስገቡ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ይጠይቋትና ፡ ታስረዳ ፡ ነበር ። በተለይ ፡



ጨዋታው ፡ ሞቅ ፡ ብሎ ፡ እንሳቅ ፡ ገንነው ፡ አየሩን ፡ በሞሉት ፡ ቁጥር ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ ልቡ ፡ እንደመሰቀቅ ፡ እያለም ፡ እንደሆን ፡ እንጃ ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እየመጣ ፡ ይህን ፡ ገበታ ፡ ይጎበኘው ፡ ነበር ።

ግብዣው ፡ የተፈጸመው ፡ ማታ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በደስታ ፡ ተካፋይነቱ ፡ በልቶና ፡ ጠጥቶ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ አቶ ፡ አዳፍሬ ፡ ዎስቱን ፡ አለቆችና ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የጎረቤት ፡ ሽማግሌዎችን ፡ የግድ ፡ ቆዩ ፡ አላቸው ። በዚህ ፡ ሰዓት ፡ አሳላፊዎችና ፡ የአሳላፊዎች ፡ ረዳቶች ፡ በአንድ ፡ አቶልቋይ ፡ ዙሪያ ፡ ተሰልፈው ፡ አጨዳችን ፡ ረገፈ ፡ ይሉ ፡ ነበር ። እንሆ ፡ አሁን ፡ ጨዋታ ፡ ደርቷል ፤ ንግግሮችም ፡ ሁሉ ፡ በመደመጥ ፡ እየተመሩ ፡ ጥያቄና ፡ መልሶች ፡ መፈራረቅ ፡ ይዘዋል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የጨዋታ ፡ አርእስት ፡ ሆኖ ፡ ጥያቄዎችንና ፡ መግለጮችን ፡ ያስከተለው ፡ ቅኔ ፡ ነበር ። አቶ ፡ በላይነህና ፡ እምኃ ፡ ከገበታ ፡ መልስ ፡ የጨዋታው ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡ ለመጠየቅ ፡ ወይም ፡ ለመመለስ ፡ ተፈቅዶላቸው ፡ ተራቸውን ፡ እየጠበቁ ፡ ያወጉ ፡ ነበርና ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ተውኔቶች ፡ መጻፍና ፡ አለመጻፋቸውን ፡ ለመረዳት ፡ ጠየቀ ። ለዚህም ፡ መልስ ፡ ባለመብቱ ፡ አለቃ ፡ ክንፉ ፡ ስለሆኑ ፦

« አቶ ፡ በላይነህ ፡ ከባድ ፡ አሳሳቢ ፡ ጥያቄ ፡ በመጠየቅህ ፡ እጅግ ፡ እንደሰታለን ። ከሁሉ ፡ አስቀድሜ ፡ ተውኔት ፡ ማለት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለመግለጽ ፡ እንዲፈቀድልኝ ፡ የሁላችሁንም ፡ ፈቃድ ፡ እለምናለሁ ። ተውኔት ፡ ማለት ፡ ጨዋታ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ ቃል ፡ ተዋነየ ፡ ካለው ፡ የግዕዝ ፡ ግስ ፡ የመጣ ፡ ነው ። ተዋነየም ፡ እንደ ፡ ልጁ ፡ እንደተውኔት ፡ የጨዋታን ፡ ቤት ፡ ባለመልቀቁ ፡ ተጫወተ ፡ ማለት ፡ ነው ።

የጨዋታ ፡ ዓይነቱ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ አሁን ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ የያዝነው ፡ የአሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ተግባር ፡ ከጨዋታ ፡ ውስጥ ፡ አይወጣም ። ሰዎች ፡ ከየብጤአቸው ፡ ጋር ፡ የሚያደርጉት ፡ ንግግር ፡ ሁሉ ፡ በጠቅላላው ፡ ጨዋታ ፡ ነው ። ልጆችም ፡ በየመጠናቸው ፡ ወይም ፡ በየደረጃቸው ፡ የሚያደርጉት ፡ ንግግር ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ ጨዋታ ፡ ነው ። በጨዋታ ፡ አሳብ ፡ መቀበልና ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ አሳብ ፡ ሲሰጡና ፡ ሲቀበሉ ፡ አጻር ፡ ማየትና ፡ መስማት ፡ የተለመዱ ፡ ተግባሮች ፡ ናቸው ። ተውኔቶች ፡ በአራት ፡ መልኮች ፡ ሊታዩ ፡ ይችላሉ ።

አንደኛ በቀም ፡ ነገራም ፡ ወርቃ ፡ ወርቅ ፡ የአሳብ ፡ አለዋወጦች ፡ ይገለጻሉ ።

ሁለተኛ ፍሬ ፡ ከገለባ ፡ ሆነው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልኮች ፡ ይታያሉ ።

ሦስተኛ በምሳሌያውያን ፡ ንግግሮች ፡ እንደባሕር ፡ ማሽላ ፡ ተሸፋፍነው ፡ ይቀርባሉ ።

አራተኛ ፡ በድምፅ ፡ አልባ ፡ ተግባሮች ፡ ይገለጻሉ ። እንግዲህ ፡ ሁሉንም ፡ ባንድነት ፡ ስንጠቀልላቸው ፡ የጨዋታን ፡ መልክ ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ሰዎች ፡ ተጫዋቾችና ፡ ተመልካቾች ፡ ይህች ፡ ዓለም ፡ መጨዋቻ ፡ ኑሮም ፡ አጫዋች ፡ ሆነው ፡ እናገኛቸዋለን ።

ሁላችሁም ፡ እንደምታውቁት ፡ የትምህርት ፡ መልኩ ፡ ብዙ ፡ ነው ። በቀጥታ ፡ በክፍል ፡ የሚሰጥ ፡ ትምህርት ፡ አለ ። ቀጥሎ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ከተቻለ ፡ በሙከራና ፡ በምርምር ፡ የሚሰጥ ፡ ትምህርት ፡ አለ። ሦስተኛ ፡ በምሳሌ ፡ የሚሰጥ ፡ ትምህርት ፡ አለ ። አሁን ፡ እንግዲህ ፡ ተውኔትን ፡ በትምህርት ፡ መልክ ፡ እንመልከተውና ፡ ከሦስቱ ፡ ባንዱ ፡ ክፍል ፡ እንመድበው ። ለእኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ምንም እንኳ ፡ ተውኔት ፡ የክፍል ፡ ትምህርትን ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ መስሎ ፡ ቢታይ ፡ ከምሳሌያውያን ፡ ትምህርቶች ፡ ውስጥ ፡ አላወጣውም ። አሁን ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ በትምህርትነት ፡ መልኩ ፡ የገለጽሁት ፡ ተውኔት ፡ በትያትር ፡ ሥርዓት ፡ የሚቀርብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሥርዓት ፡ አልቦ ፡ ንግግር ፡ ወይም ፡ ተራ ፡ ጨዋታን ፡ አይደለምና ፡ እንዳንደነቃቀፍ ፡ አደራዬን ፡ አስከትላለሁ ።

እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ተነሣንበት ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እንመለስና ፡ በግዕዝ ፡ በተውኔት ፡ መልክ ፡ የተሰናዱ ፡ ጽሑፎች ፡ መኖርና ፡ አለመኖራቸውን ፡ እንናገር ። መልሱ ፡ በቁጥራቸው ፡ መብዛትና ፡ ማነስ ፡ ከሚገኘው ፡ ጥርጣሬ ፡ በስተቀር ፡ አዎን ፡ ተጽፈዋል ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የግዕዝ ፡ መጻሕፍት ፡ መቃጠልና ፡ መዘረፍ ፡ ያጠቃቸው ፡ በመሆናቸው ፡ በየቅርቡ ፡ ቦታ ፡ አይገኙም ፡ ይመስለኛል ። ብቻ ፡ በታላላቅ ፡ ገዳማት ፡ ባንዳንድ ፡ ዋሾችና ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እጆች ፡ አይታጡም ፡ » ሲሉ ፡ መልስ ፡ ሰጡ ።

አሁንም ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ « አዳፍሬ ፡ ክቡር ፡ ፊቃድዎ ፡ አይሰልቸኝና ፡ የቅኔ ፡ መምህራን ፡ ሁሉ ፡ እንደመጻሕፍትና ፡ እንደዜማ ፡ መምህራን ፡ የሚያስተምሩባቸው ፡ ምርጥ ፡ ምርጥ ፡ የቅኔ ፡ መጻሕፍት ፡ ለቅኔ ፡ ትምህርት ፡ በየደረጃው ፡ አሉትን ? » ሲል ፡ ደግሞ ፡ ጥያቄውን ፡ አቀረበ ።

መምህር ፡ ከንፋ ፡ « ወዳጄ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አሁንም ፡ ጣዕምና ለዛ ፡ ያለውን ፡ ጥያቄ ፡ በማቅረብህ ፡ መደሰቴን ፡ በመግለጽ ፡ እኛ ፡ ቅኔዎች ፡ በጉንጫችሙ ፡ የተባልን ፡ መምህራን ፡ እያለን ፡ ምን ፡ ምኖች ፡ መጻሕፍት ፡ በቅኔ ፡ ት/ቤት ፡ እንዲኖሩ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ይመስልሃል ? በእውነቱ ፡ ባለማስፈለጉ ፡ የሉንም ። መጻሕፍት ፡ የሉም ፡ ማለቴ ፡ ሳይሆን ፡ የቅኔ ፡ መምህራን ፡ በቃላቸው ፡ ቅኔውን ፡ በየዓይነቱና ፡ በየደረጃውም ፡ እየዘረፉ ፡ ስለሚያስተምሩ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የቅኔ ፡ መምህራን ፡ መጽሒፍ ፡ ጋሻው ፡ ባለመሆናቸው ፡ የቅኔ ፡ መጻሕፍትና ፡ መምህራን ፡ ናቸው ። ይህም ፡ የቅኔ ፡ ጥበባችን ፡ እነሆ ፡ በከፍተኛነት ፡ እየተገመተ ፡ ዓለምን ፡ እንዳስደነቀ ፡ ይኖራል ። ምናልባት ፡ ይህን ፡ መግለጫ ፡ ገና ፡ ለመጀመሪያ ፡ መስማትህ ፡ እንደሆነ በልብህ ፡ ጽላት ፡ ጽፈህ ፡ ያዘው ፡ » ሲሉ ፡ ደግመው ፡ አስረዱ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ የነበሩትን ፡ ሁሉ ፡ በመገረምና ፡ በቅኔአቸው ፡ ኵራት ፡ ነካኩአቸው ።

ሦስተኛም ፡ ከልጅ ፡ እግሮቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ እንዲፈቀድለት፡ ጠየቀና ፡ « በየአብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ እሑድ ፡ እሑድና ፡ በበዓላት፡ ቀናት ፡ ዘወትር ፡ በአዲስነት ፡ የሚፈሰው ፡ ቅኔ ፡ ምንድር ፡ ነው ? » ሲል ፡ ድምፁን ፡ አሰማ ።

መምህር ፡ ደጉ ፡ ነገር ፡ « በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ እንዴት ፡ ያለው ፡ ጥያቄ ፡ ይቀርብ ፡ ጀመር ! ያልሰማው ፡ መጣ ፡ ያላጤነው ፡ ይሏችኋል ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ኅበዝ ፡ ነው ። በየበዓላቱ ፡ ነክነት ፡ እየተደረሰ ፡ አምላክን ፡ ማመስገኛ ፡ ነው ። ቅኔ ፡ ራሱ ፡ የምስጋና ፡ ወይም ፡ ለአምላክ ፡ የመገዛት ፡ ምልክት ፡ ነው ። እንዲያውም ፡ በከንቱ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከቃል ፡ ድግምት ፡ በስተቀር ፡ ምን ፡ ምን ፡ ያውቃሉ ፡ እያሉ ፡ ያሙናል ፡ እንጂ ፡ ዘወትር ፡ ምሥጢሩን ፡ ኀሊናችን ፡ በተረዳው ፡ መሠረት ፡ አዳዲስ ፡ ቅኔን ፡ እየደረስን ፡ ፈጣሪያችንን ፡ የምናመሰግንበት ፡ ድርሰት ፡ ነው ። ይህም ፡ ዘወትር ፡ የቅኔ ፡ ፈጣሪዎች ፡ ማለት ፡ በየቀኑ ፡ ደራሲዎች ፡ መሆናችንን ፡ ይገልጻል ።

ብቻ ፡ ጥቂት ፡ የሚቆጨን ፡ በጽሑፍ ፡ አለመቀመጡ ፡ ነው ፡ » ሲሉ ፡ መለሱለት ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

አቶ ፡ ደገፋና ፡ አምኃ ፡ በተወሰነው ፡ ቀጠሮ ፡ ወደ ፡ ሳላይሽ ፡ ወጥተው ፡ በሰዓቱ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቀረቡ ። የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅም ፡ ከነረዳቶቹ ፡ ቀረበ ። ጊዜው ፡ ልክ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ከሩብ ፡ ሆኗል ። ዳኞቹ ፡ በውዝፍ ፡ ያደረ ፡ ነገር ፡ ጀምረው ፡ በማጣራት ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ በጸጥታ ፡ ሲሠሩ ፡ ይታያሉ ።

ዳኞቹ ፡ የተሠየሙበት ፡ ሰገንታዊ ፡ ሥፍራ ፡ ግርማን ፡ ተኀናጽፎ ፡ የሚያስፈራና ፡ የሚያርድ ፡ ሆኗል ። ተቺዎች ፡ ከግራና ፡ ከቀኝ ከላይ ፡ ወደታችና ፡ አግድም ፡ ተኮልኩለው ፡ ነገረተኞችንና ፡ አዳማጮችን ፡ ይመለከታሉ ። ከዳኞች ፡ በስተኋላ ፡ ባለው ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የኀላ ፡ ሥዕል ፡ የዳኞቹን ፡ አመራር ፡ የነገረተኞቹን ፡ ሥራትና ፡ የተቺዎቹን አሰነዛዘር ፡ ቁልቁል ፡ ይመለከታል ። ከሥዕሉ ፡ ግርጌ ፡ የፍርድ ፡ ሚዛን ፡ በድምቀቱ ፡ ዓይኖችን ፡ እየጋበዘ ፡ በተጨማሪነት ፡ የዳኞቹን ፡ ራስ ፡ ቁልቁል ፡ ያስተውላል ።

ከነገረተኞች ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እንደዚሁም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሁሉ ፡ ተመልካቾች ፡ አግዳሚ ፡ ወንበሮችን ፡ መልተው ፡ ተርፈው ፡ በቁመት ፡ ቆመዋል ። አጫጭሮች ፡ ከፊት ፡ መጠነኞች ፡ ከመካከል ፡ ረጃጅሞች ፡ በስተኋላ ፡ ቆመዋል ። ጠበቆችና ፡ ነገረተኞች ፡ ከዳኞቹ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቆመዋል ። ባለተራ ፡ ነገረተኞች ፡ ከቀረቡት ፡ ነገረተኞች ፡ ኋላ ፡ ተቀምጠው ፡ ተራቸውን ፡ ይጠባበቃሉ ። እነሆ ፡ ፍርድ ቤቱ ፡ በሥርዓታዊ ፡ መልኩ ፡ በመጠኑ ፡ ተገልጾ ፡ ለመታየት ፡ ችሏል ። በተለይ ፡ ከብርሃን ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ የማያስተላልፉ ፡ ባለመስታዎት ፡ መስኮቶች ፡ አየርን ፡ እንደማያምጉ ፡ ሆነው ፡ ሲከፈቱ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ አትክልት ፡ አበቦች ፡ የሚመጡት ፡ መዓዛች ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ እያሰኙ ፡ የቤቱን ፡ አየር ፡ በየሰኮንዱ ፡ በየደቂቃውና ፡



በየሰዓቱ ፡ ያድሱታል ። ስለዚህ ፡ ያላንዳች ፡ መታወክ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ይቀጥላል ።

ሁለተኛው ፡ ተራ ፡ የአቶ ፡ ደገፋና ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡ ነበርና ፡ ተጠርተው ፡ በቀዳሚዎቻቸው ፡ ሥፍራ ፡ ተተኩ ። ዳኞቹም ፡ ፋይሉን ፡ ከፈቱ ። በቀኝ ፡ የተቀመጠው ፡ ዳኛ ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡ እንዲያቀርብ ፡ በተጠየቀው ፡ መሠረት ፡ አስረጅቹን ፡ እንዲደረድር ፡ ጠየቀ ። ነገር ፡ ግን ፡ ነገረ-ፈጁ ፡ አንዳችም ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ ባለመቻሉ ፡ ይገባልን ፡ ብቻ፡ አንቆ ፡ ይዞ ፡ ለመከራከር ፡ ሽንጡን ፡ ገተረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግራ ፡ ወንበሩ ፡ « እስኪ ፡ ይገባልን ፡ አጠብቃለሁ ፡ ብለህ ፡ የምታቀርበውን ፡ አስተሳሰብ ፡ እያብራራህ ፡ አቅረበው ፡ » ሲል ፡ ጠየቀ ።

ነገረ-ፈጅ ፡ « ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በብዙ ፡ ሥፍራዎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ጠላት ፡ የቀበራቸው ፡ መሣሪያዎች ፡ እየተገኙ ፡ ሲወጡ ፡ ሁሉም ፡ በቀጥታ ፡ ለመንግሥት ፡ መግባታቸውን ፡ የማያውቅ ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ይህም ፡ የሸክላ ፡ አገልግል ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ ተቆፍሮ ፡ ከተገኘ ፡ እንደመሣሪያዎቹ ፡ ሁሉ ፡ የመንግሥት ፡ ሀብት ፡ መሆኑ ፡ ነውና ፡ ለመንግሥት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ ይገባዋል ፡ ስል ፡ የይገባል ፡ ክርክሬን ፡ አቀርባለሁ ። »

ግራ ፡ ወንበሩ ፡ « በል ፡ ለወደፊቱ ፡ አንዳችም ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ አልችልም ፡ ክርክሬንም ፡ በይገባል ፡ ብቻ ፡ እቀጥላለሁ ፡ ስትል የመጨረሻ ፡ ቃልህን ፡ ስጥና ፡ ነገሩ ፡ ይቀጠል ። »

የመንግሥት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡ « ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ይሙት ፡ አስረጆች ፡ የሉኝም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ክርክሬን ፡ በይገባል ፡ እቀጥላለሁ ። »

የተከበሩት ፡ የመካከለኛው ፡ ዳኛ ፡ ማለት ፡ በፕሬዚዳንትነት ፡ የተቀመጡት ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ የነገሩን ፡ አመራር ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በጸጥታ ፡ ሲያዳምጡ ፡ ቆይተዋል ። አሁን ፡ ግን ፡ አቶ ፡ ደገፋን ፡ ለመጠየቅ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሆኖአል ።

ክቡር ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ « ተከሳሽ ፡ አንተ ፡ እንደከሳሽ ፡ ክርክርህን ፡ በይገባል ፡ ለመቀጠል ፡ ትፈቅዳለህን ? ወይስ ፡ በአስረጆችህ ፡ መሠረት ፡ ትከራከራለህ ? »

ተከሳሽ ፡ « ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ የበቁ ፡ አስረጂዎች ፡ ግልባጮች ፡

ክፊት ፡ በሚገኘው ፡ ፋይል ፡ ውስጥ ፡ ከመከላከያዬ ፡ ጋር ፡ ተያይዘው ፡ ይገኛሉ ። ስለዚህ ፡ በአስረጀቼ ፡ መሠረትነት ፡ እከራከራለሁ ፡ እንጂ ፡ ይገባልን ፡ አልቀበለውም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የመቀበልንና ፡ ያለመቀበልን ፡ መብት ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማግኘት ፡ የሚቻል ፡ መሆኑንና ፡ አለመሆኑን ፡ እስካሁን ፡ አላውቅም ። »

ክቡር ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ « ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በእምነት ፡ ክዶት ፡ ክርክር ፡ መሠረት ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ በማስረጃ ፡ መሠረት ፡ ያከራክራሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ማስረጃን ፡ ተከትሎ ፡ በአገባብ ፡ የሚመጣ ፡ ይገባልም ፡ ሲገኝ ፡ እንዳመጣጡ ፡ አከራክረው ፡ ፍርድን ፡ ይሰጣሉ ። እንግዲህ ፡ የሥራቶች ፡ ምስሶ ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ በአስረጅችህ ፡ መሠረትነት ፡ ክርክርህን ፡ እንድትገፋ ፡ ይፈቀድልሃል ። »

ተከሳሽ ፡ « ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለተከሰስሁበት ፡ ክርክር ፡ መልስ ፡ ስሰጥ፡

አንደኛ ፡ መሬቱ ፡ የኔና ፡ የወንድሜ ፡ መሆኑንና ፡ ባለመሬትነታችንን ፡ የሚገልጹ ፡ ሰነዶች ፡ አያይዣለሁ ።

ሁለተኛ ፡ ከመሬታችን ፡ ውስጥ ፡ የተገኘው ፡ ሀብት ፡ የወንድሜ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጹ ፡ አስረጆች ፡ ቀርበዋል ።

ሦስተኛ ፡ ሀብቱ ፡ የተቀመጠበትን ፡ ምክንያትና ፡ ለእኔማን ፡ እንደሚሰጥ ፡ የሚገልጽ ፡ አብሮ ፡ ይገኛል ። ስለዚህ ፡ ክቡር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በነዚህ ፡ አስረጆች ፡ መሠረትነትና ፡ ቢያስፈልግም ፡ በሚቀርቡ ፡ ምስክሮች ፡ ቃላት ፡ ፍርዱን ፡ ሊሰጠን ፡ ይችላል ። »

ዳኞቹ ፡ ከችሎቱ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ መማከሪያ ፡ ክፍላቸው ፡ ገብተው ፡ በብዙ ፡ ተከራክረው ፡ ውሳኔዎችን ፡ ይዘው ፡ ተመለሱ ። ሦስቱም ፡ ዳኞች ፡ - « የመንግሥት ፡ ሀብት ፡ ማለት ፡ በእውነቱ ፡ የሕዝብ ፡ ሀብት ፡ ማለት ፡ ነው ። መንግሥት ፡ የሕዝብ ፡ ጠባቂና ፡ አስተዳዳሪ ፡ ነው ። ራሱ ፡ መንግሥት ፡ የቆመው ፡ በሕዝብ ፡ ፈቃድ ፡ ስለሆነ ፡ በፈቃድ ፡ የቆመለትን ፡ ሕዝብ ፡ መብት ፡ መጠበቅ ፡ ዓይነተኛ ፡ ሥራው ፡ ነው ። እያንዳንዱም ፡ ድኃ ፡ የመንግሥቱ ፡ መንቀሳቀሻ ፡ ሀብት ፡ እንዲደረጅና ፡ የመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ እንዲቀና ፡ ማሰብ ፡ ግዴታዊ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ሁለቱንም ፡ አስተያየቶች ፡ መዝነን ፡ የሚከተለውን ፡ ፍርድ ፡ ሰጥተናል ።



አንደኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ባቀረበልን ፡ አስረጆች ፡ መሠረት ፡ የሸክላው ፡ አገልግል ፡ ሀብት ፡ ለአቶ ፡ እውነቱ ፡ መከታ ፡ ወራሾች ፡ እንዲሰጥ ፡ ፈርደናል ። የሸክላው ፡ አገልግል ፡ ሀብት ፡ ከዚሁ ፡ ቀርቦ፡ በውስጡ ፡ ያሉ ፡ ዝርዝር ፡ ነገሮች ፡ እንዲታዩም ፡ ጨምረን ፡ ወስነናል ።

ሁለተኛ ፡ የመንግሥት ፡ ነገረ-ፈጅ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሸክላውን ፡ አገልግል ፡ ሀብት ፡ ጉዳይ ፡ ተከታትሎ ፡ በማቅረቡ ፡ እያመሰገን በደንቡ ፡ መሠረት ፡ ከዚህ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ቀረጥ ፡ ተቀብሎ ፡ ለመንግሥት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ያስገባ ፡ ስንል ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርዳችንን ፡ ሰጥተናል ። »

## ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ወደ ፡ ት/ቤት ፡ የምትመለስበት ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ ። ወደ ፡ ት/ቤት ፡ ስትመለስ ፡ ባዶ ፡ እጅዋን ፡ እንዳትሄድ ፡ የዳቦ ፡ ቆሎ፡ ጭኮ ፡ ምጥን ፡ በርበሬና ፡ በጨውና ፡ በምጥን ፡ በርበሬ ፡ ተለውሶ ፡ የደረቀ ፡ ቋንጣ ፡ በሥራት ፡ ተዘጋጀላት ። ሁሉም ፡ ለየብቻቸው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቆች ፡ ተከተው ፡ እንደገና ፡ ባንድ ፡ ታላቅ ፡ የእንጨት ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ታሽጉ ። ፍራፍሬዎችም ፡ ደግሞ ፡ በአንዳንድ ፡ ሌላ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ እንደ ፡ ሙሽራ ፡ ተሸፋፍነው ፣ ተቀመጡ ። በእነዚሁም ፡ ላይ ፡ መክደኛው ፡ እንደማይከፈት ሆኖ ፡ ተጠነቀረባቸው ። ልብሶቹ ፡ በሚገባ ፡ ተዘጋጅተዋል ። የጥጥ ፡ የናይለን ፡ የተልባ ፡ እግርና ፡ የሐር ፡ ልብሶቿ ፡ ታጥበውና ፡ ተተኩሰው ፡ በሻንጣ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባቸውን ፡ ሥፍራ ፡ ያዙ ። እንደዚሁም፡ የሱፍ ፡ ልብሶቿ ፡ ደኅና ፡ ሆነው ፡ ተጠርገው ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ። በጠቅላላው ፡ የጉዞዋ ፡ መሰናዶ ፡ በሚገባ ፡ ተከናወነ ።

እምኃና ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ ከትምህርት ፡ ቤትዋ ፡ እኔ ፡ ላድርሳት እኔ ፡ ላድርሳት ፡ በመባባል ፡ ጥቂት ፡ ከተከራከሩ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ እንዲያደርስዋት ፡ ፈቀደችላቸውና ፡ ሦስት ፡ የመሂጃ ፡ ቲኬቶች ፡ ተቆረጡ ። ማለዳ ፡ የተነሣው ፡ ፈጣን ፡ አውቶቡስ ፡ ከቀኑ ፡ በአሥራ

አንድ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከተፍ ፡ አለ ። አውቶቡሱም ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ወርደው ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ መጠነኛ ፡ ሆቴል ፡ ሄደው ፡ አረፉ ። በዚህም ፡ ሆቴል ፡ እንደ ፡ ደማሜ ፡ ከአውራጆቻቸውና ፡ ከየወረዳቸቸው ፡ መጥተው ፡ ያረፉ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ። ደማሜም ፡ ባገኘቻቸው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደሰተች ። እነርሱ ፡ ቀድመዋት ፡ ነበርና ፡ የገቡት ፡ ከነሽኝዎቿ ፡ ለራት ፡ ጋበዟትና ፡ አብረው ፡ ሲጨዋወቱ ፡ አመሹ ።

ደማሜ ፡ ለብቻዋ ፡ አንዲት ፡ የተጣዳች ፡ ክፍል ፡ ተዘጋጅችላትና ፡ ታጅባ ፡ ከተሸኘች ፡ በኋላ ፡ ገብታ ፡ ተኛች ። ነገር ፡ ግን ፡ የሆቴሉ ፡ ክፍሎች ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ተጣብበው ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ አምኃና ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ ለሁለት ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ አገኙ ። እነርሱም ፡ በተራቸው ፡ ከክፍላቸው ፡ ገብተው ፡ ስለ ፡ ጉዞአቸውና ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ጉዳይ ፡ በአልጋቸው ፡ ላይ ፡ ጋደም ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ ሲነጋገሩ ፡ አምሽተው ፡ እንቅልፍ ፡ ገረዘዛቸውና ፡ ተኙ ። ሁሉም ፡ ያሉበትን ፡ ሳያውቁ ፡ ለጥ ፡ ብለው ፡ ወድቀው ፡ አደሩ ። ማለት ፡ በአንድ ፡ ጎናቸው ፡ ብቻ ፡ ተኝተው ፡ አደሩ ።

በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ ሦስቱም ፡ ለሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሩብ ፡ ጉዳይ ፡ ተነሥተው ፡ ፊታቸውን ፡ ታጥበው ፡ ልብሳቸውን ፡ ለውጠውና ፡ አብበው ፡ ወደ ፡ ምግብ ፡ መጡ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ለቁርስ ፡ ጋብዛቸው ፡ የነበሩትን ፡ መምህራንና ፡ ተማሪዎች ፡ በክፍሉ ፡ አሳላፊ ፡ አስጠራቻቸውና ፡ መጡ ። ልጆቹም ፡ መጥተው ፡ ሰላምታን ፡ ከተለዋወጡ ፡ በኋላ ፡ ሥፍራ ፡ ሥፍራቸውን ፡ ያዙ ። ቁርስ ፡ ተጀመረ ። ለስታ ፡ ቅቤና ፡ ዳቦ ፡ ቅንጬ ፡ ሙቅ ፡ የዕንቁላል ፡ ጥብስና ፡ ዳቦ ፡ የስሊጥ ፡ ልቅልቅ ፡ አነባበሮና ፡ የሽንብራ ፡ ዱቢት ፡ ቀረቡ ። እንደያስፈላጊነታቸው ፡ እየቀረቡ ፡ ልጆች ፡ ተመገቧቸው ። ቁጢ ፡ የገብስ ፡ ሻይና ፡ ቡና ፡ እንደዚሁም ፡ ትኩስ ፡ ወተት ፡ ቀረቡ ። በቀረበው ፡ ቁርስ ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ሲደሰቱ ፡ አምኃ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተገረመ ።

ከመገረሙም ፡ የተነሣ ፡ « ለስታ ፡ ቅቤ ፡ አራስ ፡ ልጅ ፡ እንዲውጠው ፡ ይሰጣል ፡ እንጂ ፡ ዐዋቂ ፡ ከዳቦ ፡ ጋር ፡ እንዲበላው ፡ ሲሰጥ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ አላየሁም ። ቅቤ ፡ ባገሬ ፡

አንደኛ ፡ ለወጥ ፡ ያገለግላል ።



ሁለተኛ ፡ ከድልህ ፡ ጋር ፡ ተለውሶ ፡ እንጀራ ፡ ላይ ፡ እየተለቀለቀ ፡ ይበላል ።

ሦስተኛ ፡ ቅቤውና ፡ ድልሁ ፡ ተለውሶ ፡ በእንጀራ ፡ እየተጠቀሰ ፡ ይበላል ።

አራተኛ ፡ እንጀራ ፡ ተለቅልቆ ፡ እየተጨበጠበት ፡ ይበላል ። ስለዚህ ፡ ለስታ ፡ ቅቤ ፡ ያላንዳች ፡ ድልህ ፡ ወይም ፡ ምጥን ፡ እንዲያው ፡ ከዳቦ ፡ ላይ ፡ ተለጥፎ ፡ ሲበላ ፡ ገና ፡ ዛሬ ፡ ማየቴ ፡ ስለሆነ ፡ እጅግ ፡ ተገርሚያለሁ ፡ » ሲል ፡ በመናገሩ ፡ እንደገና ፡ ሁሉም ፡ በእርሱ ፡ ተገረሙበትና ፡ በአንድነት ፡ ከት ፡ ብለው ፡ ሳቁ ።

አምኃ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ከአምሳለ ፡ ገነት ፡ ወጥቶ ፡ የማያውቅ ፡ ለጎጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ጉብኝት ፡ እንግዳ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ካልሄዱና ፡ ካላዩ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አይታወቅም ። እነሆ ፡ ከቤት ፡ ካልወጡ ፡ ለዓለም ፡ እንግዳ ፡ በመሆን ፡ የራስን ፡ ሞኝነት ፡ መግለጽ ፡ ይመጣና ፡ መገረምን ፡ ይፈጥራሉ ።

ልጆቹ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጨዋቶችን ፡ እያነሡና ፡ እየተነጋገሩ ፡ ቁርሳቸውን ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ በሉ ። በቁርሳቸውም ፡ ዝግጅት ፡ መደሰታቸውን ፡ ገልጸው ፡ ለአሳላፊው ፡ ጠቀም ፡ ያለ ፡ ጉርሻ ፡ ሰጡት ። ከቁርስ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ እንደተነሡ ፡ ሁሉም ፡ ዕቃቸውን ፡ በሥርዓት ፡ በሥርዓት ፡ እያደረጉ ፡ ታክሲ ፡ ተከራይተው ፡ ወደ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሄዱ ። ከእዚያም ፡ እንደደረሱ ፡ ሞግዚታቸው ፡ በደስታ ፡ ተቀብለው ፡ ወደየተመደበላቸው ፡ ቦታ ፡ መሯቸው ። እነሆ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርት ፡ ወደዚህ ፡ የመምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብታ ፡ ሥፍራዋን ፡ ያዘች ። አምኃና ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ረድተው ፡ ከሠፈሯና ፡ ከክፍልዋ ፡ ካደረሷት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሆቴላቸው ፡ ተመለሱ ።

ልክ ፡ ለሰባት ፡ ሰዓት ፡ ሩብ ፡ ጉዳይ ፡ ሲሆን ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ወደወንድሞቿዋ ፡ ተመለሰችና ፡ አብራ ፡ ምሳዋን ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ተጋበዘች ። እነርሱ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ደንገጥ ፡ ስላሉ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ያቀረቅራሉ ። ደማሜም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ያንዱን ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ የሁለተኛውን ፡ ዓይኖች ፡ እየተመለከተች ፡ እርስዋም ፡ በበኩልዋ ፡ ትስጋለች ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዛሬም ፡ ቡና ፡

ከማረፊያቸው : እንዲያመጣላቸው : አሳላፊውን : አስጠንቅቀው : ወደማረፊያቸው : አመሩ ።

አቶ : በላይነህ : ወይዘሪት : ደማሜ : ወደ : አዲስ : አበባ : በተቻላት : ጊዜ : ብትመጣና : ነፋስ : ብትለውጥ : በብዙ : ነገር : እንደሚረዳት : ገለጸላት ። ከዚህም : አያይዞ : አምኃ : ይዞአት : ለመምጣት : እንደሚችልና : ለአምኃም : መልካም : ለውጥ : እንደሚሆንለት : ጨምሮ : አሳብ : ሰጠ ። ሁለቱም : « ወርቅ : አሳብ : ነው ፤ ይህንም : አሳብ : እንደ : መልካም : ጥሪ : ቆጥረን : ምናልባት : በገና ዕረፍት : ወይም : በፋሲካ : እንመጣ : ይሆናል ። ነገር : ግን : ከፋሲካው : ጊዜ : ይበልጥ : ጥቂት : ሰፋ : ያለ : የዕረፍት : ጊዜ : የሚገኘው : በገና : በዓል : ነውና : በዚያን : ጊዜ : ሳንመጣ : አንቀርም : » ብለው : ለአቶ : በላይነህ : የጋራ : መልስ : ሰጡት ። ደማሜ : ንግግርዋን : በመቀጠል : « ለማናቸውም : ነገር : አንዳንድ : ጊዜ : ደብዳቤዎችን : ብንለዋወጥ : ማናቸውንም : ነገር : ልንነጋገር : እንችላለን ፤ » ስትል : ባለተስፋ : ቃልዋን : ለአቶ : በላይነህ : ገለጸችለት ።

ቡናቸውን : ጠጥተው : ካረፉ : በኋላ : ሦስቱም : የደብረ : ማርቆስን : ከተማ : ለመጎብኘት : ወጣ : አሉ ። መጀመሪያ : ወደፊረስ : ቤት : የሚወስደውን : መንገድ : ይዘው : ሲያመሩ : አንድ : ባለታክሲ : ድንገት : ቀረበና : « እመቤቴና : ጌቶቼ : አሁን : ስመለከታችሁ : አገር : የምትጎበኙ : እንግዶችን : ትመስላላችሁ ። ብትፈቅዱ : በመጠነኛ : ዋጋ : ይህች : ታክሲ : ዛሬ : የእናንተ : ሆና : ለማምሸት : ትችላለች ። እኔም : ከዚህ : በፊት : ብዙዎችን : ሰዎች : ስላስጎበኘሁ በብዙ : ነገር : ልረዳችሁ : እችላለሁ ፤ » ሲል : ጥያቄውን : አቀረበ ። ወይዘሪት : ደማሜም : « እውነቱን : ነው ፤ እርሱ : ከእኛ : የበለጠ : ያውቃል ፤ ሥራው : ይህ : ነው ፤ » ስትል : አረጋገጠች ። በዚህ : ጊዜ : ሁሉም : በነገሩ : ተስማሙበት ። መጀመሪያ : አብያተ : ክርስቲያናቱን ፤ ቀጥሎም ፤ ያራቱን : ማዕዘን : መንገዶች ፤ ሦስተኛ ፤ ገበያውን ፤ አራተኛ : የሕዝብ : መናፈሻውንና : አምስተኛ : የከተማውን : መጻሕፍት : ቤት ፤ ለመጎብኘት : ተስማምተው : ከታክሲዋ : ውስጥ፡ ገቡና ፡ በፕሮግራማቸው : መሠረት : ሽው : አሉ ። ምንም : ያህል : አጣርታ : ከንታሪካቸው : የተጠቀሱትን : ቦታዎች ፤ ባታውቃቸው ፤ በመጠኑ : አጥንታቸው : ነበርና : ከባለታክሲው : ጋር ፤ እየተረዳዱ :



ጉብኝቱን : በሥርዓት : ፈጸሙት ። ከጉብኝቱ : መልስ : ወይዘሪት : ደማሜን : ከትምህርት : ቤትዋ : አድርሰው : ተሰናበትዋት ። ከዚያም : ወደ : ሆቴላቸው : ተመልሰው : ባለታክሲውን : ገንዘብ : ሰጥተው : ከምስጋና : ጋር : አሰናበቱት ።

ማታ : ራታቸውን : ከመመገባቸው : በፊት : ከአውቶቡስ : ተራ : ሄደው : ወደ : አውራጃቸው : የሚሄደውን : ተረኛ : ጠይቀው አገኙና : ሁለት : ቲኬቶች : አስቆርጠው : ለእሑድ : ጉዞአቸው : ሥፍራዎችን : ያዙ ። ከዚህ : በኋላ : እየተጨዋወቱ : ወደ : ሆቴላቸው : ተመልሰው : አደሩ ። ጥዋት : ልክ : በአሥራንድ : ሰዓት : ተኩል : የሚሄዱበት : አውቶቡስ : ወደ : ሆቴላቸው : መጥቶ : ድምፁን : አሰማ : እነርሱም : በሆቴሉ : ዘበኛ : ተቀስቅሰው : በአውቶቡሳቸው : ተሳፍረው : ወደ : አምሳለ : ገነት : መጡ ።

አቶ : በላይነህ : አዳፍሬ : ወደ : አምሳለ : ገነት : ከተመለሰ : በኋላ : ምንም : ያህል : ሳይቆይ : ወደ : አዲስ : አበባ : የመመለሻው: ቀን : ደረሰና : ቤተሰቦቹ : ሁሉ : ተጨነቁ ። ነገር : ግን : በሥራ : ላይ : ቀልድ : ወይም : እዩዩ : ገብተው : ለማስቀረት : አይችሉምና : እንግዲያውስ : ስንቅ : እናዘጋጅልህ : ቢሉት : ከምጥን : ቋንጣና : በርበሬ : በስተቀር : ምንም : እንደማያስፈልገው : ገለጸላቸው ። ይሁንና : በስንቅ : በኩል : እርሱ : በነገራቸው : ሲስማሙ : አንድ : ወይም : ሁለት : ነገሮች : ማዘጋጀት : አስፈላጊዎች : ሆነው : ታዩአቸው ። ስለዚህ : ሁለት : ታኒካ : ቅቤና : ሁለት : ታኒካ : ማር : በተጨማሪ : አዘጋጁለት ።

« እስኪ : አሁን : የቅቤውና : የማሩ : ድንቅርቅር : ምንድር : ነው ? እንዴትስ : አድርጌ : አሳፍሬ : ከአዲስ : አበባ : ላደርሰው : ነው ? » ብሎ : አቶ : በላይነህ : ቢነጫነጭ : ማን : ይስማው ? እንዲያው : ብቻ : ይጠቅምሃልን : ይዞ : ቀረ ። ቂጣውና : ንግግሮቹ : በከንቱ : ባከኑበት ።

እናቱ : ከባለቤቷ : ከአቶ : አዳፍሬ : ጋር : ተመካክራ : አንድ : ገረድ : ይዛ : ሄዳ : ቤቱን : በሥርዓት : አቋቁማለት : እንድትመለስ : ተዘጋጀች ። « አይሆንም : ተይ : እማዬ : ምንም : አይቸግረኝ : » እያለ : ቢያስረዳ : ፈጽሞ : የሚሰማው : አላገኝም ። ስለዚህ : እናትና ልጁ : አንድ : አሽከርና : አንዲት : ገረድ : አስከትለው : ዓርብ : ቀን

ከአምሳለ ፡ ገነት ፡ ተሳፍረው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ መጡ ። ደብረ ማርቆስ ፡ ሲደርሱ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ተቀበለቻቸውና ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አርፈውበት ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ሆቴል ፡ አመሩ ። ከሆቴሉ ፡ ደርሰው ፡ ዕቃቸውን ፡ አሳርፈው ፡ ቦታ ፡ እንደያዙ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ተሰናብታቸው ፡ ወደ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤቷ ፡ ተመለሰች ። እናቲቱ ፡ ስለሆቴል ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አታውቅም ፡ ነበርና ፡ የሆቴሉን ፡ ጌታ ፡ አቀባበልና ፡ የአሳላፊዎቹን ፡ መሽቆጥቆጥ ፡ ስታይ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተገረመች ። በወሬ ፡ የምትሰማውን ፡ ሁሉ ፡ ባለማመንዋ ፡ አሁን ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንግዳ ፡ ሆነባት ። ነገር ፡ ግን ፡ አስገራሚ ፡ ጥያቄዎችዋን ፡ በዝግታ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እየተቀበለ ፡ ልጅዋ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ ባስረዳት ፡ ጊዜ ፡ እያደር ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ መገንዘብ ፡ ጀመረች ። ራታቸውን ፡ በልተው ፡ እናትና ፡ ልጁ ፡ ጥቂት ፡ ደጅ ፡ ለደጅ ፡ ተንሸርሽረው ፡ ሲያበቁ ፡ ገብተው ፡ ተኙ ።

በማግሥቱ ፡ ቅዳሜ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ሰዓት፡ ሩብ ፡ ጉዳይ ፡ ድረስ ፡ በማስተማራቸው ፡ ደማሜ ፡ አልመጣችም ። በሰዓት ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ምሳዋን ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ልትሳተፍና ፡ ልትጨዋወት ፡ ስትል ፡ መጣች ። እናትና ፡ ልጁም ፡ ከበር ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ይጠብቋት ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ እንደደረሰች ፡ ተያይዘው ፡ መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ማረፊያቸው ፡ ሄደው ፡ አሥር ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ አረፉ ። ከዚህ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ቢጨዋወቱ ፡ ለአቶ ፡ በላይነህ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለው፡ ነበር ። ብቻ ፡ የምሳን ፡ ሰዓት ፡ ማስተላለፍና ፡ የሠራተኞችን ፡ የዕረፍት ፡ ሰዓት ፡ ማባከን ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ አሳስቦ ፡ ወደምግብ ፡ ቤቱ ፡ ሦስቱም ፡ ተያይዘው ፡ መጡ ። አዲስ ፡ ወደዳር ፡ ፈንጠር ፡ ያለች ፡ አነስተኛ ፡ ጠረጴዛ ፡ መርጠው ፡ ቁጭ ፡ እንዳሉ ፡ አንድ ፡ ሽቁጥቁጥ ፡ አሳላፊ ፡ መጥቶ ፡ የሆቴሉን ፡ ምግብ ፡ ዓይነቶች ፡ ዝርዝር ፡ እንደተለመደው ፡ አቀረበ ። እነርሱም ፡ እንደየፍላጎታቸው፡ በመረዳዳት ፡ ምግባቸውን ፡ እየመራረጡ ፡ በማስመጣት ፡ ከጣፋጭ ፡ ጨዋታ ፡ ጋር ፡ በዝግታ ፡ በሉ ። ቡናቸውን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ማረፊያቸው ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ እንዲመጣላቸው ፡ አዘው ፡ ከዚያው ፡ ተቀምጠው ፡ ጥቂት ፡ ተጨዋወቱ ፡ ከጨዋቶቹም ፡ አርእስት ፡ አንዱ ፡ የወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ መልመድና ፡ የትምህርት ፡ ጭብጥ ፡ ነበር ።



# ምዕራፍ ፡ ፳፮ ።

እንደተለመደው ፡ አምኃ ፡ የጀመረውን ፡ ሥራ ፡ ቀጠለ ። እንደዚሁም ከሰዓት ፡ በፊት ፡ ከአምሳለ ፡ ገነት ፡ አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ትምህርቶችን ፡ መማር ፡ ጀመረ ። ተግባራውያን ፡ ትምህርቶችን ፡ ግን ፡ በትርፍ ፡ ጊዜው ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ በፕሮግራም ፡ መሠረት ፡ ሊማራቸው ፡ አልቻለም ። ብቻ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እርሱም ፡ የሚያስተምረው ፡ የተግባር ፡ ትምህርት ፡ ስለሆነ ፡ በተግባር ፡ ትምህርት ፡ ረገድ ፡ እምብዛም ፡ አልተጎዳም ።

የቅኔና ፡ የዜማ ፡ ትምህርቱ ፡ ለአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ቅጽላው ፡ እጅግ በጣም ፡ ረዳው ። በተለይ ፡ በአማርኛ ፡ በኩል ፡ የድርሰትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከመከታተልና ፡ በአጻጻፉ ፡ ልምምድ ፡ ከማድረግ ፡ በስተቀር ፡ ከችሎታው ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ አልገጠመውም ። እንዲያውም ፡ የግዕዝ ፡ ዕውቀቱ ፡ ለእንግሊዝኛው ፡ ቋንቋ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ረዳው ። ከድሮ ፡ ወይም ፡ ከጥንት ፡ ቋንቆች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ አንዱን ፡ ያጠና ፡ እንደሆነ ፡ ለጥንት ፡ ቋንቆች ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ይሆንለታል ፡ እየተባለ ፡ እስከዛሬ ፡ ሲነገር ፡ የኖረው ፡ በዚህ ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ እውነተኛነቱን ፡ መሰከረ ። የእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ስለቀናው ፡ የቀሩትም ፡ ትምህርቶች ፡ ሁሉ ፡ እየገፉ ፡ ይሄዱ ፡ ጀመር። ለካስ ፡ ልጓማቸው ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ኖሯል ። ስለዚህ ፡ በሦስት ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የተሟላ ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርትን ፡ አጠናቅቆ ፡ ወደሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚያስተላልፈውን ፡ ፈተና ፡ ከምስጋና ፡ ጋር ፡ አለፈው ።

አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ «ዕድሜ ፡ ከገፋ ፡ በኋላ ፡ ትምህርት ፡ አይገባም ፤» እያሉ ፡ አዳሜን ፡ ሲያሰንፉ ፡ ልምጥምጥ ፡ አስተያየታቸውን፡ ጣጥሶት ፡ ብቅ ፡ ያለው ፡ አምኃ ፡ ፋርሽ ፡ አደረገባቸው ። ሰው ፡ መንፈሱን ፡ አንቅቶ ፡ አእምሮውን ፡አትክቶ ፡ ጆሮውን ፡ አቆቁሮ ፡ አንድ ሥራን ፡ ለማከናወን ፡ ከተነሣ ፡ ከድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ በስተቀር ፡ ሊያግደው ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ የለም ። እንደዚህ ፡ ያለውንም ፡ ተግባር ፡

፡ ግር ፡ የገፋፋው ፡ ቁርጠኛ ፡ መንፈስ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ ጀምሮ ፡ ፍጻሜ ፡ ሊያደርሰው ፡ የሚችል ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ራሱ ፡ መሥራት የማይችል ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ አንጻር ፡ እየተመለከተ ፡ « ሊሠራ ፡ አይቻልም ፡ » እያለ ፡ ዘለዓለም ፡ ሰውን ፡ ሲያሰንፍ ፡ ይኖራል ። እግዚአብሔር ፡ ከእንቅፋትነት ፡ የሚሰውረው ፡ ሰው ፡ ምንኛ ፡ የተባረከ ፡ ይሆን ! መንፈሱንና ፡ መላ ፡ ሰውነቱንስ ፡ በሥራ ፡ የጠመደለት ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ የታደለ ፡ ይሆን !

አምኃ ፡ መንፈሱ ፡ የረጋለት ፡ ደርባባ ፡ የሚያውቀውን ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ ዘወትር ፡ የሚጣጣር ፡ ከባልንጀሮቹና ፡ ከቤተሰቦቹ ፡ ጋር ፡ በመግባባት ፡ ተባብሮ ፡ የሚሠራ ፡ አዲስ ፡ ሥራን ፡ የመፍጠርና ፡ የማሳየት ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ በመንፈሳዊ ፡ ቅናት ፡ መላ ፡ ሰውነቱ ፡ ዘወትር ፡ እንደነደደ ፡ የሚኖር ፡ የኑሮን ፡ ትግል ፡ ለመቋቋም ፡ በቁርጠኛ ፡ መንፈስ ፡ የተነሣ ፡ መሰል ፡ ጎልማሳ ፡ ነው ። የልጁ ፡ ብልኅነት በየተግባሮቹ ፡ ሁሉ ፡ እየተገለጠ ፡ በመሄዱና ፡ ጠባዩም ፡ ባለመለወጡ ፡ ሰው ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ እየወደደውና ፡ እያከበረው ፡ ሄደ ። የቅኔ ፡ ትምህርቱ ፡ የማውጠንጠኛ ፡ አእምሮውን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ስለሳለውና ፡ የተግባር ፡ ዝንባሌው ፡ በብዙ ፡ ስለገፋፋው ፡ አስተያየቱንና ፡ ሥራውን ፡ እያመዛዘነ ፡ ይመራል ።

አምኃ ፡ ከሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ በተመላላሽነት ፡ መማርን ፡ መርጦ ፡ አቶ ፡ ደገፉም ፡ አንድ ፡ የግል ፡ ክፍል ፡ ሰጥተውት ፡ ሲማር ፡ የቤተሰቡንና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አገልግሎት ፡ በበለጠ ፡ ትጋት ፡ እያከናወነ ፡ በመሄዱ ፡ አንዳንድ ፡ ልጆችን ፡ አስወቀሰ ። ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ሥራውን ፡ በትጋት ፡ የሚያካሂደው ፡ የራሱ ፡ ተፈጥሮ ፡ ወይም ፡ ባሕርይ ፡ መርቆት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእርሱ ፡ ሥራ ፡ መጽሔትነት ፡ ሌሎቹ ፡ እንዲወቀሱ ፡ አይደለም ። ተወቃሾቹ ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ አምኃ ፡ በወላጆች ፡ እጦት ፡ ሰውነቶቻቸው ፡ ያልተነኩና ፡ መንፈሶቻቸው ፡ ያልተቀጠቀጡ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ እንደ ፡ አምኃ ፡ ካልሆኑ ፡ ተብሎ ፡ እምብዛም ፡ ሊወቀሱ ፡ አይገባም ። አደጋና ፡ ችግር ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የሚሰጡትን ፡ ትምህርት ፡ ምናልባት ፡ አንዳንድ ፡ ታላላቅ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ እንኳ ፡ አይሰጡም ፡ ይሆናል ። እነሆ ፡ አምኃን ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ስለው ፡ ያደረሱት ፡ አደጋ ፡ ችግር ፡ ትምህርትና ፡ የዘወትር ፡ ጥረት ፡ ናቸው ።



የወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ምክር ፡ አምኃን ፡ የትምህርት ፡ ተገዢ ፡ አደረገው ፡ ብለን ፡ ብንናገር ፡ ከአደጋ ፡ ከችግር ፡ ከዜማና ፡ ከቅኔ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ እንደዚሁም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎትና ፡ ከማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የተቀበላቸውን ፡ የትጋትና ፡ የሥራ ፡ መንፈስ ፡ መዘንጋት ፡ የለብንም ። አምኃ ፡ በማስተዋል ፡ ብዙ ፡ ነገሮችን ፡ ባይገነዘብና ፡ ከኑሮው ፡ ጋር ፡ እያዋሐደ ፡ ወይም ፡ እያነጻጸረ ፡ ዕለታዊ ፡ ኑሮውን ፡ ባይመራ ፡ አሁን ፡ ካለበት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ ያዳግተናል ። ከዚህም ፡ አያይዘን ፡ ስናስተነትን ፡ ብልኀት ፡ እንደገንዘብ ፡ በሣጥን ፡ ውስጥ ፡ የማይቆለፍ ፡ ዘወትር ፡ ሥሩብኝ ፡ የሚል ፡ የሰው ፡ ተፈጥሮታዊ ፡ መሣሪያ ፡ መሆኑን ፡ እንገነዘባለን ።

የአምሳለ ፡ ገነት ፡ አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሁለተኛ ደረጃ ፡ ትምህርትን ፡ ጨምሮ ፡ እንዲያስተምር ፡ ከተደረገ ፡ ወዲህ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ብዙ ፡ ነገሮችን ፡ አሻሽላለች ። የሣሙና ፡ የዘይት ፡ የልብስና ፡ የቃጫ ፡ ፋብሪኮች ፡ ተከፍተውባት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎችንና ፡ የሕዝብ ፡ ብዛትን ፡ ጨምራለች ። መንደርነትዋ ፡ ቀርቶ ፡ ወደ ፡ አነስተኛ ፡ ከተማነት ፡ ተለውጣለች ። ሱቆች ፡ ሆቴሎች ፡ በተጨማሪ ፡ አነስተኞች ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ የተመላላሽ ፡ መታከሚያዎችና ፡ ሆስፒታሎች ፡ መከፈት ፡ ጀምረዋል ። እነሆ ፡ አምኃና ፡ የአቶ ፡ በላይነህ ፡ እናት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተደነቁባቸው ፡ ነገሮች ፡ አሁን ፡ በተራነት ፡ በአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድና ፡ በአካባቢዋ ፡ ሁሉ ፡ ተለምደዋል ።

አምሳለ ፡ ገነት ፡ እያደገችና ፡ እየተስፋፋች ፡ መጥታ ፡ ከአነስተኛ ፡ ከተማ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ስለደረሰችና ፡ በዕድገት ፡ ስለተደሰተች ፡ ተከታዩን ፡ መዝሙር ፡ በለዘበ ፡ ድምፅዋ ፡ ትዘምራለች ።

## መዝሙረ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ።

ስንት ፡ ሺ ፡ ዘመናት ፡ ባዘን ፡ ተጨብጬ ፡
ዋ ፡ ዘመን ፡ መልካሙ ፡ ታየሁ ፡ ተገልጬ ።

ሀብቴ ፡ ድሮም ፡ ነበር ፡ በሆዴ ፡ ተረግዞ ፡
አዋላጆች ፡ ጠፍተው ፡ ምጤም ፡ ዘመን ፡ ጉዞ ።

ጊዜው ፡ ደረሰና ፡ ቢመጣ ፡ ትምህርት ፡
ከተፎ ፡ አዋላጆች ፡ ዘመንን ፡ ቀደሙት ፡፡

አይዞሽ ፡ አይዞሽ ፡ ብለው ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ቢይዙኝ ፡
ማዕድንና ፡ እርሻን ፡ መንቶችን ፡ ወለድኩኝ ፡፡

ልጆቼ ፡ ርቀውኝ ፡ በሆዴ ፡ ውስጥ ፡ ሳሉ ፡
ትምህርት ፡ ገለጻቸው ፡ ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡፡

ቡሩካን ፡ ሕፃናት ፡ መወለድ ፡ ያላቸው ፡
ዘመዴን ፡ አዝማዴን ፡ አግተለተሏቸው ፡፡

ትምህርት ፡ ብልኀቴ ፡ ትምህርት ፡ ሆዴ ፡
ትምህርት ፡ ሕይወቴ ፡ ትምህርት ፡ ጓዴ ፡

ከትቢያ ፡ አንሥተህ ፡ ስሜን ፡ አገነንኸው ፡
ሕዝቤን ፡ አነሣኸው ፡ ሕዝቤን ፡ አበላኸው ፡
ሕዝቤን ፡ አዛመድኸው ፡ አወዳጀኸው ፡
እግዚአብሔር ፡ ይክፈልህ ፡ ዋጋህ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡፡

## የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሠራተኞች ፡ መዝሙር ፡፡

እንደምን ፡ ነሽ ፡ ሥራ ፡ እንደምን ፡ ነሽ ፡ ሕይወት ፡
የወዝ ፡ ፍሬ ፡ እንዴት ፡ ነሽ ፡ መድኅነ ፡ ፍጥረት ?

ባንቺ ፡ ተንቀሳቅሰን ፡ ባንቺ ፡ ተረማምደን ፡
ሥራን ፡ ጀምረናል ፡ ከችግር ፡ ልንድን ፡፡

በጊዜ ፡ ወርቅነት ፡ በብልኀነት ፡ ትግል ፡
ድንቁርና ፡ ተሻር ፡ ከሥርህ ፡ ተመንገል ፡፡

ኑሮ ፡ ታብብልን ፡ በጣም ፡ ተሻሽላ ፡
በማዕድንና ፡ እርሻ ፡ ትዳሯን ፡ አብስላ ፡፡
መገላበጥ ፡ ቀረ ፡ መኮሳመን ፡ ቀረ ፡
ሥራ ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ ጤንነት ፡ ፈጠረ ፡፡



ተመስገን ፡ እግዚአብሔር ፡ የዓለማት ፡ ጌታ ፡
ከትቢያ ፡ እያነሣህ ፡ በሀብት ፡ እምትመታ ፡
በሥራ ፡ ለሚቀርብ ፡ አሳላፊ ፡ ተርታ ፡
ለእኛ ፡ ለድሆችህ ፡ ዘወትር ፡ ገበታ ፡፡

አምሳለ ፡ ገነት ፡ መጀመሪያውኑ ፡ ስትቆረቆር ፡ በአራት ፡ ማዕ
ዘን ፡ መልክ ፡ ተቀይሳ ፡ ስለነበር ፡ አሁን ፡ አድጋ ፡ መንገዶችዋ ፡ በድ
ንጋይ ፡ ሲነጠፉና ፡ በክስክስ ፡ ኮረቶች ፡ ሲዳመጡ ፡ እንዳችም ፡
ችግር ፡ አልፈጠረችም ፡፡ ማለት ፡ የድሆች ፡ ቤቶች ፡ እየፈረሱ ፡ መጉ
ላላት ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ አልመጣም ፡፡ «ግምት ፡ አነሰኝ ፡ ያውም ፡
ቢሆን ፡ በሰዓቱ ፡ አልደረሰኝም ፡» ማለት ፡ ፈጽሞ ፡ የለም ፡፡ እንደ
ዚሁም ፡ «እኔ ፡ ወራሽ ፡ ነኝ ፡ እገሌ ፡ ግን ፡ አይደለም ፡ ስለዚህ ፡
ግምቱ ፡ ለኔ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለእገሌ ፡ ወይም ፡ ለእገሊት ፡ መሆን ፡
አይገባውም ፡» የሚያስኙ ፡ ሁኔታዎች ፡ አልተፈጠሩም ፡፡

አም፡ኃና ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ አብረው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በማያጋቸው
ፍቅራቸው ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የጸና ፡ ሆነ ፡፡ አም፡ኃ ፡ የአጎቱን ፡ ልጆች ፡
መሻሻልና ፡ የራሱን ፡ ትምህርታዊ ፡ ዕድገት ፡ እየተመለከተ ፡ ለአም
ሳለ ፡ ገነት ፡ ባለውለተኛ ፡ የመሆን ፡ ስሜት ፡ እያደረበት ፡ ሄደ ፡፡ አም
፡ኃን ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በቤተሰባዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡
አንድ ፡ ጊዜም ፡ ችግር ፡ አልገጠመውም ፡ የማለት ፡ መንፈስ ፡ እንዳ
ያድርብን ፡ እሰጋለሁ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉም ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጡ ፡
በመሆናቸው ፡ አምሳለ ፡ ገነትን ፡ የበለጠ ፡ አስወደዳት ፡ እንጂ ፡ አላ
ስጠላትም ፡፡ ስለዚህ ፡ መንደሪቷ ፡ ወደ ፡ ከተማነት ፡ ስትለወጥ ፡ እር
ሱም ፡ በትምህርት ፡ አድጎ ፡ ከሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ስለደረሰ
ተደስቶ ፡ ኮራባት ፡፡

አንድ ፡ ቀን ፡ በከተማዋ ፡ መጸሕፍት ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ከውጭ ፡
አገር ፡ ተምሮ ፡ መጥቶ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የአስተዳደር ፡ ኢን
ስፔክተር ፡ የሆነና ፡ የአምስት ፡ ዓመታት ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ያለው ፡
ጎልማሳ ፡ ስለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ንግግር ፡ መስጠቱ ፡ በማስታወቂያ ፡
ወጣ ፡፡ አም፡ኃ ፡ እንደዚህ ፡ የመሳሰሉትን ፡ ነገሮች ፡ አጥብቆ ፡ ይከታ
ተል ፡ ስለነበር ፡ ሄዶ ፡ ለመስማት ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረገና ፡ በተወ
ሰነው ፡ ቀን ፡ ለባብሶ ፡ ወደ ፡ ተጠቀሰው ፡ አዳራሽ ፡ መጣ ፡፡

ኢንስፔክተሩ ፡ በከፍተኛ ፡ ባለጌጠኛ ፡ መስበኪያ ፡ ላይ ፡ ቆሟል ። እጀጠባብና ፡ ተፈሪ ፡ ቅድ ፡ ሱሪውን ፡ ደንቅሮ ፡ መርዶፉ ፡ ኮቱን ፡ ደርቧል ። በሥርዓት ፡ የተቆለፉት ፡ የደረቱና ፡ የእጁ ፡ ነጫጭ ፡ አዝራሮች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከኤሌክትሪክ ፡ ብርሃን ፡ ጋር፡ ይሳደባሉ ። በአንድ ፡ ድርብ ፡ ቀጭን ፡ ኩታ ፡ አደግድጎ ፡ ለማጋፈር ፡ የተዘጋጀ ፡ ቆፍጣና ፡ ሊጋባን ፡ መስሏል ።

ሰዎቹ ፡ አዳራሹን ፡ ሞልተውት ፡ በየመስኮቶቹ ፡ ላይ ፡ ተንጠላጥለዋል ። ኢንስፔክተሩ ፡ የአዳማጮቹን ፡ አቅጣጫ ፡ በሙሉ ፡ ለመጨበጥ ፡ ችሏል ። ንግግሩም ፡ እንዳይባክን ፡ የድምፅ ፡ ማጉሊያ ፡ ተደርጎለታል ፡ ከአዳማጮቹም ፡ አብዛኞቹ ፡ መካከለኛ ፡ ዕድሜ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። በስተቀር ፡ በመጠኑ ፡ ወጣቶች ፡ ጎልማሶችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ናቸው ።

## ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡

«ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ከምንስ ፡ የተገኘ ፡ ነው ? መሥራቹስ ፡ ማን ፡ ነው ? ምን ፡ ጥቅምስ ፡ አለው ? እንዴትስ ፡ እየተሻሻለ ፡ ሊሄድ ፡ ይችላል ?

እስኪ ፡ አሁን ፡ በጥያቄ ፡ መልክ ፡ የቀረቡትን ፡ አረፍተ ፡ ነገሮች ፡ በተራ ፡ እንመልከታቸው ።

አንደኛ ፤ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ማለት ፡ የጋራ ፡ ኑሮ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፤ እየተረዳዱ ፡ አብሮ ፡ መኖር ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሦስተኛ ፤ ከየራስ ፡ መብትን ፡ ቀንሶ ፡ በተወጣጣና ፡ ተወጣጥቶ ፡ አንድ ፡ መልክን ፡ በያዘ ፡ ፈቃደኛ ፡ መብት ፡ ሥር ፡ መተዳደር ፡ ማለት ፡ ነው ።

አራተኛ ፤ ተደጋግፎና ፡ ተረዳድቶ ፡ ሰዎች ፡ ሊያደርጉላችሁ ፡ የምትፈቅዱትን ፡ እናንተም ፡ እስተካክላችሁ ፡ አድርጉላቸው ፡ ያለውን ፡ ጠብቆ ፡ መኖር ፡ ነው ። አሁን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በአራት ፡ ላይ ፡ ተዘርዝረው ፡ የተሰጡት ፡ መግለጫች ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አይለያዩም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ባንዱ ፡ ያልተብራራልን ፡ ምናልባት ፡ በሁለተኛው ፡ ወይም ፡ በሦስተኛው ፡ ወይም ፡ በአራተኛው ፡ ሊብራራልን ፡ ይችላል ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ተገልጸዋል ።



ከዚህ ፡ በላይ ፡ በመጠኑ ፡ ስለ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ትርጉም ፡ ተናግረናል ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ በዝርዝር ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ እየተመለከትን ፡ እንድናውቀው ፡ ያስፈልጋል ። መጀመሪያ ፡ ቤተሰብ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ብንመለከተው ፡ ለወደፊቱ ፡ ርምጃችን ፡ በረዳትነት ፡ የሚያገለግለን ፡ ይሆናል ። ቤተሰብ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የተመሠረተው ፡ ከሁለት ፡ የግዕዝ ፡ ቃላት ፡ ነው ። እነርሱም ፡ ቤትና ፡ ሰብእ ፡ ናቸው ። ቤት ፡ በቁሙ ፡ በአማርኛ ፡ ተወርሰዋል ። ሰብእ ፡ የሚለውን ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ፊደል ፡ አጉድሎ ፡ ነው ፡ የወረሰው ። በአማርኛ ፡ ሰው ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሰብእ ፡ ከሚለው ፡ የግዕዝ ፡ ቃል ፡ ተሻሽሎ ፡ የተመሠረተ ፡ ይመስላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ገና ፡ ማረጋገጫ ፡ አላገኘሁለትም ። እንግዲህ ፡ ቤትና ፡ ሰብእን ፡ በአንዳንድ ፡ ነጠላ ፡ ትርጉም ፡ ከተረዳናቸው ፡ በአንድነት ፡ የሚሰጡትን ፡ ፍቺ ፡ ለመመልከት ፡ የሚያዳግተን ፡ ነገር ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ቤተሰብ ፡ ማለት ፡ የራስ ፡ ወገን ፡ ማለት ፡ ነው ። የራስ ፡ ወገንም ፡ ማለት ፡ የኔ ፡ ተብሎ ፡ በአንድነት ፡ የሚኖርና ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ የተሳሰረ ፡ ማለት ፡ ነው ። በቤት ፡ ሰውና ፡ በራስ ፡ ሰው ፡ ትርጉም ፡ መልክ ፡ ቢመለከቱት ፡ ያስኬዳል ። አንድ ፡ ቤተሰብ ፡ ስንል ፡ አባትን ፡ እናትን ፤ ልጆችንና ፡ የልጅ ፡ ልጆችን ፡ ጠቅልለን ፡ እንናገራለን ። አንድ ፡ አባት ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ወልዶና ፡ ልጆችን ፡ ድሮ ፡ በዙሪያው ፡ ወይም፡ በአጠገቡ ፡ ቢያሠፍራቸው ፡ የልጆቹና ፡ የልጅ ፡ ልጆቹ ፡ መሪ ፡ ይሆናል ። እንዚህ ፡ ባንድ ፡ አባት ፡ ምራት ፡ ኑሮአቸውን ፡ የሚቀጥሉ ፡ ልጆችና ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ እነሆ ፡ አንድ ፡ ቤተሰብን ፡ መሥራች ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ በአሁኑ ፡ ዘመን ፡ የቤተሰብ ፡ ትርጉም ፡ ከድሮው ፡ ጥቂት ፡ ጠበብ ፡ ብሎ ፡ ይታያል ። ቤተሰብ ፡ ስንል ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ በኅብረት ፡ እየተጋገዙ ፡ የሚኖሩትን ፡ ብቻ ፡ መወሰናችን ፡ ነው ። ይህንም ፡ ቤተሰብ ፡ የሚመሠርቱት ፡ ወላጆችና ፡ ልጆች ፡ እንደዚሁም ፡ በጥገኝነት ፡ ወይም ፡ በአገልጋይነት ፡ አብረው ፡ የሚኖሩት ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ አግብተው ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ የሚኖሩት ፡ ልጆች ፡ ከወላጆቻቸው ፡ ግንኙነት ፡ የላቸውም ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ወይም ፡ የልጆቹ ፡ ዝምድና ፡ ያንስባቸዋል ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ብቻ ፡ እነርሱም ፡ እንደወላጆቻቸው ፡ ቤተሰቦች ፡ መሥራቾች

ሆኑ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ትርጕም ፡ የቤተሰብን ፡ ሐረግ ፡ እየመዘዙ ፡ ከመኩራት ፡ አያግድም ። ማለት ፡ በጨዋነታቸው ፡ ወይም ፡ በአጥንተ ፡ ጥሩነታቸው ፡ ወይም ፡ በትምህርታቸው ፡ ወይም ፡ በጀግንነታቸው ፡ ወይም ፡ በአቅኚነታቸው ፡ ከመመካት ፡ የሚከለክል ፡ ነገር ፡ የለም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የእኛ ፡ ቤት ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ አይወድም ፡ ይህን ፡ ይንቃል ፡ ይህን ፡ ያከብራል ፡ እየተባለ ፡ የሚነገረውን ፡ ዘር ፡ ጠቀስ ፡ ክብር ፡ ለመናገር ፡ ይቻላል ።

ቤተሰብን ፡ በሌላ ፡ መልኩ ፡ ሲመለከቱት ፡ እንደገና ፡ ሰፋ ፡ ያለ ትርጕምን ፡ ሊያመጣ ፡ የሚችል ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። አንድ ፡ ቤተሰብ ፡ ከጎረቤቶቹ ፡ ጋር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ በመቀራረብ ፡ የኖረ ፡ እንደሆነ ፡ እገሌና ፡ እኔ ፡ ቤተሰብ ፡ ነን ፡ ይላል ። ትርጕሙም ፡ በጣም ፡ ከመዛመዳችን ፡ ወይም ፡ ከመቀራረባችን ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ቤተሰብ በመረዳዳትና ፡ በመደጋገፍ ፡ እንኖራለን ፡ ማለት ፡ ነው ። እነሆ ፡ አሁን ፡ የቤተሰብ ፡ ትርጕም ፡ ከሥጋ ፡ ዝምድና ፡ አልፎ ፡ አቀረቦች ፡ የኑሮ ፡ ዘመዳሞችን ፡ ሲያስተሳስር ፡ ይታያል ።

የአንድ ፡ ቤተሰብ ፡ መሪዎች ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ናቸው ፤ ከሁለቱም ፡ ዋናው ፡ መሪ ፡ ባል ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ባል ፡ በጣም ፡ በመምራቱ ፡ ላይ ፡ እየል ፡ ማለቱን ፡ ትቶ ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ በመመካከር ፡ ቤተሰቡን ፡ ቢመራ ፡ ምራቱ ፡ የሁለቱም ፡ ሆኖ ፡ የምራቱም ፡ ውጤት የጋራ ፡ ይሆናል ። ይህን ፡ አስተያየት ፡ የሚቀበሉና ፡ የማይቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ምናልባት ፡ መሳ ፡ ለመሳ ፡ አይሆኑም ፡ ይሆናል ፤ ማለት ፡ ለአንዱ ፡ ደኅና ፡ የሆነው ፡ ለሌላው ፡ ጎጂ ፡ መስሎ ፡ ይታየው ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ቁርጥ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ለመስጠት ፡ አይቻልም ። ነገር ፡ ግን ፡ የእኛ ፡ ዋና ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ አይደለም ። የአንድ ፡ ቤት ፡ አስተዳደር ፡ ባንድ ፡ ወይም ፡ በሁለት ፡ ሰዎች ፡ ቢመራ ፡ የእኛን ፡ አሳብ ፡ የሚያደናቅፍብን ፡ አይሆንም ።

የአንድ ፡ ቤተሰብ ፡ ሰዎች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተግባር ፡ ይዘው ፡ ኑሮአቸውን ፡ አሸንፈው ፡ ለመኖር ፡ ዘወትር ፡ በፕሮግራማቸው ፡ መሠረት ፡ ይሠራሉ ። አባት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የቀን ፡ ሥራውን ፡ ወደ ፡ ሚያከናውንበት ፡ ሲሄድ ፡ ምናልባት ፡ እናት ፡ በቤት ፡ ትውል ፡ እንደሆነ ፡ በአቀደችው ፡ ፕሮግራም ፡ መሠረት ፡ ሥራዋን ፡ ትጀምራለች ። ረዳት ፡ ገረድም ፡ እንዳለቻት ፡ ሥራዋን ፡ ከፍላ ፡ በማስረዳት ፡



ትሰጣታለች ። ምናልባት ፡ ለሥራ ፡ የደረሱ ፡ ልጆች ፡ እንዳሉ ፡ ልጆቹም ወደየሥራቸው ፡ ይሄዳሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ገና ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ ያሉትም ፡ እንደሆነና ፡ አሁንም ፡ ገና ፡ የጀመሩትም ፡ ቢሆኑ ፡ ሁሉም ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይሄዳሉ ። የወንድ ፡ አሽከርም ፡ ምናልባት ፡ ተቀጥሮ ፡ እንደሆነ ፡ አልጋችን ፡ ወደ ፡ ማንጠፍ ፡ ክፍሎችን ፡ ወደ ፡ ማጽዳት ፡ ልብሶችን ፡ ወደ ፡ ማጠብና ፡ ወደ ፡ መጥረግ ፡ ወደመተኮስም ፡ ወይም ፡ ወደሱቅ ፡ ሮጥ ፡ ብሎ ፡ ዕቃ ፡ ለመግዛት ፡ መላክም ፡ ሥራው ፡ ይሄዳል ። ምናልባት ፡ ተጧሪ ፡ እናትና ፡ አባት ፡ በዚሁ ፡ ቤት ፡ እንዳሉ ፡ ወንዱ ፡ አያት ፡ የደጃፍና ፡ የጓሮ ፡ አትክልት ፡ ሊመለካከቱና ፡ ሊለባኙ ፡ የፈረሰ ፡ አጥርንም ፡ ሊያቃኑ ፡ ወይም ፡ ሊያጠባብቁ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የማይሄዱትን ፡ ሕፃናት ፡ እያጫወቱ ፡ ሊያስተምሩ ፡ ይችላሉ ። በተለይ ፡ ተረታ ፡ ተረቶችን ፡ በመንገር ፡ ልጆችን ፡ ለማስደሰትና ፡ ትምህርትን ፡ ለማስወደድ ፡ ይችላሉ ። እጅግ ፡ በጣም ፡ ካላረጁም ፡ ጽሕፈትንና ፡ ንባብንም ፡ ለማስተማር ፡ ይችላሉ ። በፍቅርም ፡ ለመምራት ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታቸው ፡ ይፈቅድላቸዋል ። እንደዚሁም ፡ ሴት ፡ አያት ፡ ቢኖሩ ፡ ቤትን ፡ በመጠበቅ ፡ ሽንኩርትንና ፡ ድንችን ፡ በመላጥ ፡ የምድጃውን ፡ እሳት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በመቆሳቆስ ፡ የተቀደደ ፡ የልጆችን ፡ ልብስ ፡ በመጠቃቀም ፡ ይረዳሉ ። እንደወንዱ ፡ አያትም ፡ ለማስተማር ፡ ይችላሉ ።

አሁን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በጠቀስነው ፡ ቤተሰብ ፡ ውስጥ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ እንዳለው ፡ ገልጸናል ። እያንዳንዱም ፡ የቤተሰብ ፡ አባል ፡ የያዘው ፡ ሥራ ፡ ለቤተሰቡ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። አባትና ፡ እናት ፡ የቤተሰብ ፡ ገቢ ፡ ምንጭ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። የቀረው ፡ ቤተሰብ ፡ ደግሞ ፡ ገንዘቡ ፡ ሳይባክን ፡ በሥራት ፡ እንዲያገለግል ፡ የሚሠራ ፡ ነው ። ልጆች ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በመሄዳቸው ፡ ለቤተሰቡ ፡ ምንም ፡ የማይረዱ ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በሚያመጡት ፡ ትምህርት ፡ ሊረዱ ፡ ይችላሉ ። እንደዚሁም ፡ ከትምህርት ፡ መልስና ፡ ትምህርት ፡ በሌለባቸው ፡ ቀናት ፡ በቤት ፡ ሥራ ፡ ረገድ ፡ ወላጆቻቸውን ፡ ያገለግላሉ ። እንዲያውም ፡ አንዳንዶቹ ፡ በትርፍ ፡ ጊዜያቸው ፡ ሥራ ፡ ይዘው ፡ ራሳቸውንና ፡ ቤተሰባቸውን ፡ የሚረዱም ፡ አይታጡም ። ስለዚህ ፡ ጠንቃቃ ፡ ባለፕሮግራም ፡ ቤተሰብ ፡ ራሱን ፡ በሥራ ፡ ጠምዶና ፡ ኑሮውን ፡ አሸንፎ ፡ የመንግሥ




ቱንም ፡ ግብር ፡ በሰዓቱ ፡ ከፍሎ ፡ ደስታና ፡ ሐዘንን ፡ እያፈራረቀ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይኖራል ።

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተሰጠው ፡ ማስረጃ ፡ አንድ ፡ ቤተሰብ ፡ ኑሮውን ፡ እንዴት ፡ እንደሚመራ ፡ በመጠኑ ፡ ተብራርቷል ። አሁን ፡ በተነገረውም ፡ መሠረት ፡ የአንድ ፡ መንደር ፡ ቤተሰቦች ፡ በትጋት ፡ ቢሠሩና ፡ ራሳቸውን ፡ ቢያውሉ ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ብልጽግና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተሸጋግሮ ፡ በብዙ ፡ ቤተሰቦች ፡ ውስጥ ፡ ሊገኝ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ሲፈጠር ፡ በአንድ ፡ ቤተሰብ ፡ ወይም ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ይጠፋል ። ስለዚህ ፡ ጉልበት ፡ በከንቱ ፡ ሊባክን ፡ አይች ልም ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ሥራ ፡ አይወዘፍም ፤ ሥራ ፡ ካልተወዘፈ ፡ ጊዜ ፡ አይባክንም ። ጊዜም ፡ ካልባከነ ፡ አንዳች ፡ የሥራ ፡ ውጤት ፡ አይታጣም ። ስለዚህ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ኑሮ ፡ በሰላም ፡ ይቀጥላል ።

አንድ ፡ ቤተሰብ ፡ ችግሩን ፡ በቀላሉ ፡ ለማስወገድ ፡ ሊያቅተው ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ቤተሰቦች ፡ ወይም ፡ የአንድ ፡ መንደር ፡ ሰዎች ፡ በመረዳዳት ፡ የአንድን ፡ ቤተሰብ ፡ ችግር ፡ ሊያስወግዱ ፡ ይች ላሉ ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ በየተራ ፡ የቤተሰቦች ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ ይወገ ዳል ፤ ወይም ፡ ብዙዎቹ ፡ ችግሮች ፡ ተመሳሳዮች ፡ ይሆኑና ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የብዙ ፡ ቤተሰቦች ፡ ችግር ፡ ይቃለላል ። ይህን ፡ አስተሳሰብ ፡ ስንመለከተው ፡ ብዙ ፡ ቤተሰቦች ፡ የአንድ ፡ መንደር ፡ ቤተሰብን ፡ መሥራቾች ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ።

እንግዲህ ፡ የአንድ ፡ ቤተሰብ ፡ መሠረት ፡ ምን ፡ እንደሆነና ፡ ብዙ ፡ ቤተሰቦች ፡ አንድ ፡ መንደራዊ ፡ ቤተሰብን ፡ እንደ ፡ ሚመሠ ርቱ ፡ ተረድተናል ። ይህኑ ፡ አስተሳሰብ ፡ እያሳደግነው ፡ ብንቀጥል ፤ ብዙ ፡ መንደሮች ፡ አንድ ፡ አጥቢያዊ ፡ ቤተሰብን ፡ ይመሠርታሉ ። አሁንም ፡ ብዙ ፡ አጥቢያዎች ፡ አንድ ፡ ቀበሌያዊ ፡ ቤተሰብን ፡ ይመሠር ታሉ ። ብዙ ፡ ቀበሌዎችም ፡ በተራቸው ፡ አንድ ፡ ወረዳን ፡ ይመሠር ታሉ ። ብዙ ፡ ወረዶችም ፡ እንደዚህ ፡ አንድ ፡ አውራጃን ፡ ይመሠር ታሉ ። ሲያያዝ ፡ እያደገ ፡ በመጣው ፡ መሠረት ፡ አውራጆችም ፡ በተ ራቸው ፡ አንድ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛትን ፡ ይመሠርታሉ ። አሁን ፡ በመደ ምደሚያው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ አንድ ፡ መንግሥታዊ ፡ ቤተሰብን ፡ ይመሠርታሉ ።

አሁን ፡ እንዳደመጣችሁትና ፡ እንደተመለከታችሁት ፡

የአንድን ፡ መንግሥት ፡ አቋም ፡ የመሠረቱት ፡ ቤተሰቦች ፡ ናቸው ። እንግዲህ ፡ የቤተሰቦች ፡ እድገትና ፡ ውድቀት ፡ አንድ ፡ መንግሥትን፡ ሊጠቅመውና ፡ ሊጎዳው ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እያንዳንዱ ፡ ቤተሰብ ፡ ከቤተሰብ ፡ ተግባሩ ፡ እንዳይወጣና ፡ እንደጠፋው ፡ በግ ፡ የእረኛውን ፡ ጉልበት ፡ እንዳያባክን ፡ ተግቶ ፡ መሥራት ፡ አለበት ። እንደዚሁም ፡ ማለት ፡ ማናቸውም ፡ ቤተሰብ ፡ ራሱን ፡ በፕሮግራም ፡ ጠምዶ ፡ ለኑሮው ፡ የሚጠቅመውን ፡ ነገር ፡ እንዲሠራና ፡ ሠርቶ ፡ ካገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ለራሱ ፡ መገልገያ ፡ ሥራና ፡ ሠራተኞች ፡ የሚሆን ፡ ግብር ፡ እንዲከፍል ፡ ታላቅ ፡ ጥረት ፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። አንድ ፡ ሕዝብ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ቢፈጥር ፡ የመንግሥታዊ ፡ ቤተሰብ ፡ አመራር ፡ እጅግ ፡ በጣም፡ የተቃና ፡ ይሆናል ፡ » ሲል ፡ ኢንስፔክተሩ ፡ ንግግሩን ፡ ደመደመ ።

በዚያ ፡ የነበሩ ፡ አዳማጮች ፡ « ይህን ፡ እውነተኛና ፡ ቅንነት ፡ የተመላበት ፡ ንግግር ፡ ከወዴት ፡ አመጣው ? » ብለው ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደንቀው ፡ አመሰገኑት ።

አምኃ ፡ እውነቱ ፡ የኢንስፔክተሩን ፡ ንግግር ፡ በጥንቃቄ ፡ ተከታትሎት ፡ ነበርና ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡ አገኘበት ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

መቼም ፡ የሰው ፡ ዕውቀታዊ ፡ ደረጃ ፡ ሲያድግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ እየበዙና ፡ ክፍሎችና ፡ ደረጆችም ፡ እየጨመሩ ፡ መሄዳቸው ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለሥራ ፡ በጣም ፡ ምቹ ፡ ያልሆኑ ፡ ቦቶች ፡ ምቹቶችን ፡ እስኪያገኙ ፡ ድረስ ፡ የዕድገት ፡ አቅጣጫቸውን ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ይለውጣሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ተከለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የኮለጅነትን ፡ ሙሉ ፡ ደረጃ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ የማደግን ፡ ተግባር ፡ ያግዘው ፡ ነበር ። እነሆ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ሥራውን ፡ በጠቃሚነት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ መላልሶ ፡ በማስመስከሩ ፡ በትምህርት ፡ ዕድገት ፡ በአርት ፡ ትምህርት ፡ መጠን ፡ ትምህርትን ፡ (ዲግሪን ፡)



ለመስጠት ፡ እንዲችል ፡ የሁለት ፡ ዓመታት ፡ መቀጸያ ፡ ማዘገ ፡ ለትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ መጣለት ። ፕሬዚዳንቱ ፡ በማግሥቱ ፡ የትምህርት ፡ ቤቱን ፡ መምህራንና ፡ ተማሪዎች ፡ በትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ታላቅ ፡ አዳራሽ ፡ አሰብስቦ ፡ የጋራ ፡ ደስታቸውን ፡ የያዘችውን ፡ ደብዳቤ ፡ አነበበላቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግድግዳቹ ፡ እስኪሰነጠቁ ፡ ድረስ፡ ጭብጨቦች ፡ አስተጋቡ ። አዳራሹንም ፡ የደስታ ፡ አየር ፡ መላው ።

ፕሬዚዳንቱ ፡ « የእስከዛሬው ፡ የመምህራንና ፡ የተማሪዎች ፡ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ የክቡራን ፡ ገገርዎችና ፡ የፕሬዚዳንቱ ፡ ኅብረታዊ ፡ ተግባር ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ እያሳደገ ፡ አምጥቶ ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ካለበት ደረጃ ፡ ላይ ፡ አድርሶታል ። ለወደፊትስ ፡ ከእንዴት ፡ ያለ ፡ ምሳሌነትና ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ያደርሰው ፡ ይሆን ? በእኔ ፡ በኩል ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ የወደፊቱ ፡ ሥራችን ፡ ገልጾ ፡ ያስረዳልናል ፡ ስል ፡ እመልሳለሁ ፡ » ብሎ ፡ መልሱን ፡ ሰጠ ።

ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ በመምህራን ፡ ዕውቀታዊ ፡ ዕድገት ፡ ዘወትር ፡ የምታስብ ፡ ስለነበረች ፡ በአሁኑ ፡ ፕሮግራም ፡ በጣም ፡ ተደሰተች ። ነገር ፡ ግን ፡ ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ተመርቃ ፡ ሥራ ፡ የመያዝና ፡ በትዳር ፡ የመጠመድ ፡ ምኞት ፡ ስለነበር ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ቅር ፡ ሳትሰኝ ፡ አልቀረችም ። ለሁሉም ፡ ነገር ፡ አሳቧን ፡ ለአቶ ፡ ደገፉና ፡ ለአቶ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ መግለጽ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ታያትና ፡ የፕሮግራሙን ፡ ለውጥ ፡ የሚገልጹ ፡ ደብዳቤዎችን ፡ ጻፈች ።

አቶ ፡ ደገፉ ፡ ያላንዳች ፡ ማመንታት ፡ ፕሮግራሙን ፡ ፈጽማ ፡ መጠነ ፡ ትምህርትዋን ፡ እንድትቀበል ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑንና ፡ ይህም ለወደፊቱ ፡ ድካሟን ፡ በእጥፍ ፡ የሚመልስ ፡ መሆኑን ፡ ዘርዝሮ ፡ ጻፈላት ። ከዚህም ፡ እያይዞ ፡ የአባታቸው ፡ ገንዘብ ፡ ለአሁኑ ፡ ትምህርታቸውና ፡ ለወደፊት ፡ መቋቋሚያቸውም ፡ እንደሚበቃቸው ፡ አረጋገጠላት ። እርሱም ፡ በተጨማሪ ፡ በሚቸግራቸው ፡ ሁሉ ፡ የአባትነት ፡ ርዳታውን ፡ እንደማያቋርጥ ፡ ገለጸላት ። አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ግን ፡ ቅር ፡ እየተሰኘ ፡ ብትቀጥል ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ ጻፈላት ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያቀደውም ፡ ነገር ፡ በቶሎ ፡ እንደማይፈጸም ፡ በመገመት ፡ « ሰው ፡ ያስባል ፡ ፈጻሚው ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ » ሲልም ፡ በደብዳቤው ፡ ውስጥ ፡ ሳይጠቅስ ፡ አልቀረም ።

ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ የሁለቱንም ፡ ደብዳቤዎች ፡ መልስ ፡ ካገ

ኞች ፡ በኋላ ፡ ውሳኔ ፡ ማድረግ ፡ ቸግሯት ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ እንደቆሬ ፡ ውኃ ፡ በመዋለል ፡ ቆየች ፡፡ እንዲት ፡ የምትወዳት ፡ ባልንጀራዋ ችግርዋን ፡ ተመልክታ ፡ «ከሁሉም ፡ የሚበልጥብሽ ፡ የአንቺ ፡ ራስሽን ፡ በገዛ ፡ ራስሽ ፡ መቻል ፡ መሆኑን ፡ በጥንቃቄ ፡ መገመት ፡ ነው ፡፡ የቀረው ፡ ትርፍ ፡ ነው ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ይመጣል ፡» ስትል ፡ መክረቻትና ፡ ትምህርትዋን ፡ በተወሰነው ፡ ፕሮግራም ፡ መሠረት ፡ ለማከናወን ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረገችና ፡ የሁለቱን ፡ ዓመታት ፡ ትምህርት ፡ በሥራት ፡ አጠናቃ ፡ ዘለቀች ፡፡

ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ የመጨረሻውን ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መጠነ ፡ ትምህርትዋን ፡ (ዲግሪዋን) ፡ በከፍተኛ ፡ ማዕርግ ፡ ተቀበለች ፡፡ የምስክር ፡ ወረቀትዋን ፡ በተቀበለችበት ፡ ቀን ፡ የበዓሉ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ መከታ ፡ አምኃ ፡ እውነቱ ፡ ወይዘሮ ፡ ላቅሻቸው ፡ አቶ ፡ በላይነህና ፡ ሁለት ፡ ትንንሾች ፡ የአጎትዋ ፡ ልጆች ፡ መጥተው ፡ ነበር ፡፡ ንግግሮችና ፡ ጭብጨቦች ፡ ሲያስተጋቡ ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶችም ፡ ይነዙ ፡ ነበር ፡፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ አያሌ ፡ መምህራን ፡ በመመረቃቸው ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የከተማው ፡ ሕዝብና ፡ የምሩቃኑ ፡ ዘመዶችና ፡ ወዳጆች ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደሰቱ ፡፡ የትምህርት ፡ ችግርም ፡ በብዙ ፡ እንደሚቃለል ፡ ተስፋ ፡ አድርገው ፡ የበዓሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ፡፡

ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ «በየትኛው ፡ አውራጃ ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተደልድዬ ፡ ይሆን ?» እያለች ፡ ስትጨነቅ ፡ ሳለች በመተከል ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ከፍተኛ ፡ የአንደኛና ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መመደብዋን ፡ የሚያበሥር ፡ ደብዳቤ ፡ የጎጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ጻፈላት ፡፡ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ የደረሳት ፡ ወደ ፡ አምሳለ ገነት ፡ ከሄደች ፡ በኋላ ፡ ነበርና ፡ የአቶ ፡ ደገፉን ፡ ቤት ፡ በደስታ ፡ ባሕር ፡ አዋኘው ፡፡ በአምሳለ ፡ ገነት ፡ ከፍተኛ ፡ የአንደኛና ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የመደልደልዋ ፡ ወሬ ፡ በአቶ ፡ አዳፍሬም ፡ ቤት ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታን ፡ አስገኘ ፡፡ አቶ ፡ አዳፍሬ ፡ ከነባለቤታቸው ፡ መጥተው ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለሽ ፡ አሏት ፡፡

አቶ ፡ ደገፉ ፡ በዚሁ ፡ ክረምት ፡ ለልጆቹ ፡ አንድ ፡ ባላምስት ፡ ክፍል ፡ ቤት ፡ ሊሠራ ፡ ባቀደው ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ደንበኛ ፡ የግንብ ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ የእንጨት ፡ ቤት ፡ ሠሩላቸው ፡፡ ቤቱ ፡ ሁለት ፡ የመኝታ ፡ ክፍሎችን ፡ አንድ ፡ ሣሎንን ፡ አንድ ፡ የምግብ ፡ ቤትንና ፡ የሽንት ፡ ቤትን ፡ ይዟል ፡፡ ወጥ ፡ ቤቱና ፡ የዕቃ ፡ ቤቱም ፡ ከዋናው ፡ ቤት ፡ ሳይያያዝ ፡ ከቤቱ ፡ በስተኋላ ፡ በተገቢ ፡ ተመጣጣኝ፡ ርቀት ፡ ተሠርቷል ፡፡ በቤቱ ፡ ሥራ ፡ መላ ፡ ቤተሰቡ ፡ በብዙ ፡ ተጋግዞ ፡ ደክሞበታል ፡፡ ስለዚህ ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ በሥራ ፡ ተካፋይነታቸውና ፡ ከፍጻሜ ፡ እንዲደርስ ፡ በመድከማቸው ፡ ከልብ ፡ ተደሰቱ ፡፡

የቤቱ ፡ ቀለምና ፡ የማድቤቱ ፡ ጽዳት ፡ እንዳለቀ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜና ፡ አምኃ ፡ ለብቻቸው ፡ ጎጆ ፡ የሚወጡ ፡ መስሏቸው ፡ ነበር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ዝግጅት ፡ ለአሁኑ ፡ ጎጆ ፡ መውጣት ፡ አለመሆኑን፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ከራት ፡ መልስ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አስረዳቸው ፡፡ ቢሆንም ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ከመስከረም ፡ ጀምራ ፡ ስለምታስተምርና ፡ አምኃም ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ስላለበት ፡ ብቻ ፡ ቤቱን ፡ በመኝታና ፡ በጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ረገድ ፡ እንዲጠቀሙበት ፡ ፈቀዱላቸው ፡፡ ከእርሱም ፡ ልጆች ፡ አምኃና ፡ ደማሜ ፡ ከፈቀዱ ፡ እየሄዱ ፡ ለማጥናትና ፡ በዚያው ፡ ለመተኛት ፡ የማይቃወም ፡ መሆኑን ፡ ጨምሮ ፡ ገለጸላቸው ፡፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሦስቱ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ ተነሣና ፡ አንባጓሮን ፡ አበቀለ ፡፡ ሕፃናቱም ፡ ነገሩ ፡ በቡጢ ፡ የሚያልቅ ፡ መሰላቸውና ፡ ጥቂት ፡ ተቦጣቦጡ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ አምኃ ፡ በቶሎ ፡ ገላገላቸው ፡፡ አቶ ፡ ደገፉ ፡ ሕፃናቱን ፡ ለመቅጣት ፡ ቢያስብ ፡ የመጀመሪያው ፡ ጥፋት ፡ የእርሱ ፡ ሆነ ፡ ስለዚህ ፡ እንዲያው ፡ በደፈናው ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጥፋት ፡ እንዳይለመድ ፡ ብሎ ፡ ጠቅላላ ፡ ግሣጼውን ፡ ብቻ ፡ ወረወረ ፡፡

መስከረም ፡ ጠባ ፡ አደይ ፡ አበቦች ፡ ሁሉ ፡ በያለበት ፡ ፈኩ ፡ ዓለመ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ደምቆ ፡ መታየት ፡ ጀመረ ፡፡ እነሥራህ ፡ ብዙ ፡ የተባሉ ፡ ንቦች ፡ ከማንም ፡ የበለጠ ፡ በመደሰታቸው ፡ አበቦችን ፡ እየሳሙ ፡ ይመጠምጧቸው ፡ ጀመር ፡፡ ደስታ ፡ ደስታ ፡ ደስታ ፡ የሚለውንም ፡ ድምፅ ፡ አዕዋፍ ፡ ከያለበት ፡ በመምጣት ፡ ያሰሙና ፡ ያንጓርብቡ ፡ ጀመር ፡፡ እንስት ፡ ማሽላ ፡ ራሶች ፡ ማሰሪያቸውን ፡ ናቅ፡ አድርገው ፡ ጎፈሬ ፡ ራሶቻቸውን ፡ በተፈጥሮ ፡ አስከምከመው ፡ አበጣጠሩአቸው ፡፡ ብዙዎች ፡ ተክሎች ፡ ሳቁ ፡ ጉራማሌያውያን ፡ ጥርሶቻ

ቸውንም ፡ አሳዩ ። የበልግ ፡ ማሽላ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ አበራሮና ፡ ደንቀሌ ፡ ወንጭፎችን ፡ አበጁ ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ በያለበት ፡ ደመራ ፡ ደመራ ፡ ይል ፡ ጀመር ። ወጣቶቹ ፡ የጅራፍ ፡ ግርፊያ ፡ የችቦ ፡ ውጊያና ፡ ጭፋሮ ፡ ናፈቀን ፡ ይሉ ፡ ገቡ ።

ተማሪ ፡ ሁሉ ፡ በጋለና ፡ በታደሰ ፡ መንፈስ ፡ እስይ ፡ የትምህርት ቤቶች ፡ መከፈቻ ፡ ሊደርስልን ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ተደሰተ ። ያለፈውን ፡ ዓመት ፡ ትምህርቱንም ፡ ማስታወስ ፡ ጀመረ ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ተሜ ፡ ስለ ፡ ተከታተላቸው ፡ ልብ ፡ ወለዶችና ፡ የጥበብ ፡ ትምህርቶች ፡ መነጋገርና ፡ መከራከርን ፡ አመጣ ። ሰው ፡ በአዲሱ ፡ ዓመት ፡ አዲስ ፡ የሥራ ፡ ንቃትን ፡ ወልዶ ፡ ልብን ፡ በሚሞላ ፡ ተስፋ ፡ ተቀሰቀሰ ። ማናቸውም ፡ ነገር ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ይፈጸማል ፡ የሚለውንም ፡ ተስፋኛ ፡ ወሬ ፡ ተመካበት ። መምህራን ፡ ሁሉ ፡ የአለፈውን ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ እየተመለከቱ ፡ ለዚህ ፡ ዓመት ፡ አስፈላጊውን ፡ ፕሮግራም ፡ በየአርእስታቸው ፡ ማውጣት ፡ ያዙ ።

መጀመሪያ ፡ በብዙ ፡ ናፍቆት ፡ የተጠበቀው ፡ የደመራ ፡ በዓል ፡ ደረሰ ። ተራዳ ፡ የመሳሰሉ ፡ እንጨቶች ፡ ከእያንዳንዱ ፡ ቤተሰብ ፡ እየመጡ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ተረተርን ፡ ሠሩ ። ይህ ፡ በየአጥቢያው ፡ የተወሰነ ፡ የደመራ ፡ በዓል ፡ ካህናትን ፡ ሽማግሌዎችን ፡ ጎልማሶችን ፡ ወጣቶችንና ፡ ሕፃናትን ፡ ለአንድነት ፡ ጸሎት ፡ ያዘጋጃቸዋል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጫወታ ፡ ሰዎችን ፡ ከየመሰሎቻቸው ፡ ጋር ፡ አዋሕዶ ፡ እያዘፈነ ፡ ያስጨፍራቸዋል ። ደመራ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ተብሎ ፡ ምናልባት ፡ ብንጠየቅ ፡

አንደኛ ፡ አይሁዶች ፡ ሰውረውት ፡ የነበረው ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ መስቀል ፡ የተገኘበት ፡ ምልክት ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፡ የአንድነት ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እንመልሳለን ። እነሆ መስቀልን ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ እየተቀበልን ፡ በያመቱ ፡ እናስተናግደዋለን ።

መስከረም ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ደርሶ ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ በየቦታው ፡ ተከፈቱ ። መምህራንና ፡ ተማሪዎች ፡ የቢሮ ፡ ሠራተኞችም ፡ በሰዓቱ ፡ መጡ ። እንዳጋጣሚ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ እንድታስተምርበት ፡ የተመደበችበትና ፡ አምኃ ፡ የሚማርበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አንደኛንና ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃን ፡



ያጣመረ ፡ አንድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እነዚህ ፡ ሁለት፡ የሙታን ፡ ትራፊዎች ፡ ከአቶ ፡ ደገፉ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ በዚሁ ፡ በተከፈተበት ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ ሲያከቸክቹ ፡ ከተፍ ፡ አሉ ። ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ወደ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ስታመራ ፡ ልጆቹ ፡ ደግሞ ፡ ወደባልንጀሮቻቸው ፡ ሄደው ፡ ተቀላቀሉ ። ወዲያው ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ መምህራንና ፡ ተማሪዎች ፡ እንዲሰበሰቡ፡ ትእዛዝ ፡ አስተላለፈና ፡ ስብሰባው ፡ ከመ ፡ ቅጽበት ፡ ተከናወነ ። በስብሰባውም ፡ ላይ ፡ መምህራንና ፡ ተማሪዎች ፡ ከቍጥር ፡ ሳይጎድሉ ፡ በመመለሳቸው ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ በጣም ፡ መደሰቱን ፡ ገለጸ ። ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ ከራሱ ፡ ጀምሮ ፡ መምህራንና ፡ ተማሪዎች ፡ በበለጠ ፡ ትጋት ፡ መሥራት ፡ እንዳለባቸው ፡ አስረዳ ። በተለይም ፡ የአምሳለ ፡ ገነትና ፡ የአካባቢዎቿ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ መሰል ፡ ሞዴል ፡ የሚያደርጉት ፡ ይህን ፡ አጣማሪ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምሳሌነቱን እንዳያጣ ፡ በበለጠ ፡ ትጋት ፡ መሥራት ፡ የሁሉም ፡ ዓይነተኛ ፡ ዓላማ መሆኑንም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ደጋግሞ ፡ ተናገረ ። መምህራንና ፡ ተማሪዎችም ፡ አንገታቸውን ፡ ቀለስ ፡ በማድረግ ፡ ፈቃደኞች ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጸው ፡ የስብሰባው ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ።

ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ከስብሰባው ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ሥራ መሪው ፡ ቢሮ ፡ ተጠርታ ፡ ገባች ። ሥራ ፡ መሪው ፡ ቅድም ፡ የጀመረላትን ፡ የሥራ ፡ መልክ ፡ በመቀጠል ፡ በማናቸውም ፡ የማስተማር ፡ ችግር ፡ በኩል ፡ እንደሚረዳት ፡ በትሕትና ፡ ገልጾ ፡ የምታስተምርበትን ፡ ክፍል ፡ ጭምር ፡ የሚያመለክት ፡ የጊዜ ፡ ሠሌዳ ፡ ሰጣት ። ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ ትምህርቶች ፡ ሁሉ ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ መሄድ ፡ ስላለባቸው ፡ በተቻላት ፡ መጠን ፡ ከመጀመሪያው ፡ ተጠንቅቃ ፡ እንድትመራቸው ፡ አሳስቦ ፡ ወደክፍልዋ ፡ ራሱ ፡ እየመራ ፡ አመጣትና ፡ ከክፍልዋ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ አስተዋወቃት ። ቀጥሎም ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ የዚሁ ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ተወላጅ ፡ በመሆንዋ ፡ የአምሳለ ፡ ገነትን ፡ ችግር ፡ እንደምታውቅና ፡ በብዙ ፡ ለመርዳት ፡ እንደምትችል ፡ ገለጸላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሥራዋን ፡ እንድትቀጥል ፡ ፈቅዶላት ፡ ወደ ፡ ቢሮው ፡ ተመለሰ ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ባለፈው ፡ ክረምት ፡ አልመጣም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ሳለ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ በአም

ሳለ ፡ ገነት ፡ መመደብዋን ፡ ከራስዋ ፡ ደብዳቤ ፡ ተረድቶ ፡ ነበርና ፡ ሥራ ፡ የምትጀምርበትንና ፡ የሥራዋን ፡ ርምጃ ፡ የሚሰማበትን ፡ ጊዜ ፡ በናፍቆት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ። እርስዋም ፡ ይህንኑ ፡ ነገር ፡ ዐውቃ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ደፍጣ ፡ ሥራዋን ፡ ብቻ ፡ በትጋት ፡ ታከናውና ለች ። ይሁንና ፡ ስለጤንነታቸውና ፡ ስለኑሮአቸው ፡ ዘወትር ፡ መጻጻ ፋቸውን ፡ አላቋረጡም ።

የአስተማሪነትን ፡ ተግባር ፡ በተለይ ፡ በአሁኑ ፡ አያያዟ ፡ ከተለ ማመደች ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንደሚከተለው ፡ ጻፈችለት ።

አምሳለ ፡ ገነት ፡

ኅዳር ፡ — ፲፱ ፡ —— ዓ. ም.

ለክቡር ፡ ወንድሜ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡

ባያሌው ፡ እንደምን ፡ ሰንብተሃል ? እኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመ ስገን ፡ ደኅና ፡ ነን ። ዕረፍት ፡ አግኝተህ ፡ መጥተህ ፡ ትጎበኘናለህ ፡ ስንል ፡ ይኸውና ፡ እስካሁን ፡ ለመምጣት ፡ አልቻልህም ። ብቻ ፡ ለመ ምጣት ፡ ያልቻልኸው ፡ በሥራ ፡ ብዛት ፡ እንጂ ፡ በጤንነት ፡ መቃ ወስ ፡ ምክንያት ፡ አለመሆኑን ፡ በደብዳቤህ ፡ ስለተረዳን ፡ ከሥጋት ፡ ድነናል ።

በዚህ ፡ ያለነው ፡ ሁላችንም ፡ ደኅና ፡ ነን ። ሁላችንም ፡ ወደየሥ ራችን ፡ ተሠማርተን ፡ ውለን ፡ እንገባለን ። በማስተማር ፡ ሥራዬ ፡ ተደስቼበታለሁ ፡ ልጆቼም ፡ ትምህርትን ፡ እንደውኃ ፡ የተጠሙ ፡ ሆነው ፡ አግኝቻቸዋለሁ ። እኔም ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ትምህርቴን ፡ በሥርዓት ፡ እያዘጋጀሁ ፡ ሳስተምራቸው ፡ ይገባቸዋል ። ጥያቄዎች ንም ፡ ያኸርጎደጉዳሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርቱ ፡ የበለጠ ፡ ይበራላቸ ዋል ።

የክፍልና ፡ የቤት ፡ መልመጃችን ፡ እያዘጋጀሁ ፡ በሥራ ፡ ስመረ ምራቸው ፡ አብዛኞቹ ፡ ልጆች ፡ ከግምቴ ፡ በላይ ፡ ሆነው ፡ አገኛቸዋ ለሁ ። ስለዚህ ፡ ዘወትር ፡ በልጆቹ ፡ ትጋት ፡ በመደሰቴ ፡ ሥራዬ ፡ እየ ተቃናልኝ ፡ መሄድ ፡ ይዟዋል ። አንድም ፡ ልጅ ፡ ትምህርቱ ፡ በሚገባ መልከ ፡ ሳይገባው ፡ የሚሰጠውን ፡ ማስታወሻ ፡ በቃል ፡ እንዳያጠና ፡ ገና ፡ ማስተማር ፡ ስጀምር ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ተመካክሬበት ነበርና ፡ አሁን ፡ አልተቸገርሁበትም ። ስለዚህ ፡ በጠቅላላው ፡ የሥራዬን ፡ አመራር ፡ እኔን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቼንም ፡ አስደስቷል ።



ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳሳሰብሁህ ፡ የአሁኑን ፡ ሥራህን ፡ እንደያ ዝህ ፡ ወደ ፡ መተከል ፡ ብትዛወር ፡ ሁላችንም ፡ እንደሰትና ፡ በበለጠ ፡ መንገድ ፡ እንረዳዳ ፡ ነበር ። የአንተ ፡ ፈቃድ ፡ መሆኑንና ፡ አለመሆ ኑን ፡ እንጃ ፡ እንጂ ፡ በመንግሥት ፡ ፈቃድ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ምንም ፡ የሚያዳግት ፡ ነገር ፡ የለም ። ዛሬ ፡ አብዛኞቹ ፡ ወጣቶች ፡ ከመናገሻ ፡ ከተማችን ፡ መውጣት ፡ ስለማይፈቅዱ ፡ የአንተ ፡ ፈቅዶ ፡ ወደ ፡ ባላ ገር ፡ ለመዛወር ፡ ማሳሰብ ፡ ምንም ፡ ተቃዋሚ ፡ ነገር ፡ የሚፈጥር ፡ አይመስለኝም ። ስለዚህ ፡ ብትሞክር ፡ መልካም ፡ ይመስለኛል ።

ልጆቹና ፡ መላ ፡ ቤተሰቦቻችን ፡ የናፍቆት ፡ ሰላምታቸውን ፡ ያቀርቡልሃል ። ለአምኃ ፡ አንድ ፡ መጠነኛ ፡ የአልጀብራ ፡ መጽሐፍ ፡ ገዝተህ ፡ ብትልክለት ፡ ባለውለታህ ፡ እኔ ፡ መሆኔን ፡ አሳስብሃለሁ ። በል ፡ ደኅና ፡ ሁንልን ፡ በሰላምም ፡ ለመገናኘት ፡ ያብቃን ።

አክባሪ ፡ እኅትህ ፡

ደማሜ ፡ እውነቱ ፡

## ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

አምኃ ፡ እውነቱ ፡ በትምህርቱ ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ። እኅቱ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በቋንቋና ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ትምህርቶች ፡ በጣም ፡ እየረዳችው ፡ ስለገሠገሠ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ አንደኛ ውን ፡ ተርም ፡ እንደጨረሰ ፡ ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ትምህርት ፡ ተዛወረ ። ልጁ ፡ በቍጥር ፡ የተለየ ፡ ስጦታ ፡ አለው ። ስለዚህ ፡ በጥ በብ ፡ ትምህርት ፡ ውስጥ ፡ የፊዚክስ ፡ ጥናት ፡ ሊያግደው ፡ አልቻ ለም ። መቼስ ፡ አልጀብራና ፡ ጂዖሜትሪ ፡ የውኃ ፡ መንገድ ፡ ሆነውለ ታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የሚያግዱት ፡ የታሪክና ፡ የቅኔ ፡ ትምህርቶቹ ፡ ናቸው ።

ወደ ፡ ሦስተኛ ፡ ክፍል ፡ ከተዛወረ ፡ በኋላ ፡ የሚተኛባቸውና ፡ የሚጫወትባቸው ፡ ሰዓቶች ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የተወሰኑ ፡ ሆኑ ። ይሁ ንና ፡ በቤተሰብ ፡ አባልነቱ ፡ ድሮ ፡ ይፈጽማቸው ፡ የነበሩት ፡ ነገሮች፡ ፈጽመው ፡ አልተጓደሉበትም ። ብቻ ፡ እንቅልፍ ፡ አነሰው ፡ ባለፈው

ጊዜ ፡ ሊሠራው ፡ ይገባው ፡ የነበረውን ፡ እያስታወሰ ፡ ይቆጨውና ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ይነደው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ማሟላት ፡ ወይም ፡ ማጣጣት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ በብዙ ፡ ሥራና ፡ ጥናት ፡ ራሱን ፡ ጠመደ ። በአሁኑም ፡ ይዞታው ፡ ይታመማል ፡ ወይም ፡ ይሰለቻል ፡ እየተባለ ፡ ሲጠበቅ ፡ ከክፍሉ ፡ ልጆች ፡ አምስተኛ ፡ ሆነና ፡ ወደ ፡ አራተኛው ፡ ዓመት ፡ ክፍል ፡ እየተደሰተ ፡ ተዛወረ ። በሥራውም ፡ ጎረቤቶቹንና ፡ መላ ፡ ቤተሰቡንም ፡ አስደነቀ ።

ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ከምታስተምራቸው ፡ ልጆች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ አፍንጫ ፡ ጎራዳ ፡ ደመ ፡ ግቡ ፡ ጠይም ፡ ልጅ ፡ ከወ ደማሜ ፡ ዘንድ ፡ ትመጣጣ ፡ ነበር ። ይህች ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ አምኃ ፡ የትምህርት ጊዜ ፡ የባከነባት ፡ በመሆንዋ ፡ እጅግ ፡ በጋለ ፡ ትጋት ፡ የምትሠራ ፡ ልጅ ፡ ነች ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ወ/ ደማሜ ፡ የምትመላለሰው ። በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ከአምኃ ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ ወደ ፡ መተዋወቅ ፡ ደረሱ ። እንደዚሁም ፡ በበኩሉ ፡ በሚቸግራት ፡ ሁሉ ፡ ስለሚረዳት ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ መቀራረብ ፡ ጀመሩ ። በተለይ ፡ እርሱ ፡ ይረዳት ፡ የነበረው፡ በቋጥርና ፡ በቋንቋ ፡ በኩል ፡ ነበር ። በቀሩት ፡ ግን ፡ ወ/ ደማሜን ፡ ማስቸገሯን ፡ ቀጠለች ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ታላቁ ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ አጣማሪ ፡ ት/ ቤት ፡ ስፖርት ፡ የሚያሳይበት ፡ ቀን ፡ ደረሰና ፡ ተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ በስፖርቱ ፡ ሙያቸው ፡ ለመወዳደር ፡ ዕድል ፡ አገኙ ። ከነዚህም ፡ ዕድለኞች ፡ አንድዋ ፡ የትምህርት ፡ ጊዜ ፡ ያለፈባት ፡ ወይዘሪት ፡ እጅግ አየሁ ፡ ነበረች ። ይህች ፡ ልጅ ፡ ትምህርት ፡ እንደመውደድዋ ፡ መጠን ፡ እስፖርትንም ፡ በጣም ፡ አጥብቃ ፡ ትወዳለች ። እንዲያውም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በምትወረውራቸው ፡ ቃላት ፡ ወደፊት ፡ በእስፖርት ፡ ሴቶችን ፡ ለማስተማር ፡ የምትፈቅድ ፡ ትመስላለች ። ዝንባሌዋና ፡ ሥራዋ ፡ በመተባበራቸው ፡ ባልንጀሮቿ ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ይደነቁባት ፡ ነበር ። ይህች ፡ ልጅ ፡ በዚህ ፡ ውድድር ፡ አንደኛ ፡ ሆና ፡ በመሸለም ፡ ብዙ ፡ ወንዶችን ፡ አስናቀች ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በወሬ ፡ አርእስትነት ፡ ለአንድ ፡ ሳምንት ፡ ሕዝብን ፡ አገልግላለች ።

አምኃ ፡ እውነቱ ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ጎበዝ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ወይዘሪት ፡ እጅግአየሁ ፡ እስፖርትን ፡ ከሰውነቱ ፡ ጋር ፡ ያጣመረ ፡ ወጣት ፡ ወይም ፡ ጎልማሳ ፡ አይደለም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እስፖር



ተኞችን ፡ የማይወድ ፡ ሰው ፡ አይደለም ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከወይዘሪት ፡ እጅግአየሁ ፡ ጋር ፡ ለጥናት ፡ ጉዳይ ፡ በሚገናኙበት ፡ ጊዜ ፡ የስፖርትን ፡ ጠቃሚነት ፡ እያነሡ ፡ መጫወታቸው ፡ አልቀረም ። እነሆ፡ እነዚህ ፡ ልጆች ፡ በየምክንያቱ ፡ ሲጫወቱና ፡ ትምህርታቸውን ፡ ሲቀጽሉ ፡ ሳይታወቃቸው ፡ የጋራ ፡ ፍቅር ፡ በግርፋት ፡ አጠናገራቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንዲያው ፡ መተሳሰር ፡ እንዲያው ፡ ምክንያት ፡ መፈለግ ፡ ብቻ ፡ ሆነ ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ አጥንት ፡ ውስጥ ፡ እየገባ ፡ ማስቸገር ፡ መናገጃም ፡ መፈለግ ፡ ጀመር ፡ ጀመር ፡ ማድረግ ፡ ያዘ ።

አዬ ፡ ጉድ ! አቶ ፡ ፍቅር ፡ ሞኙ ፡ በነዚህ ፡ ልጆች ፡ ሥር ፡ ሊሰድ ነው ፡ እያደርም ፡ የተደላደለ ፡ ሥፍራንም ፡ ሊፈልግ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ አቶ ፡ ትምህርት ፡ ምን ፡ ሊበጀው ፡ ይሆን ? እንዲያው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሊሸነፍ ፡ ይሆን ? እንጃ ፡ እስኪ ፡ ሁሉንም ፡ ወደፊት ፡ ማየት ፡ ይሻላል ፡ መሰለኝ ። በመጀመሪያው ፡ ተርም ፡ በሚያስደስቱ ፡ ማርኮች ፡ ፈተናውን ፡ ያለፈው ፡ ልጅ ፡ በሁለተኛው ፡ ተርም ፡ በአነስተኛ ማርኮች ፡ ፈተናውን ፡ አለፈው ። መምህሮቹ ፡ ለየብቻ ፡ እየጠሩ ፡ ምን ፡ ችግር ፡ እንደገጠመው ፡ ቢጠይቁት ፡ ከመድከሙ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ እንደሌለበት ፡ ገለጸላቸው ። ለሰው ፡ የማይገልጹት ፡ ችግር ፡ የችግር ፡ ችግር ፡ ስለሆነ ፡ አምኃ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አዘነ ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ምሥጢሩን ፡ ለእኅቱ ፡ ገለጸላትና ፡ አጽናንታው ፡ አንድ ፡ ብልኀት ፡ እንደምትፈልግለት ፡ ተስፋ ፡ ሰጠችው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ እኅቱ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ብታጽናናው ፡ በራሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚጉላላው ፡ አሳብ ፡ ሊለቀው ፡ አልቻለም ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ እጅግ ፡ አየሁን ፡ በምክር ፡ ልትረዳት ፡ ፈለገችና ፡ እኔ ፡ ስማርም ፡ ሳስተምርም ፡ በትምህርት ፡ በኩል ፡ የሚገጥሙትን ፡ ችግሮች ፡ አጥንቻቸዋለሁ ። አሁን ፡ የአንቺ ችግር ፡ ከፊተኛው ፡ በጣም ፡ ተቃልዋል ። ስለዚህ ፡ ዘወትር ፡ መጠየቅ ፡ ልምድ ፡ እንዳይሆንብሽ ፡ በገዛ ፡ ራስሽ ፡ እንድትታገይ ፡ ያስፈልግሻል ። ብቻ ፡ በአሥር ፡ ወይም ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እኔን ፡ ወይም ፡ አምኃን ፡ እየጠየቅሽ ፡ ብትረጂ ፡ አይከፋም ። አለበለዚያም ፡ ከሆነልሽ ፡ ጨርሰሽ ፡ በገዛ ፡ ራስሽ ፡ ልትቀጽይ ፡ ትችያለሽ ፡ ብላ ፡ አስማምራ ፡ አስረዳቻት ። ወይዘሪት ፡ እጅግ ፡ አየሁም ፡ ነገሩ ፡

ገባትና ፡ የመጨረሻውን ፡ ተርም ፡ እንደምንም ፡ ብላ ፡ በመታገሥ ፡ ለማሳለፍ ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረገች ። ስለዚህ ፡ እንደተመከረችው ፡ በአሥር ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ብቅ ፡ እያለች ፡ ብዙ ፡ ሳትቆይ ፡ እልም ፡ ትል ፡ ጀመር ።

እምኃም ፡ እንደገና ፡ የሥራ ፡ መንፈሱ ፡ ስለተቀሰቀሰለት ፡ ልጅቱን ፡ እያደር ፡ ረሳ ፡ ያደርጋት ፡ ጀመር ። እንዲያውም ፡ የሥራ ፡ ብዛት ፡ ስለአዋከበው ፡ በባላት ፡ ቀናት ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ እየሄደ ፡ ያጠና ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ሁናቴ ፡ ላይ ፡ ከትምህርት ፡ ጋር ፡ ሲፋተግ ፡ ሳለ ፡ የአሥራሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ የመጨረሻ ፡ ፈተና ፡ ተቃረበ ። ስለዚህ ፡ በመጨረሻ ፡ ኃይል ፡ ጥናቱን ፡ ሲያርገበግበው ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡ ያሰኝ ፡ ነበር ። የእሁኑ ፡ አያያዝ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜን አላስደሰታትም ፡ ነበርና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ሰዓት ፡ በመጠበቅ ፡ ከሥራ ፡ ልትነጥለው ፡ ፈለገች ። ነገር ፡ ግን ፡ ማን ፡ ቢሰማ ፡ እንዲያው ፡ መታከት ፡ ሆነ ። ብቻ ፡ በመጨረሻ ፡ አየርን ፡ በሚሰነጥቀው ድምፅዋ ፡ እየዘመረች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ታሳርፈው ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደተመለከትነው ፡ እምኃ ፡ እውነቱ ፡ መልካም ፡ የዜማ ፡ ትምህርትን ፡ አግኝቷል ። ቀጥሎም ፡ በዘመናዊ ፡ ትምህርት ፡ ስልት ፡ ተለማምዶታል ። ስለዚህ ፡ መንፈሱ ፡ መጀመሪያ ፡ የተገራበትና ፡ የተኮተኮተበት ፡ ትምህርት ፡ ስለሆነም ፡ እንደሆን ፡ እንጃ ፡ የዜማ ፡ ነገር ፡ ሲነሣ ፡ መንፈሱ ፡ ይርዳል ። እነሆ ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ በመጠኑ ፡ አእምሮውን ፡ ልታሳርፍለት ፡ ወይም ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ ጊዜያት ፡ ልታድስለት ፡ ቻለች ።

ፈተናው ፡ ደረሰ ፤ የፈተና ፡ መቀበያው ፡ ፕሮግራም ፡ ወጥቶ ፡ ለየተፈታኞቹ ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ተሰጠ ። እነሆ ፡ የመውጣትና ፡ የማዘቀጥ ፡ አሳቦች ፡ በተራ ፡ ይመጡና ፡ ተፈታኞችን ፡ ይጎበኟሉ ። ቅሩ ፡ ቢሏቸው ፡ እሺ ፡ አይሉም ፤ እንዲያው ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። በየጊዜው ፡ እየመጡ ፡ መበጥበጣቸውን ፡ አይተውም ። ፈተናው ፡ ተጀመረ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አጃቢዎች ፡ እነ ፡ አቶ ፡ ሥጋት ፡ አሁን ፡ ሄደው ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሳይታሰቡ ፡ መጣ ፡ እያሉ ፡ ሁለት ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ከተፈታኞቹ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ሰነበቱ ። አስቸጋሪ ፡ ምጥ ፡ እንዳሠቃያት ፡ ሴት ፡ በእሳር ፡ በመከራ ፡ ተገላገሉ ። አቶ ፡ አሳብም ፡ መልኩን ፡ እየለወጠ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ የሚጫወተው ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡



ነው ? ወይ ፡ ጉድ ! ይገርማል ፡ እኮ ! የአሁኑ ፡ ሥጋት ፡ ደግሞ ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ ሠርተነው ፡ ይሆን ? እናልፈው ፡ ይሆን ? ወይስ ፡ እንወድቅ ፡ ይሆን ? ማለት ፡ ሆነና ፡ ቁጭ ፡ አለ ።

አንዳንዶቹ ፡ የማይርዱት ፡ ልበ ፡ ደንዳኖቹ ፡ ወይም ፡ ልበ ፡ ሙሉዎቹ ፡ ደግሞ ፡ ያልሠሩት ፡ አይገኝ ፤ የሠሩት ፡ ደግሞ ፡ አይቀር ፤ ስለዚህ ፡ ቢርበደበዱ ፡ ምን ፡ ይመጣል ? በበጎ ፡ ነገር ፡ በኩል ፡ ቢመለከቱት ፡ የሚያተርፈው ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ የለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አካላትን ብቻ ፡ እንደ ፡ ቅንቅን ፡ እየበላ ፡ ይጨርሰዋል ። ስለዚህ ፡ ስጋት ፡ የሰውነት ፡ መጨረሻ ፡ ከሆነ ፡ ስለምን ፡ ፈቅደን ፡ ለእንግድነት ፡ ቦታ ፡ ሰውነታችንን ፡ እናዘጋጅለታለን ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ያጽናኑታል ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ እንደሌሎቹ ፡ ልጆች ፡ አይምሸከሸኩም ።

የፈተናው ፡ ውጤት ፡ በሚነገርበት ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አቅራቢያ ፡ ተሰበሰቡ ። በናፍቆትም ፡ የዲሬክተሩን ፡ መምጣት ፡ ሲጠባበቁ ፡ ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አቅራቢያ ፡ አንድ ፡ በሞተር ፡ ቢስክሌት ፡ የሚከንፍ ፡ ሰው ፡ ዲሬክተሩን ፡ እንደገጫቸውና ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ እንደጣላቸው ፡ ተሰማ ። ወዲያው ፡ ምክትል ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ማናቸውም ፡ ሥራ ፡ እንደተለመደው ፡ እንዲመራ ፡ ለአንድ ፡ ለታፈረ ፡ መምህር ፡ አደራውን ፡ ሰጥቶ ፡ ወደ ፡ አደጋው ፡ ሥፍራ ፡ እየሮጠ ፡ መጣ ። እንደመጣም ፡ በቶሎ ፡ አገላብጦ ቢመለከታቸው ፡ ጉዳቱ ፡ ለሞት ፡ የሚያሠጋ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘውም ። ነገር ፡ ግን ፡ በቶሎ ፡ ወደ ፡ ሆስፒታል ፡ ይዟቸው ፡ ሄደና ፡ ከምርመራ ክፍል ፡ አደረሳቸው ። ሐኪሞቹም ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምረው ፡ «ለሞት ፡ ወይም ፡ ለአካለ ፡ ጎደሎነት ፡ የሚያደርስ ፡ አደጋ ፡ አላገኛቸውም ። ብቻ ፡ አሁን ፡ ለጊዜው ፡ ሲወድቁ ፡ የአወዳደቁ ፡ ኃይል ፡ ሰውነታቸውን ፡ በሙሉ ፡ ስላናወጠው ፡ እየታከሙ ፡ ለብቻቸው ፡ ማረፍ ፡ ያስፈልጋቸዋል ፡» ብለው ፡ ባንድ ፡ በተለየ ፡ ክፍል ፡ አስተኟቸው ።

የአሥራሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ልጆች ፡ የራሳቸውን ፡ ጉዳይ ፡ ረስተው ፡ ጭንቀታቸውንና ፡ ሐዘናቸውን ፡ ወደ ፡ ዲሬክተሩ ፡ አደጋ ፡ አዞሩት ። ዲሬክተሩም ፡ ድነው ፡ እስኪወጡ ፡ በየቤታቸው ፡ የግል ፡ ሥራቸውን ፡ እየሠሩ ፡ ተቀመጡ ። ወደ ፡ ሆስፒታልም ፡ እየመጡ ፡

ባንድነት ፡ ማስታወሻቸውን ፡ እየሰጡ ፡ ይመለሱ ፡ ጀመር ። በእግዚ
አብሔር ፡ ቸርነትና ፡ በሐኪሞቹም ፡ የዘወትር ፡ ርዳታ ፡ ባሥር ፡ ቀና
ቸው ፡ ድነው ፡ ከሆስፒታል ፡ ወጡ ። ከቤት ፡ ሆነው ፡ እንዲያርፉ ፡
ከሐኪሞች ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብለው ፡ ነበርና ፡ ሃያ ፡ ቀናት ፡ሙሉ ፡ ከሚ
ወዱት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ተለይተው ፡ ሰነበቱ ። ነገር ፡ ግን ፡ የአሥራ ፡
ሁለተኛን ፡ ልጆች ፡ የፈተና ፡ ውጤት ፡ በእምቦልብ ፡ እያደረጉ ፡ ለእ
ያንዳንዱ ፡ ልጅ ፡ ላኩለት ። ከአምሳ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ዐሥር ፡
ልጆች ፡ ከማለፊያው ፡ አልደረሱም ። ከቀሩትም ፡ አራቱ ፡ እንደገና ፡
በአንዳንድ ፡ ትምህርት ፡ ጠንካራ ፡ ፈተና ፡ እንደሚሰጣቸው ፡ ተገለ
ጸላቸው ። ሠላሳ ፡ ስድስቱ ፡ ግን ፡ በሚገባ ፡ ፈተናውን ፡ አልፈው
ታል ። ከአለፉትም ፡ አምስቱ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ በአሰኘ ፡ ማዕርግ ፡ አል
ፈዋል ።

አምኃ ፡ እውነቱ ፡ ፈተናውን ፡ ካለፉት ፡ ልጆች ፡ አንዱ ፡ ነው ።
እርሱም ፡ በፈተናው ፡ ከመጀመሪያው ፡ አሥሩ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡
ተወዳድሮ ፡ ስምንተኛ ፡ ማዕረግ ፡ በማግኘቱ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተገር
ሟል ። ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ የአምኃ ፡ በፈተና ፡ መሸቀንጠርና ፡ ያገ
ኘውን ፡ ማዕርግ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተደነቀች ። በምክርዋም ፡
እንደጠቀመችው ፡ ተረዳች ። እንደዚሁም ፡ መላ ፡ ቤተሰቡ ፡ ልጁ ፡
ክፍል ፡ ዘልሎ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ማዕርግ ፡ ፈተናውን ፡ በማለፉ ፡
ተገረመ ። አምኃ ፡ አሁን ፡ ባለበት ፡ የትምህርት ፡ ዕድገት ፡ ላይ ፡
ሦስት ፡ ትምህርታውያን ፡ ደረጆችን ፡ ማለፉ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ አን
ደኛ ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ በኩል ፡ ዜማንና ፡ ቅኔን ፡ ሁለተኛ
የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርትን ፡ ሦስተኛ ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህ
ርትን ፡ ማከናወኑ ፡ ነው ።

ወይዘሪት ፡ እጅግ ፡ አየሁም ፡ ታታሪ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ነበረች ፡ በዚሁ
ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የስምንተኛውን ፡ ዓመት ፡ ፈተና ፡ አራግ
ፋው ፡ ብቅ ፡ አለች ። ይህችም ፡ ልጅ ፡ በወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ምክር ፡
በጣም ፡ ተጠቅማለች ። ዘወትር ፡ የልጆችን ፡ ዓይን ፡ በማጭለግ ፡
ፈንታ ፡ መንፈስዋን ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ አዞራለች ። ይህች ፡ ልጅ ፡
እንደ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ በተከለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህራን ፡ ማሠል
ጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትምህርትዋን ፡ አከናውና ፡ መምህር ፡ ለመ
ሆን ፡ አስባለች ።



አምኃና ፡ ወይዘሪት ፡ እጅግአየሁ ፡ ከፈተናቸው ፡ በኋላ ፡ እንደ
ገና ፡ የተቋረጠውን ፡ ፍቅራቸውን ፡ አድሰው ፡ በመጠኑ ፡ ብን ፡ ማለ
ትን ፡ ጀመሩ ። በአሁኑ ፡ ፍቅር ፡ ውስጥ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ተደሰ
ተች ፡ እንጂ ፡ ለማቋረጥ ፡ ፈጽማ ፡ አልሞከረችም ። ይሁንና ፡ መፈራ
ትና ፡ አክብሮት ፡ የበለጠ ፡ እየተጨመረላት ፡ ሄደ ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ ደገፉ ፡ ስለመዛወሩ ፡ ጉዳይ ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡
ያህል ፡ ደጅ ፡ ከጠና ፡ በኋላ ፡ ባሰበው ፡ መንገድ ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡
ከንቲባ ፡ ሆኖ ፡ ተሾመ ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙት ፡ ባልንጀሮቹ ፡
ሁሉ ፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ አሁን ፡ ካለበት ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ ተወርውሮ ፡
በአነሰ ፡ የሥራ ፡ መደብ ፡ ላይ ፡ መቀመጡ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡
ነው ? እያሉ ፡ በጣም ፡ ተጉተመተሙ ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የአምሳለ ፡
ገነትን ፡ ዕድገት ፡ ፈጽመው ፡ ያላጠኑና ፡ አገራቸውን ፡ በሥርዓት ፡
ያልተማሩ ፡ ይመስላሉ ፡ በማለት ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ሳይነቅፏቸው ፡
አልቀሩም ። አንድ ፡ ቀን ፡ አቶ ፡ በላይነህን ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለህ ፡
ለማለት ፡ ከመጡ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ። ክርክሩም ፡
የለም ፡ ጠፎቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠረፎች ፡ መጀመሪያ ፡ መቅናት ፡
ይገባቸዋል ። የለም ፡ ያው ፡ ማኸሉ ፡ የዝንጀሮው ፡ አገር ፡ መጀመሪያ
መሻሻል ፡ አለበት ፡ የሚያሰኝ ፡ ነበር ።

የለም ፡ ጠፍ ፡ ማቅናትን ፡ ደጋፊዎች ፡

፩ ፡ አቶ ፡ ቀለሙ ፡ ዘለቀ ፡

፪ ፡ አቶ ፡ መራጉት ፡ መንግሥቱ ፡

፫ ፡ አቶ ፡ መልአኩ ፡ አሻግሬ ፡

የተበላ ፡ ማሻሻልን ፡ ደጋፊዎች ፡

፩ ፡ አቶ ፡ ይጥና ፡ የኔነህ ፡

፪ ፡ አቶ ፡ ድንበሩ ፡ ዋሲሁን ፡

፫ ፡ አቶ ፡ መክት ፡ ሰጠኝ ፡

አንድ ፡ አስታራቂ ፡ ሽማግሌ ፡

አቶ ፡ ቀለሙ ፡ ዘለቀ ፡

ሰው ፡ በተፈጥሮው ፡ ለኑሮው ፡ የሚመችውን ፡ ቦታ ፡ የመም
ረጥ ፡ ስጦታ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ በመፈጠሩ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡
ሲለኝ ፡ አያቶቼና ፡ ቅድም ፡ አያቶቼ ፡ የኖሩበትን ፡ ቦታ ፡ ለቅቄ ፡ በኢ

ትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ተዘዋውሬ ፡ መልካም ፡ ሥፍራዎችን ፡ አልመርጥም ፡ የሚለውን ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ስሰማ ፡ አንጀቴ ፡ ያራል ። አባቶቻችን ፡ ያልተገላበጠ ፡ ያራል ፡ እያሉ ፡ የሚተርቱት ፡ ምሳሌ ፡ የሚያያገለግለው ፡ ለጕሮ ፡ ብቻ ፡ ይሆን ? በእኔ ፡ አስተያየት ፡ አይደለም ።

ይህም ፡ ይቅርና ፡ ኢትዮጵያስ ፡ ማለት ፡ በተለይ ፡ ማኸል ፡ አገራችን ፡ ብቻ ፡ ነውን ? አይመስለኝም ። እንግዲያስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምንለው ፡ አገር ፡ ከጠረፍ ፡ እስከ ፡ ጠረፍ ፡ ያሉትን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ አውራጃች ፡ ወረዳች ፡ ቀበሌዎች ፡ አጥቢያዎችና ፡ መንደሮች እንደዚሁም ፡ ሰው ፡ በመሥፈር ፡ ገና ፡ ያላቀናቸውን ፡ ጭምር ፡ ከሆነ ለምን ፡ እየተዘዋወርን ፡ አቅንተን ፡ በሀገራችን ፡ ሀብት ፡ አንጠቀምም ? ብለን ፡ ራሳችንን ፡ ብንጠይቅ ፡ መልሱ ፡ ምን ፡ ይሆን ?

አቶ ፡ ይጥና ፡ የኔነህ ፡

በእንግሊዝኛ ፡ «ተንከባላይ ፡ መርግ ፡ ሽበቱን ፡ እንደያዘ ፡ ለመቆየት ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ሽበትን ፡ ለማውጣት ፡ አይችልም ፡ እየተባለ ፡ ይነገራል ፡» ሲሉ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሁላችንም ፡ ሰምተናል ። እንደዚሁም ፡ ከቦታ ፡ ቦታን ፡ በማማረጥ ፡ የሚንቀዋለል ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ መሠረታዊ ፡ መኖሪያን ፡ ለማደራጀት ፡ ስለሚያቅተው ፡ ተዘዋዋሪ ፡ አሞራን ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ ዛሬ ፡ አዲስ ፡ መስሎ ፡ ይታይ ፡ እንጂ ፡ ጥንታውያን ፡ አባቶቻችን ፡ ሲጠቀሙበት ፡ የቆየ ፡ አሳብ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሄዶ ፡ አዲስ ፡ አገርን ፡ ወይም ፡ ጠረፍን ፡ ማልማት ፡ የሚባለው ፡ አማርኛ ፡ የአባቶቻችንን ፡ አሳብ ፡ በጣም ፡ አጥብቆ ፡ የሚቃረን ፡ ነው ። ቢሆንስ ፡ የዱር ፡ አራዊትን ፡ ማጥፋት ፡ ይገባልን ? እግዚአብሔር ፡ ለእኛ ፡ ጸጋውን ፡ ሲሰጠን ፡ ጊዜ ፡ ቆላ ፡ ቆላውን ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወይና ፡ ደጎችን ፡ ለነዝሆን ፡ ለእኔ ፡ እንበሳ ፡ ለእነቀጭኔና ፡ ለእነጎሽ ፡ መልቀቅ ፡ አይገባንምን ?

ስለዚህ ፡ ይህንኑ ፡ ያለንበትን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቢያንስብን ፡ ወይም ፡ ቢደኸይብን ፡ በመጠኑ ፡ በትንንሹ ፡ እየተከፋፈልንና ፡ እያዳበርን ፡ መኖር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንስሳቱንና ፡ አራዊቱን ፡ እየተቃወምን ፡ ቦታን ፡ አስለቅቀን ፡ ማባረርና ፡ ማጥፋት ፡ የሚገባን ፡ አይመስ



ለኝም ። ሰው ፡ በሥጋዊ ፡ ሰውነቱ ፡ እንስሳ ፡ መሆኑን ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ይረሳል ? እርግጥ ፡ ነው ፡ እንስሳት ፡ የተፈጠሩት ፡ ለሰው ፡ አገልግሎት ፡ ነው ። ይህንም ፡ አስተሳሰብ ፡ የሚክድ ፡ ሰው ፡ የለም ። ታዲያ ፡ እነዚህ ፡ እንስሳት ፡ ካልኖሩና ፡ ኑረውም ፡ ካልበሉ ፡ ለመኖርና ፡ ሰውን ፡ ለማገልገል ፡ ፈጽሞ ፡ አይችሉም ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እየተመለከትን ፡ የያዝነውን ፡ በማሻሻል ፡ ፈንታ ፡ ስለምን ፡ እንስሳትንና ፡ አራዊትን ፡ ለመቀማት ፡ እንመኛለን ?

አቶ ፡ መራኁት ፡ መንግሥቴ ፡

በታሪክ ፡ እንዳጠናነውና ፡ ከአባቶቻችንም ፡ እንደሰማነው ፡ የድሮውና ፡ የዛሬው ፡ ኑሮ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የተለያየ ፡ ነው ። የድሮ ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነበር ፡ እንደዚሁም ፡ ፍላጎታቸው ፡ ከቀበሊያቸው ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አያልፍም ፡ ነበር ። ማለት ፡ በትንሽ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ዘመናዊውን ፡ የሰውነት ፡ አጠባበቅ ፡ ባለማወቃቸው ፡ በሽሮና ፡ በእንጀራ ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቆሎንና ፡ ንፍሮን ፡ በመቀላቀል ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ቅቤን ፡ ሥጋንና ፡ ወተትን ፡ እንደዚሁም ፡ ዕንቁላልን ፡ የሚአገኙትና ፡ የሚጠቀሙበት ፡ ሰዎች ፡ ቍጥር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ጥሩ ፡ ሥረተ-ሰውነትንና ፡ አእምሮን ፡ ከተመዛዘነ ፡ ባሕርይ ፡ ጋር ፡ ይዞ ፡ ለመገኘት ፡ የሚቻለው ፡ መልካም ፡ ኑሮ ፡ በተጠበቀ ፡ ሰውነት ፡ ስለሆነ ፡ በእንጀራ ፡ በሽሮ ፡ በቆሎና ፡ በንፍሮ ፡ ብቻ ፡ ለመወሰን ፡ የማይቻል ፡ እየሆነ ፡ መሄድ ፡ ያዘ ። በዚሁም ፡ አንጻር ፡ የልብስ ፡ ደረጃ ፡ እያደገ ፡ ሄደ ። ስለዚህ ፡ በትንሹ ፡ ሠርቶ ፡ ይበቃኛል ፡ የሚለው ፡ አማርኛ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ተሻረ ።

ድሮም ፡ አባቶቻችን ፡ አንድ ፡ ላንድ ፡ ይዘውት ፡ የነበረው ፡ መሬት ፡ ዛሬ ፡ ለብዙዎች ፡ ሲተነተን ፡ በጣም ፡ እያነሰ ፡ ሄደ ። እንደዚሁም ፡ ከመሬቱ ፡ ሽንሽን ፡ ጋር ፡ የመሬቱ ፡ ቅባት ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ አነሰ ። በማከር ፡ በማዳበር ፡ በማሳረፍም ፡ በኩል ፡ የሚደረገው ፡ ጥረት ፡ መሬቱ ፡ ከሚሰጠው ፡ አዝመራ ፡ ጋር ፡ አልወዳደር ፡ አለ ። ታዲያ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ ሲፈጠር ፡ ሰው ፡ የድካሙን ፡ ዋጋ ፡ በማትረፍረፍ ፡ የሚያገኝበት ፡ መንገድ ፡ ፈልጎ ፡ ጠፍ ፡ ሥፍራ

ዎችን ፡ ቢያቀና ፡ ምን ፡ የሚያስደንቅና ፡ የሚያስገርም ፡ ነገር ፡ ሊኖር ይችላል ? እንስሳትና ፡ አራዊት ፡ ለሰው ፡ አገልግሎት ፡ እንዲውሉ ፡ ከተፈጠሩስ ፡ ሰው ፡ እነርሱን ፡ ሥራ ፡ አሲዞ ፡ መኖሪያቸውን ፡ ቢጠቀምበት ፡ ምን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ አለ ? ሰውስ ፡ ይህን ፡ በመሥራቱ ፡ መቼ ፡ የአምላክን ፡ ትእዛዝ ፡ አፈረሰ ? ስለዚህ ፡ ያልቀኑ ፡ ሥፍራዎችን ፡ ማቅናት ፡ የመሻሻል ፡ መሻሻልን ፡ እንደሚያመጣ ፡ ተገንዝቦ ፡ አእምሮን ፡ አስፍቶ ፡ በሰፊዪቱ ፡ አገራችን ፡ መጠቀም ፡ ያስፈልጋል ።

አቶ ፡ ድንበሩ ፡ ዋሲሁን ።

ሀብት ፡ ፍለጋ ፡ የሚሉት ፡ አማርኛ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጣጣ ፡ ማምጣቱን ፡ ዛሬ ፡ ለእናንተ ፡ መንገር ፡ ለአንበሳ ፡ ሥጋን ፡ እንደመምተር ፡ ይሆናል ። በእውነቱ ፡ በቀላሉና ፡ በትንሹ ፡ ሠርቶ ፡ ከዘመድና ፡ ከወዳጅ ፡ ሳይለያዩ ፡ በሥጠኑ ፡ መኖር ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ነው ። በብዙ ፡ መሥራትና ፡ ተንዛዝቶ ፡ መኖር ፡ ግን ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ዘወትር ፡ የማይግን ፡ ጉጉት ፡ ይፈጥራል ። ቅናትና ፡ ምቀኝነትንም ፡ ይጨምርና ፡ ሰውን ፡ የጥቅም ፡ ባሪያ ፡ ብቻ ፡ ያደርገዋል ። ይበቃኛል ፡ ማለት ፡ ከሰው ፡ ልጅ ፡ አንጎል ፡ በጭራሽ ፡ ተመንጥቆ ፡ ከሄደ ፡ ሰው ፡ በያዘው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ የማይደሰት ፡ መሆኑ ፡ ይቀራል ። ዘወትር ፡ የበለጠ ፡ ነገርን ፡ በመፈለግ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ መድከም ፡ ራስን ፡ ያናውጠዋል ። ስለዚህ ፡ በግዕዙ ፡ « ዘበልአ ፡ በአቅም ፡ የኀድር ፡ በሰላም ፡ » ያለውን ፡ አጥብቆ ፡ መመልከት ፡ ይሻላል ፡ ይረዳልም ። ይህንም ፡ የግዕዙን ፡ በትርጉም ፡ የሚመስል ፡ አልጠግብ ፡ ባይ ፡ ሲተፋ ፡ ያድራል ፡ እየተባለ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከአሁን ፡ ድረስ ፡ ይኸው ፡ በመነገር ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

ትንሽ ፡ እኮ ፡ ነገሩን ፡ ጠለቅ ፡ አድርጎ ፡ አለማሰብ ፡ ነው ፡ እንጂ ቢታሰብበት ፡ ተወልዶ ፡ ያደጉበት ፡ አገር ፡ ከማናቸውም ፡ አገር ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ የተሻለ ፡ ነው ። በተወለዱበት ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ፍቅሮች ፡ አሉ ። የዘመድ ፡ የጎረቤት ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ወዳጆች ፡ የተራሮች ፡ የወንዞች ፡ የምንጮች ፡ የአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሸለቆችና ፡ የደኖች ፡ ፍቅሮች ፡ ማለት ፡ ነው ። እነዚህን ፡ ትተዋቸው ፡ ወደ ፡



ሩቅ ፡ አገር ፡ ሲሄዱ ፡ በጣም ፡ ይናፍቃሉ ፡ ዓይንም ፡ ያወጣሉ ። በሌላ መልክ ፡ ደግሞ ፡ ስንመለከት ፡ የነዚህ ፡ ፍቅር ፡ ሲጠፋ ፡ የሰው ፡ ልጅ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሰንሰለት ፡ የሚጠፋ ፡ ሆኖ ፡ ይታየናል ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ የተወለደበትንና ፡ ያደገበትን ፡ በጥንካሬ ፡ እያሻሻለ ፡ መሄድ ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ፡ ኑሮውን ፡ ማሻሻል ፡ አለበት ፡ በሚል ፡ አማርኛ ፡ ከበረሃ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ከእንስሳት ፡ ጋር ፡ መዋጋት ፡ የለበትም ። ተዋግቶም ፡ በማሸነፍ ፡ ሊያጠፋቸው ፡ የሚያስፈልገው ፡ አይደለም ።

አቶ ፡ መልአኩ ፡ አሻግሬ ፡

በዓይናችን ፡ የምናየውን ፡ ነገር ፡ እንደምስክር ፡ አድርገን ፡ ብንቀበል ፡ የእስከአሁን ፡ ክርክራችን ፡ ጊዜን ፡ ማባከን ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። እስኪ ፡ በአንደኛ ፡ ምሳሌነት ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ እንመርምራት ። ግርማዊ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሳይቆረቁሯት ፡ የአራዊት ፡ መጎድሪያና ፡ መፈንጫ ፡ ነበረች ። አንዳችም ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሆን ፡ ጥቅም ፡ አትሰጥም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ከተቆረቆረች ፡ ወዲህ ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ነገዶች ፡ ተሰበሰቡባት ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ ተከፈቱባት ። እያደርም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንብርት ፡ ሆነች ። በአፄ ፡ ምኒልክ ፡ የተጀመረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መዋሐድ ፡ እነሆ ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተፈጸመባት ።

እንደዚሁም ፡ ድሬዳዋን ፡ ሁለተኛ ፡ ምሳሌ ፡ አድርገን ፡ ብንመለከታት ፡ መጀመሪያ ፡ የነበረችበትንና ፡ አሁን ፡ የደረሰችበትን ፡ ለማወዳደር ፡ እንችላለን ። መቼም ፡ መጀመሪያ ፡ እልም ፡ ያለች ፡ በረሃ ፡ እንደነበረች ፡ ማንም ፡ የሚክድ ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ዘመዶቻችን ፡ ከያለበት ፡ ተሰብስበውባት ፡ እነሆ ፡ ገነትን ፡ ሊያስመስልዋት ፡ ቻሉ ። እንግዲህ ፡ አባቶቻችን ፡ « ሰብእ ፡ ይቄድሶ ፡ ለመካን ፡ ወመካንኒ ፡ ይቄድሶ ፡ ለሰብእ ፡ » ብለው ፡ የተናገሩት ፡ እውነት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ድሬዳዋ ፡ በረሃ ፡ ነበረች ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ የተዋበች ፡ ከተማ ፡ አደረጋት ። እንደዚሁም ፡ ድሬዳዋ ፡ የንግድ ፡ እንብርት ፡ ሆና ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አበልጽጋለች ። በዚህ ፡ አስተያየት ፡ ቦታና ሰው ፡ ተረዳድተው ፡ ብልጽግናን ፡ ያስገኛሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ

ሰው ፡ ጠፍ ፡ ቦቶችን ፡ እያቀና ፡ ራሱንና ፡ ወገኑን ፡ ለመጥቀም ፡ መጣር ፡ አለበት ።

አቶ ፡ መከት ፡ ሰጠኝ ፡

ባባቱ ፡ አረዳ ፡ ላይ ፡ የማይተካ ፡ ልጅ ፡ እንደወደል ፡ አህያ ፡ ያና ፋል ፡ እያናፋም ፡ አገር ፡ ላገር ፡ ይዞራል ። በመዞሩም ፡ የሰው ፡ አህያ ፡ እያስከዳ ፡ ጅብ ፡ ያስበላል ፤ ራሱም ፡ ድንገት ፡ ይበላል ። ስለዚህ ፡ መዞርና ፡ ማቅናት ፡ ክርክርን ፡ ፈጣሪዎች ፡ መሆናቸው ፡ ሳይታለም ፡ የተፈታ ፡ ነው ። እንግሊዞችና ፡ ፈረንሳዮች ፡ አገር ፡ በማቅናት ፡ በብዙ ፡ ተፋጅተዋል ። እኛም ፡ እንግሊዞችንና ፡ ፈረንሳዮችን ፡ ባን ሆን ፡ እኛና ፡ አራዊትን ፡ ልንሆን ፡ እንችላለን ። ስለዚህ ፡ ከአራዊት ፡ ጋር ፡ ስንታገል ፡ ማለቃችን ፡ የማይቀር ፡ ነው ፡ ምናልባት ፡ እኛም ፡ ብናሸንፍ ፡ እነርሱን ፡ መጨረሳችን ፡ የማይቀር ፡ ይሆናል ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ አገርን ፡ በማልማት ፡ ፈንታ ፡ ማጥፋት ፡ ይሆናል ። የአራዊ ትን ፡ ጸጥታ ፡ መንካት ፡ ሰላምን ፡ ከማጥፋት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አይር ቅም ።

ስለዚህ ፡ በኔ ፡ አስተያየት ፡ በያዙት ፡ ነገር ፡ ተደስቶ ፡ ያንኑ ፡ የያዙትን ፡ ነገር ፡ ለማሻሻል ፡ መጣር ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡ እየተሰደዱ ፡ ጠፍ ፡ ቦቶችን ፡ ማጥፋት ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። ይህ ፡ ካልሆነማ ፡ ሁሉም ፡ በያለበት ፡ ይቁም ፡ የሚለው ፡ አሳብ ፡ ሊፈርስና ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሊበረግግ ፡ ነው ።

አንድ ፡ አስታራቂ ፡ ሽማግሌ ፡

እናንት ፡ ተከራካሪዎች ፡ እስኪ ፡ ነገሬን ፡ አድምጡት ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ አንሥቶ ፡ ትዳሩን ፡ ለማሻሻል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቦቶችን ፡ ያልመረጠ ፡ ማን ፡ ነው ? ሰው ፡ የተፈጠረው ፡ በእስያ ፡ እንደሆነ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይነግረናል ። ለመሆኑ ፡ ዛሬ ፡ ዓለምን ፡ የመላት ፡ በእስያ ፡ የተፈጠረው ፡ ዘር ፡ ነው ? ወይስ ፡ አይደለም ? ብለን ፡ ታሪ ክን ፡ ብንጠይቅ ፡ ራሱ ፡ በእስያ ፡ የተፈጠረው ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ እናገኝ ዋለን ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ በማኸል ፡ አገር ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ እየ



በዛ ፡ ሲሄድ ፡ የአገር ፡ ማቅናት ፡ ተግባር ፡ እየቀጠለ ፡ ይሄዳል ፡ ማለት ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ በአሁኑ ፡ አስተሳሰብ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ በገዛ ፡ መንግሥቱ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ያልለማውን ፡ ቢያለማ ፡ ከሕግ ፡ ውጭ ፡ ይሠራል ፡ ለማለት ፡ የምንደፍርበት ፡ መን ገድ ፡ የለም ። የሕዝብ ፡ ቁጥር ፡ ሲጨመር ፡ ለሰው ፡ ሕይወት ፡ የሚያ ስፈልጉ ፡ ነገሮችም ፡ መብዛት ፡ አለባቸው ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ያስፈልጋቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ያልቀኑትን ፡ ቦቶች ፡ ማቅናትና ፡ የሰውን ፡ መጠነኛ ፡ ፍላጎት ፡ ማጥ ገብ ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ ተጨብጦ ፡ በችግር ፡ ከመዋረድ ፡ ይሻላል ።

አሁን ፡ እናንተ ፡ ሁለት ፡ ተከራካሪዎች ፡ ነገሩን ፡ በትክክል ፡ ብትመለከቱት ፡ ሰው ፡ እንደየፍላጎቱ ፡ ይኑር ፡ የሚለውን ፡ አሳብ ፡ ለመጨበጥ ፡ ትችላላችሁ ፡ ማለት ፡ ባለበት ፡ መቀመጥ ፡ የሚፈልግ ፡ እዚያው ፡ እንዳለ ፡ ይቀመጥ ፡ ማቅናትን ፡ የሚፈልግ ፡ ግን ፡ እየሄደ ፡ ያቅና ፡ ማለት ፡ ነው ።

የአቶ ፡ በላይነህ ፡ እንግዶች ፡ የጋለ ፡ ክርክር ፡ ከብዙ ፡ ውዝግብ፡ በኋላ ፡ አልቆ ፡ እንግዶች ፡ እየተሰናበቱ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንግዳ ፡ አልመጣም ። አቶ ፡ በላይነህ ፡ ራቱን ፡ ከበላ ፡ በኋላ ፡ ለወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈላት ።

አዲስ ፡ አበባ ፡
የፖስታ ፡ ሣ ቍጥር ፡ ፻፰ ፡
ታኅሣሥ ፡ — ፲፱፻ — ዓ. ም.

እጅግ ፡ ለተወደድሽ ፡ ክብርት ፡ እኅቴ ፡ ወ ደማሜ ፡

እንደምን ፡ ሰንብተሻል ? ናፍቆት ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ይሰማሽ ፡ ይሆን ? እኔ ፡ እዚህ ፡ በብዙ ፡ እቸገራለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ችግሬ ግታትን ፡ ሊያገኝ ፡ ነው ፡ መሰለኝ ። በዚህ ፡ ሰሞን ፡ በሬዲዮና ፡ በጋ ዜጣ ፡ እንደተረዳሽው ፡ በሥራ ፡ ወደ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ተዛውሬአ ለሁ ። ይህ ፡ ወሬ ፡ እንደሚያስደስትሽ ፡ አምናለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የገረመኝ ፡ አንቺና ፡ እኔ ፡ ባሰብነው ፡ መሠረት ፡ አለመሆኑ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ከዛሬው ፡ የበለጠ ፡ መሥራት ፡ አለብንና ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በአጭር ፡ ታጥቀሽ ፡ ጠብ

ቷኝ ። ምናልባት ፡ ከኔ ፡ የተለየ ፡ አሳብ ፡ እንዳለሽ ፡ እስከ ፡ አሥር ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በደብዳቤ ፡ ልትገልጭልኝ ፡ ትችያለሽ ። ስለዚህም ፡ መጻፍ ፡ ባትፈቅጂ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ይገዬ ፡ መምጣት ፡ እንዳለብኝ ፡ ጻፊልኝ ። እኔ ፡ የምገባበትን ፡ ቀን ፡ ለአባባ ፡ በቴሌግራም ፡ አስታውቃቸዋለሁ ።

ብቻ ፡ ክቡር ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ራስ ፡ ዘመነ ፡ መልካሙ ፡ ወንበራንና ፡ በለያን ፡ ለመጎብኘት ፡ ይሄዳሉ ፡ ማለትን ፡ ስለሰማሁ ፡ ጥቂት ቅር ፡ ብሎኛል ። ምክንያቱም ፡ ከክቡርነታቸው ፡ መሪ ፡ ቃላትን ፡ ይዞ ፡ መምጣት ፡ ስለሚያስፈልገኝ ፡ ነው ። አለበለዚያ ፡ ግን ፡ የበታች ፡ ሹማምንትን ፡ እጅ ፡ ነስቼ ፡ እመጣና ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ እመለስ ፡ ይሆናል ።

ክብርት ፡ እኅቴ ፡ በይ ፡ እስክንገናኝ ፡ ድረስ ፡ ደኅና ፡ ሁኚልኝ ። ለመላ ፡ ቤተሰቡ ፡ የናፍቆትና ፡ የአክብሮት ፡ ሰላምታዬን ፡ አቅርቢልኝ ።

ያንቺው ፡ አክባሪ ፡

በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡

ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ በደረሳት ፡ ጊዜ ፡ ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ እውነቱ ፡ የትዳር ፡ ኅሎዋ ፡ እውነት ፡ እየሆነ ፡ መሄዱን ፡ ተገነዘበችው ። ይህም በጣም ፡ አስደሰታት ። የብቻ ፡ ኑሮ ፡ ብቻ ፡ ትግል ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ከጓደኛ ፡ ጋር ፡ የኑሮን ፡ ትግል ፡ አብሮ ፡ መግፋት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ከአሁኑ ፡ የትዳር ፡ ፕላንዋን ፡ ማቀድ ፡ ጀመረች ። አዲስ ፡ ተስፋም ፡ በመንፈስዋ ፡ ፈጥራ ፡ የራስዋን ፡ ዓለም ፡ አዘጋጀች ። ከማስተማር ፡ ሥራዋ ፡ ጋር ፡ አስተባብራም ፡ በሥራት ፡ ልትመራው ፡ አሰበች ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ከተማ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኮሚቴዎች ፡ ጠቅላይ ፡ ኮሚቴ የአቶ ፡ በላይነህን ፡ መቀበያ ፡ መሰናዶ ፡ ለማዘጋጀት ፡ አንድ ፡ ጊዜያዊ ፡ ኮሚቴ ፡ ቀደም ፡ አድርጎ ፡ መርጦ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ በተሟላ ፡



ድርጅት ፡ ላይ ፡ ተገኘ ። ሽማግሌዎችም ፡ በድርጅቱ ፡ ተደስተው ፡ የአቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬን ፡ መምጣት ፡ በመጠባበቅ ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ የጎጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነ ፡ መልካሙ ፡ ከአሜድላና ፡ ከወንበራ ፡ ጉብኝታቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ከከተማው መግቢያ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ አገኟቸው ። ክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነም ፡ ከሽማግሌዎቹ ፡ አንድ ፡ ሁለቱን ፡ አስጠርተው ፡ « ስለምን ፡ እዚህ ፡ ተሰብስባችኋል ? ጉዳያችሁስ ፡ ምንድር ፡ ነው ? » ብለው ፡ ቢጠይቁ ፡ አዲሱን ፡ ከንቲባቸውን ፡ የሚጠባበቁ ፡ መሆናቸውን ፡ ገለጹላቸው ። ክቡርነታቸው ፡ የሕዝቡ ፡ ስብሰባ ፡ ለአቤቱታ ፡ አለመኑን ፡ ተረድተው ፡ መንገዳቸውን ፡ ሊቀጥሉ ፡ ሲሉ ፡ እነሆ ፡ ከንቲባው አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ከተፍ ፡ ብሎ ፡ ከመኪና ፡ ወረደና ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነን ፡ እጅ ፡ ነሣ ። ክቡርነታቸውም ፡ በመኪና ፡ ውስጥ ፡ እንደሆኑ ፡ እጅ ፡ ነሡት ። ሕዝቡ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነን ፡ ሲያቸውና ፡ ግልብጥ ፡ ብሎ ፡ መጥቶ ፡ እጅ ፡ ነሣቸው ። ቀጥሎም በሁለት ፡ ሽማግሌዎች ፡ አማካይነት ፡ ክቡርነታቸው ፡ በፈቀዱት ፡ ቦታ ፡ ምሳ ፡ እንዲጋበዙለት ፡ ጠይቆ ፡ ተፈቀደለትና ፡ ግብዣው ፡ የግብዣው ፡ መሰናዶ ፡ በተደረገበት ፡ ቦታ ፡ እንዲሆን ፡ ተወሰነ ።

ይህ ፡ ዕድለኛ ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሕዝብ ፡ ሳያስበው ፡ በከንቲባው ፡ ምክንያት ፡ ጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዢውን ፡ ለመጋበዝ ፡ ስለታደለ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደስቶ ፡ በክቡራን ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ መሪነት ፡ እንግዶቹን ፡ ከከተማው ፡ አዳራሽ ፡ አስገባቸው ። መሰናዶው ፡ በመትረፍረፍ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ አላጠጠም ። ክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነና ፡ የክብር ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ይህ ፡ ያልታሰበ ፡ ግብዣ ፡ ከግምታቸው ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኙት ፡ ተደነቁ ፡ ተገረሙም ። የአዳራሹም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በበኩሉ ፡ ስቦአቸው ፡ ከመገረም ፡ በላይ ፡ አዋላቸው ።

ተቀባዮቹና ፡ እንግዳው ፡ ንግግር ፡ እንዲያደርጉ ፡ ከክቡር ፡ ጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ ተፈቀደላቸውና ፡

« ክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነ ፡ መልካሙ ፡

ክቡራት ፡ ወይዛዝርትና ፡ ክቡራን ፡ መኳንንት ፡

ዛሬ ፡ በዚህች ፡ ዕድለኛ ፡ ቀን ፡ በአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሽማግሌዎች ፡

ስም ፡ ሆኜ ፡ እንድናገር ፡ ስለተፈቀደልኝ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።
የዛሬው ፡ ደስታ ፡ ድርብ ፡ ደስታን ፡ ይዞ ፡ በመገኘቱ ፡ የአምሳለ ፡ ገነ
ትን ፡ ሕዝብ ፡ አስከብሮታል ። ይህንም ፡ የክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነን ፡
አስከብሮት ፡ ለመቀበል ፡ የቻለችው ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ እውነትም ፡
አምሳለ ፡ ገነት ፡ ናት ። የዛሬው ፡ በዓልዋ ፡ ከታሪክዋ ፡ ዕድገት ፡
ውስጥ ፡ የማይለይ ፡ አንድ ፡ ክፍልን ፡ ይይዛል ።

አምሳለ ፡ ገነት ፡ በከንቲባነት ፡ የተቀበለቻቸው ፡ አቶ ፡ በላይ
ነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ አስተምረን ፡ ያሳደግናቸው ፡ ልጃችን፡
ወንድማችንና ፡ አገልጋያችን ፡ ነበሩ ። እነሆ ፡ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡
በተሻሻለ ፡ ዕውቀት ፡ ይረዱን ፡ ዘንድ ፡ በክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነ ፡ አሳቢ
ነት ፡ ተሾመው ፡ መጥተዋል ። የአገሩን ፡ ሰርዶ ፡ ባገሩ ፡ በሬ ፡ እንደ
ሚባለው ፡ ሁሉ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ ማናቸውንም ፡ ችግራችንን ፡ ተረ
ድተው ፡ ለማቃለል ፡ እንደሚጥሩልን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

እኛም ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ከተማ ፡ ሕዝብ ፡ የችግርን ፡ ጉዳት ፡
በመረዳዳት ፡ ልናስወግደው ፡ የምንጥር ፡ ሰዎች ፡ ነን ። ይህም ፡ ተግባ
ራችን ፡ ለብዙ ፡ ከተሞች ፡ ምሳሌ ፡ እስከ ፡ መሆን ፡ ደርሶአል ። ስለ
ዚህ ፡ ከንቲባችን ፡ በሚያደርጉት ፡ መሻሻል ፡ ማናቸውንም ፡ ልማት ፡
በኅብረት ፡ ለመሥራት ፡ ፈቃደኞች ፡ ነን ። ይህንም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡ ገልጠነዋል ፤ አሁንም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጥረት ፡ እን
ደምንገልጠው ፡ ከልብ ፡ እንሞክራለን ። »

መልስ ፡

« ክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነ ፡ መልካሙ ፤
ክቡራት ፡ ወይዛዝርትና ፡ ክቡራን ፡ መኳንንት ፤
የአምሳለ ፡ ገነት ፡ አባቶቼና ፡ እናቶቼ ፡ እንዲሁም ፡ እኅቶቼና ፡
ወንድሞቼ ፤

ይህች ፡ የዛሬዪቱ ፡ ቀን ፡ ያጎናጸፈችኝ ፡ ድርብ ፡ ደስታ ፡ መላ ፡
ሰውነቴን ፡ አሙቆታል ። ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእናንተ ፡ ለባለወሮ
ታዎቼ ፤ ለክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነ ፤ ለእናንተም ፡ ለአምሳለ ፡ ገነት ፡
ሕዝብ ፡ ራሴን ፡ የተቀደሰ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጌ ፡ ለመሥራት ፡ እን
ድችል ፡ ይረዳኝ ፡ ዘንድ ፡ የዘወትር ፡ ምኞቴ ፡ መሆኑን ፡ በአክብሮት ፡



እገልጻለሁ ፤ » ሲል ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ተናግሮ ፡ የአዳራሹን ፡
ሕዝብ ፡ ከማስተንተን ፡ ውስጥ ፡ ጨመራቸው ።

በዓሉ ፡ እንደተፈጸመ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነ ፡ መልካሙ ፡ በመ
ጡበት ፡ አኳኋን ፡ መኳንንቱን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ ሳላይሽ ፡ አመሩ ።
ሕዝቡም ፡ እየተሰናበተ ፡ ተመለሰ ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ ዘመነን ፡ ለመሸኘት ፡
ፈልጎ ፡ አብሮ ፡ ለመነሣት ፡ ቢሞክር ፡ ሳይፈቀድለት ፡ ቀርቶ ፡ ለማረ
ፊያ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀለት ፡ ቦታ ፡ ታጅቦ ፡ ሄደ ። በተወሰነው ፡ ፕሮግ
ራም ፡ መሠረት ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ ከምሳ ፡ መልስ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡
ያህል ፡ አርፎ ፡ ከእንግዳ ፡ መቀበያው ፡ ሳሎን ፡ መጥቶ ፡ ጠያቂ ፡ እን
ግዶቹን ፡ ሲቀበል ፡ ቆይቶ ፡ ከምሽቱ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡
ቤተ ፡ ዘመዱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ቤት ፡ ሄደ ። በዚህም ፡
ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተሰብስቦ ፡ ጠበቀው ። ሁሉንም ፡ በመልካም ፡ ፈገ
ግታ ፡ እየተቀበለ ፡ አነጋገራቸው ።

ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እየተሰናበተ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡
መጣችና ፡ በናፍቆት ፡ የበሰለ ፡ ፍቅሯን ፡ አቀረበችለት ። እስካሁን ፡
ድረስ ፡ ያልደከመው ፡ ጠንካራ ፡ ሰውዬ ፡ አሁን ፡ በፍቅር ፡ ግልምጫ
ዛለ ። እንደማላብም ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ የግድ ፡ እንደምንም ፡ ብሎ
አንሠራራና ፡ ጨዋታ ፡ ጀመሩ ። ደግነቱ ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ በዚህ ፡
ሰዓት ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። ስለዚህ ፡ ማናቸውም ፡
ርብትበታና ፡ መልካዊ ፡ ለውጥ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አልወጣም ። እነሆ ፡
በናፍቆት ፡ ፍቅር ፡ ስስት ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ ለእራት ፡ ተጠሩ ፤ ይሁንና ፡
ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ጉዳይዋን ፡ ገልጻ ፡ በሽኝ ፡ ወደ ፡ ቤትዋ ፡ ስትመ
ለስ ፡ አቶ ፡ ደገፉና ፡ ወይዘሮ ፡ ላቅሻቸው ፡ ካቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡
ቤተሰብ ፡ ጋር ፡ በራት ፡ ላይ ፡ ተገኙ ። አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡
ሥራውን ፡ በማግሥቱ ፡ ጀመረ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ማናቸውንም ፡
ሥራ ፡ ምክትል ፡ ከንቲባውንና ፡ ዋና ፡ ዴሬክተሩን ፡ እንደዚሁም ፡
ዋና ፡ ጸሐፊውን ፡ ሳይዝ ፡ ወይም ፡ ሳያማክር ፡ አይሠራም ፡ ነበር ።
ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ምክንያቱን ፡ ሳይረዳና ፡ ጠቃሚነቱን
ሳይገነዘብ ፡ አይሠራውም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በማዋከብ ፡ እንሥራ ፡
ሲሉት ፡ እጅግ ፡ ይቸግር ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ የቸኮለች ፡ አፍስሳ ፡ ለቀ
መች ፡ እንደሚባለው ፡ ያለ ፡ ነገርን ፡ የማይፈቅድ ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡

በቶሎ ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሠራተኞች ፡ ዘንድ ፡ ተረጋገጠለት ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ የማያዳግም ፡ ሥራን ፡ ለመሥራት ፡ ታላቅ ፡ መሣሪያ ፡ ሆኖ ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ተገለጠ ። አንዳንድም ፡ ያልገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩም ፡ በትዕግሥት ፡ እንዲያስረዱ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ዘወትር ፡ ይቆጣጠር ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ሥራውን ፡ በተለመደው ፡ አቅድ ፡ መሠረት ፡ ሲሠራ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቱን ፡ ሠራተኞች ፡ ሰበሰበ ።

«ክቡራን ፡ አባቶቼና ፡ ወንድሞቼ ፡

አብዛኞቻችሁ ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ተወላጆች ፡ መሆናችሁን ፡ ዐውቃለሁ ። የቀራችሁትም ፡ አምሳለ ፡ ገነትን ፡ እንደተወለዳችሁበት ፡ መንደር ፡ ወይም ፡ ከተማ ፡ እንደምትወዱአት ፡ አምናለሁ ። አሁን ፡ በዚህ ፡ የተሰበሰባችሁት ፡ ሁሉ ፡ ለአንድ ፡ ዓይነት ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ መሰናዳታችሁን ፡ ዐውቃለሁ ። ይኸውም ፡ የአምሳለ ገነትን ፡ ሕዝብ ፡ በቅንነት ፡ ማገልገል ፡ ነው ። አምሳለ ፡ ገነት ፡ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ መንደር ፡ ብጤ ፡ ነበረች ። ነገር ፡ ግን ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አድጋ ፡ እነሆ ፡ መጠነኛ ፡ ከተማ ፡ ከመሆን ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ በመድረስዋ ፡ የከንቲባ ፡ ቦታ ፡ ሆናለች ። አምሳለ ፡ ገነት እንደዚህ ፡ በፍጥነት ፡ ለማደግ ፡ የቻለችው ፡ በእናንተና ፡ በከተማው፡ ሕዝብ ፡ ኅብረታዊ ፡ ሥራ ፡ መሆኑ ፡ ሳይታለም ፡ የተፈታ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ሁላችሁንም ፡ በተለምዶ ፡ አነጋገር ፡ አደራ ፡ የምላችሁ የጀመራችሁት ፡ ዕድገት ፡ በበለጠ ፡ ፍጥነት ፡ እየቀጠለ ፡ የሚሄድበትን ፡ መንገድ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ አድርጋችሁ ፡ እንድትይዙ ፡ ነው ። ሥራ ፡ እጅ ፡ ሲበዛበት ፡ ይሸሻል ፡ ማለት ፡ እጅ ፡ ሲያጠቃው ፡ ይፈራል ። ስለዚህ ፡ የሁላችሁም ፡ አእምሮችና ፡ እጆች ፡ በሽቅድምድም፡ ሥራውን ፡ እንዲያጣድፉ ፡ ብትሞክሩ ፡ ማናቸውም ፡ ሥራችን ፡ ለነገ አያድርም ። ስለዚህም ፡ ዋናው ፡ መድኃኒት ፡ ሥራው ፡ የኔ ፡ አይደለም ፡ እያሉ ፡ እንቅፋት ፡ ከመሆን ፡ መራቅ ፡ ነው ። የኅብረትና ፡ የሥራ ፡ ጠላት ፡ ፉክክር ፡ መሆኑን ፡ ሁላችሁም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተረዳችሁት ፡ አምናለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ደግሞ ፡ ማሳሰቡም ፡ የሚጠቅም ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ አሁን ፡ አሰለቸኋችሁ ።

ሥራን ፡ በማጣደፍ ፡ ለመሥራት ፡ የሁላችንም ፡ መንፈስ ፡ በመ



## የአምሳለ ፡ ገነትን ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ የሚያሳይ ።



ቻኮል ፡ ይሠራል ፡ ይህም ፡ መልካም ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ ነው ። ነገር
ግን ፡ ሥራን ፡ ከማቻኮል ፡ በፊት ፡ ሥራን ፡ የሚያቻኩሉ ፡ የሥራ ፡
ድርጅቶችን ፡ መፍጠር ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ይህንም ፡ የሥራ ፡
አከፋፈልና ፡ አመራር ፡ በሥራት ፡ እንደገና ፡ የሚደለድልልን ፡
አንድ ፡ የማዘጋጃን ፡ አስተዳደር ፡ በሥራት ፡ ያጠናና ፡ የአምስት ፡
ዓመታት ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ያለው ፡ ዐዋቂ ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ ከአዲስ ፡
አበባ ፡ ይመጣልናል ። ስለዚህ ፡ ለወደፊቱ ፡ ከሥራ ፡ አመራር ፡ የተ
ሻሉትን ፡ ዘዴዎች ፡ እያማረጥን ፡ ለመሥራት ፡ ፈቃደኞች ፡ ከሆን ፡
ሥራውንና ፡ ራሳችንን ፡ ለመጥቀም ፡ እንደምንችል ፡ የተረጋገጠ ፡
ነው ። የተሻለ ፡ ሥራን ፡ የሚሠራ ፡ ጊዜንና ፡ ተጨማሪ ፡ ወጭን ፡ ስለ
ሚቀንስ ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ ማለት ፡ ደመወዝ ፡ እንዲያገኝ ፡ ያስፈል
ገዋል ። ስለዚህ ፡ በሥራ ፡ መወዳደር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡
ነገር ፡ መሆኑን ፡ ከዛሬ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከድሮ ፡ ጀምራችሁ ፡ ታው
ቁታላችሁና ፡ በብዙ ፡ ማሳሰብ ፡ አያስፈልግም ።

በሥራ ፡ መነቻቸፍ ፡ መነቋቆር ፡ መቃሰፍና ፡ መወነጃጀል ፡
የሥልጣኔ ፡ ርምጃን ፡ ቀናሾች ፡ እንደሆኑ ፡ ከዘመናችን ፡ በፊት ፡
የነበሩ ፡ ታሪኮች ፡ ያስገነዝቡናል ። ሩቅ ፡ ወደኋላ ፡ ሳንመለስ ፡ አባቶ
ቻችን ፡ በእርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜያቸውን ፡ ባያጠፉ ፡ ኖሮ ፡ ዛሬ ፡
ከያዝነው ፡ ወደበለጠ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንደርስ ፡ ነበር ። እነርሱ ፡ መሠ
ረት ፡ ሊጥሉልን ፡ ሲገባቸው ፡ ጊዜያቸውን ፡ በመጨቃጨቅ ፡ አሳለ
ፉት ። እነሆ ፡ እኛ ፡ የእነርሱንና ፡ የእኛን ፡ ሥራ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አጣ
ምረን ፡ ለመሥራት ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ እንደክማለን ። ባንደክምም ፡
እንኳ ፡ መድከም ፡ እንዳለብን ፡ ስለሚሰማን ፡ ሰውነታችን ፡ መዛሉ ፡
አልቀረም ። ስለዚህ ፡ የራስን ፡ ጊዜ ፡ ማሳለፍ ፡ የሚቀጥለውን ፡ ትው
ልድ ፡ ጊዜ ፡ ማባከን ፡ ነውና ፡ በፍቅርና ፡ በኅብረት ፡ ለመሥራት ፡
አጥብቀን ፡ እንጣር ፡ » ሲል ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ ንግግሩን ፡ ገታ ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ ለሥራው ፡ በጣም ፡ አሳቢ ፡ ሠራተኛ ፡ በመሆኑ
ዘወትር ፡ እንቅልፍ ፡ የማይወስደው ፡ አውጠንጣኝ ፡ ሰው ፡ ነው ።
ይህ ፡ አውጠንጣኝነቱ ፡ ሰውነቱን ፡ ከመዳበር ፡ ይከልክለው ፡ እንጂ ፡
ሥራውን ፡ እየተቃና ፡ እንዲሄድ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ረድቶታል ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሠራተኞቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ባስረዳው ፡ መሠረት ፡
የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ በመልካም ፡ ድርጅት ፡ እንዲቋቋምለት ፡



ያን ፡ የማዘጋጃ ፡ አስተዳደርን ፡ አጥንቶ ፡ በሥራ ፡ የተለማመደውን ፡
ዐዋቂ ፡ በብዙ ፡ ጥረት ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ አስመጣና ፡ የአምሳለ ፡ ገነ
ትን ፡ ማዘጋጃ ፡ በሥራትና ፡ በደንብ ፡ አቋቋመው ። የመሥሪያ ፡
ቤቱም ፡ ድርጅት ፡ በ፹፱ ፡ ገጽ ፡ ቻርት ፡ እንደተገለጸው ፡ ሆኖ ፡ እን
ዲገኝ ፡ ተደልድሏል ። አምሳለ ፡ ገነት ፡ ገና ፡ ስትቆረቆር ፡ ጀምሮ ፡
መልካም ፡ ዕድል ፡ የገጠማት ፡ ከተማ ፡ ነች ። እነሆ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡
አዳፍሬን ፡ ያህል ፡ ታላቅ ፡ ትጉህ ፡ ሠራተኛ ፡ አምላክ ፡ ሰጣት ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡ ብቻ ፡
የማያምን ፡ ግሩም ፡ ሰው ፡ ነው ። እርሱ ፡ የሚያምነው ፡ በዕውቀቶችና ፡
በጥበቦች ፡ ጠቅላላ ፡ ማዕከላዊ ፡ ውጤት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ማናቸ
ውም ፡ መሻሻል ፡ ከመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከሕዝቡም ፡
መምጣት ፡ ማስፈለጉን ፡ በመገንዘብ ፡ ከዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡
ጋር ፡ በኅብረት ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩትን ፡ ኮሚቴዎች ፡ በተሻሻለ ፡
መልክ ፡ እንደገና ፡ አቋቋማቸው ። «የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ማዘጋጃ ፡ አገ
ልጋይነቱ ፡ ለአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሕዝብ ፡ ከሆነ ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡
ሕዝብ ፡ በጉዳዩ ፡ ተካፋይ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ የሚለው ፡ አማርኛ ፡
በከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ላይ ፡ መታየት ፡ ይገባዋል ፡ » ሲል ፡ አቶ ፡ በላይ
ነህ ፡ አዳፍሬ ፡ የሥራውን ፡ መንፈስ ፡ ዘረጋ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡
አምሳለ ፡ ገነትን ፡ የኔ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ እያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይጠራ
ትና ፡ ይጥርላት ፡ ጀመር ። እነሆ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ የኔ ፡ አምሳለ ፡
ገነት ፡ የሚለውን ፡ ሁኔታ ፡ በመፍጠሩ ፡ ማናቸውም ፡ የአምሳለ ፡
ገነት ፡ ከተማ ፡ አስተዳደር ፡ በጠቅላላ ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄደ ።

የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ዕድገት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እያደገ ፡ በመሄዱ ፡
አቶ ፡ በላይነህ ፡ ፋታ ፡ አጣ ፡ ቤቶቹም ፡ እንደልብ ፡ ሊያገኙት ፡ የማ
ይቻል ፡ ሆነ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ከበሽታ ፡ ላይ ፡ ይወድቃል ፡ ብለው
ዘወትር ፡ ያስቡለትና ፡ ይሠጉለት ፡ ነበር ። ወ ደማቹ ፡ አብዛኛውን ፡
ጊዜ ፡ ልታነጋግረው ፡ ስትፈልግ ፡ ይቀጥራትና ፡ በሥራ ፡ ብዛት ፡
ይቀራል ፤ እርስዋ ፡ እንዳትመጣ ፡ ደግሞ ፡ ገና ፡ ሕገኛው ፡ በዓል ፡
አልተፈጸመም ። በእርሱ ፡ ጊዜ ፡ ማጣት ፡ የተነሣ ፡ ሁለቱን ፡ ጓደኛ
ሞችና ፡ መላ ፡ ቤተሰቡን ፡ እጅግ ፡ አሰጋው ። በእውነትም ፡ አንድ ፡
ቀን ፡ ማታ ፡ በጣም ፡ የሚያስቸኩል ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ የቢሮው ፡ ፊት፡
ለፊት ፡ መስኮት ፡ ክፍት ፡ ኖሮ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ተወርዋሪ ፡ ነፋስ ፡ ከሽ

ንጡ ፡ ላይ ፡ ጠቅቶ ፡ ጣለው ። ለጊዜው ፡ ምንም ፡ አልተሰማውም ፡
ነበርና ፡ ሥራውን ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ ቆይቶ ፡ ከምሽቱ ፡ በአራት
ሰዓት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲመጣ ፡ ተሰማው ። እቤትም ፡ እንደደረሰ ፡
ራት ፡ ለመብላት ፡ ተሣነው ። ስለዚህ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ከአልጋው ፡
ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ተኛ ። ማንንም ፡ እንዳይጠሩ ፡ ለአሽከሮቹ ፡ ጥብቅ ፡
ትእዛዝ ፡ በመስጠቱ ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ በብርቱ ፡ ሲሠቃይ ፡ አንድም
ሰው ፡ አልመጣም ። እንዳይነጋ ፡ የለምና ፡ ነጋ ፡ ሲነጋ ፡ ማንም ፡ ሰው
ሳይሰማ ፡ ወደ ፡ ሆስፒታል ፡ ሄደ ። ተረኛው ፡ ሐኪም ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡
ዋናውን ፡ ሐኪም ፡ በስልክ ፡ አስጠራውና ፡ መጣ ። እንደደረሰም ፡
አቶ ፡ በላይነህን ፡ ሲጨነቅ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አዘነለት ። ወዲያ
ውም ፡ በሚገባ ፡ መርምሮ ፡ የሚዋጥና ፡ በመርፌ ፡ የሚሰጥ ፡ መድኃ
ኒት ፡ በቶሎ ፡ አዘዘለት ። ቀጥሎም ፡ ለብቻው ፡ በሚገኝ ፡ ሞቃት ፡
ክፍል ፡ ራሱ ፡ አስወስዶ ፡ አስተኛው ። ነፋስ ፡ ባጠቃው ፡ ጎኑ ፡ በኩ
ልም ፡ በቅባት ፡ ታሽቶ ፡ በጥጥ ፡ ተሸፍኖ ፡ እንዲታሠር ፡ አደረገ ።
እስኪሻለውም ፡ ከወላጆቹና ፡ ከወ/ ደማሜ ፡ በስተቀር ፡ ማንም ፡
ከአቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ክፍል ፡ እንዳይገባ ፡ ተደረገ ።

በስምንት ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ በጣም ፡
በጎ ፡ ሆነ ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደም ፡ የተቀላቀለበትን ፡
አክታ ፡ ማሳየቱ ፡ አልቀረም ። የአቶ ፡ በላይነህ ፡ የሳንባ ፡ ንካት ፡ በወ
ይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ ባልንጀሮች ፡ በኩል ፡ ስጋትን ፡ ፈጥሮ ፡ ኖሮ ፡
አንድ ፡ ቀን ፡ ጎልቶ ፡ ተገለጸ ። አንድ ፡ ቀን ፡ አንድዋ ፡ አብሮ ፡ አደግ
ባልንጀራዋ ፡ «ወይዘሪት ፡ ደማሜ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አንቺው ፡
ራስሽ ፡ ታውቂበታለሽ ፡ ብዬ ፡ ስለጋብቻሽ ፡ ምንም ፡ ተነጋግረን ፡
አናውቅም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሳይሰማው ፡ ትጭጭቱን ፡ ውስጥ ፡ ውስ
ጡን ፡ ጨረሺው ። በዚህም ፡ እጅግ ፡ ተገርመን ፡ ውጤቱን ፡ በመጠባ
በቅ ፡ ላይ ፡ ሳለን ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ያልታሰበ ፡ አደጋ ፡ መጣ ። ይኸው
እርሱ ፡ ሳይጠነቀቅ ፡ አሁንም ፡ ከሥራው ፡ ገብቶ ፡ ይሰላል ። በአክታ
ውም ፡ ውስጥ ፡ ደም ፡ አለበት ። አንቺ ፡ የሳንባ ፡ ንክ ፡ ሰው ፡ አግብ
ተሽ ፡ ሕይወትሽን ፡ በመላ ፡ ልታጨልሚው ፡ ትፈቅጃለሽ ፡ እንዴ ?
ይህ ፡ ነገር ፡ እኮ ፡ በጣም ፡ አሳሳቢ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡
ልታስቢበት ፡ ይገባሻል ፡» ብላ ፡ መከረቻት ።

«ክብርት ፡ እኅቴ ፡ ወይዘሪት ፡ መሰለች ፡ ስለአሳብሽና ፡ ስለም



ክርሽ ፡ አመሰግንሻለሁ ። ብቻ ፡ ጥቂት ፡ እንዳስረዳሽ ፡ ፍቀጅልኝ ።

ሰዎች ፡ በጋብቻ ፡ ሲጣመሩ ፡ መጀመሪያ ፡ ወደፊት ፡ የሚመጣ
ውንና ፡ የሚሆነውን ፡ ገምተው ፡ በኅብረት ፡ ለመቀበል ፡ ስምምነት ፡
ያደርጋሉ ። ይህንም ፡ ስምምነት ፡ ከፍተኛ ፡ አደጋ ፡ እንጂ ፡ ልክስክ
ሶች ፡ ነገሮች ፡ አያፈርሱትም ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የጋ
ብቻ ፡ ስምምነትን ፡ ሲፈጽሙ ፡ አስተያየታቸው ፡ ለመልካሙ ፡ ቀን ፡
ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። የአሁኑ ፡ የአንቺ ፡ የእኅቴ ፡ የወይዘሪት ፡ መሰ
ለች ፡ አስተያየት ፡ ለመልካሙ ፡ ቀናት ፡ ብቻ ፡ የሚጋቡትን ፡ ይደግ
ፋል ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ ከእንስሶች ፡ የማይሻል ፡ ዝቅተኛ ፡ አስተያ
የት ፡ ነው ። ሰውን ፡ እንዳላዋቂ ፡ ያስቆጥረዋል ። ከሆዱ ፡ አልፎም ፡
እንደማያስብ ፡ ያስገምተዋል ። ስለዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አስተያ
የት ፡ እንዲታረም ፡ ሁላችንም ፡ በበኩላችን ፡ ልንጥርበት ፡ ይገባል ።
አንቺም ፡ እኅቴ ፡ ተምረሽ ፡ እንዳላዋቂዎች ፡ ከመገበዝ ፡ መታገሥ ፡
አለብሽ ፡ አለበለዚያ ፡ ዕውቀትሽ ፡ ሁሉ ፡ እንደግብዞች ፡ ይቆጠርብ
ሻል ። እውነተኞችና ፡ እምነተኞችም ፡ ይንቁሻል ። ስለዚህ ፡ ለወደ
ፊቱ ፡ ያልተመጠነና ፡ ያልተለካ ፡ አስተያየት ፡ እንዳትሰጭ ፡ ለአ
ፍሽ ፡ ልጓምን ፡ አብጂለት ፡» ብላ ፡ አሳሰበቻትና ፡ ሁለቱም ፡ በመን
ፈስ ፡ ትካዜ ፡ ወደየሥራቸው ፡ ሄዱ ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ እሆስፒታል ፡ ውስጥ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡
ያልተካሄዱ ፡ ሥራዎችን ፡ ጨርሶ ፡ ሳይድን ፡ እንደምንም ፡ ተበራቶ ፡
አጣራና ፡ ምክትል ፡ ከንቲባውን ፡ ለማናቸውም ፡ ሥራ ፡ አደራ ፡
ብሎ ፡ በአይሮፕላን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥቶ ፡ በተፈቀደለት ፡
መሠረት ፡ ሕክምናውን ፡ ቀጠለ ። በዘመናዊ ፡ መድኀኒት ፡ የተተከለ
በትን ፡ ሳል ፡ ለመንቀል ፡ በብዙ ፡ ታገለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሊነቀልለት ፡
አልቻለም ። በመጨረሻም ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ወደ ፡ ጅቡቲ ፡
ሄዶ ፡ እንዲያርፍ ፡ ሐኪሞች ፡ በጉባዔያቸው ፡ አዘዙትና ፡ ወደ ፡ አም
ሳለ ፡ ገነት ፡ ሳይመለስ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ጅቡቲ ፡ ወርዶ ፡ ሁለት ፡
ወር ፡ ያህል ፡ አረፈ ። በአሁኑ ፡ ዕረፍት ፡ ላይ ፡ በመጠኑ ፡ ተሻለው ፡
ይሁንና ፡ ሕመሙ ፡ ፈጽሞ ፡ ሊተወው ፡ አልቻለም ።

የተወሰነው ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜው ፡ እንዳለቀ ፡ በቶሎ ፡ ወደ ፡
አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመልሶ ፡ እንደገና ፡ በጥብቅ ፡ ተመረመረ ። በዚህ ፡
ጊዜ ፡ ነፋስ ፡ በነካው ፡ ጎኑ ፡ በኩል ፡ እንዲቀደድ ፡ ሐኪሞቹ ፡ ተስ

ማሙ ። ይህንም ፡ ውሳኔ ፡ ሲያስረዱት ፡ ምንም ፡ ጉዳት ፡ እንደማያገኘው ፡ መላልሰው ፡ ገለጹለት ። እርሱም ፡ የማይቀር ፡ ነገር ፡ መሆኑን፡ በመጨረሻው ፡ ተረድቶ ፡ መቀደዱንና ፡ ከሕመሙ ፡ መገላገሉን ፡ መረጠ ።

ድኅ ፡ ጉጉ ፡ ነው ። ለመሆኑ ፡ ሰውነትን ፡ ለቢለዋ ፡ አሳልፈው ፡ ሲሰጡ ፡ በጉታ ፡ መገኘቱንና ፡ አለመገኘቱን ፡ በቀጥታ ፡ እንዴት ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይቻላልና ፡ ነው ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ በቶሎ ፡ ተቀዶ ፡ ከበሽታው ፡ ለመገላገል ፡ የፈለገው ? የሚሰጥም ፡ ሰው ፡ በባሕር ፡ ውስጥ እንዳለ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የሚንሳፈፍ ፡ ገለባን ፡ ይጨብጣል ፡ እንደሚባለው ፡ እንኳ ፡ በጣም ፡ ተስፋው ፡ ባይቀል ፡ የተረጋገጠ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ብቻ ፡ ወደፊት ፡ ምጥ ፡ እንደተያዘች ፡ ሴት ፡ እገላገላለሁ ፡ ብሎ ፡ ማሰብም ፡ መልካም ፡ አስተያየት ፡ ስለሆነ ፡ በጎን ፡ ነገር ፡ መመኘት ፡ ምንም ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

የአቶ ፡ በላይነህ ፡ እናትና ፡ አባት ፡ በስልክ ፡ ተጠርተው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ የሚቀደድበት ፡ ቀን ፡ ተወሰነ ። እናቲቱ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንቧለሌ ፡ ትል ፡ ገባ ። አባትየው ፡ ግን ፡ «እግዚአብሔር ፡ የሰጠንን ፡ ልጅ ፡ አሁኑን ፡ ለመውሰድ ፡ ካሰበ ፡ እርሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ለልጁ ፡ የተሻለውን ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ ነውና ፡ ምንም ፡ መዋለል ፡ አይገባም ። እንዲያውም ፡ ልቅሶአችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳያሳዝነው ፡ እፈራለሁ ። ስለዚህ ፡ አንቺ ፡ እንቴ ፡ የበላይነህ ፡ እናት ፡ እባክሽ ፡ ልቅሶሽን ፡ ተወት ፡ አድርጊው ፡» ብሎ ፡ ራሱንና ፡ ሚስቱን ፡ አጽናና ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ በብዙ ፡ ጠንቃቃ ፡ ሐኪሞች ፡ ከጧቱ ፡ በሦስት ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ተቀደደ ። የመቅደዱም ፡ ተግባር ፡ ከዓርባ ፡ አምስት፡ ደቂቆች ፡ የበለጠ ፡ አልፈጀም ። ወደ ፡ ክፍሉም ፡ እንደተመለሰ ፡ ለአራት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ዕድሜ ፡ እናትና ፡ አባቱ ፡ ገብተው ፡ እንዳያዩት ፡ ተከለከሉ ። አዬ ፡ ምጥ ! አዬ ፡ ጭንቅ ! እናቲቱ ፡ በእርግጥ ፡ ልትሞት ፡ ደረሰች ። አንዳንድ ፡ እናቲቱን ፡ የተመለከቱ ፡ አስታማሚዎች ፡ «እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ መውለድ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ እንዲያውም ፡ ምን ፡ አባቱ ፡ ሳይወለድ ፡ ቢቀር ፡» እያሉ ፡ በጣም ፡ ተበሳጩ ።

የአቶ ፡ በላይነህ ፡ ወላጆች ፡ አሁን ፡ ተፈቀደላቸውና ፡ ወደ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ ክፍል ፡ ገቡ ። እንደገቡም ፡ እንዳያነጋግሩት ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ነበርና ፡ ሥፍራ ፡ ይዘው ፡ እርሱ ፡ እስኪናገር ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ጠበቁ ። እርሱም ፡ ጥቂት ፡ ቆየት ፡ እንዳሉ ፡ « አይዞአችሁ ፡ በጎ ፡ ነኝ ። ምንም ፡ አልል ። እስከዚህም ፡ የሚያሳስብና ፡ የሚያስለቅስ ፡ ነገር ፡ የለም ፡» ብሎ ፡ በጠቅላላ ፡ አስረዳቸው ። የአባቱን ፡ ጥንካሬ ፡ አልዘነጋውም ፡ ብቻ ፡ ሁለቱም ፡ አብረው መጨነቃቸውን ፡ በመመልከት ፡ በደፈናው ፡ ተናገረ ። እናቲቱም ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ እንባዋን ፡ በመሐረብ ፡ ጠራረገችና ፡ «እኛ ፡ ምን ፡ አለብን ፡ አካላትህን ፡ ለቢለዋ ፡ አሳልፈህ ፡ የሰጠኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ። ስለዚህ ፡ ምን ፡ የሆን ፡ መሰለህና ፡ ታጽናናናለህ ፡» ስትል ፡ መለሰችለት ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ነገር ፡ በትንቢት እንደተናገረው ፡ በሽታው ፡ በተቀደደ ፡ ጊዜ ፡ ከሥር ፡ ተነቅሎ ፡ ስለወጣለት ፡ እያደር ፡ በጣም ፡ እየተሻለውና ፡ ሰውነቱ ፡ እየወፈረ ፡ ወይም ፡ እየተመለሰ ፡ መሄድ ፡ ጀመረ ። እንደልቡም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ለመውጣት ፡ ችሎታን ፡ አገኘ ። ሐኪሞቹ ፡ በዚህ ፡ ሥራቸው ፡ ማለት አቶ ፡ በላይነህን ፡ ቀደው ፡ በማዳናቸው ፡ በጣም ፡ ተመሰገኑበት ። እርሱንም ፡ እንደምሳሌ ፡ እያደረገ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይነጋገርበት ፡ ጀመር ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ በየጊዜው ፡ በደብዳቤ ፡ እያደረገ ፡ ለወይዘሪት፡ ደማሜ ፡ ይልክላት ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ ለአምሳለ ፡ ገነት ፡ ምክትል ፡ ከንቲባ ፡ ይጽፍለት ፡ ነበር ። ደማሜም ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ ምክትል ፡ ከንቲባም ፡ በደብዳቤው ፡ ምክንያት ፡ መደሰታቸውንና ፡ የመጨረሻ ፡ ከፍተኛ ፡ ምኞታቸውን ፡ በየጊዜው ፡ ይገልጹለት ፡ ነበር ።

በተለይ ፡ ደማሜ ፡ «እንግዲህ ፡ ሰውነቱን ፡ ካገኘውና ፡ ከሰው ፡ እኩል ፡ በጤንነቱ ፡ ከተራመደ ፡ የተሠነዘረብን ፡ ትርኪ ፡ ምርኪ ፡ ሁሉ ፡ ወደየሥርቻው ፡ ተመልሶ ፡ ይገባል ። አፍሮ ፡ የማይተከዝ ፡ በእምነት ፡ የጸና ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለመሆኑ ፡ አሁን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ወሮታን ፡ ልሰጠው ፡ እችላለሁ ? የምችለው ፡ በቅንነት ፡ እየተራመድሁ ፡ ስሙን ፡ ማመስገን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡» እያለች ፡ በገዛ ፡ ራስዋ ፡ ለብቻዋ ፡ እየሆነች ፡ አስተነተነች ።

## ምዕራፍ ፡ ፴ ።

አምኃ ፡ ወዲያው ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርትን ፡ እንዳጠናቀቀ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ለሃያ ፡ ልጆች ፡ ትምህርተ ፡ መርድእ ፡ መጣ ። ትምህርተ ፡ መርድእ ፡ ማለትም ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ስኮላርሺፕ ፡ ማለት ፡ ነው ። ትምህርተ ፡ መርድእ ፡ የመጣው ፡ ከ፴፪ቱ ፡ ልጆች ፡ ለመጀመሪያዎቹ ፡ ሃያ ፡ ልጆች ፡ እንዲሰጥ ፡ ነው ። እንዳጋጣሚ ፡ አምኃ ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ አሥር ፡ ልጆች ፡ ውስጥ ፡ ስለነበር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደሰተ ። ትምህርተ ፡ መርድእ ፡ ለአምሳለ ፡ ገነት ፡ ልጆች ፡ መምጣቱንና ፡ እርሱም ፡ ትምህርተ ፡ መርድእ ፡ ለማግኘት ፡ መቻሉን ፡ ለቤቶቹ ፡ በነገራቸው ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ደስታና ፡ ሐዘን ፡ ሆነ ። መቼም ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ እንደሚገምተው ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ልጁ ፡ በዕድሜ ፡ ገፍቶ ፡ ሳለ ፡ በትምህርቱ ፡ ከክፍል ፡ ወደ ፡ ክፍል ፡ እየዘለለ ፡ በቅርብ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ሁለተኛውን ፡ የትምህርት ፡ ጠቅላላ ፡ ክፍል ፡ ከማጠናቀቁም ፡ በላይ ፡ ይህ ፡ ዕድል ፡ ስላጋጠመው ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ሐዘን ፡ የተሰማቸው ፡ ተለይቷቸው ፡ ለትምህርት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ በመሄዱ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ደስታና ፡ ሐዘን ፡ ተቀላቅለው ፡ ሊያስቸግሯቸውና ፡ ሊያስደርጽዋቸው ፡ የቻሉት ።

ወደውጭ ፡ አገር ፡ ለትምህርት ፡ የሚሄዱት ፡ ሁሉ ፡ የሚማሩትና ፡ ተመልሰው ፡ የሚሠሩት ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲመዘን ፡ የትምህርት ፡ ዕድገት ፡ ክፍል ፡ አጥንቶ ፡ ስለነበር ፡ አምኃ ፡ በስጦታው ፡ መሠረት ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ መሐንዲስነትን ፡ እንዲመርጥ ፡ ተጠየቀ ። እርሱም ፡ ያላንዳች ፡ ማመንታት ፡ ጥያቄውን ፡ እጅ ፡ በመንሣት ፡ ተቀበለና ፡ መራጮቹን ፡ በጣም ፡ አስደሰታቸው ። ከሁለት ፡ ልጆች ፡ በስተቀር ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤትን ፡ አስተዳደር ፡ እንዲያጠና ፡ የተፈቀደለት ፡ ልጅ ፡ አልነበረም ። ከአሥራ ፡ ሰባቱ ፡ ልጆች ፡ ዘጠኙ ፡ የእርሻንና ፡ የቅመማን ፡ ትምህርት ፡ አዛምደው ፡ እንዲያጠኑ ፡ ፈቀዱ ። ሁለቱ ፡ የሕግን ፡ ትምህርት ፡ እንዲያጠኑ ፡ ፈቀዱ ። ሦስቱ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ትምህርትን ፡ ሲያጠኑ ፡ ሦስቱ ፡ ደግሞ ፡ ዕድገተ ፡ ትምህርትን ፡ ለመማር ፡ መረጡ ። አሁን ፡ ለተዘረዘሩት ፡ ቦታች ፡ ሁሉ ፡ የአምሳለ ፡ ገነት ፡ የትምህርት ፡ ዕድገት ፡ ክፍል ፡ አስፈላጊ ፡ ሠራተኞችን ፡ እንዲያደርግባቸው ፡ አስቀድሞ ፡ አስቦ ፡ ነበር ፡ ስለዚህ ፡ ልጆቹ ፡ ሲመለሱ ፡ የሚሠሩትን ፡ ነገርና ፡ የሚሠሩበትን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በማወቃቸው ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደሰቱ ። አሁን ፡ የትምህርታቸው ፡ ዓይነት ፡ በመወሰኑ ፡ የቀራቸው ፡ መሄዱና ፡ ተግቶ ፡ ለተመደቡበት ፡ ሥራ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ መመለሱ ፡ ነው ። አምላክ ፡ ይርዳቸው ፡ ማለት ፡ ይገባል ።

ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሚሄድ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ አንዳንድ ፡ የአገራችንን ፡ ልብስ ፡ እንዲያሰፋ ፡ በተወሰነው ፡ መሠረት ፡ ሃያውም ፡ ልጆች ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ልብሶችን ፡ አሰፉ ። በተጨማሪም ፡ በዓመት ፡ በዓልና ፡ በአንዳንድ ፡ ታላላቅ ፡ ሥፍራዎች ፡ የሚዘመሩ ፡ መዝሙራትን ፡ ከነዜማ ፡ ምልክታቸው ፡ እየጻፉ ፡ የተቻላቸውን ፡ ያህል ፡ አጠኑ ። እንደዚሁም ፡ ለየሚሄዱበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የአገርን ፡ ሥራ ፡ የሚያሳይ ፡ መሣሪያ ፡ አዘጋጁ ። በእውነቱ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የተላኩት ፡ ልጆች ፡ የእነዚህን ፡ ያህል ፡ አገርን ፡ የሚያስጠሩና ፡ የሚያስከብር ፡ ሲያደርጉ ፡ አልታዩም ። ብቻ ፡ ከነዚህ ፡ በፊት ፡ ይሄዱ ፡ የነበሩት ፡ ምጥን ፡ በርበሬንና ፡ ቋንጣን ፡ በመያዝ ፡ በጠቅላላ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተማሪዎች ፡ ላይ ፡ ወቀሳን ፡ ሳያስነሡ ፡ አልቀሩም ። ስለዚህ ፡ የሃያው ፡ ልጆች ፡ መሰናዶ ፡ ምናልባት ፡ ይሽረው ፡ ይሆናል ። ዝግጅታቸውም ፡ ለወደፊቱ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሚሄዱትን ፡ ልጆች ፡ እያስጠነቀቀ ፡ በቀና ፡ መንገድ ፡ ይመራቸው ፡ ይሆናል ።

እነዚህ ፡ ልጆች ፡ የሚነሡበት ፡ ቀን ፡ ተቃረበ ። ቤተሰቦቻቸውም ፡ በጣም ፡ ተጨነቁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ልጆቹ ፡ ሊቀሩ ፡ አይችሉም ፡ አንድዩ ፡ በመሄዳቸው ፡ ተቆርጦ ፡ ስማቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ለየሚሄዱበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተላልፏል ። ይህም ፡ ባይሆን ፡ ቃልን ፡ ሰጥቶ ፡ ልጅን ፡ ማስቀረት ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ እንዲያው ፡ መጨነቅና ፡ መዋተት ፡ ብቻ ፡ ሆነ ፡ በወላጆች ፡ ዘንድ ፡ የተያዘው ። በሚሄዱበት ፡ ቀን ፡ አይሮፕላኑ ፡ በጧት ፡ መጣ ። ልጆች ፡ ወላጆችና ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ አይሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ መጥተው ፡ ይተረማመሱ ፡ ጀመር ። ጥቂት ፡ እንደቆዩ ፡ የተሣፋሪ ፡ መንገደኞች ፡

ስም ፡ በዝርዝር ፡ ተጠራ ። ዕቆች ፡ ሁሉ ፡ አስቀድመው ፡ ተማፍረው ፡ ነበርና ፡ አሁን ፡ መንገደኞች ፡ ቁናማቶቻቸውን ፡ ብቻ ፡ እየያዙ ፡ በመሥመር ፡ ተሰለፉ ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ ሲጠራ ፡ ብቻ ፡ ይገባል ። መጣደፍ ፡ መጋፋት ፡ መሽቀዳደምና ፡ ቦታ ፡ መምረጥ ፡ እዚህ ፡ የሉም ። ሁሉም ፡ በተራ ፡ ይገባል ። ቀድሞ ፡ ከገባውም ፡ ቀጥሎ ፡ ይቀመጣል ። ስለዚህ ፡ እንዳችም ፡ አስቸጋሪና ፡ አሳካሪ ፡ ነገር ፡ በዚያ ፡ ፈጽሞ ፡ አይገኝም ።

አይሮፕላኑ ፡ ሞተሩን ፡ ሲያስነሣ ፡ የተማፋሪዎች ፡ እጆች ፡ መሐረቦች ፡ እንደያዙና ፡ ሳይዙ ፡ ይርገበገቡና ፡ ይወዛወዙ ፡ ጀመር ። እንደዚሁም ፡ የሸኝዎች ፡ እጆች ፡ በተራቸው ፡ አየሩን ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ አመናተሉት ። እንቦችም ፡ እየተቀነዘፉ ፡ መንሰቅሰቅና ፡ መንፈቅፈቅ ፡ ሥራቸውን ፡ ሠሩ ። አይዞህ ፡ አይዞህሽና ፡ አይዟችሁም ፡ በያለበት ፡ ተሰሙ ። በመልስ ፡ ላይም ፡ አንዳንድ ፡ እናቶች ፡ ተብረከረኩ ። የተማሪዎች ፡ ወላጆች ፡ ወደየቤታቸው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ሐዘናቸውና ፡ ብቡታቸው ፡ አልበርድ ፡ በማለቱ ፡ ጐረቤቶች ፡ እየተሰበሰቡ ፡ የማጽናናትን ፡ ተግባር ፡ ፈጸሙ ። በጨዋታቸውም ፡ ላይ ፡ የትምህርትን ፡ ጥቅም ፡ እያገነኑና ፡ የአውሮፓን ፡ ሥልጣኔ ፡ መስፋፋት ፡ እየዘረዘሩ ፡ አንዳንዶች ፡ ሰዎች ፡ አስረዱ ። የልጆቹም ፡ መሄድና ፡ ሥልጣኔን ፡ ከምንጩ ፡ መቅዳት ፡ የቤተሰቦችን ፡ የልጆቹን ፡ የራሳቸውን ፡ ኑሮና ፡ የአምሳለ ፡ ገነትን ፡ ዕድገት ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ እንደሚያሻሽል ፡ ጭምር ፡ በጨዋታ ፡ እያደረጉ ፡ አስረዱ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እያደር ፡ ቤተሰቦች ፡ በግዳቸው ፡ እየተጽናኑና ፡ እየበረቱ ፡ መሄድ ፡ ያዙ ።

ተማፋሪዎቹ ፡ ልጆች ፡ በተወሰነው ፡ ፕሮግራም ፡ መሠረት ፡ ካርቱም ፡ ሲደርሱ ፡ አይሮፕላኑ ፡ አረፈና ፡ ለአንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ዕረፍት ፡ ተደርጎ ፡ ምሳ ፡ ተበላ ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንዶቹ ፡ ልጆች ፡ ማታ ፡ አዳር ፡ ላይ ፡ እንበላ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ አይቋጭልንም ፡ እያሉ ፡ ባዶ ፡ አንጀታቸውን ፡ አስረው ፡ ተቀመጡ ። ከዚህ ቀደም ፡ በአይሮፕላን ፡ ላይ ፡ የመሣፈር ፡ ልምምድም ፡ ባለማድረጋቸው ፡ መጀመሪያ ፡ ራሳቸውን ፡ ቀጥሎም ፡ ቤተሰባቸውን ፡ እየወቃቀሱ ፡ አፍጥጦ ፡ መቀመጥ ፡ ብቻ ፡ ሆነ ። ከመካከላቸውም ፡ አንዱ ፡ ልጅ ፡ «ከኃጢአት ፡ በስተቀር ፡ ተንቶ ፡ መተው ፡ ያለበት ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡



እግዚአብሔርንና ፡ ሰውን ፡ ካልአስቀየመ ፡ በስተቀር ፡ በመለማመድ ፡ ሊሠሩት ፡ ይገባል ፡» ሲል ፡ አስተያየቱን ፡ አቀረበ ። ይህንም ፡ አሳብ ፡ ሁሉም ፡ ተቀበሉት ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ያገኛቸውን ፡ ችግር ፡ ሊያቃልልላቸው ፡ አልቻለም ።

ከምሳ ፡ መልስ ፡ ቡናቸውን ፡ ጠጣጡና ፡ ጉዞአቸውን ፡ እንደገና ፡ ወደካይሮ ፡ ቀጠሉ ። ካይሮም ፡ በጊዜ ፡ ለመግባት ፡ ቻሉ ። በተወሰነው ፡ ፕሮግራም ፡ መሠረት ፡ በካይሮ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ አረፉ ። ካይሮን ፡ በሚገባ ፡ ጎበኟት ። ፒራሚዶቹም ፡ ከጉብኝቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ይዘው ፡ ነበር ። ከተማሪዎቹ ፡ አብዛኞቹ ፡ ዐባይን ፡ በትንሾቹ ፡ ጀልባ ፡ ሳይሞክሩት ፡ አልቀሩም ። በአገራችን ፡ በታላላቅ ፡ ሸለቆች ፡ ውስጥ ፡ እየተንደረደረ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የሚያስቸግረው ፡ ዐባይ ፡ እዚህ ፡ በሜዳ ፡ ለሜዳ ፡ ወንዝ ፡ በዝግታ ፡ ይጓዛል ። እንደልብም ፡ ወደፊትና ፡ ወደኋላ ፡ በጀልባ ፡ ያስኬዳል ። በጀልባም ፡ ሰዎች ፡ ሲተላለፉ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ጎሾች ፡ ከሀባይ ፡ ውስጥ ፡ እየገቡ ያረፈባቸውን ፡ ሐሩር ፡ ያበርዳሉ ። እነሆ ፡ ዐባይ ፡ የእንስሳትና ፡ የሰዎች ፡ መናፈሻና ፡ ሐሩር ፡ ማብረጃ ፡ የአዝርዕትም ፡ መለምለሚያ ፡ ነው ። ልጆቹ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በማየት ፡ ሲደነቁ ፡ የካይሮ ፡ መንገዶች ፡ በዐባይ ፡ ውኃ ፡ ሲታጠቡ ፡ ለመመልከት ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ አጋጠማቸው ።

ከካይሮ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ አቴን ፡ ሲበሩ ፡ የሜዲቴራኒያንን ፡ ባሕር ፡ ቁልቁል ፡ እየተመለከቱ ፡ አለፉት ። ልጆቹ ፡ የሜዲቴራኒያንን ፡ ባሕር ፡ ቁልቁል ፡ ሲመለከቱ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ሥፍራቸውን፡ የተለዋወጡ ፡ እየመሰላቸው ፡ ግራ ፡ ይገባቸው ፡ ነበር ። የሜዲቴራኒያንን ፡ ባሕር ፡ ሲያቋርጡ ፡ መንደሮችን ፡ የሚመስሉትን ፡ ደሴቶች ፡ ለመመልከትና ፡ ከትምህርታቸው ፡ ጋር ፡ ለማገናዘብ ፡ ቻሉ ። በመጨረሻ ፡ አቴን ፡ ሲደርሱ ፡ አንድ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጭፍን ፡ የሆነ ፡ ጉም ፡ አጋጠማቸውና ፡ የሚደረገው ፡ መላ ፡ ለጊዜው ፡ ጠፋ ። ነገር ፡ ግን ፡ በአቴን ፡ አቅራቢያ ፡ ወደምትገኝ ፡ ወዳንዲት ፡ ትንሽ ፡ ከተማ ፡ ሄደው ፡ አረፉ ። በአቴን ፡ ላይ ፡ የተዘጋጀው ፡ ፕሮግራም ፡ እንዳይፈርስ ፡ በማለት ፡ ተማፋሪዎች ፡ ሁሉ ፡ በመኪና ፡ ወደአቴን ፡ መጡ ። በአቴንም ፡ አስቀድሞ ፡ ቦታ ፡ ወደተያዘላቸው ፡ ሆቴል ፡ ገብተው ፡ አረፉ ። በዚች ፡ ከተማ ፡ ለመቆየት ፡ የተፈቀደው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡

ተኩል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ጊዜያቸውን ፡ በመሻማት ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ የሰበከባቸውን ፡ ታላላቅ ፡ ታሪከኞች ፡ ቦታዎች ፡ እየተጠናከሩ ፡ ለመጎብኘት ፡ ቻሉ ። በቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱትን ፡ አንዳንድ ፡ ስሞች ፡ በተለይ ፡ በማየታቸው ፡ ለደስታቸው ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም ።

በመጨረሻ ፡ ወደጀርመን ፡ ለመብረር ፡ ተዘጋጁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በተባለው ፡ ቀን ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ጉም ፡ ሆነና ፡ አላስሄድም ፡ አላቸው ። ስለዚህ ፡ ያላንዳች ፡ ፕሮግራም ፡ በዚያ ፡ ዕለት ፡ በአቴን ፡ ዋሉ ። የአይሮፕላኑ ፡ መሪና ፡ ነጂው ፡ ተናደው ፡ እጅግ ፡ ተብሰለሰሉ፡ ይሁንና ፡ ጉሙ ፡ ስምቶ ፡ ጉዟቸውን ፡ ለመቀጠል ፡ አላስቻላቸውም ። ከአገራችን ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ ከጌታችን ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ግንኙነት ፡ አለው ፡ እየተባለ ፡ የሚወራለትን ፡ የሆሜርን ፡ የትያትር ፡ አዳራሽ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ተማሪዎቹ ፡ ለመጎብኘት ፡ ዕድል ፡ አጋጠማቸው ። እንዳጋጣሚም ፡ ባለቅኔው ፡ ሆሜር ፡ ስለኢትዮጵያውያን ፡ ጀግንነት ፡ የጻፈው ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተተርጉሞ ፡ በዚያው ፡ ተገኘ ። ይህም ፡ ጽሑፍ ፡ ልጆቹን ፡ እጅግ ፡ አስደስታቸው ። የኢትዮጵያውያንም ፡ ጀግንነት ፡ በአውሮጳውያን ፡ ዘንድም ፡ የታወቀ ፡ መሆኑንም ፡ አስረዳቸው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ዕድገት ፡ ትምህርትን ፡ ለመማር የሚሄዱት ፡ ልጆች ፡ በተጨማሪ ፡ የግሪክን ፡ ቋንቋ ፡ አጥንተው ፡ የአገራቸውን ፡ ታሪክ ፡ ለመመራመር ፡ አሰቡ ።

በማግሥቱ ፡ ቀኑ ፡ መልካም ፡ ስለሆነላቸው ፡ እየተደሰቱ ፡ ከአቴን ፡ ተነሥተው ፡ ከምዕራብ ፡ ጀርመን ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ከቦን ፡ ገቡ ። ጉዞአቸው ፡ በተቃና ፡ ሁኔታ ፡ አለቀላቸው ። በምዕራብ ፡ ጀርመን ፡ የሚቀመጠው ፡ የትምህርት ፡ ረዳት ፡ ከቦን ፡ አይሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ይጠባበቃቸው ፡ ነበርና ፡ ወዲያው ፡ ከአይሮፕላኑ ፡ እንደወረዱ ፡ ለማረፊያ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀላቸው ፡ ሥፍራ ፡ ወሰዳቸው ። ይህ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የተማሪዎች ፡ ረዳት ፡ በቦን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለቆየ ፡ እንደ ፡ አዲስ አበባ ፡ ቦንን ፡ ቆጥሯት ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ይኖራል ። ተማሪዎችንም ፡ እየተቀበለ ፡ እንደራሱ ፡ ተመልክቶ ፡ በሚቸግራቸው ፡ ሁሉ ፡ ይረዳቸዋል ። አሁን ፡ በአረፉበት ፡ ቦታ ፡ ስምንት ፡ ቀናት ፡ ያህል ፡ ተቀምጠው ፡ አገር ፡ ከተላመዱ ፡ በኋላ ፡ የትምህርት ፡ ረዳታቸው ፡ ወደየተመደቡባቸው ፡ ት/ቤቶች ፡ ራሱ ፡ እየወሰደ ፡ አስገባቸው ። እንደዚ



ሁም ፡ ማናቸውም ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደሚፈጽምላቸውና ፡ በየጊዜው ፡ እንደሚጠይቃቸው ፡ ተስፋ ፡ ሰጣቸው ።

ወደጀርመን ፡ አገር ፡ ለትምህርት ፡ የሚላክ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ የአራት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ጀርመንኛን ፡ እንዲያጠና ፡ ይገደዳል ፡ አስቀድሞ ፡ አጥንቶ ፡ የመጣ ፡ ተማሪ ፡ ግን ፡ አይጠየቅበትም ። የጀርመንና ፡ የእንግሊዝ ፡ ቋንቋዎች ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደምናውቀው ፡ አምኃ ፡ እውነቱ ፡ የቋንቋ ፡ ስጦታ ፡ አለው ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሊቸግረው ፡ አልቻለም ። አምኃ ፡ በሒሳብና ፡ በፊዚክስ ፡ ትምህርት ፡ በኩል ፡ እያወዳደረ ፡ ለማጥናት ፡ እንዲመቸው ፡ ከመምህራኑ ፡ ጋር ፡ ተመካክሮ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ የተጻፉ ፡ ታላላቅ ፡ መጻሕፍትን ፡ ገዛ ። አምኃ ፡ ከገባበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ለመጨረስ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሦስትም ፡ ዓመታት ፡ የቀሯቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተማሪዎች ፡ ነበሩና ፡ በእነርሱ ፡ እየተረዳ ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ በቶሎ ፡ ተለማመደ ።

የመጀመሪያውና ፡ የሁለተኛው ፡ ትምህርታውያን ፡ ዓመታት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሳይታወቁት ፡ አለፉ ። አምኃ ፡ በየጊዜው ፡ በትምህርት ፡ እየጠነከረ ፡ ሄደ ። በትምህርቱ ፡ እንኳን ፡ ለክፍሉ ፡ ልጆች ፡ ለከፍተኞችም ፡ ረዳት ፡ እየሆነ ፡ በመምራቱ ፡ በተማሪዎች ፡ ዘንድ ፡ የመወደድንና ፡ የመከበርን ፡ ሁኔታዎች ፡ ፈጠረ ። በተለይማ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ተማሪዎች ፡ በማናቸውም ፡ በኩል ፡ እንደታላቅ ፡ ወንድም ፡ ሆኖ ፡ በሚቸግራቸው ፡ ሁሉ ፡ ይረዳቸው ፡ ጀመር ። ይህም ፡ ጉብዝናው ፡ በትምህርት ፡ ረዳቱ ፡ ኀላፊ ፡ ዘንድ ፡ ታውቆ ፡ የብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተማሪዎች ፡ ሞግዚት ፡ እንዲሆን ፡ አስመረጠው ። ወደጀርመን ፡ ከመጣ ፡ አንሥቶ ፡ ከወይዘሪት ፡ እጅግአየሁ ፡ ጋር ፡ መጻጻፉን ፡ አላቋረጠም ፡ ነበርና ፡ በሦስተኛው ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ላይ ፡ በመጣለት ፡ ደብዳቤ ፡ እጅግ ፡ ደነገጠ ፡ አዘንና ፡ ለቅሶም ፡ ለጊዜው ፡ አስቸገሩት ። ሁለቱም ፡ ተራርቀው ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ ይህ ፡ የማይለወጥ ፡ አሳዛኝ ፡ ሁኔታ ፡ በግድ ፡ መጣ ። ስለዚህ ፡ እንደምንም ፡ ተጣጥሮ ፡ ጊዜ ፡ የፈጠረውን ፡ ችግር ፡ ለማሸነፍ ፡ ከመድከም ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ ሊያደርግ ፡ አልቻለም ። አምኃ ፡ በትርፍ ፡ ጊዜው ፡ የሚሠራ ፡ ነገር ፡ መፈለግ ፡ ጀመረ ። ነገር ፡ ግን ፡

አጥብቆ ፡ የፈለጉት ፡ ነገር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በቶሎ ፡ አይገኝምና ፡ እንዲያው ፡ ይታክትና ፡ ይባክን ፡ ጀመር ። አንድ ፡ ቀን ፡ ከመኖሪያ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ሲተክዝ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መዝጊያውን ፡ አንኳኳ ። አምኃም ፡ በቅልጥፍና ፡ ተነሥቶ ፡ ቢከፍት ፡ የትምህርት ፡ ረዳታቸው ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። በፈገግታ ፡ ተቀብሎ ፡ አስገብቶት ፡ እየደጋገሙ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሰላምታቸውን ፡ ከተለዋወጡ ፡ በኋላ ፡ የትምህርት ፡ ረዳቱ ፡ መቼም ፡ በትምህርትህ ፡ ጎበዝ ፡ መሆንህን ፡ መምህራንህ ፡ በየጊዜው ፡ ይገልጹልኛል ። እኔም ፡ እስከአሁን ፡ ድረስ ፡ የምከራብህ ፡ ተማሪ ፡ ከመሆን ፡ ደረጃ ፡ ባለመንቃንቅህ ፡ እጅግ ፡ ተደስቻለሁ ።

እነሆ ፡ አሁን ፡ በድንገት ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እንድሄድ ፡ ከቦን ፡ አምባሳደራችን ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ተነሥቼ ፡ ስሄድ ፡ አንድ ፡ በትምህርት ፡ የበሰለ ፡ ግብረ-ገባዊ ፡ ሰው ፡ ከተማሪዎቹ ፡ መካከል ፡ በተጠባባቂነት ፡ መተካት ፡ አስፈለገኝ ። እንደምታውቀው ፡ አንድ ፡ ጸሐፊ ፡ አለኝ ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ ተማሪዎችን ፡ መርዳትና ፡ ማስተናገድ ፡ አያውቅም ። ስለዚህ ፡ አሁን ፈቃድህ ፡ ቢሆን ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ የትምህርት ፡ ረዳት ፡ ተጠባባቂ ፡ እንድትሆን ፡ በሥራህና ፡ ባመልህ ፡ መርጨሃለሁ ። አደራህን ፡ ጥያቄዬን ፡ በእሉታ ፡ መልስ ፡ አታሳፍርብኝ ። ይህንም ፡ ጉዳይ ፡ ከትምህርት ፡ ቤታችሁ ፡ ዲን ፡ ጋር ፡ ተነጋግሬበት ፡ የማያስቸግርህ ፡ ሆኖ ፡ አግኝቼዋለሁ ። ምናልባት ፡ በዚህ ፡ ባቀረብሁት ፡ ሥራ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከክፍል ፡ ብትቀር ፡ ይህንኑ ፡ ትምህርት ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ እንድታገኘው ፡ ተነጋግሬበታለሁ ፡ » ብሎ ፡ ጉዳዩን ፡ ዘርዝሮ ፡ ለአምኃ ፡ ባስረዳው ፡ ጊዜ ፡ ምርጫውን ፡ በደስታ ፡ ተቀበለው ። ይህ ፡ አጋጣሚ ፡ ነገር ፡ ለአምኃ ፡ ከቤቱ ፡ ድረስ ፡ ሰተት ፡ ብሎ ፡ የመጣለት ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ለዕረፍት ፡ ሊዘጋ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ሲቀረው ፡ ነበር ። ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ለዕረፍት ፡ እንደተዘጋ ፡ አምኃ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ረዳቱ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መጥቶ ፡ ሥራውን ፡ በሥርዓት ፡ ተረከበ ። አስፈላጊውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተነጋግሮ በማስታወሻ ፡ ያዘ ። ጸሐፊውንም ፡ ተስፋ ፡ በሚሰጡ ፡ ቃላት ፡ አበረታታው ።

አምኃ ፡ እውነቱ ፡ ገና ፡ የትምህርት ፡ ረዳቱ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡



አበባ ፡ ከመመለሱ ፡ በፊት ፡ ሥራውን ፡ ጀመረ ። የተጠባባቂነቱም ፡ ደብዳቤ ፡ ቦን ፡ ካለው ፡ አምባሳደር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መጣለት ። አምኃ ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ እንግዳ ፡ ባለመሆኑ ፡ አንዳችም ፡ የሚያውክ ፡ ነገር ፡ ሳይገጥመው ፡ በሥርዓት ፡ መራው ። አምባሳደሩም ፡ የሥራውን ፡ ችሎታና ፡ በተማሪዎች ፡ ዘንድ ፡ ያገኘውን ፡ ፍቅር ፡ በመረዳት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየጠሩ ፡ ያበረታቱት ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሥራ ፡ የሚጠይቀው ፡ አንደኛ ፡ የሥራ ፡ ችሎታን ፡ ይዞ ፡ በትጋት ፡ መሥራት ፡ ሁለተኛ ፡ በቅንነት ፡ የተማሪዎችን ፡ ችግር ፡ እያጠኑ ፡ የሚቃለልበትን ፡ ዘዴ ፡ ፈጥሮ ፡ ከተማሪዎች ፡ ጋር ፡ በኅብረት ፡ መሥራትን ነው ። አምኃ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲሁ ፡ በተፈጥሮ ፡ ስጦታው ፡ በትምህርትና ፡ በሌላም ፡ በኩል ፡ ተማሪዎችን ፡ የሚገጥማቸውን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ይጥር ፡ እንደነበረ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተረድተናል። አሁን ፡ የተጨመረበት ፡ ሥራ ፡ የገንዘብ ፡ አወጣጥንና ፡ የአስተዳደርን ፡ ተግባር ፡ ያጠቃልላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሥራው ፡ ከትርፍ ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ በተለይ ፡ ለአምኃ ፡ አይፈጅበትም ፡ ነበር ።

ተጠባባቂ ፡ የትምህርት ፡ ረዳትነቱን ፡ ሥራ ፡ በጀመረ ፡ በሁለት ፡ ወሩ ፡ አራተኛውም ፡ የትምህርት ፡ ዓመት ፡ ሊከፈት ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሲቀረው ፡ ለወይዘሪት ፡ እጅግአየሁ ፡ እንደሚከተለው ፡ ጻፈላት ፡

ቦን ፡

ምስራባዊ ፡ ጀርመን ፡

ነሐሴ — ፲፱፻ — ዓ. ም.

ለተከበርሽ ፡ ውድ ፡ እኅቴ ፡ ወይዘሪት ፡ እጅግአየሁ ፡

ደብዳቤ ፡ ከተጻጻፍንበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ለጤናሽ ፡ እጅጉን ፡ ባያሌው ፡ እንደምን ፡ አለሽልኝ ? እኔ ፡ ቸሩ ፡ መድኅኔ ፡ ዓለም ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ ደኅና ፡ ነኝ ። ብቻ ፡ በዘመድና ፡ በወዳጅ ፡ ናፍቆት ፡ ዓይኔ ፡ ምንጥቅ ፡ ብሎ ፡ ሊወልቅ ፡ ነው ።

የኔ ፡ እጅግአየሁ ፡ ምነው ፡ ደብዳቤሽ ፡ እንዲህ ፡ ዘገየብኝ ? ምነው ? ምን ፡ ሆንሻል ? እንደገና ፡ ተጨማሪ ፡ ሐዘን ፡ አገኘሽ ፡ እንዴ ? ለማናቸውም ፡ ነገር ፡ በየጊዜው ፡ የሚገጥምሽን ፡ ችግር ፡ ብትገልጭልኝ ፡ መልካም ፡ ነበር ፡ እኮ !

የዛሬ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ አባትሽና ፡ እናትሽ ፡ ልጆቹን ፡ ሁሉ ፡

ትተው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ መሰናበታቸውን ፡ በደብዳቤሽ ፡ ስትገልጭልኝ ፡ የተሰማኝ ፡ ሐዘን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደነበር ፡ ለመግለጽ ፡ በእውነቱ ፡ ፀባዩን ፡ በጭልፋ ፡ ሆኖ ፡ ከመገኘት ፡ በላይ ፡ ነው ። ይኸውልሽ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በትርፍ ፡ ጊዜዬ ፡ ሥራ ፡ ለመያዝ ፡ በብዙ ፡ ደክሜ ፡ አጣሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ባላሰብሁትና ፡ ሐዘኔ ፡ በተበራታበት ፡ ጊዜ ፡ በምዕራብ ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ ለሚገኙት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተማሪዎች ፡ ተጠባባቂ ፡ የትምህርት ፡ ረዳት ፡ እንድሆን ፡ ተመረጥሁ ። ምርጫውንም ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተቀበልሁት ። እነሆ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በመጠኑ ፡ ባለደመወዝ ፡ ሆኜ ፡ ሥራዬን ፡ እሠራለሁ ። ከዚያን ፡ በፊትና ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ካተረፍሁት ፡ ፻ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ለችግርሽ ፡ መርጃ ፡ ልኬልሻለሁ ።

አይዞሽ ፡ አታስቢ ፡ እኔም ፡ ዘመዶቼም ፡ ሆነን ፡ ትምህርትሽን ፡ እስክትጨርሺ ፡ ድረስ ፡ እንረዳሻለን ። እኔ ፡ ትምህርቴን ፡ ጨርሼ ፡ ለመመለስ ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡ ቀርተውኛል ። መቼም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ በተጠባባቂነት ፡ የያዝሁት ፡ ሥራ ፡ አስቸጋሪም ፡ ቢሆን ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ ከትምህርት ፡ ጋር ፡ በመቋጠር ፡ ሳልጨርስ ፡ አልቀርም ። ይህ ፡ ሥራዬ ፡ እስካለና ፡ ወይም ፡ ባይኖር ፡ ወደፊት ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ፈልጌም ፡ ቢሆን ፡ እረዳሻለሁ ። አንቺ ፡ ግን ፡ ትምህርትሽን ፡ ለመጨረስ ፡ ገና ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ይቀሩሻል ። ስለዚህ ፡ ችግርሽ ፡ ገና ፡ በቶሎ ፡ ተቃላይ ፡ አይሆንም ። ምናልባት ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የምታደርጊው ፡ የማስተማር ፡ ልምምድ ፡ ለአምስተኛውና ፡ ለስድስተኛው ፡ ዓመታት ፡ ትምህርታውያን ፡ ጊዜያት ፡ ይረዳሽ ፡ ይሆናል ። ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ሳልሆን ፡ ሌሎችም ፡ ረዳቶች ፡ ታገኚ ፡ ይሆናል ። እኅቴ ፡ ወ/ ደማሜና ፡ አማቼ ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ እስከዛሬ ፡ ያደረጉልሽን ርዳታ ፡ እንደማያቋርጡ ፡ በደብዳቤያቸው ፡ አረጋግጠውልኛል ።

ስለዚህ ፡ ሁለቱን ፡ ወንድሞችሽንና ፡ እኅትሽን ፡ በትምህርት ፡ ልታሳድጊያቸው ፡ ትችያለሽ ። እነርሱ ፡ በጉልበታቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ሲረዱ ፡ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ በገንዘብ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጣጣ ፡ ትችያቸዋለሽ ። ለወደፊቱ ፡ እነርሱም ፡ በትርፍ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ እንዲያገኙ ፡ እኔ ፡ በተለይ ፡ እጥርበታለሁና ፡ ስለወደፊቱ ፡ ነገር ፡ ፈጽመሽ ፡ አታስቢ ።



በይ ፡ ደኅና ፡ ሁኚልኝ ፡ የእሥራኤል ፡ አምላክ ፡ በደገኛው ፡ መልአኩ ፡ ያስጠብቅሽ ። የኔም ፡ መንፈስ ፡ ዘወትር ፡ እንደማይለይሽ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

ያንችው ፡ አክባሪ ፡ እምቢ ፡ እውነቱ ።

እምቧ ፡ እውነቱ ፡ ወደውጭ ፡ አገር ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ በወዳጅነት ፡ መልክ ፡ እጅግአየሁ ፡ እንድታስጠጋው ፡ የሚጥር ፡ አንድ ፡ ጎልማሳ ፡ ብዙ ፡ ተከታትሎአት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ የማትበገር ለት ፡ ስትሆንበት ፡ ጊዜ ፡ እንደገና ፡ በትዳር ፡ መልክ ፡ ደጅ ፡ ጥናቱን ፡ ቀጥሎ ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ተኩል ፡ ያህል ፡ ደከመ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ከእምቧ ፡ ጋር ፡ መጻጻፍዋን ፡ ባታቋርጥ ፡ በእንግዳው ፡ ደጅ ፡ ጥናት ወደ ፡ መሸነፉ ፡ አዘነበለች ። ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ እንግዳው ፡ ይቀርባት ፡ የነበረው ፡ ዘመዴ ፡ ነኝ ፡ በሚል ፡ ስም ፡ ስለሆነ ፡ ውስጠ ፡ ምሥጢሩን ፡ ለማወቅ ፡ አልተቻለም ፡ ነበር ።

እነወርቅና ፡ እነብር ፡ እነብረታብረቶች ፡ በእሳት ፡ ካልተፈተኑ ፡ እውነተኛ ፡ ባሕርያቸውን ፡ እንደማያሳዩ ፡ እንዲሁም ፡ ሰው ፡ በችግር ፡ ወይም ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ ካልታየ ፡ በስተቀር ፡ እውነተኛ ፡ ባሕርዩ ፡ በውል ፡ ተገልጾ ፡ ሊታይ ፡ አይችልም ። ይህም ፡ አነጋገር ፡ ከጥንት ፡ ተያይዞ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ደራሽና ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ ሙላት ፡ ተከልባሽ ፡ አይደለም ። ከጥንት ፡ ታሪክ ፡ ተነሥተን ፡ የዚህን ፡ አነጋገር ፡ ጥሬት ፡ እውነተኛነት ፡ ለማረጋገጥ ፡ ብንፈልግ ፡ የአንዳንድ ፡ ተራ ፡ ሰውን ፡ የመንደሮችን ፡ የአጥቢያዎችን ፡ የቀበሌዎችን ፡ የወረዶችን ፡ የአውራጆችን ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛቶችን ፡ የታላላቅ ፡ መሪዎችንና ፡ የነገሥታትን ፡ ታሪክ ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምረን ፡ ልንረዳ ፡ እንችላለን ። ታሪክም ፡ እንደአግዛፊ ፡ መነጽር ፡ አጉልቶ ፡ ሊያሳየን ፡ ይችላል ። ከዚህ ፡ ምርመራ ፡ በኋላ ፡ የሰው ፡ ጥራትና ፡ ልክ ፡ ሊታወቅ ፡ ይችላል ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ በመጠኑ ፡ ለእምቧ ፡ በተጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ወእጅግ ፡ እየሁን ፡ መከራ ፡ አግኝቷት ፡ ነበር ። መከራውም ፡ ከትምህርት ሊያቋርጣት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልቀረውም ። ብቻ ፡ ዕድሜ ፡ ለዘመድ ፡ ዕድሜ ፡ ለጎረቤት ፡ ዕድሜ ፡ ለአባትና ፡ ለእናት ፡ ወዳጆች ፡ እንደዚሁም ፡ ለአምሳለ ፡ ገነት ፡ ሕዝብ ፡ በተለይ ፡ ማዘጋጃ ፡ ላቋቋማቸው ፡ የትምህርት ፡ ዕድገትና ፡ የርዳታ ፡ ኮሚቴዎች ። አለበለዚያማ፡

የእጅግአየሁ ፡ ወንድሞችና ፡ እኅቶች ፡ የትም ፡ ወድቀው ፡ ይቀሩ ፡ ነበር ።

እጅግ ፡ አየሁም ፡ ምንም ፡ በሙሉ ፡ በመንግሥት ፡ ርዳታ ፡ ብትማር ፡ ለአንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ መግዣ ፡ ልዩ ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ያስፈልጋታል ። በዚሁም ፡ ላይ ፡ አሳዛኙ ፡ መከራ ፡ ተጭኖ ፡ ከነቤተሰብዋ ፡ ከችግር ፡ ላይ ፡ ጥሏታል ። እነሆ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ተኩል ፡ ደጅ ፡ ጠኚዋ ፡ ገሸሽ ፡ አድርጓት ፡ ሸርተት ፡ አለ ። የዝምድናውንም ፡ ወሬ ፡ ደበቅ ፡ ደበቅ ፡ ማድረግ ፡ ጀመረ ። ሸውሻዋው ፡ ነፋሱ ፡ ሰው ፡ ችግር ፡ የማያገኛቸውን ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ይወዳል ፡ ያፈቅራልም ። በችግር ፡ ሲቆራመዱም ፡ አይርቅም ፡ አብሮም ፡ ይለፋል ፡ ማለት ፡ ከቶ ፡ ዘበት ፡ ነው ። እነሆ ፡ ወደ ፡ ጥንት ፡ ታሪካችን ፡ ሳንመለስ ፡ ሴቷ ፡ ልጅ ፡ ጉድዋን ፡ በዕንባ ፡ ስታጥብ ፡ ሬት ፡ እየነሣ ፡ ጥሏት ፡ ገሸሽ ፡ ይላል ። ምናልባትም ፡ የሌለባትን ፡ ስም ፡ ለመስጠትና ፡ ስሟንም ፡ ለማሳደፍ ፡ ይጥር ፡ ይሆናል ። ወይ ፡ ጉድ ! ጉዳት ፡ ተፈጥሮ ፡ ችግር ፡ እንደሞረድ ፡ በመሳል ፡ ሲፈትግ ፡ የአዲስ ፡ ጉዳት ፡ ጭመራው ፡ ድንቅርቅር ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ይባላል ! !

እነሆ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ በአሳቡ ፡ ያልተለያት ፡ አምኃ ፡ እውነቱ ፡ ግን ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ አይዞሽ ፡ ሲል ፡ ይጽፍላታል ። አምኃ ፡ እውነተኛው ፡ አፍቃሪዋ ፡ በሌጣ ፡ ወረቀት ፡ ብቻ ፡ አላጽናናትም ፡ እጁንም ፡ ዘረጋላት ፡ እንጂ ። በሥራው ፡ የደጉና ፡ የክፉውም ፡ ቀን ፡ ወዳጅና ፡ አፍቃሪ ፡ መሆኑንም ፡ አስተባብሮ ፡ በተገቢው ፡ ጊዜ ፡ ገለጸ ። እንግዲህ ፡ ወ እጅግ ፡ አየሁ ፡ የአምኃን ፡ ፍቅር ፡ ምን ፡ ታደርገው ፡ ይሆን ?

ወ እጅግ ፡ አየሁ ፡ በስሕተትዋ ፡ እየተጸጸተች ፡ የአምኃ ፡ ደብዳቤ በመጣላት ፡ ቁጥር ፡ ፊቷን ፡ በዕንባ ፡ ታጥብ ፡ ጀመር ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ « አዬ ፡ እኔ ! በአሳሳች ፡ ጎልማሳ ፡ እውነተኛውን ፡ ልቤን ፡ የቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምኃዬን ፡ ላጣው ፡ ነበር ። ወይ ፡ ጉድ ! ደካማነቴ ፡ ከቶ ፡ እንዴት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ! ብቻ ፡ ለወደፊቱ ፡ አንተ ፡ ቸሩና ፡ ቅዱሱ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ አምኃ ፡ መንፈሴን ፡ አጽናው ፡ እጅግም ፡ አበርትተህ ፡ ከአምኃ ፡ ጋር ፡ ለመጣር ፡ አብቃኝ ። ሰው ፡ የምሆንበትን ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ አሳየኝ ፡ » እያለች ፡ ዘወትር ፡ መጸለይ ፡ ጀመረች ።



## ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬን ፡ እንደገና ፡ ፈጥሮ ፡ የመመለስ ፡ ያህል ፡ አድርጎ ፡ አዳነው ። አሁን ፡ አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ ፈጽሞ ፡ ድኖ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የተሰጠውን ፡ ዕረፍት ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ለመመለስ ፡ ተዘጋጀ ። ማናቸውንም ፡ ለመከላከያ ፡ የሚያገለግል ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ገዝቶ ፡ ያዘ ። ቴሌግራምም ፡ ወደ ፡ ምክትሉ ፡ ከንቲባና ፡ ወደቤቶቹ ፡ አስተላለፈ ። የዛሬው ፡ ጉዞው ፡ በተለይ ፡ ክድሮ ፡ ባልንጀሮቹ ፡ ጋር ፡ በመሆኑ ፡ ለደስታው ፡ ወሰን ፡ አልነበረውም ። በመንገድም ፡ የልጅነታቸውን ፡ ጊዜ ፡ ተግባር ፡ እያነሡ ፡ ብዙ ፡ ተጫዋወቱ ። በተለይም ፡ እነርሱ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ ስምንት ፡ ስምንት ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ ቆይተው ፡ ስለነበር ፡ የአምሳለ ፡ ገነትን ፡ ዕድገት ፡ አጥብቀው ፡ ጠየቁት ። በውጭ ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ በየጊዜው ፡ በጋዜጣ ፡ ላይ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ያደረገችው ፡ ርምጃ ፡ እየተገለጸ ፡ ያነቡ ፡ ነበርና ፡ እውነተኛው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ደጋግመው ፡ ጠየቁ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ አዳፍሬ ፡ እንዳችም ፡ አጋናኝ ፡ ቃል ፡ ሳይጨምር ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ በጋዜጣ ፡ ከተነገረላት ፡ በላይ ፡ እየሆነችና ፡ በተፋጠነ ፡ ርምጃ ፡ ብዙዎቹን ፡ ጓደኞቹዋን ፡ ጥላቸው ፡ የትና ፡ የት ፡ እንደተሽቀነጠረች ፡ አረጋገጠላቸው ። ርምጃዋ ፡ ባንድ ፡ ዓይነት ፡ በኩል ፡ ሳይሆን ፡ በሁሉም ፡ መሥመሮች ፡ መሆኑንም ፡ ጭምር ፡ በማብራራት ፡ እየዘረዘረ ፡ አስረዳቸው ።

ከባልንጀሮቹም ፡ ውስጥ ፡ ሦስቱ ፡ ሐኪሞች ፡ አንዱ ፡ መሐንዲስ ፡ ሁለቱ ፡ ቀማሚዎች ፡ ( ኬሚስትስ ፡ ) ነበሩ ። እነዚህ ፡ ጎልማሶች ፡ በሙሉ ፡ በአምሳለ ፡ ገነት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሥፍራዎች ፡ ተዘጋጅተውላቸዋል ። አዲስ ፡ ሥራን ፡ በመፈለግ ፡ ጊዜንና ፡ ገንዘብን ፡ ጉልበትንም ፡ እንዳያባክኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ተጠንቶ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንደሚመጥናቸውና ፡ በበለጠ ፡ ትጋት ፡ ለመሥራት ፡ እንደሚያስችላቸው ፡ ተደርጎላቸዋል ። መጀመሪያ ፡ አም

ሳለ ፡ ገነት ፡ ሲገቡ ፡ ዘመዶቻቸውንና ፡ ወዳጆቻቸውን ፡ እየጠየቁ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀናት ፡ ያርፋሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በየተደለደሉበት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ይቀመጡና ፡ በእ[illegible] መብት ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ።

ጎልማሶቹ ፡ ጨዋታቸውን ፡ በሰፊው ፡ ዘርግተው ፡ እየተደማመጡ ፡ አሳቦችን ፡ ሲለዋወጡና ፡ ሲያረጋግጡ ፡ ሲያጠኑም ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የበረረ ፡ ሳይመስላቸው ፡ ከአምሳለ ፡ ገነት ፡ የአይሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ደረሱ ። አይሮፕላኑም ፡ እንዳረፈ ፡ ሥርዓተ ፡ አይሮፕላኑን ፡ ፈጽመው ፡ ወርደው ፡ ከሕዝብ ፡ ሲቀላቀሉ ፡ መተቃቀፍ ፡ መሳሳም ፡ ዕንቦችንም ፡ መቀንዘፍ ፡ ዋና ፡ ተግባሮች ፡ መስለው ፡ ለጊዜው ፡ በተቀባይ ፡ ዘመዶች ፡ ዘንድ ፡ ተገለጹ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጎልማሶች ፡ እየተነጣጠሉ ፡ ከየቤተሰባቸው ፡ ጋር ፡ ወደየቤታቸው ፡ ጊዜው ፡ በፈቀደው ፡ ማኋኋዣ ፡ አመሩ ። ከዚህም ፡ አያይዞ ፡

«ደስታ ፡ ኑብርህ ፡ ስንት ፡ ይሆን ? ሕፃን ፡ ሲወለድ ፡ ትመጣለህ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ በያለበት ፡ ታስፈነድቃለህ ። በግርዘት ፡ በክርስትና ፡ በልደት ፡ በዓላት ፡ ሁሉ ፡ ፈተናን ፡ በማለፍ ፡ ትምህርትን ፡ በመጨረስ ፡ እነዚህንም ፡ በመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ ትመጣለህ ። ሁሉንም ፡ ተደሳቾች ፡ በሠርግ ፡ ደምድመህ ፡ እንደገና ፡ ወደኋላ ፡ ትመለሳለህ ። ከቶ ፡ የዛሬው ፡ ዓይነትህ ፡ ምን ፡ ይሆን ? የዛሬው ፡ ፍሥሐህ ፡ ትምህርትን ፡ ጨርሶ ፡ ኑሮን ፡ የመጀመሪያው ፡ በዓል ፡ ማድረግ ፡ ነው ። በል ፡ እስኪ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነተኛና ፡ ፍሬያማ ፡ በዓል ፡ ያድርግልህ ። አደራህን ፡ በሐዘን ፡ ተለውጠህ ፡ ወዳጆችህን ፡ እንዳታሳዝን ፡ አጥብቀህ ፡ ተጠንቀቅ ፡» ስትል ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ማስጠንቀቂያዋን ፡ አሰማምራ ፡ ወረወረች ።

አቶ ፡ በላይነህ ፡ ወደ ፡ አምሳለ ፡ ገነት ፡ ተመልሶ ፡ ሥራውን ፡ ከጀመረ ፡ ብዙ ፡ ሳምንቶች ፡ አለፉ ። ወይዘሪት ፡ ደማሚም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እቤትዋ ፡ ሲመጣ ፡ በምክርና ፡ በሥራ ፡ ትረዳው ፡ ነበር ። በአሁኑ ፡ ሁኔታ ፡ ኑሮን ፡ ለመቀጠል ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የሚያጠግብና የሚያስደስት ፡ ሆኖ ፡ አላገኙትም ። ስለዚህ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ተጋብተው ፡ በማናቸውም ፡ በኩል ፡ የሚገጥማቸውን ፡ የኑሮ ፡ ትግል በኅብረት ፡ ለማስወገድ ፡ መቻል ፡ እንደሚያስፈልጋቸው ፡ አጥብቀው ፡ ተገነዘቡ ። ይህንም ፡ ድርድር ፡ ሁለቱም ፡ ለወላጆቻቸው ፡



አቀረቡና ፡ የሠርጉ ፡ መሰናዶ ፡ በሁለቱም ፡ ቤቶች ፡ በኩል ፡ ሊጀመር ፡ ሲል ፡ አቶ ፡ በላይነህና ፡ ደማሚ ፡ ተማክረው ፡ ሠርጋቸውን ፡ [illegible]ል ፡ መልስ ፡ በቁርስ ፡ ብቻ ፡ እንዲያከብሩ ፡ ቁርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረጉ ። ይህን ፡ አሳብ ፡ የሁለቱም ፡ ወላጆች ፡ ተቃውመውት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ አንድ ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ በግብዣ ፡ ወይም ፡ በክርስትና ፡ ስም ፡ ወደፊት ፡ ደግመው ፡ ለመደሰት ፡ ስለሚችሉ ፡ አሁን ፡ ለየብቻ ፡ መድከም ፡ እንደማያስፈልጋቸው ፡ ገልጸው ፡ ከከተማው ፡ ዳር ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ባለጥሩ ፡ ግቢ ፡ ቤት ፡ እንዲገዛላቸው ፡ ብቻ ፡ ጠየቁ ። ቢቻል ፡ ግዢው ፡ ከሠርጉ ፡ በፊት ፡ እንዲፈጸምላቸው ፡ አሳስበው ፡ አስፈላጊውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁለቱም ፡ አውጥተው ፡ ለየወላጆቻቸው ፡ ሰጡ ። እንዳጋጣሚ ፡ ከከተማው ፡ ትንሽ ፡ ፈንጠር ፡ ያለ ፡ ባላትክልታም ፡ ግቢ ፡ አገኙላቸውና ፡ ገዙላቸው ። ቤቱም ፡ ግቢውም አዲስ ፡ መልክ ፡ እንዲያመጣና ፡ እንዲጸዳ ፡ በሚገባ ፡ ታደሰ ። አትክልቱም ፡ በሥርዓት ፡ ተሠርተው ፡ በሚገባ ፡ ተጠበቁ ።

ዋ.ጋው፡ የኢ.ት. $0.20